*"ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎአድራጐት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡"*

የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3፡፡

ይህ አንቀጽ የህፃናትን መብት በተመለከተ መሠረታዊ መብት ብቻ ሳይሆን መሪ (Guiding) መርህ ነው፡፡ መርሁ የህፃናትን ጉዳይ በሚያስተናግዱ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በአጠቃላይ በተለይም ደግሞ በፍርድ ቤቶች የህፃናትን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ መሰረት ይሆናል፡፡ ይህ መርህ እውቅና ያገኘው በ20ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን ነው፡፡ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀዳሚዎቹ አመታት የልጆች አስተዳደግን አስመልክቶ ክርክር ሲነሳ ፍ/ቤቶች የሚሰጡት ውሳኔ ከእናት ይልቅ አባት ለልጆች መልካም አስተዳደግ የተሻለ ነው የሚል አስተሳሰብ መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ ለዚህ አስተሳሰብ መሠረቱ ወንዶች በኢኮኖሚ የነበራቸው የተሻለ አቅም እና የልጆች ሥነ-ምግባር በመቅረፅ ረገድ የተሻለ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነበር፡፡ 'ሴት ያሳደገው'፣ 'የሴት ልጅ' የሚሉ ስድቦች የነበሩበት ዘመን የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ናቸው፡፡ አሁንም ቢሆን በአገራችን ተመሳሳይ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አይጠፉም፡፡ ይህ አስተሳሰብ ቆየት ብሎ Tender Years Doctrine በሚል ሌላ ገዢ መርሕ ተተክቷል፡፡ በዚህኛው መርሕ መሠረት በተፈጥሮ እንክብካቤ የማድረግ ተሰጥኦ ያላት እናት ስለሆነች ከ13 ዓመት በታች ላሉህ ፃናት ሌሎች ለሞግዚትነት ብቁ የማያደርጓት ነገሮች እስከሌሉ ድረስ ልጆችን ለማሳደግ ከአባት ይልቅ እናት ትመረጣለች የሚል ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ አገራችንን ጨምሮ በበርካታ አገሮች ሲንፀባረቅይስተዋላል፡፡

ከ20ኛው ክፍለዘመን አጋማሽ በኋላ ገዢእየሆነ የመጣው አስተሳሰብ የህፃናት መብት እና ደህንነት ቀደምትነት መርህ ነው፡፡ ይህ መርህ የተካው ከላይ የተመለከቱትንና ሌሎች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን አስተሳሰቦች ሲሆን ይህ መርህ በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንና በህገ-መንግስት ደረጃ እውቅና ያገኘው በቅርብ ጊዜ ነው፡፡ መርሁ በዓለም አቀፍ እና አሕጉር አቀፍ ብሎም በህገ-መንግስት ደረጃ እውቅና ማግኘቱ ለመብቱ የተሰጠው የላቀ ቦታ ከማመልከቱም በላይ የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ከመርሁ ጋር ተገናዝበው እንዲወጡ ያስችላል፡፡

መርሁ የህፃናትን መብትና ጥቅም በማራመድ ረገድ ያለው ፋይዳ አከራካሪ ባይሆንም ይህንኑ መርህ ተገቢ ባልሆነ መልኩ በመተርጐም ለልጆቹ ጠቃሚ ያልሆኑ ነገሮች ነገር ግን የህፃናትን ጥቅምና ደሕንነት ለማረጋገጥ እንደተፈፀሙ ተደርገው የሚወሰዱ እርምጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ የሴት ልጅ ግርዛትና በአካል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ቅጣቶች ለህፃናት ጥቅም ጐጂ ስለመሆናቸው ሳይንሳዊ በሆነ ማስረጃም ጭምር ከመረጋገጣቸው በተጨማሪ የወንጀል ድርጊትም መሆናቸዉ በህግ ተደንግጐ እያለ እነዚህን ድርጊቶች የሚፈፅሙ ሰዎች ድርጊቱን የሚፈፅሙት ለህፃናት ደህንነት ሲሉ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እንደዚህ አይነቱ አስተሳሰብ መርሁን ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ በመተርጎም በህፃናት አካላዊ እና መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ጉዳት ማድረስ ተገቢ አለመሆኑን የኮንቬንሽኑን አፈፃፀም የሚመለከተው አለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ኮሚቴ ባዘጋጃቸው ሪፖርቶች ገልጿል፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚቻለው "የህፃናት መብት እና ደህንነት ቀደምትነት መርህ ምን ማለት ነው? በእያንዳንዱ ጉዳይ ይህንን መርህ ማረጋገጥ የሚቻለውስ እንዴት ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ መርህ ለማናቸውም ጉዳይ እና በማናቸውም ጊዜ ሊሰራ የሚችል ትርጉም እስካሁን አልተሰጠውም፡፡ እንዲያውም ለመርሁ የተሟላ ትርጉም መስጠት የሚቻል መሆኑም አጠራጣሪ ነው፡፡ የመርሁ ዋና ፋይዳ ሌሎች ድርጊቶች እና ህጎችን በመተርጎም ረገድ ያለው ጠቀሜታ ነው፡፡ ጉዳዩ ላይ ከተፃፉ ጽሁፎች እና ከህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ማብራሪያዎች መገንዘብ የሚቻለው ጉዳዩ እንደ የአገሩ ነባራዊ ሁኔታ መታየት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በአገራት መካከል የሀብት፣ የእድገት ደረጃ፣ የባሕል እና ሌሎች ልዩነቶች ያሉ በመሆኑ እያንዳንዱ ሁኔታ /ድርጊት/ በአገራት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ማየት እና ማመዛዘን ይጠይቃል፡፡ ይህ ማለት ግን በሁሉም

አገራት ተቀባይነት ያላቸው የልጆችን መብት እና ደህንነት ተቀዳሚ ለማድረግ የሚረዱ ዝቅተኛ መመዘኛዎች ማዘጋጀት አይቻልም ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ አገራት ይህንን መርህ ተግባሪዊ ለማድረግ የሚያስችል ዝርዝር መመሪያዎች ወይም የሕፃናት መብትና ደሕንነት መጠበቂያ መመዘኛዎች አሏቸው፡፡

በእንግሊዝ አገር እ.ኤ.አ በ1989 በወጣው የህፃናት ህግ (Children's Act) ላይ የሰፈሩትን መመዘኛዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በተጠቀሰው ሕግ መሠረት የህፃናት መብትና ደህንነት ለማስቀደም የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ዉስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

1. ጉዳዩ የሚመለከተው ልጅ ትክክለኛ ፍላጐት እና ስሜት፤
2. የልጆችን የአሁንና የወደፊት አካላዊ እና ስሜታዊ ወይም የትምህርት ፍላጎጐት፤
3. የሁኔታዎች መለዋወጥ በልጁ የአሁንና የወደፊት ህይወት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ውጤት፤
4. የልጁን እድሜ፣ ፆታ፣ የቀድሞ ታሪክ ወይም ሌላ ባህሪዎች፤
5. አሁን የደረሰ ወይም ወደፊት ሊደርስ የሚችል ጉዳት ወይም ስቃይ፤
6. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቤተሰቦች ወይም ሌሎች ሰዎች አቅም ወይም ችሎታ፤
7. ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመወሰን ያለው የሥልጣን ስፋት፡፡

ከላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የልጆችን ጥቅም የማስቀደም ጥያቄ ሲነሳ በእኛም የህግ ሥርዓት ተግባራዊ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህግ-መንግስት አንቀጽ 36 እና በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ መግቢያ እንዲሁም በህጉ ዝርዝር ድንጋጌዎች ላይ የህፃናት መብት እና ደህንነት ቀደምትነት መርህ እውቅና የተሰጠው በመሆኑ ከላይ የተመለከቱትን መመዘኛዎች ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

የህፃናትን ጥቅም እና ደህንነት በማስቀደም ረገድ መታለፍ የሌለበት ጠቃሚ ቁምነገር የልጆቹን የተሳትፎ መብት ማረጋገጥ ነው፡፡ የልጆችን መብት ለማስከበር ሀሳባቸውን መግለፅ ለሚችሉ ህፃናት እድሉን መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ህፃኑ የሚሰጠው ሀሳብም እንደ እድሜው እና የአስተሳሰብ ብቃት ተገቢውን ክብደት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይህ መብት በህፃናት መብቶች

ኮንቬንሽን በአንቀጽ 12 በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ስለ ህፃናት ሁሉንም ነገር አሳዳጊዎቻቸዉ ያውቁላቸዋል ብሎ የህፃናቱን ሀሳብ አለመቀበል የህፃናትን ትክክለኛ ጥቅም ለመረዳት እንቅፋት ይሆናል፡፡

የህፃናትን መብት እና ጥቅም ለማስቀደም ሌላው ጠቃሚ ነጥብ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ዐበይት መርሆች ተብለው በኮንቬንሽኑ አንቀጽ 2፣ 3፣ 6፣ እና 12 ላይ የተመለከቱት አንቀጾች ተያያዥና ተመጋጋቢ በመሆናቸው በተቻለ መጠን ተግባራዊ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው ለህፃናት ጥቅም ቅድሚያ መስጠት የሚለዉ መርህ ለሁሉም ጉዳይ እንዲሁም በማናቸውም ጊዜ ሊያገለግል የሚችል ፍቺ ስለሌለው የኮንቬንሽኑን መሠረታዊ መርሆዎች፣ የእያንዳንዱን ጉዳይ ልዩ ባሕሪይ እና የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለልጆች ጥቅም ቅድሚያ መስጠት ይገባል፡፡

### 3.3. የመኖርና የእድገት መብት

*1) የኮንቬንሽኑ አባል አገሮች ማንኛውም ህፃን የመኖር መብት እንዳለው ዕዉቅና ይሰጣሉ፡፡*

*2) የኮንቬንሽኑ አባል አገሮች በሚቻላቸው ሁሉ የህፃናትን በህይወት የመኖር እና የማደግ መብት ያረጋግጣሉ፡፡*

የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 6፡፡

ይህ መርህ ለህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን የማእዘን ድንጋይ ነው፡፡ የመኖር መብት በበርካታ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችም ሆነ በህገ-መንግስታችን ላይ በግለጽ ተመክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የሞት ወይም የመፈታት እድል የሌለው የእድሜ ልክ እስራት በህፃናት ላይ ማስተላለፍ የተከለከለ ስለመሆኑ በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 37/ሀ/ ላይ ተደንግጓል፡፡

ይህ መርሕ መንግስታት ህፃናት ላይ የሞት ፍርድ ወይም የመፈታት እድል የሌለው የእድሜ ልክ እስራት እንዳይፈርዱ ከመከልከሉ በተጨማሪ ህፃናት በህይወት መኖር እንዲችሉ የሚያስችል አዎንታዊ እርምጃ እንዲወሰድ ይጠይቃል፡፡ በዚህ ረገድ መንግስታት የህፃናት ሞትን (infant mortality) እንዲሁም በሕይወት የመኖር አማካይ እድሜን (life expectancy) ለመጨመር የሚያስችል ሥራ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይህ መብት በጣም ሰፊ ስለሆነ ከሌሎች መብቶች ጋር ተገናዝቦ መታየት አለበት። የህፃናት በህይወት የመኖር እና የእድገትመብትን ማረጋገጥ የሚቻለው በዚህ መልኩ ሲተረጐም ብቻ ነው። ህፃናትን አስመልክቶ ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ የቀለብ፣ የጉዲፈቻ ፣ የሞግዚትነት፣ ልጆች ከየትኛው ቤተሰብ ጋር ማደግ እንዳለባቸው፣ እንዲሁም ሌሎች የፍትሃብሄር እና የወንጀል ጉዳዮችን ዳኞች ሲያስተናግዱ የህፃናትን በህይወት መኖር እንዲሁም በአካልና በአእምሮ ጐልብተው እንዲያድጉ ለማድረግ ተገቢ የሆነውን አሰራር መከተል ይጠበቅባቸዋል።

ፍ/ቤቶች በሚሰጧቸው የቀለብ ውሳኔዎች ልጆች በአካል እና በአእምሮ ያደጉ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በ1999 ዓ.ም. የቀለብ አወሳሰን መመሪያ (Manual) አዘጋጅቶ በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ አድርጓል። ይኸው አስገዳጅ ያልሆነ መመሪያ በተለይዩ ጊዜያት እየዳበረ መጥቶ በዳኞች ስምምነት በ2006 ዓ.ም. ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል። በዚህ መመሪያ መሰረት የልጆችን የመኖርና የማደግ መብት ለማረጋገጥ የተሻለ አማራጭ ተደርገው ከተወሰዱት ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች የቀለብ ክፍያ መጠን ሲሰላ ጋብቻው ሳይፈርስ ልጆች ሲያገኙ የነበረውን ጥቅም ማስቀጠል የሚለውና ልጆች ለተሟላ እድገት ከምግብ ውጭ መጫወትም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ተገንዝቦ ለጫወታና መዝናናት የሚወጣ ወጭ የቀለብ አካል እንዲሆን ማድረግን ይመለከታል።

የልጆች የመኖርና የማደግ መብት ከቀለብ ውሳኔ ጋር ብቻ የሚያያዝ አይደለም። የልጆች ወላጆች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከሌላ አካል ጋር ባላቸው ክርክር የሚሰጡ ውሳኔዎችም የልጆችን ጥቅም ታሳቢ ሊደረጉ የሚችሉበት ሁኔታም አለ። ለምሳሌ በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ ሰው የሚያሳድጋቸውና የሚንከባከባቸው ልጆች ካሉት በአንድ በኩል ተገቢውን ቅጣት የሚያገኝበትን በሌላ በኩል ደግሞ በቅጣቱ ምክንያት ስራዉን አጥቶ ልጆቹ የሚቸገሩበት ሁኔታ እንዳይኖር ማድረግ እንደሚቻል ከሚከተለው ውሳኔ ማየት ይቻላል።

ጠጥቶ በመንዳትና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረሱ በካናዳ ሀገር በቶሮንቶ ዲስትሪክት ፍ/ቤት ተከሶ ጥፋተኛ የተባለ አንድ በዜግነቱ አልጄሪያዊ የሆነ ሾፌር ለቅጣት ማቅለያ ባቀረበው ሀሳብ አምስት አካለ

መጠን ያልደረሱ ልጆች ያሉት መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማስረዳቱ ፍ/ቤቱ ተከሳሹ በእስራት መቀጣት ያለበት መሆኑን በማመኑ በመደበኛ የስራ ቀናት መደበኛ ስራውን አየሰራ ስምንት(8) ቅዳሜና እሁዶች በእስራት እንዲቀጣ ወስኗል፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በስራ ቀናት እንዲታሰር ያላደረገው ከስራው በእስራት ምክንያት ቢቀር ስራዉን ሊያጣ የሚችለበት እድል በመኖሩ መሆኑን አትቷል፡፡ ከስራው ከተባረረ ደግሞ አምስት ልጆች ለችግር ይጋለጣሉ፡፡ ይህ ደግሞ የልጆችን ጥቅምና ደህንነት ይጐዳል፡፡

በማናቸውም የክርክር ሂደት አንደነገሩ ሁኔታ የልጆችን የመኖርና የማደግ መብት ታሳቢ ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ከዚህ ውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3.4. ሀሳብን የመግለፅ መብት

ይህ መብት ከህፃናት መብት እድገት አኳያ እንደ ትልቅ ለውጥ የሚታይ ነው፡፡ ህፃናት ስለ ራሳቸው መናገር ስለማይችሉ አሳዳጊዎቻቸዉ ስለ እነሱ ይናገሩላቸዋል ከሚለው አስተሳሰብ ወደ ህፃናት ስለራሳቸው ያውቃሉ፣ ፍላጐታቸውንም መግለፅ ይችላሉ ወደሚለው አስተሳሰብ መሸጋገርን የሚያመላክት መብት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ይኸዉ መብት ከአራቱ ዋና ዋና የህፃናት መብቶች መርሆች አንዱ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህ መብት በህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 12 ላይ በሚከተለው ሁኔታ ሰፍሮ እናገኘዋለን፡-

1. *የኮንቬንሽኑ አባል አገሮች የራሱ ሀሳብ ያለው እና ሀሳቡን መግልፅ የሚችል ህፃን እሱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ያለምንም ፍርሀት ሀሳቡን እንዲገልፅ ያደርጋሉ፡፡ ህፃኑ የሚያቀርበው ሀሳብ እንደእድሜውና የአእምሮዉ እድገት ተገቢ ክብደት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡*
2. *በመሆኑም የአገራት የሥነ-ሥርአት ህጐች በሚፈቅዱት መሰረት በተለይ የህፃናትን ጥቅም በሚመለከቱ መደበኛ ፍ/ቤቶች እና የአስተዳደር ፍ/ቤቶች ህፃናት ራሳቸዉ በቀጥታ፣ በተወካያቸዉ አማካኝነት ወይም በሚመለከተዉ አካል አማካኝነት ሀሳባቸዉን እንዲገልፁ እድል ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡*

ይህ አንቀጽ በዋናነት ሦስት ነጥቦች ይዟል፡-

- ህፃናትሀሳባቸዉን የመግለጽ ችሎታ እንዳላቸዉ እውቅና ይሰጣል፣
- ህፃናት እነሱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሀሳብ የመስጠት መብት ያላቸው መሆኑን፣ እና
- ህፃናት የሚሰጡት ሀሳብ እድሜያቸውንና ብስለታቸዉን ባገናዘበ ሁኔታ ክብደት ሊሰጠው እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡

ይህ አንቀጽ በዚህ መብት ለመጠቀም ዝቅተኛ የእድሜ ወለል አያስቀምጥም፡፡ ህፃኑ ያቀረበው ሀሳብ ሊሰጠው የሚገባው ክብደት ከሕፃኑ እድሜና የብስለት ደረጃ ጋር የሚያያዝ ሲሆን ህፃኑ ሀሳብ ማቅረብ የሚችል ከሆነ ሀሳቡን እንዲያቀርብ እድል የመስጠቱና የመሰማት መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደነገሩ ሁኔታ ወኪሎቹ ወይም አግባብ ያለው አካል ስለልጁ ጥቅም እንዲያስረዱ እድል ሊሰጣቸው እንደሚገባ በፍ/ቤቶች እና በአስተዳደር አካላት ላይ ግልጽ ግዴታ ተጥሏል፡፡

## 4. ፍርድ ቤቶችን ለህፃናት ምቹ ስለማድረግ

### 4.1. አጠቃላይ

ፍ/ቤቶች ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ተደራሽ /ምቹ እና ቅርብ/ መሆን አለባቸው፡፡ ከጤነኛ ፍርድ ቤት መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ተደራሽነት ነው፡፡ ፍ/ቤቶችን ተደራሽ ከሚያደርጉ ነገሮች ውስጥ የባለጉዳዮች አያያዝ፣ አሳታፊነት፣ ቅርበት፣ ምቹነት፣ ቅልጥፍናና ውጤታማነት ይገኙበታል፡፡ እነዚህ መስፈርቶች ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የሚያገለግሉ ቢሆንም አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ባላቸው ልዩ ባሕሪይ ምክንያት ልዩ አያያዝ ይሻሉ፡፡ ህፃናት ልዩ አያያዝ ከሚሹ የሕብረሰብ ክፍሎች ዉስጥ አንዱ ናቸው፡፡ ለህፃናት የሚደረግ አያያዝ አካላዊ እና አእምሮአዊ እድገታቸውን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡ ፍ/ቤቶች ለህፃናት ተደራሽ እና ምቹ ናቸው የሚባሉት አሰራራቸው እና አደረጃጀታቸው የህፃናት መብቶች መሠረታዊ መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ሲደራጁ ነው፡፡ እነዚህ አሰራሮችና አደረጃጀቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የህፃናትን የአሁንና የወደፊቱን ስብእና የማይጎዱ፤

2. ንቁ እና የተሟላ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የሚረዱ፤
3. ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችሉ፤
4. የህፃናትን ጥቅም ሊያስቀድሙ የሚችሉ ውሳኔዎች እና ትዕዛዞች ማስጠት የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

ፍ/ቤትን ለህፃናት ተስማሚ ለማድረግ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በችሎት እና ከችሎት ውጭ የሚሰሩ ሥራዎች ብለን ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡

### 4.2. በችሎት ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች

ህፃናት በተለያዩ ደረጃዎች ጉዳይ ኖሯቸው ወደ ፍ/ቤት ሲመጡ በችሎት ውስጥ የሚሰሩ ሥራዎች ከላይ እንደተመለከተው 1ኛ ተሳትፎአቸውን የሚያበለፅጉ፣ 2ኛ ሥነ-ልቦናቸው እንዳይጎዳ ጥበቃ የሚያደርጉ እንዲሁም፣ 3ኛ ውሣኔዎችን ባጭር ጊዜ የሚሰጡና የእነርሱን ጥቅም ያገናዘቡ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉትን ስራዎች መስራት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

### *4.2.1. የችሎት አደረጃጀት*

ዳኞች ለየትና ከፍ ባለ ቦታ መቀመጣቸው፣ ዳኞች፣ አቃቤ ህጎችና ጠበቆች ጥቁር ካባ መልበሳቸው፣ የችሎት ሥነ-ስርዓት አስከባሪዎች እና ፖሊሶች በአይነቁራኛ እያንዳንዱን የችሎት ውስጥ እንቅስቃሴ መቆጣጠራቸው ችሎቱን የፀጥታ ድባብ የሰፈነበት ወይም አስፈሪ ያደርገዋል፡፡ ይህ ሁኔታ እንኳንስ ህፃናትን አካለመጠን ለደረሱ ሰዎችም ዘና ብለው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አያደፋፍርም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ህፃናት፣ ለምሣሌ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ህፃናት፣ ወደ ችሎቱ እንዲገቡ የሕንፃው መግቢያ የተመቻቸ መሆን ይኖርበታል፡፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜም የምልክት ቋንቋ ወ.ዘ.ተ... መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

ህፃናት ወደ ፍ/ቤት በምስክርነት፤ በወንጀል ጉዳይ ገብተው ሲገኙ ወይም ወንጀል ፈፅመዋል ተብለው በተከሳሽነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳይ በቀጥታ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ከሆኑ የሚከራከሩት

በወኪላቸው በኩል ቢሆንም እንደነገሩ ሁኔታ የእነሱን ሀሳብ መስማት አስፈላጊ ሲሆን ቀርበው ሀሣባቸውን እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ምንም እንኳን ከሳሽ እና ተከሳሽ ባይሆኑም በእነሱ ጉዳይ ላይ ሌሎች ወገኖች በሚከራከሩበት ሁኔታ፣ ለምሳሌ የሞግዚት እና አስተዳዳሪ መሾምና መሻር፣ የጉዲፈቻ እና የመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡ የጉዳዮቹ ባሕሪ የተለያየ በመሆኑ የችሎት አደረጃጀቱም አንድ አይነት ሊሆን አይችልም፡፡ በመሆኑም የችሎት ሁኔታ ምን መምሰል እንዳለበት ለመወሰን ልጆች በተለያዩ ሁኔታዎች፣ ለምሳሌ ምስክር ሆነው ሲመጡ፣ ወንጀል ሰርተው ሲገኙ እና በሌሎች ጉዳዮች ብሎ ከፋፍሎ መመልከቱ ይጠቅማል፡፡

## *ሀ. ህፃናት በወንጀል ጉዳይ ገብተው ሲገኙ*

> *"አካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የተከሰሰበትን ነገር የሚሰማውችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚያነጋግረው አኳኋንና ሁኔታ የተለየ ይሆናል"*
>
> *የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 176/2/፡፡*

በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ በግልጽ እንደተደነገገው አካለመጠን ያልደረሱ ወጣቶች ጉዳይ መታየት ያለበት ከአዋቂዎች በተለየ ሁኔታ ነው፡፡ በእንግሊዝኛው ቅጂ በግልጽ እንደሰፈረውም ሂደቱ ኢ-መደበኛ መሆን አለበት፡፡ ይህ ማለት ለአዋቂዎች ተፈፃሚ የሚሆነው ሥነ-ሥርዓት ለህፃናት ተፈፃሚ እንዳይሆን ከመከልከሉም በተጨማሪ የልጆቹን ስብእና በማይጎዳ እንዲሁም ተሳትፎአቸውን በሚያበለጽግ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን የሚጠይቅ እንደሆነ ከሥነ-ሥርዓት ህጉ አጠቃላይ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በወንጀል ጉዳይ የገቡ አካለመጠን ያልደረሱ ወጣቶች ጉዳይ አያያዝም ሆነ የችሎቱ አደረጃጀት ለአዋቂዎች ተግባራዊ የሚሆነው የችሎት አደረጃጀት ሳይሆን ለህፃናት ምቹ እና እንግዳ ያልሆነ መሆንአለበት፡፡ ሕፃናት በቤታቸው እና በትምህርትቤታቸው የለመዱት የስብስባ አይነት አቀማመጥ ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ ሀሳባቸውን ለመግለጽ ይረዳቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ አሰራር በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተሞክሮ አጥጋቢ ውጤት አስገኝቷል፡፡



*የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በወንጀል የፍትህ ሂደት የገቡ ልጆች ጉዳይ የሚታይበት ችሎት፡፡*

በፎቶው ላይ የሚታዩት ዳኛው እና ረዳቱ፣ የማሕበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች፣ ተከሳሾች እና የተከሳሾች ጠበቃ ናቸው፡

### ለ. ህፃናት በምስክርነት ሲቀርቡ

ህፃናት የወንጀል ጥቃት ሰለባ በመሆናቸው ወይም ወንጀል ሲፈፀም በማየታቸው ምክንያት ምስክር ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ምንም እንኳን የደረሰባቸውን አካላዊ እና/ወይም ሥነ-ልቦናዊ ጥቃት በተቻለ ፍጥነት እንዲረሱ ለማድረግ የሚደረገዉ ጥረት ላይ ስለጉዳዩ ማንሳቱ የራሱ የሆነ ችግር ያለበት ቢሆንም ለፍትሕ አስተዳደሩ ውጤታማነት የግድ አስፈላጊ በመሆኑ በምስክርነት መቅረባቸው የሚበረታታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ህፃናት የወንጀል ጥቃት የፈፀመባቸውን ሰው ፊት ማየታቸው ስቃያቸውን የሚያስታውሳቸውና የሚያበዛባቸው ከመሆኑም በላይ በፍርሀት ትክክለኛውን የምስክርነት ቃል ለመስጠት ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡

ይህን ችግር ለማስወገድ ህፃናት የምስክርነት ቃል መስጠት ያለባቸው በችሎት ውስጥ ሳይሆን ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ ልዩ ክፍል መሆን

አለበት፡፡ ይህ ክፍል ከችሎቱ ጋር በአንድ በኩል ብቻ በሚያሳይ መስታወት የተያያዘ ሆኖ ችሎት ውስጥ ያለው ሰው መስካሪውን ልጅ እንዲያይ መስካሪው ግን በችሎት የሚደረገውን እንዳያይ ተደርጎ ሊሰራ ይችላል፡፡ ወይም መስካሪው ልጅ ከችሎትራቅ ባለ ክፍል እንዲሆን ተደርጐ ምስሉ እና ድምፁ ወደ ችሎት ከክፍሉ ውስጥ በተገጠመ ካሜራ እና ችሎቱ ውስጥ ባለ ቴሌቭዥን (Closed Circuit TV) አማካኝነት ከችሎት ጋር የተገናኘ ሆኖ ህፃናቱ በአጋዥ ባለሙያ አማካይነት በችሎት ለሚቀርብላቸው ጥያቄ መልስ እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ የወንጀል ጥቃት ሰለባ የሆኑ ህፃናት ወይም ማንኛውም ለምስክርነት የወጣ ህፃን በችሎት ውስጥ ያሉ ተከራካሪ ወገኖች ግን ህፃኑ ባለበት የምስክርነት መስጫ ክፍል የሚሆነውን ሁሉ ለማወቅ መብት አላቸው፡፡ የችሎቱ አደረጃጀትም ይህን መርህ መሠረት ያደገ መሆን አለበት፡፡ ይህ አሰራር በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ሆኗል ፤ውጤትም አስገኝቷል፡፡



*በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አካለ መጠን ያልደረሰች ወጣት ከችሎት ውጭ በተዘጋጀ ልዩ ክፍል በአጋዥ ባለሙያ እርዳታ የምስክርነት ቃል ስትሰጥ፡፡*



*በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በህፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የሚታዩበት ችሎት፡፡*

ከዚህ በተጨማሪ ህፃናት በወንጀል ጉዳይ ላይ የጥቃት ሰለባ እና ምስክር ሲሆኑ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር አካላት ሊከተሏቸው የሚገቡ መመሪያዎች (Guidelines) በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር በሚገኘው የኢኮኖሚ እና ሶሻል ካውንስል ተዘጋጅቷል፡፡ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2005 ተቀባይነት ያገኘው "በወንጀል የጥቃት ሰለባና ምስክር የሆኑ ህፃናትን የሚመለከት ፍትሕ ላይ የተዘገጀ መመሪያ" ተብሎ የሚታወቀውን ሰነድ መሠረት ያደረገዉ በዋነኝነት የህፃናትን ጥቅም ማስቀደም የሚለውን መርህ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም 10 መብቶችን አካቷል፡፡ ይህ መመሪያ ሁሉም የወንጀል ፍትህ አካላት እንዲጠቀሙበት የተዘጋጀ ነው፡፡ በዝርዝር መታየት እና መጠናት ያለበት ቢሆንም እግረ መንገድ ነጥቦቹን ማየቱ ጠቃሚ በመሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. በፍቅር  እና በሀዘኔታ የመያዝ መብት፤
2. ከአድሎ የመጠበቅ መብት፤
3. መረጃ የማግኘት መብት፤
4. ሀሳብን እና ፍላጎትን (Conecern) የመግለፅ መብት፤
5. ትርጉም ያለው እርዳታ የማግኘት መብት፤
6. የግል ሕይወት (Privacy) የመከበርና የመጠበቅ መብት፤
7. በፍትሕ ሂደቱ  ውጣ ውረድ እንዳይደርስበት የመጠየቅ መብት፤
8. ደህንነቱ የመጠበቅ መብት፤
9. ካሳ የማግኘት መብት፤
10. ልዩ ልዩ፡- የመከላከል /ከአደጋ የመጠበቅ እርምጃ /መብት

## ሐ. ህፃናትን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች

ህፃናት በወንጀል ጉዳዮች ሲጠረጠሩ በተከሳሽነት፣ የወንጀል ጥቃት ሰለባ ሲሆኑ ወይም ወንጀል መፈፀሙን አይተዋል ከተባለም በምስክርነት ሊቀርቡ እንደሚችሉና ሲቀርቡም ምን መደረግ እንዳለበት ከላይ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በፍትሐብሔር ጉዳዮች በሞግዚቶቻቸው /ወኪሎቻቸው/ አማካኝነት ክስ ከሰው ወይም ተከሰው የሚቀርቡበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ እነሱ ተከራካሪ ባልሆኑበት በእነሱ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሌሎች ወገኖች ክርክር የሚያካሂዱበት ሁኔታም አለ፡፡ በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽ ከሚሆኑት ውስጥ የጉዲፈቻ፣ የሞግዚት፣ የቀለብ፣ ልጆችን የመጐብኘት መብት እና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

ህፃናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የክርክሩ ተካፋይ ሲሆኑ ስሜታቸውንና ፍላጐታቸውን ለማወቅ ጥረት መደረግ አለበት፡፡ በተለይም ከላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ክርክሩ እነሱን የሚመለከት ሆኖ እያለ የህፃናትን መብት ብቻ ወክሎ የሚከራከር ሰው በሌለበት ሁኔታ የሌሎችን ክርክር ብቻ ሰምቶ በህፃናቱ ህይወት ላይ መወሰን ተገቢነት አይኖረውም፡፡ ይህን ችግር መቅረፍ የሚቻለው ህፃናትን በሚመለከቱ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ ልጆች ሊሳተፉ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ወይም በአንዳንድ የህግ ስርዓቶች እንደሚደረገው ለህፃናት መብት የሚቆም አካል በማቆም ነው፡፡ የህፃናት ተሳትፎ የተፈለገውን ግብ ሊያመጣ የሚችለው የህፃናትን ተሳትፎ የሚያቀጭጩ አሰራሮችን ተሳትፎ በሚያበረታቱ አሰራሮች መተካት ሲቻል ነው፡፡ ህፃናትን ማነጋገር አስፈላጊ በሆነባቸው ሁኔታዎች ቢቻል በባለሙያ እገዛ ለልጆች ምቹ በሆነ ቦታ፤ ልጆችን ከማነጋገር በተጨማሪ አስፈላጊው ጥናት ተደርጐ ለዳኛው በሪፖርት መልክ ቢቀርብ ይመረጣል፡፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ወይም ካልተመረጠ ግን በርካታ ሰዎች ባሉበት በችሎት ውስጥ ሳይሆን በዳኞች ጽ/ቤት እንደነገሩ ሁኔታ ወላጆቻቸው ባሉበት ወይም በሌሉበት ኢ-መደበኛ (Informal) በሆነ መንገድ ማነጋገር ተገቢ ነው፡፡



*የማሕበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ከፍቺ በኂላ ልጆች ከማን ጋር ማደግ እንዳለባቸው ለመወሰን ይረዳ ዘንድ ልጆችን ሲያነጋግሩ*

ዝቅተኛ የእድሜ ወለል ማስቀመጥ ሳያስፈልግ በሁሉም የጉዳይ አይነቶች ልጆችን በሚገባቸው ቋንቋ ለማነጋገር መሞከር ተገቢ ነው፡፡

በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ዳኞች አከራካሪ ነገር ሲኖር ወይም ዳኛው በራሱ አነሳሽነት ምርመራ ያስፈልጋል ብሎ ካሰበ የማሕበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች በጉዳዩ ላይ ጥናት አድርገው ሪፖርት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ያዛል፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎቹ ሪፖርት ሲያጠናቅሩ ሊሰሩት ከሚገባው ነገር ውስጥ አንዱና ዋናው የልጆችን ፍላጐት አጥንቶ ማቅረብ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ መሰራት ካለባቸው ስራዎች ውስጥ እንዱ ልጆችን ማነጋገር እና መረዳት ይገኝበታል፡፡

በፌደራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ይህ አሰራር የተጀመረው በ1998 ዓ.ም ሲሆን ፍ/ቤቱ የሰለጠነ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያ ስላልነበረው በአፍሪካ ህፃናት ፖሊሲ መድረክ (African Child Policy Forum) ይሰሩ ለነበሩ ባለሙያዎች የትብብር ጥያቄ በማቅረብ ስራዎች ይሰሩ ነበር፡፡ ፍ/ቤቱ በቋሚነት ተጨማሪ ባለሙያዎችን መቅጠር ሲጀምርና የማህበራዊ ሳይንስ ክፍሉ ሲጠናከር ስራዉ በፍ/ቤቱ ባለሞያዎች መሰራት ቀጥሏል፡፡

ለልጆች ጥቅምና ደህንነት የሚበጅ ዉሳኔ ለመስጠት የሚያግዝ መመሪያ በ2005 ታትሞ በልጆች አስተዳደግ ዙሪያ ለሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች እና ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ ይህ መመሪያ ልጆችን በሚመለከት በማናቸውም ጉዳይ ላይ የልጆችን ፍላጎት ለማረጋገጥ ልጆችን ማነጋገርን ጨምሮ ስለ ልጆቹ የሚያውቁ ሰዎችን ሁሉ ማነጋገር ጠቃሚ እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

### *መ. ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጪ የልጆችን ጉዳይ ማስተናገድ*

ፍ/ቤት የልጆች ቦታ አይደለም፡፡ ህፃናት ፍ/ቤት መቅረብ ያለባቸው ሁኔታዎች የግድ ሲሉ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ልጆች በመደበኛው የስራ ሰዓት በትምህርት ገበታ ላይ እንደሚሆኑ ይታወቃል፡፡ በመደበኛው የስራ ሰአት ፍ/ቤት እንዲገኙ ማድረግ ትምህርታችውን በአግባቡ እንዳይከታተሉ ከማድረጉም በላይ ከትምህርት ቤት የቀሩበትን ምክንያት ለጓደኞቻቸውም ሆነ ለመምህራቸው መናገር ላይመቻቸው ይችላል፡፡ ማንኛውም ሰው ስለመልካምና ስለሚያኮራ ነገር እንጂ ስለሚያሳቅቅና ለሰው ሊነግሩት ስለሚያሳፍር ነገር ማውራትን አይወድም፡፡

ህፃናትም ትምህርት ቤት የቀሩት በወንጀል ነገር ገብተው በመገኘታቸው ወይም የወንጀል ጥቃት ሰለባ በመሆናቸው ወይም እናትና አባታቸው በመፋታታቸው ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ተፈልገው ፍ/ቤት እንዲመጡ ቢጠየቁ ለጓደኞቻቸውም ሆነ ለአስተማሪያቸው ይህን ነገር ለመናገር ላይፈቅዱ ይችላሉ፡፡ ምናልባትም እውነቱን ላለመናገር ሲሉ የዉሸት ሌላ ምክንያት ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ህፃናት ፍ/ቤት የሚቀርቡ ከሆነ በተቻለ መጠን ከስራ ሰአት ውጪና ቅዳሜና እሁድ ቢሆን ይመረጣል፡፡

የፌደራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ከመጋቢት ወር 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ህፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች በተለይም የልጅ አስተዳደግ ጉዳዮች እሮብ ከቀኑ 11፡30 እስከ ምሽቱ 1፡00 ሰዐት እንዲሁም በወር አንድ ቅዳሜ ቀን በልዩ ሁኔታ የሚታይበት አሰራር ተግባራዊ አድርጓል፡፡

ይህ ችሎት ለሰራተኛ እናቶችም ትልቅ እፎይታ የሰጠ ችሎት ነው፡፡ እናቶች በመደበኛው የስራ ሰዓት በቀለብ ጉዳይ በተደጋጋሚ ከስራቸው

ፈቃድ እየጠየቁ መውጣታቸው የስራ ግንኙነታቸውንም ሆነ የስራ ዋስትናቸውን አደጋ ላይ የሚጥልበት ሁኔታ እንዳለ ይታወቃል፡፡ ሆኖም ከስራ ሰአት ውጪ በሚሰሩ ችሎቶች መስተናገዳቸው ለእነሱም ሆነ ለልጆቻቸው ኢኮኖሚያዊም ሆነ ሥነ-ልቦናዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

## *4.2.2. የችሎት ሂደቱ ኢ-መደበኛ መሆን ያለበት ስለመሆኑ*

ችሎት ለህፃናት አመቺ እንዲሆን የተለያዩ በተለምዶ የምንከተላቸውን አሰራሮች በመለወጥ ማስተካከል ይገባል፡፡ ከዚህ በታች ጥቂቶቹ ተዘርዝረዋል፡፡

- ***ካባ አለመልበስ***

የዳኞችም ሆነ የክርክር ተሳታፊዎች ካባ መልበስ ህፃናት ያልለመዱት አዉድ የሚፈጥርባቸዉ በመሆኑ ሀሳባቸውን አሰባስበው በነፃነት ለመግለፅ ሊቸገሩ ይችላሉ፡፡ በመደበኛው ችሎት ውስጥ ያለካባ ማስቻል የተለመደ አይደለም፡፡ የህፃናትን ተሳትፎ የሚገድበው ዳኛውና ሌሎች ተሳታፊዎች የለበሱት ካባ ብቻ ሳይሆን ችሎቱን የማስቻያው ቦታ አጠቃላይ ሁኔታም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የህፃናትን ጉዳይ የሚያዩ ችሎቶች እንደ ነገሩ ሁኔታ ራሳቸውን ችለው ለልጆች በሚመች ሁኔታ ቢደራጁ መልካም ነው፡፡ ይህን አሰራር ዳኛውም ሆነ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በካባ ምትክ መደበኛ ልብሳቸውን ሊለብሱ ይገባል፡፡ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 177/2/ "አካለመጠን ያልደረሰ ወጣት የተከሰሰበት ነገር የሚሰማው ችሎት በሌላ ነገር ተሰይሞ ከሚነጋገረው አኳኋንና ሁኔታ የተለየ ይሆናል" የሚለው ድንጋጌ የሚያሳስበውም ይህንኑ ቁምነገር ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የችሎት አደረጃጀቱም ሆነ የችሎት አመራሩ እንዲሁም የአለባበስ ሁኔታው ከመደበኛዉ ችሎት የተለየ መሆን አለበት፡፡

- ***ጥብቅ የሆነ የሥነ-ሥርዓት ሂደት አለመከተል***

የፍርድ ሂደት መመራት ያለበት ህጉ በሚጠይቀው መልኩ መሆን እንዳለበት አያጠያይቅም፡፡ ህፃናት በወንጀል ጉዳይ ተሳታፊ ሆነዉ ሲገኙ የጉዳዩ አያያዝ ኢ-መደበኛ መሆን እንዳለበት የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 176/2 በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም ህፃኑ በተከሣሽነትም ሆነ በምስክርነት

ሲቀርብ ዋናው ነገር መሆን ያለበት ሕፃኑ ሀሳቡን በአግባቡ ሊገልፅ የሚችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንጂ ለአዋቂዎች ተፈፃሚ በሚሆን የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ታስሮ የህፃኑን የተሳትፎ መጠን የሚገድብ መሆን የለበትም፡፡

በሌሎች ጉዳዮችም ቢሆን መርሁ መሆን ያለበት ህፃናት የሚያስፈልጋቸው እገዛ ተደርጐላቸው እንኳን የተሳትፏቸው መጠን አጥጋቢ ላይሆን እንደሚችል በመገመት በተቻለ መጠን ለተሳትፎ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ማስወገድ ነው፡፡ ይህን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የህፃናትን ተሳትፎ በሚጠይቁ ጉዳዮች ሁሉ የሥነ-ሥርዓት ህጉ ተሳትፎን በሚያቀጭጭ ሳይሆን በሚያበረታታ መልኩ በመተርጐም ነው፡፡

ለምሳሌ ህፃኑ አንድ ነገር ተጠይቆ በወቅቱ መልስ ሳይሰጥ ቆይቶ ትዝ ሲለው ምላሽ ቢሰጥ የሰጠውን መልስ አለመቀበል ተሳትፎዉን ይገድባል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም የተዘበራረቀና ያልተዳራጀ መልስ መስጠቱን እንደ ሀሰተኛ መስካሪ መቁጠርም የልጆችን የእድገት ደረጃ አለማገናዘብ ነው የሚሆነው፡፡

በሌላ በኩል ተሳታፊ ወገኖች ሕፃኑን የመጠየቅ መብት በሥነ-ሥርዓት ህጉ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሆኖም የሚጠይቁት ጥያቄ የህፃኑን ስብእና ሊጎዳ የሚችል እንዲሁም ህፃኑ ተደናግጦ ወይም ፈርቶ ትክክለኛውን ነገር እንዳይናገር የሚያደርገው መሆን የለበትም፡፡ በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ እንኳን ህፃን አዋቂም በነፃነት ለመናገር አይደፍርም፡፡ ይህ እንዳይሆን ዳኛው የሚጠይቁትን ጥያቄ ሊቆጣጠርና ሊያርም ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በችሎት ሂደት ሕፃናት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ችሎቱ አስፈሪ ሳይሆን ምቹ ወይም ሳቢ መሆን አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ የችሎት ሁኔታ ህፃናት ከለመዱት የቤታቸው እና የትምህረት ቤት ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### *4.2.3. የችሎት ቋንቋ አጠቃቀም*

ህፃናት ለሚጠየቁት ጥያቄ መልስ እንዲሰጡ ወይም ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ከተፈለገ በችሎት ውስጥ የምንጠቀምባቸው ቃላት ለህፃናት የሚመጥኑ መሆን አለባቸው፡፡ ለህፃናት የሚመጥኑ ቃላት ማለትም ህፃናት

ሊረዷቸው የሚችሉ እንዲሁም የህፃናትን ሥነ-ልቦና የማይጐዱ ማለት ነው፡ ፡ የህፃናት ተሳትፎ ትርጉም ያለው እንዲሆን በቋንቋ አጠቃቀም ረገድ የሚከተሉትን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

1. ሙያዊ ቃላቶችን አለመጠቀም፡- እንደሚታወቀው በፍ/ቤት የህግ ባለሙያዎች የሚጠቀሙባቸው ቃላት ሙያዊ ናቸው፡፡ እነዚህን ቃላት እንኳን ህፃናት ይቅርና የሙያው ባለቤት ያልሆኑ ጐልማሳ ሰዎችም ሊረዷቸው ይቸግራቸዋል፡፡
2. የሚጠየቁ ጥያቄዎች አጭር፣ ቀላልና በተጨባጭ ሁኔታዎች እንዲገልፁ ማድረግ፡- ህፃናት የተሟላ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲቻል እነሱ በሚጠቀሙባቸው፣ ካልተቻለም በቀላሉ ሊገባቸው በሚችል ቃላት በባለሙያ እገዛ ማናገር ያስፈልጋል፡፡
3. ለህፃናት እገዛ የሚያደርግ ባለሙያን መጠቀም፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዘዴዎች ተግባራዊ በማድረግ ህፃናት በችሎት ቋንቋ ምክንያት የሚጋጥሟቸውን ችግሮች ማስወገድ ይቻላል፡፡

### 4.2.4. የባለሙያ እገዛ ማግኘት

የህፃናትን ፍላጐትና ጥቅም ለማስጠበቅ ህፃናት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም በአካላዊና በአእምሮአዊ እድገታቸው ምክንያት ሀሳባቸውን በቀጡ ላይገልፁ እንዲሁም ጥቅማቸው የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ ማስረዳት ሊያዳግታቸዉ ይችላል፡፡ ሀሳባቸውን የመግለፅ ችግር ባይኖርባቸውም የፍትሕ ሂደቱ የሚጠይቀው የህግ እውቀት ስለሌላቸው ካለባለሙያ እገዛ የተሟላ እና ውጤት ያለው ተሳትፎ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም ተሳትፏቸው እንዲበለፀግና ፍትህ እንዳይጓደል የማሕበራዊ ሳይንስ እና የህግ ባለሙያዎችን እገዛ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ማንኛውም የወንጀል ተከሳሽ ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥመው ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 20/5/ ላይ በግልፅ ተደንግጓል፡፡ ህፃናት በአካላዊ እና አእምሮአዊ እድገታቸው ያልበሰሉ በመሆናቸዉ ምክንያት በወንጀል ጉዳይ

ተከሰው ሲቀርቡ የህግ ባለሙያ እገዛ ካላገኙ በስተቀር ፍትህ ሊጓደል እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ህፃናት የወንጀል ጥቃት ሰለባ ሲሆኑም ሆነ በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ በክስ ሂደት ላይ ተሳትፏቸውን ለማበልፀግ ከሚደረግላቸው ድጋፍ በተጨማሪ ከገቡበት ቀውስ እንዲወጡ የሚረዳ የማሕበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እገዛም ያስፈልጋቸዋል፡፡ በሌጋ እድሜያቸው ያጋጠማቸውን ችግር በባለሙያ እርዳታ እንዲወገድላቸው ካልተደረገ እነዚህ ችግሮች አብረው ሊያድጉና ለእነሱም ሆነ ለሕብረተሰቡ ጠንቅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### 4.2.5. የህፃናትን ጥቅም ቅድሚያ ሰጥቶ ለመወሰን የሚያስቸል መመሪያ ማዘጋጀት

ፍ/ቤቶች ለህፃናት ተስማሚናቸው የምንለው በጉዳዩ አያያዝ ብቻ ሳይሆን በውጤቱም ጭምር ነው፡፡ የፍ/ቤቶች ወይም የሌሎች የፍትህ ተቋማት ሥራ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የሚሰጡት ውሣኔዎች የህፃናትን ጥቅም ለማስቀደም የሚያስችል ህግና ለህጉ አፈፃፀም ምቹ የሆነ ዝርዝር አሰራር ሲዘረጋ ነው፡፡

የህፃናትን ጥቅምን ያስቀደመ ሥራ ለመሥራት ጥቅማቸውን ለመመዘን የሚያስችል መመሪያ (guideline) ሊኖር ይገባል፡፡ በመሆኑም በቀለብ አወሳሰን፣ በልጆች ማቆያ፣ በሞግዚት አሿሿም፣ በጉዲፈቻ እና በመሳሰሉት ጉዳዮች የልጆችን ጥቅም ማስቀደም የግድ እንደሆነ በዝርዝር ህጎች ጭምር ተደንግጓል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮችም ሆነ በሌሎች ጉዳዮች የተሳካ ሥራ መሥራት የሚቻለው የልጆችን ጥቅም ለማስቀደም የሚያስችሉ መመሪያዎች (guidelines) እና መመዘኛ ነጥቦች (check lists) ማዘጋጀት ሲቻል ነው፡፡ ይህ ሲሆን የሚሰጡት ውሳኔዎች የልጆችን ጥቅምና ደህንነት ከማረጋገጣቸው በተጨማሪ አሰራሩን ተገማችና ተቀባይነት ያለው ያደርገዋል፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህጋችን ለቤተሰብ ህጉ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች ህጉ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው መስተዳድሮች፤ ደንቦች ደግሞ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚወጡ ደንግጓል፡፡ እነዚህ ደንቦችና

መመሪያዎች በሚመለከታቸው አካላት ባለመውጣታቸው የፌደራል ፍ/ቤት የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የልጆችን ጉዳይ የሚያስተናግዱበት አስገዳጅ የስራ መዘርዝር እንዲሁም ለቀለብ አወሳሰን፤ ለጉዲፈቻ ጉዳይ አመራር እና አስገዳጅ ሁኔታ ሲኖር ከወላጆች መካከል ከጋራ የመኖሪያ ቤት ማን መውጣት አለበት በሚሉ ጉዳዮች ላይ አስገዳጅ ያልሆኑ ማጣቀሻ ጽሁፎች ተዘጋጅተው ዳኞች እንዲጠቀሙባቸው ተደርጓል፡፡

## 4.2.6. የፍርድ ሂደቱ ቅልጥፍና

ህፃናት በክርክር ሂደት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ እንደነገሩ ሁኔታም ራሳቸው ወይም በወኪሎቻቸው አማካይነት ክርክራቸውን የሚያቀርቡበት ሁኔታ አለ፡፡ በወንጀል ነገር ገብተው ሲገኙ በተከሳሽነት ወይም የወንጀል ሰለባ ሲሆኑ በምስክርነት በቀጥታ የክርክሩ ተካፋይ ይሆናሉ፡፡ በፍትሐብሄር ጉዳዮች ጥቅማቸውን ለማስከበር በሞግዚቶቻቸው እና ወኪሎቻቸው አማካኝነት በውርስም ሆነ በሌሎች የፍትሐብሄር ክርክሮች በከሳሽነት እና በተከሳሽነት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ህፃናት በከሣሽነት፣ በተከሣሽነት ወይም በምስክርነት ደረጃ የክርክሩ ተካፋይ ባይሆኑም በጉዲፈቻ፣ ከፍች ውጤቶች ጋር በተያያዘ በሚነሱ የቀለብ እና የልጆች አስተዳደግ ጉዳይ፣ ሞግዚት እና አስተዳዳሪን መሾም፣ ወይም መጨመርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ክርክሮች ከልጆች ጥቅም ጋር በቀጥታ የተያያዙ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚሰጥ ውሣኔ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በሆነ መልኩ በልጆች ህይወት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

እነዚህና የመሳሰሉት ክርክሮችን እልባት ለመስጠት የሚወሰደው የጊዜ እርዝማኔ በአጠቃላይ በልጆች ህይወት ላይ በተለይም በአካልና አእምሮአዊ እድገት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የጉዳዮች መዘግየት ፍትህን እንደሚያቀጭጭ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ህፃናት ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅምና እንክብካቤ በወቅቱ ካላገኙ የተስተካከለ አካላዊ እና አእምሯዊ ሁኔታ ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በፍትህ መዘግየት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመሸከም አካላዊ እና አእምሯዊ ሁኔታቸው አይፈቅድላቸውም፡፡

ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ከማናቸውም ጉዳይበተለየ ሁኔታ ባጭር ጊዜ የህፃናትን ጉዳይ እልባት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር መዘርጋትን ያስፈልጋል፡፡ ይህን ለማድረግ የመጀመሪያ ርምጃ የፍ/ቤቶች የሥራ እቅድ ላይ የህፃናትን ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥቶ መሠራት እንዳለበት ግዴታ የሚጥል የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ሥርዓት (case flow management system) መኖር አለበት፡፡

### 4.3. ከችሎት ውጭ በፍርድ ቤት የሚሰሩ ሥራዎች

ህፃናት ጉዳይ ኖሯቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ወደ ፍ/ቤት የሚመጡበት ሁኔታ በርካታ ነው፡፡ ጉዳይ ኖሯቸው የሚመጡ ህፃናት ወደ ችሎት ከመሄዳቸው በፊት የተወሰነ ቆይታ በግቢው ውስጥ ማድረጋቸው የግድ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ህፃናት እንደአዋቂዎች ስሜታቸውን መቆጣጠር ይከብዳቸዋል፡፡ ህፃናት በባህሪያቸው ስልቹዎች እና በአንድ ተግባር ላይ ለረጅም ጊዜ መቆየት ስለማይችሉ በዚህ ቆይታቸው የሚያዩትና የሚያጋጥማቸውን ነገር ስለ ትልቁ የፍትሕ ተቋም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ትዝታ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በመሆኑም በፍ/ቤት ቆይታቸው ደህንነታቸውንና ሥነ-ልቦናቸውን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች ተጠብቀው እንዲቆዩ፣ እንዲሁም ስለ ፍ/ቤት መልካም ትዝታ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሥራ መሠራት አለበት፡፡

ይህን አይነት ሁኔታ ለመፍጠር በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ይጠይቃል፡፡ ሆኖም የሚከተሉትን ተግባራዊ በማድረግ ብቻ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል በተግባር ጭምር ታይቷል፡፡

- **የጨቅላ ህፃናት ንጽሕና መጠበቂያ እና መመገቢያ ቦታ**

ወላጆች ህፃናት ልጆቻቸውን በተለያየ ምክንያት ይዘው ፍ/ቤት ይመጣሉ፡፡ ወላጆች ለረጅም ጊዜ ህፃናትን በፍ/ቤት ይዘው መቆየት ካለባቸው ልብስ መቀየርና መመገብ ሊኖርባቸው ይችላል፡፡ ባለን አነስተኛ አቅም ለሌላ ሥራ የተዘጋጀ ክፍል ውስጥ በመጋረጃ በመክፈል ለዚሁ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ የመቀየሪያ ጠረጴዛና ውሃ በማዘጋጀት ብቻ ለወላጆችና ሕፃናት ከፍተኛ እገዛ ማድረግ ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አቅም በፈቀደ መጠን ህፃናቱን ሊያዝናኑ የሚችሉ መጫዎቻዎች በማዘጋጀት ህፃኑን ወደ ጨዋታው ሲያተኩር ህፃኑን የሚጠብቀው ወላጅ፣ በተለይም እናቶች ወደ ጉዳያቸው እንዲያተኩሩ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ አገልግሎት በአንዳንድ የፌደራል እና የክልል ፍ/ቤቶች ተግባራዊ ሆኗል፡፡

- **የህፃናት መቆያና መጫዎቻ ቦታ**

ፍርድ ቤት በዋናነት አካለመጠን የደረሱ ሰዎች የሚመጡበት ስፍራ ነው፡፡ ህፃናት ፍ/ቤት የሚሄዱበት በርካታ አጋጣሚዎች ቢኖሩም ከፍ/ቤቱ ተጠቃሚዎች አጠቃላይ ቁጥር አንፃር ሲታይ የህፃናት ቁጥር በጣም ውሱን ነው፡፡ ሆኖም ህፃናት ስለ ፍ/ቤት አሉታዊ አመለካከት ይዘው እንዳይሄዱና አብረዋቸው የመጡትም ሰዎች እንዳይጨናነቁ ፍ/ቤት በሚመጡበት ጊዜ ጊዜያቸውን በአዎንታዊና አዝናኝ ተግባሮች ለምሳሌ እንደጨዋታና ንባብ በመሳሰሉት እንዲያዙ መደረግ አለባቸው፡፡ ስለዚህ አቅም በፈቀደ መጠንና በአካባቢው የሚገኙ ነገሮች የልጆችን ቀልብ ሊስቡ የሚችሉ ሥዕሎች፣ መጫወቻዎች ወይም ፊልሞች እንዲያዩ ቢደረግ የልጆችም ሆነ የቤተሳባቸውን ሀሳብ ማሳረፍ ይቻላል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ፍ/ቤቶች ለሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ ተደራሽነት መልካም ከሆነ ፍ/ቤት ዋና ባሕሪዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ፍ/ቤትን ተደራሽ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ አንዱ ልዩ ፍላጐት ያላቸው የሕብረሰተብ ክፍሎችን ማስተናገድ የሚያስችል አደረጃጀት ሲኖረው ነው፡፡ ህፃናት ልዩ ፍላጎት ካላቸዉ እና እንክብካቤ ከሚጠይቁ የሕብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ናቸው፡፡

ፍ/ቤቶችን ለህፃናት ደህንነት ምቹ /ተስማሚ/ ማድረግ ፍ/ቤቶች ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ከማድረግ በላይ ትርጉም አለው፡፡ ፍ/ቤቶች የህፃናትን ደህንነት ማስቀደም እንዳለባቸው በህፃናት መብት ኮንቬንሽንም ሆነ በህገ-መንግስታችን ላይ በግልጽ የተቀመጠ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶች የህፃናትን ጥቅም የሚያስቀድም አሰራር ተግባራዊ እንዲያደርጉ ህገ-መንግስታዊ ግዴታ ጭምር አለባቸው፡፡

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የፍትሕ አካላት ሰራተኞች በተለይም ዳኞች የህፃናት መብቶችን በተመለከተ በቂ እውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ ሊይዙ ይገባል፡፡ በህፃናት መብቶች በአጠቃላይ በተለይም ደግሞ በዋና ዋና የህፃናት መብት መርሆች ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ከሌለ የህፃናት መብትን ማስከበር አይታሰብም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእነዚህን መብቶች ተግባራዊነት ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር መመሪያ ካልተዘጋጀ በጉዳዩ ዙሪያ ያየዘውን እውቀትና ክህሎት ተግባራዊ ለማድረግ አያስችልም፡፡

ከሁሉም በላይ በጉዳዩ ዙሪያ የጨበጥነዉን እውቀትና ክህሎት ተግባራዊ ልናደርገው የምንችለው በህፃናት ላይ የምንሰራው ሥራ ለህፃናቱም ሆነ ለአገር ያለውን ፋይዳ ስንገነዘብ ነው፡፡ ፍ/ቤቶችን ለህፃናት ምቹ እንዲሆኑ ከልባችን ጥረት የምናደርገው ህፃናት የነገ አገር ተረካቢ ስለሆኑ በህፃናት ላይ የዋለ ሃብት፣ ጉልበትና እውቀት በተገቢ ቦታ ላይ የዋለ የመዋዕለንዋይ ፍሰት ነው የሚል አስተሳሰብ ሲኖረን ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ ላይ የተመለከቱት የህፃናት መብት አጠቃላይ መርሆዎች የህፃናት መብቶችን ለመተርጐርም ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡ ፍ/ቤቶች ከችሎት ውስጥም ሆነ ውጭ ለህፃናት ምቹ ለማድረግ የምንሰራቸው ሥራዎች መሰረታቸው የህፃናት መብቶች መሠረታዊ መርሆዎች ናቸው፡፡ እነዚህን መርሆች መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶቻችን ለህፃናት ተደራሽና ተስማሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባሮች በጽሁፉ ላይ በዝርዝር ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡

የህፃናት መብቶችን በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ፍ/ቤቶች በዚህ ጽሁፍ ላይ በዝርዝር እንደተመለከተው 1/ መብቶችን ማወቅ እና 2/ ለመብቶቹ አተገባበር አስፈላጊ የሆኑ የሰው ሀይል ማሟላት እንዲሁም ምቹ የሆነ አደረጃጀትና አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ አለብን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የጉዳይ አያያዛችን፡(1) የህፃናት ደህንነትን፣ የአሁንና የወደፊት ስብእናቸውን የማይጎዳ፣ (2) የህፃናትን ንቁና የተሟላ ተሳትፎ የሚያበረታታ፣ እንዲሁም (3) ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ እልባት የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡ የምንሰጣቸው ውሳኔዎችም የህፃናትን ጥቅምና ደህንነት የሚያረጋጡ መሆን አለባቸው፡፡

ባጭሩ ፍርድ ቤትን ለህፃናት ምቹና ቅርብ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

- በሰብአዊ መብት ዙሪያ በአጠቃላይ፣ በተለይም በህፃናት መብቶች ዙሪያ በቂ እውቀት እንዲኖር ማድረግ እንዲሁም ለመብቱ ተግባራዊነት ቁርጠኝነት መፍጠር፣
- ለህፃናት መብቶች አተገባበር አስፈላጊ የሆኑ መሰረተልማቶች መገንባት፣
- የማህበራዊ ሳይንስ ክፍልን ማደራጀት እንዲሁም ማጠናከር የልጆችን ፍላጐትና ጥቅም ለማረጋገጥ ይረዳል፣
- ከስራ ሰዓት ውጭ (የአመሻሽ) እና የሳምንት መጨረሻ ቀን(ናት) ችሎቶችን ማቋቋም፡፡ በህፃናት መብት ዙሪያ የሚሰሩ ባለድሻዎችን በማስተባበር ለጋራ አላማ በተባበረ ኃይል የህፃናት ጥቅሞችን ያማከለ ስራ መስራት፤
- በፍ/ቤት የሚዘጋጁ የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር መመሪያዎች የልጆችን ጥቅም በተዘዋዋሪም ቢሆን ሊጐዱ የሚችሉ ጉዳዮች በልዩ ትኩረት እና ቅድሚያ ተሰጥቶ እንዲታይ እንዲያደርጉ ማድረግ
- ጠበቃ ለማቆም አቅም የሌላቸው ህፃናት ጠበቃ የማግኘት መብታቸውን ማረጋገጥ፣
- ፍ/ቤቶች የህፃናትን የግል ሕይወት ታሪክ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ እንዳለባቸው ማሳወቅ፣
- ህፃናት በሚመለከታቸው ጉዳዮች ሁሉ ትርጉም ባለው መልክ ተሳታፊ የመሆን መብት እንዳላቸው ማረጋገጥ፣
- የህፃናትን ጉዳይ በዝግ ችሎት ህጉ እንዲታይ የደነገገበትን አለማ በውል በመገንዘብ የህፃናትን ጉዳዮች አስፈለጊ በሆነ ጊዜ በዝግ ችሎት ማየት፣
- የህፃናትን ምቾት የሚያስጠብቁ መቆያና መንከባከቢያ ቦታዎች ማዘጋጀት፤ እና
- የህፃናትን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እንዲሁም ሥነ-ልቦናቸው ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ የሚያስችል የችሎት አደረጃጀት መፍጥር፡፡

# የህፃናት ደህንነት እና ጥቅሞች የቀደምትነት መብት፡- ህጉ እና ተግባራዊ አሰራሩ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎት

*መሐመድ ሲራጅ*[*]

## 1. መግቢያ

ህፃናት የነገ ባለተስፋዎች እና አገር ተረካቢዎች መሆናቸው ተደጋግሞ የሚነገር እውነታ ነው፡፡ ለዚህ ዓላማ የሚበቁትም በአካላቸውም ሆነ በአዕምሯቸው የተሟሉ፣ የተስተካከሉና አምራች ዜጋ ሆኖው ማደግ እስከቻሉ ድረስ ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ "ያልዘሩትን አያጭዱም" እንደሚባለው ነውና አምራች ዜጋ ሆነው አገርን መረከብ ይቅርና እራሳቸውን መምራት የሚሳናቸው፣ የአገርና የህዝብ ሸክም መሆናቸው ጥርጥር አይኖረውም፡፡ እናም ህፃናት ለነገ አገር ተረካቢነት ኃላፊነታቸው ይበቁ ዘንድ ዛሬ በወላጆች፣ በአሳዳጊዎች፣ በሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች፣ በህዝብና በመንግስት አካላት መሰራት ያለባቸው ስራዎች በርካታ ናቸው፡፡ የወላጆቻቸውንና የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ፍቅር፣ ድጋፍና እንክብካቤ አግኝተው ጤናቸው ተጠብቆ በትምህርትና በሥነ-ምግባር ታንፀው በአገር ፍቅር ስሜት ተኮትኩተው ለኑሮ በሚያመች ስፍራ ማደግ ይገባቸዋል፡፡

ይህንኑ ከግምት ውስጥ በማስገባትም የህፃናት መብቶችና ጥቅሞች በህገ-መንግስቱና አገሪቱ ባፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የህግ ጥበቃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ህፃናት የመብቶች ባለቤትናቸዉ፤ የመብቶቻቸዉም ተጠቃሚ መሆን አለባቸዉ፡፡ የህፃናትን መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር ምንም ዓይነት ቅድመ-ሁኔታ ሊቀርብ አይገባውም፡፡ መብቶቹን የማክበርና የማስከበር ሃላፊትና ግዴታ የተጣለው በወላጆቻቸው (በአሳዳጊዎቻቸው)፣ በህዝቡና በመንግስት ላይ ነው፡፡ ይህም ማለት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ፖሊሲዎችና ስልቶች ሲቀረፁና ህጐች ሲወጡ የህፃናት ጉዳይ ቅድሚያ ተሰጥቶት በአግባቡ ግምት ውስጥ እንዲገባ መደረግ አለበት ማለት ነው፡፡ በተለይ ፍርድ ቤት ፍትህ የሚሰጥ አካል እንደመሆኑ መጠን የህፃናትን መብቶችና ጥቅሞች አስመልክቶ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበት እሙን ነው፡፡ ሁሉም የህፃናት መብቶችና ጥቅሞች ሊባል በሚችል መልኩ ወደ ፍርድ ቤት ቀርበው ተፈፃሚነት

[*] በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኛ፡፡

ሊያገኙ የሚችሉ በመሆናቸው የፍርድ ቤቶች ኃላፊነት በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ፅሁፍ ዓላማ የህፃናትን ደህንነት እና ጠቅሞች የቀደምትነት መብት ከባበርና ተግባራዊ አፈፃፀሙ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችና የህግ ክፍተቶች ምን እንደሆኑ መለየትና የመፍተሄ ሃሳቦችን ማስቀመጥ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ፅሁፉ አራት ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍል አንድ ስለህፃናት መብቶች ምንነትና ህጋዊ መሰረታቸው አጠር ያለ ዳሰሳ ያደርጋል፡፡ በዚህ ክፍል የህፃናት መብቶች ህጋዊ መሠረት ዓለም አቀፍ ይዘት ያለው መሆኑን ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በተለይ መብቶቻቸውንና ጥቅሞቻቸውን በማክበርና በማስከበር ረገድ ከፍርድ ቤት የሚጠበቀውን ግዴታና ኃላፊነት እስከምን ድረስ እንደሆነና በተግባር የተሠሩ ስራዎችን በማንሳት ያብራራል፡፡ ጋብቻን ከፍች ማዳን ማለት ለህፃናት ምን ማለት እንደሆነ በዚህ ክፍል አሃዛዊ መረጃ በማቅረብ ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ ክፍል ሁለት ደግሞ የቀለብ አቤቱታ አቀራረብ፣ አወሳሰንና አፈፃፀም፣ ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ ይቆረጣል አይቆረጥም፣ ወ.ዘ.ተ... የሚሉትንና ሌሎች ከቀለብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮችን በማንሳት በተግባር በፌደራል መጀመሪያ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች ያለውን አሰራር ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ቀለብ በተፋጠነ የፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት አግባብ የሚታይ ስለመሆኑና ከቀለብ አወሳሰን ጋር በተያያዘ ያጋጠሙ ችግሮችን በመጠኑም ቢሆን ይፈትሻል፤ መፍትሄ ናቸው ያላቸውንም ነጥቦች ለማስቀመጥ ተሞክሯል፡፡ ሶስተኛው ክፍል የህፃናትን አስተዳደግ፣ ሞግዚትነትና ጉብኝትን በተመለከተ ጥቅማቸውን መሠረት ባደረገ መልኩ የሚወሰን መሆንና አለመሆኑን ይመለከታል፡፡ ፍርድ ቤቶች የህፃናትን አስተዳደግ በመወሰን ረገድ የተጣለባቸውን ከፍተኛ ኃላፊት በማሳየት በተግባር የሚታዩ ችግሮችንም ያስቀምጣል፡፡ ክፍል አራት በልጅነትና በወራሽነት ጥያቄዎች ዙሪያ የፍርድ ቤቶች አሰራር ላይ ከህጉ አንፃር ትንታኔ ይሰጣል፡፡ ችግሮችንም ለይቶ ለማስቀመጥ ጥረት ያደርጋል፤ መፍትሄ ናቸው ያላቸውን ሃሳቦችንም ያቀርባል፡፡

በመጨረሻም በፅሁፉ ላይ የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ ለወንድ ፆታ የተቀመጠው አገላለፅ ለሴት ፆታም እንደሚያገለግል ከወዲሁ ማሳወቅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ለዚህ ፅሁፍ ዓላማ ሲባል ህፃን ማለት ልጅ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ህፃናት ማለት ልጆች ማለት ነው፡፡ቃላቶቹም በተናጠልና በብዙነት

እንደ ቅደምተከተላቸው ተመሳሳይ ትርጉምንም የሚያመለክቱ ሲሆኑ በማፈራረቅ ወይም በማተካካት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 2. የህፃናት መብቶችና የፍርድ ቤቶች ድርሻ

### 2.1. የህፃናት መብቶች በጠቅላላው

ሁሉም የሰው ልጆች በሰብአዊ ፍጡርነታቸው የማይጣሱና የማይገፈፉ መብቶችና ነፃነቶች ባለቤቶች ናቸው፡፡ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች በማንም አካል የሚሰጡ፣ የሚቸሩ፣ ባስፈለገ ጊዜም የሚቀሙ፣ የሚወሰዱ ወይም የሚረገጡ ሳይሆኑ ሰው በሰውነቱ ብቻ የሚጐናፀፋቸው የመሆናቸው ጉዳይ ተቀባይነት ያለው ዓለም አቀፋዊ መርህ ነው፡፡ በአንድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚገኝ መንግስት ሚና ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጆች ተፈጥሮ የሚመነጩ ማንም የማይገሳቸው መሆናቸውን በማያሻማ ቋንቋ በህግ እውቅና መስጠት፣ በተግባርም ማክበርና ማስከበር ብቻ ነው፡፡ መብቶቹ በተጣሱ ጊዜ ያለአንዳች ማመንታት አጥፊዎችን ተከታትሎ በህግ አግባብ መያዝ እና ተጐጅዎችም ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግ ከዲሞክራሲያዊ መንግስት ተቀዳሚ ሚናዎች ዉስጥ አንዱ ነው፡፡[1]

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት የግለሰብንም ሆነ የቡድን መብቶችንና ነፃነቶችን አንዱ ሌላውን ሳይተካ በእኩልነት ተገቢውን እውቅና የሰጣቸው መሆኑ ብዙም አያከራክርም፡፡ ስለተግባራዊ አከባበራቸውም ዋስትና ሰጥቶቷል፡፡ በህገ-መንግስቱ ምዕራፍ 3 ሥር ተዘርዝረው ከሚገኙት የሰው ልጆች ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች መካከል ዋናዋናዎቹ መካከል የህይወት መብት፣ የአካል ደህንነት መብት፣ የነፃነት መብት፣ ከኢ-ሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ መብት፣ የእኩልነት መብት፣ የእምነት ነፃነትና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶች፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብቶች፣ የግል ህይወት የመጠበቅ መብትና ሌሎችም የግለሰብና የቡድን (የህዝብ) መብቶች ወ.ዘ.ተ... ይገኙበታል፡፡ ከዚህም ሌላ ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች

---

[1] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት በአንቀጽ 10 (1) እና በአንቀጽ 14 ሥር በግልፅ እንተመለከተው ሰብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸው ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ማንኛውም ሰው ህፃነትን ጨምሮ ሰብአዊ ፍጡር በመሆኑ ብቻ በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህነትና ነፃነቱ የመጠበቅ የማይጣስና የማይገፈፍ መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ላይ የተረጋገጡት መብቶችና ነፃነቶች ያለአንዳች ገደብ የሀገሪቱ ህግ አካል ተደርገዋል፡፡[2]

ሁሉም ሰብአዊ መብቶች የህፃናትም መብቶች ናቸው፡፡ ህፃናት በሰብአዊ ፍጡርነታቸው የአጠቃላዩ የሰው ልጆች መብቶችና ነፃነቶች ተቋዳሾች ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችል ክርክር አይኖርም፡፡ ነገር ግን ህፃናት የአጠቃላዩን የሰው ልጆች መብቶችና ነፃነቶች ተቋዳሾች መሆናቸውን እውቅና በመስጠት ብቻ በተሟላ ሁኔታ መሠረታዊ ጥቅማቸውንና መልካም አስተዳደጋቸውን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ህፃናት የወላጆቻቸውን፣ የማህረሰቡንና የመንግስትን ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው የተለየ ጥበቃ በህግ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ስለሚታመን ነው፡፡ ስለሆነም የህፃናት መብቶች ተብለው በዓለምና በአገር አቀፍ ደረጃዎች የሚታወቁና የተለየ የህግ ዕዉቅና የተሰጣቸው የህፃናት መብቶች መኖራቸው የሚታወቅ ነው፡፡ መብቶቹ የሚመሩባቸው አራት ዋና ዋና መርሆዎችም በተመሳሳይ መልኩ እውቅና አግኝተዋል፡፡

በዚህ ረገድ ዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡ ከዩናይትድ ስቴት ኦፍ አሜሪካ በስተቀር የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽንን ሁሉም የአለም አገራት አፅድቀዉ የህጎቻቸዉ አካል አድርገውታል፡፡ ኢትዮጵያም ይህንኑ ኮንቬንሽን በህዳር 29 ቀን 1984 ዓ/ም ተቀብላ አጽድቃለች፡፡ ስለሆነም 41 አንቀጾችን የያዘውና ከመስከረም 02 ቀን 1990 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በስራ ላይ የዋለው ኮንቬንሽን የአገራችን የህግ አካል ሆኗል፡ ፡ ለመብቶቹ ሁሉን አቀፍ እውቅና ማግኘት የፍልስፍና መሠረቶች ናቸው ተብለው በሰፊው የሚታመኑት አራቱ የኮንቬንሽኑ አንኳ መርሆዎችም የአገራችን ህግ አካል ናቸው፡፡ ኮንቬንሽኑ በሁሉም ፍርድ ቤቶች እንደ ሌሎቹ የአገሪቱ ህጐች ሁሉ ህፃናትን በሚመለከት ሊጠቀስ የሚችል ህግ ነው፡፡ ሆኖም ግን በፍርድ ቤቶች በሚሰጡ ውሳኔዎች፣ ብይኖችና ትዕዛዞች ላይ ኮንቬንሽኑ ልክ እንደ አገሪቱ ህግ ተቆጥሮ በሰፊው ሲጠቀስ አይታይም፡፡

[2] በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ኢትዮጵያ ተቀብላ ያፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸው በሚል ተደንግጐ ይገኛል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስትም በአንቀጽ 36 ስር ለህፃናት መብቶች በተለየ መልኩ ጥበቃ ሰጥቷቸው ይገኛል፡፡ ከእነዚህ መሠረታዊ መብቶች መካከልም፡- በህይወት የመኖር መብት፣ ስምና ዜግነት የማግኘት (ዜግነታቸውንም ያለመነጠቅ መብት)፣ በጋብቻ ዉስጥም ሆነ ከጋብቻ ዉጭ የሚወለዱ ህፃናት የእኩልነት መብት፣ ወላጆቻቸውንና አሳዳጊዎቻቸውን የማወቅና የእነሱንም የተሟላ እንክብካቤና ድጋፍ የማግኘት መብት፣ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመማር መብት፣ ጤናቸው ተጠብቆ የማደግ መብት፣ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ከማናቸውም የጉልበት ሥራና ብዝበዛ፣ ጉዳት ከሚያደርሱ ስራዎችና ልምዶች፣ ጭካኔ ከተሞላበትና ኢ-ሰብአዊ ከሆኑ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ቅጣቶች የመጠበቅ መብቶች ወ.ዘ.ተ.... ይገኙበታል፡፡ እንዲሁም ከወንጀል ጋር በተያያዘ ጉዳይ ህፃናት እጥፌዎችን ከአዋቂ አጥፊዎች ተለይተው የመያዝ መብትና ስለዚሁ ጉዳይ በወጡ ህጎችና በተደራጁ ችሎቶች የመዳኘት መብት ወ.ዘ.ተ..... ሳይጠቀሱ መታለፍ የሌለባቸው የህፃናት መብቶች ናቸው፡፡ በተለይ እጓለማውታን ልዩ የህግ ጥበቃ የማግኘት መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ በጉዲፈቻ የማደግ መብታቸውን የሚያመቻቹላው፣ ደህንነታቸውን የሚጠብቁላቸውና ትምህርታቸውን የሚያገኙበትን ሁኔታዎች የሚያዘጋጁላቸው ተቋሞችን መንግስት የማቋቋም ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ወ.ዘ.ተ.... በህገ-መንስግቱ ላይ ተመልክቷል፡፡

ህፃናት የእነዚህ መብቶች ባለቤቶችና ያለገደብ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ መብቶቹን የማስከበርና በተግባር ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ሀላፊነትና ግዴታ የተጣለው በወላጆቻቸው፣ በአሳዳጊዎቻቸው፣ በማህበረሰቡና በመንግስት ላይ ነው፡፡ የህፃናትን መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር ምንም ዓይነት ቅድመ-ሁኔታ ሊቀርብ አይገባውም፡፡ ወላጆች በዚህ ረገድ የሚጠበቅባቸው ድርሻና ኃላፊነት ከፍተኛ ነው፡፡ ከወላጆች ቀጥሎ ኃላፊነትና ግዴታ በህግ የተጣለባቸው አካላት መኖራቸው ግልፅ ነው፡፡ ህግ አውጪው አካል ህግ በሚያወጣበት ጊዜ፣ የህግ አስፈፃሚው ህጉን ሲያስፈፅምና ፖሊሲዎችን ሲቀርፅ፣ እንዲሁም የዳኝነት አካሉ ህጎችን ሲተረጉምና ውሳኔ ሲወስን ምንጊዜም ቢሆን የህፃናትን ፍላጎት ከግምት ውስጥ የማስገባት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 2.2. የህፃናትን መብቶችንና ጥቅሞችን በማስከበር ረገድ የፍርድ ቤቶች ድርሻ

በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ፍርድ ቤት የህፃናትን መብት የማስከበር ግዴታ በህግ ተጥሎበት ይገኛል፡፡ የሚሰጡ ውሳኔዎች፣ ብይኖችና ትዕዛዞች ከህፃናት ጥቅሞችና መብቶች ጋር ተቃርኖ እንዳይኖራቸው የማድረግ ብቻ ሳይሆን ጥቅማቸውን በላቀ ደረጃ የሚያስከብሩላቸው መሆናቸውን ጭምር የማረጋገጥ ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች ነው፡፡ የአገሪቱ የፍትህ ሥርዓት በጠቅላላው፣ የዳኝነት አካሉ ደግሞ በተለይ ለህፃናት መብቶችና ጥቅሞች በተግባር መረጋገጥ ልዩ ትኩረት ሊሰጥ በሚችል መልኩ መዋቀርና መደራጀት ይገባዋል፡፡[3] ፍርድ ቤቶች ለህፃናት ምቹና ተደራሽ በመሆን ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የዳኝነት አገልግሎት መስጠት ግድ ይላቸዋል፡፡

የፍርድ ቤቶች ጤናማነት ከሚመዘንባቸው ነጥቦች አንደኛው ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ተደራሽመሆናቸው ነው፡፡ ተደራሽነት በተሟላ መልኩ ተረጋግጧል ሊባል የሚችለውም ህፃናትን ጨምሮ ልዩ ድጋፍና እገዛ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አመቺነት ያለው አደረጃጀት፣ አሰራርና የክርክር አመራር ሥርዓት በመዘርጋት ተጠቃሚነታቸውን በተግባር እውን ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ የፍርድ ቤቶች እስትራቴጂክና ዓመታዊ እቅዶች ሲታቀዱ የህፃናትን ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥቶ ከግምት ውስጥ በማካተት አስገዳጅነት ያለው የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደርን መዘርጋት ይጠይቃል፡፡ የፍርድ ቤቶችን ምቹነትማ ረጋገጥ ማለት የህፃናትን ተጠቃሚነት በዳኝነት ሥርዓቱ ውስጥ እውን ማድረግ ማለት ብቻ ሳይሆን በህገ-መንግስቱ ላይ የተጣለባቸው ግዴታቸውን መወጣት ጭምር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የፌደራል ፍርድ ቤቶች በጠቅላላው የህፃናትን ልዩ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ አደረጃጀትና አወቃቀር ያላቸው መሆንና አለመሆኑን እና የሚሰጡት አገልግሎት ምቹና ተደራሽ መሆኑና አለመሆኑ ከዚህ በታች ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

[3] በዚሁ ህገ-መንግስት አንቀጽ 36 (2) ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎአድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት ይላል፡፡ ስለዚህ የፍትህ ሥርዓቱም ይህን ህገ-መንግስታዊ መርህ መከተል አለበት፡፡

### 2.3. የፍርድቤቶች ተደራሽነት በተግባር ሲፈተሽ

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀታቸውን ለህፃናት ምቹና ተደራሽ በማድረግ በኩል ሊካድ የማይችል ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ ፈርጀ ብዙ ስራዎችን እየሰራ የሚገኘውና በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሥር የተቋቋመውን የህፃናት ፍትህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ ጽ/ቤቱ አቅም ለሌላቸው ህፃናት የህግ ድጋፍና ምክር ከመስጠት ባሻገር ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት በህፃናት መብቶች አተገባበር ላይ የተለያዩ አጫጭር ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡

ከዚህም ሌላ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር ፍርድ ቤቶችን ለህፃናት ምቹ ለማድረግ እጅግ በርካታ የአደረጃጀት ስራዎችን ሰርቷል፡፡ ህፃናትን አስመልክቶ በፍርድ ቤቱ የተሰሩት ስራዎች አርአያነታቸው የጐላ ነው፡፡ በችሎት ውስጥና ከችሎት ውጪ ፍርድ ቤቶችን ለህፃናት ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የችሎት ውስጣዊ ሁኔታው ምቹ፣ የማያስፈራና የማያስደነግጥ ይሆን ዘንድ ጠንካራ አቋም ተወስዶበት አመርቂ ስራዎች ስራዎች መሰራታቸው አንደኛው ነው፡፡ የዳኞች መቀመጫ ቦታ፣ የካባ አለባበሳቸው፣ የችሎት ሥርዓት አስከባሪዎች አቋቋምና የመስተንግዶ ሁኔታዎች ለህፃናት የተመቹ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡

ህፃናት በወንጀል ፍትህ ተሳታፊ ሆነው ሲመጡ የምስክርነት ቃላቸውን ከሌላ የችሎት ታዳሚ ጋር ሳይገናኙ (ዳኞችን፣ ዓቃቢ-ህግንና ተከላካይ ጠበቆችን፤ ጥቃት ያደረሰባቸውን ተጠርጣሪ ሳይመለከቱ) ለዚሁ በተዘጋጀ ክፍል ውስጥ ሆነው መጫወቻዎች ቀርቦላቸው ምቾት እየተሰማቸው በባለሞያ አማካኝነት እየታገዙ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡና የሚሰጡት ቃል በቴሌቪዥን እስክሪን ለችሎቱ በቀጥታ እንዲተላለፍ የሚያስችለው የሲ.ሲ.ቲቪ[4] ዘዴ መቋቋም ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነው፡፡ የሥነ-ሥርዓት አካሄዱ ላላ ያለ ነው፡፡ የችሎቱ አሰያየም ኢ-መደበኛ ነው፡፡ ለህፃናት የሚቀርብላቸው ጥያቄዎችና የቋንቋ አጠቃቀማቸው

[4] በወንጀል ጉዳይ ሰለባ የሆኑ ህፃናት በምስክርነት ወደ ፍርድ ቤት መጥተው ቃላቸውን እንደሚሰጡ ይታወቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ህፃናቱ ከሌላ የችሎት ታዳሚ ጋር ሳይገናኙ ጥቃት አድርሶባቸዋል የተባለውን ግለሰብም ሳያዩት ለዚሁ በተዘጋጀ ክፍል ውስጥ ሆነው መጫወቻዎች ቀርቦላቸው ምቾት እየተሰማቸው በባለሞያ አማካኝነት እየታገዙ የምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡና የሚሰጡት ቃልም በቴሌቪዥን እስክሪን ለችሎቱ በቀጥታ እንዲተላለፍ የሚያስችለው አሰራር ሲ.ሲ.ቲቪ. ይባላል፡፡

ለህፃናት አረዳድ እና ሥነ-ልቦና የሚመጥኑ፣ ሥነ-ልቦናቸውን የማይጐዱ፣ አጭርና ግልፅ ሆነው በባለሞያ እንዲታገዙ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የህፃናትን ጥቅም ያስቀደመ ስራዎች መሰራታቸውን ለመመዘን የሚያስችሉ የተለያዩ መመሪያዎች ተዘጋጅተው በስራ ላይ መዋላቸው፣ የሚሰጡ ውሳኔዎች በተቻለ መጠን ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆኑ መደረጉ በአበረታችነት የሚወሰዱ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ስራዎች በሁሉም ችሎቶችና ፍርድ ቤቶች ሊስፋፉ መቻል አለባቸው፡፡ በዚህ ረገድ ያለውን ውስንነት መጥቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በሚፈለገው ደረጃ ላይ ተደርሷል ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የፅሁፉ ዋነኛ ዓላማ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች የህፃናትን መብቶችና ጥቅሞች አከባበር በተግባር ምን እንደሚመስል መዳሰስና የሚያጋጥሙ ችግሮች ምን ምን እንደሆኑ መለየትና ከዚያም የመፍትሄ ሀሳቦችን ማስቀመጥ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በፍትሐብሄር ጉዳይም ቢሆን ህፃናት በሞግዚቶቻቸው ወይም በወላጆቻቸው አለበለዚያም የእነሱ ጉዳይ ያገባናል በሚሉ ወገኖችም አማካኝነት ክስ ከሰውም ሆነ ተከሰው ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ የቀለብ፣ የሞግዚትነት፣ የጉብኝትና አስተዳደግ፣ የውርስ፣ ወ.ዘ.ተ.... ክርክሮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፍቺ አቤቱታ ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ከፍርድ ቤቶች ምን ይጠበቃል የሚለውን አንኳር ነጥብ በቅድሚያ መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም በጋብቻና ጋብቻን በመሰለ የግንኙነት ዘመን የሚወለዱ ህፃናትን በተመለከተ ጋብቻው እንዳይፈርስ (ወላጆቻቸው እንዳይለያዩ) ማድረግ የህፃናትን መብቶች በላቀ ደረጃ ለማስከበርና ለማረጋገጥ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ስለሚታመን ነው፡፡

## 2.4. ጋብቻን ማዳን ከሕፃናት መብቶችና ጥቅሞች መከበር አንፃር

ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ለአቅመ-አዳም ከደረሱ በኋላ ወደውና ፈቅደው በእራሳቸው ነፃ ፍላጐት የሚያቋቁሙት የህግና የህብረተሰብ ጥበቃ ያለው ተቋም (ህጋዊ ግንኙነት) ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ጋብቻ ሁሉ ውል ነው ቢባል ስህተት የለውም፡፡ ነገር ግን ልክ እንደተራ ውል ተዋዋዮቹ እስከተስማሙ ድረስ በማናቸውም ጊዜ ማንም ሰው ሳያገባው ወደማንም አካል መሄድ ሳይጠበቅባቸው በእራሳቸው ጊዜ ሊያስቀሩት/ሊያፍርሱት/ የሚችሉት ነገር አይደለም፡፡ በተግባር ያለው ሁኔታ

ምንም ይሁን ምን ጋብቻው በየትኛውም መንገድ የተቋቋመ ቢሆንም እንኳ ለማፍረስ ከተፈለገ በፍርድ ቤት ቀርቦ የመፍረስ ውሳኔ ማግኘት እንዳለበት ህጉ ይደነግጋል፡፡[5]

በእርግጥ ጋብቻ የሚመሰረተው በተጋቢዎቹ ሙሉ ፍቃድ እንደመሆኑ መጠን መፍረስ የሚገባውም በፍቃዳቸው ነው፡፡ ተጋቢዎቹ ጋብቻቸዉን በስምምነት ወይም አንደኛው ወገን አልፈልግም (በቃኝ) ስላለ ብቻ ሊያፈርሱት ይቻላቸዋል፡፡ ጋብቻው ግን መፍረስ ያለበት የፍቺ አቤቱታ ለፍርድ ቤት ቀርቦ በፍርድ ቤት ውሳኔ ነው፡፡ በስምምነትም ሆነ በተናጠል አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤትም ቢሆን ወዲያውኑ ጋብቻውን ማፍረስ አይገባውም፡፡ ከሶስት ወር ያላነሰ የማሰላሰያ ጊዜም ሊሰጥ ይገበዋል፡፡ እንዲስማሙም ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ጋብቻ ከፍርድ ቤት ውጪ በማናቸውም አካል ሊፈርስ አይገባውም፤ መፍረስ ካለበት የግድ ፍርድ ቤት ቀርቦ መወሰን ይኖርበታል፡፡ የተፈፀመ የስምምነት ፍቺም ካለ በፍርድ ቤት ቀርቦ ከህግና ከሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑ ተረጋግጦ ሲያበቃ ሊፀድቅ (ሊመዘገብ) ይገባዋል፡፡

ይህ ሁሉ የሚያመለክተን ጋብቻ ከተራ ውል ያለፈ ፋይዳ ያለው መሆኑን ነው፡፡ ለዚህም ነው ጋብቻ የህግና የማህበረሰቡ ጥበቃ ያለው ተቋም ነው የሚባለው፡፡ አጠቃላይ ማህበረሱቡና መንግስት በጋብቻ ላይ ጥቅም አላቸው፡፡ ስለዚህ በማናቸውም መመዘኛ ቢታይ ጋብቻ ከኢትየጵያ ህግ አንፃር ተራ ውል ነው ብሎ ለመናገር አይቻልም፡፡ አመሰራረቱም ሆነ አፈራረሱ የሚከናወነው በዘፈቀደ ሳይሆን በህጉ ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ተከትሎ ነው፡፡

ተፈልጐም ሆነ ሳይፈለግ ከጋብቻ ውጪ ህፃናት ይወለዳሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በጋብቻ ምክንያት ህፃናት ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ ጋብቻው ልጅ ባስገኘ ጊዜ ልጆች የጋብቻ ፍሬ ናቸው ብሎ ለመናገር ይቻላል፡፡ ህፃናት ከተወለዱ በኋላ አስፈላጊው ድጋፍና እንክብካቤ የማግኘት መብቶቻቸው መከበር አለባቸው፡፡ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ልጅ የተወለደው በጋብቻም

[5] ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ የሚመሰረት ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ መመልከቱ እንዲሁም በተሻሻለው የፌድራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 በአንቀጽ 6 ስር ይኸው ሄኔታ አፅንኦት ተሰጥቶት መታወጁ የጋብቻን ተቋምነት በሚገባ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ጋብቻ በየትኛውም መንገድ የተቋቋመ ቢሆንም የሚፈርሰው በፍርድ ቤት ውሳኔ መሆኑ በተሻሻለው የፌድራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 117 ስር ተመልክቷል፡፡

ሆነ ከጋብቻ ውጪ በመብቶች አከባበርና አፈፃፃም ላይ ምንም ዓይነት ለውጥ አይኖረውም፡፡[6] ስለዚህ ልጅ ከተወለደ በኋላ የማያቋርጥ ግዴታና ኃላፊት በወላጆች ላይ ህጉ ጥሎባቸዋል፡፡ ግዴታው ከህግ የሚመነጭ ከመሆኑም በተጨማሪ ሰው የወለደውን ልጅ ተንከባክቦ ማሳደግና ለልጅ ሲባል የሚፈለገውን መስዋዕትነት ሁሉ መክፈል በህብረተሰቡም ዘንድ የሞራል ግዴታ ነው፡፡

ጋብቻ የህግና የማህበረሰብ ጥበቃ እንዲኖረው ካደረጉት ምክንያቶች ዋነኛው የህፃናትን መሠረታዊ ጥቅሞች በፍቺ ወቅትና ከፍቺ በኋላ በአግባቡ ለመጠበቅ ታስቦ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የፍቺ አቤቱታ ለፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ሁሉ የዳኞች ተቀዳሚ ተግባር ጋብቻውን በማዳን ላይ ያተኮረ መሆን ይገባዋል የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ በተለይም ልጆች የተወለዱት በጋብቻ (ጋብቻን በመሰለ የግንኙነት) ዘመን ከሆነ ምንጊዜም ቢሆን በተቻለ መጠን እንዲስማሙ ጥረት ማድረግና ጋብቻውን (ግንኙነቱን) ማስቀጠል መቻል የልጆችን መሠረታዊ ፍላጐት ለማስጠበቅ ያለው ድርሻ በቃላት የሚገለፅ አይደለም፡፡ ከፍርድ ቤቶችም የሚጠበቀው ትልቁ ሚና ይኸው ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ጋብቻ በመፍረሱ ምክንያት በባልም ሆነ በሚስት ላይ ጉዳት የመድረሱ ነገር ሀቅ ነው፡፡ ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ የጋብቻው መፍረስ በልጆች ላይ ከፍተኛ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት አለው፡፡ ለዚህም ነው ጋብቻውን ማዳን ማለት የህፃናትን ጥቅሞችና መብቶች ማረጋገጥ ማለት ነው የሚባለው፤ ተቀዳሚው አማራጭ እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡

## 2.5. ጋብቻን በማዳን ረገድ በተግባር ያለው ሁኔታ

የፌደራል ፍርድ ቤቶችም ወጥነት ባለው መልኩ ጋብቻ እንዳይፈርስ ምክንያታዊ ጊዜ ሰጥተው አበረታች ጥረቶች እንደሚያደርጉ ከእለት ተእለት የችሎት ስራቸው በቀላሉ መገንዘብ ይችላል፡፡ ከከፍተኛና እልህ አስጨራሽ ተደጋጋሚ ጥረት በኋላ የሚታረቁ ጥንዶችም አሉ፡፡ ሆኖም ግን ጋብቻን ከፍች ማዳን የሚለው አማራጭ ብዙ ጊዜ በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሲሆን አይታይም፡፡

[6] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 4 ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ህፃናት በጋብቻ ከተወለዱት ህፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው ይላል፡፡ በመብት አፈፃፀምም ረገድም ምንም ዓይነት ልዩነት ሊደረግ እንደማይገባ ድንጋጌው አመላካች ነው፡፡

ለምሳሌ በግንቦት ወር 2007 ዓ.ም. በእርቅ የተዘጉ የፍቺ መዛግብት ብዛት በልደታ ምድብ 3ኛው የቤተሰብ ችሎት 7 ብቻ ናቸው፡፡ በፍቺ ውሳኔ የፈረሰው ጋብቻ ብዛት ግን 25 ነው፡፡ በአንድ ምድብ ችሎት እጅግ ቢያንስ በአማካኝ አንድ ፍቺና የፍቺ ውጤቶችን ተቀብሎ የሚመለከት ንዑስ የቤተሰብ ችሎት አለ፡፡ የድሬዳዋ ምድብ ችሎትን ጨምሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 11 ምድብ ችሎቶች የሚገኙ ሲሆን በዚህ ስሌት መሠረት በ11 ምድብ ችሎቶች 11 ንዑሳን የቤተሰብ ችሎቶች ይኖራሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በአንድ ወር ውስጥ በሁሉም ንዑሳን ችሎቶች በአማካኝ ቢያንስ 275 ጋብቻ እየፈረሰ የሚገኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በእርቅ የተዘጉት መዛግብት ግን 77 ብቻ ናቸው፡፡[7] እዚህ ላይም በአንድ ወር ውስጥ 77 ጋብቻን ከመፍረስ ማዳን በእራሱ ሊጣጣል የሚችል ስኬት አይደለም፡፡ ምክንያቱም አንድም ጋብቻ ቢሆን ከመፍረስ መታደግ ፋይዳው ቀላል ባለመሆኑ ነው፡፡

ንፅፅሩም መሰራት ያለበት በእርቅ ከሚዘጋው የጋብቻ መዛግብት ብዛት አኳያ ሳይሆን አዲስ ከተመሰረተው የጋብቻ ቁጥር ጋር መሆን ይገባዋል ሊባል ይቻላል፡፡ በዚህም የተነሳ ውስንነቶች ሊኖሩት ይችላሉ፡፡ የተሟላም ስዕል ላይሰጥ ይችላል፡፡ ይህ የሆነው ግን በፌደራል ደረጃ ምን ያህል ጋብቻ በቀን፣ በወርና በዓመት እንደሚመሰረት ለዚህ ፅሁፍ በሚሆን መልኩ መረጃ ስላልተገኘ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ንፅፅሩ ቢያንስ ቢያንስ ፍርድ ቤትም ሆነ ሌሎች ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተቋማት (ድርጅቶች)፣ ግለሰቦች፣ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያዎች፣ አስማሚ ማዕከላት ወ.ዘ.ተ… የቱንም ያህል ጥረት ቢያደርጉም እንኳን በመጨረሻ ጋብቻውን ከመፍረስ መታደግ ሳይቻላቸው ይቀርና የጋብቻው መፍረስ የግድ ማለቱን ያመለክታል፡፡ በአንድ ወር ውስጥ በእርቅ ከሚዘጉ የፍቺ መዛግብት አንፃር በፍቺ ውሳኔ የሚዘጉትን በንፅፅር ስንመለከተውም ቁጥሩ ያለማጋነን አስደንጋጭ ነው፡፡ የሚሰጡት የፍቺ ውሳኔዎች ብዛትና የአወሳሰን ፍጥነት ጥናትን የሚጠይቁ ቢሆንም ማንም ወገን ሊክደው የማይችለው ሀቅ ግን በየቀኑ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ጋብቻ እየፈረሰ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የፍቺ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ወይም በኋላ የልጆችን ቀለብ፣ መኖሪያ ቤት የማግኘት መብት፣ አስተዳደግ፣ ጉብኝነትና ተያያዥ ጉዳዮችን አይቶ የመወሰን ጉዳይ የማይቀር ይሆናል ማለት ነው፡፡

[7] በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ 3ኛው የቤተሰብ ችሎት የግንቦት ወር 2007 ዓ/ም የችሎት ወርሃዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ይመለከቷል፡፡

# 3. የቀለብ አቤቱታ አቀራረብ፣ አወሳሰንና አፈፃፀም

## 3.1. የቀለብ ህጋዊ መሠረትና ትርጉሙ

የቀለብን ትርጉምና ይዘቱን ከመመልከታችን በፊት ስለህጋዊ መሠረቱ ትንሽ ነገር ማለት ጠቃሚ ነው፡፡ ቀለብ የመክፈል ግዴታም ሆነ የመቀበል መብት የሚመነጨው ከህግ ነው፡፡ በአንድ በኩል ቀለብ እንዲከፍል በህግ ላይ ግዴታ የተጣለበት ሰው አለ፡፡ በሌላ በኩል ቀለብ እንዲከፈለው ወይም እንዲቀበል በህጉ ላይ መብት የተሰጠው ሰው ይኖራል፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ ሰው ከአገኘው አላፊ አግዳሚ ሁሉ ቀለብ ሊቆርጥለኝ ይገባል በማለት ሊጠይቅ አይችልም፡፡

የቀለብን ትርጉም ስንመለከተው "ቀለብ" ማለት አንድ ቀለብ እንዲከፍል በህግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ቀለብ እንዲከፍለው በህግ ላይ መብቱ ለተሰጠው ሰው የሚከፍለው ክፍያ ነው፡፡ የቀለቡ ይዘትም ለምግብ፣ ለመጠጥ፣ ለልብስ፣ ለመጠለያው፣ ለጤናው መጠበቂያው፣ ለትምህርት፣ ለትራንስፖርት፣ ለመዝናኛው ወ.ዘ.ተ. ወጪዎች የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡ ክፍያውም በአይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፡፡ የተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 197 ይኸን በዝርዝር ይደነግጋል፡፡

ቀለብ የመክፈል ግዴታም ሆነ የመቀበል መብቱ የሚመነጨው ከህግ ከሆነ ግዴታው የተጣለባቸውና የመብቱ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለመለየት ብዙም አያስቸግርም፡፡ የተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 198 እና አንቀጽ 210 ስለዚህ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በቀጥታ ወላጆችና በተወላጆች መካከል የተጣለው ቀለብ የመክፈል ግዴታና የመቀበል መብት በህጉ ላይ የተዘረጋ አንደኛው ህጋዊ የግንኙነት መስመር ነው፡፡ ለምሳሌ ወላጆች ከአብራካቸው ለሚወለዱት ልጆቻቸው ወይም በጉዲፈቻ ለሚወስዷቸዉ ልጆች ቀለብ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፡፡ ይህ ህጋዊ ግንኙነት ብዙ ሰው የሚያውቀው ሲሆን በፍርድ ቤቶችም የተለመደ የክርክር ዓይነት ነው፡፡

ሌላው ቀለብ የመክፈልና የመቀበል ህጋዊ ግንኙነት የተጣለው በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል እንደሆነ ከድንጋጌው መገንዘብ ይቻላል፡

፡ እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ ቀለብ እንዲከፈለው የሚጠይቀው ወገን ቀለብ ከፋዩ በህግ ግዴታ የተጣለበት መሆኑን ማሳየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለቡ የግድ የሚያስፈልገው መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት መሆኑ ነው፡፡ በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች መካከል ግን እድሜው ከ18 በታች ለሆነ ህፃን አባትና እናት ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ እንዳለባቸው ሳይዘነጋ ነው፡፡ በዚህ ፅሁፍ ለማሳየት የሚሞከረው ወላጆች ለልጆቻቸው የሚከፍሉትን ቀለብ የአወሳሰን ሥርዓትና ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚታዩትን ችግሮች (የህግ ክፍተቶችን) በተመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡

### 3.2. የቀለብ አቤቱታ አቀራረብና የዳኝነት ስልጣን

የቀለብ ይከፈለኝ ክስ የሚቀርበው ለፍርድ ቤት በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የመወሰኑ ስልጣን የፍርድ ቤት ነው፡፡ የቀለብ ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ እልባት (ውሳኔ) ሊሰጥበት የሚችል ነው፡፡ እናም የቀለብ ጥያቄ ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍትህ ወይም ዳኝነት የሚሰጥበት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን ወደ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊትና በኋላ ጉዳዩ በሽምግልና ሊታይ የሚችልበት አግባብ የለም ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም በሽምግልና መጨረሳቸው የሚደገፍ ነው፡፡

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ስልጣኑ የፍርድ ቤት መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ማንኛውም ፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ ቢቀርብለት ሊመለከተው ይችላል ወይ? የሚለው ነው፡፡ አንዳንድ የህግ ባለሙያዎች ቀለብ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል ይከራከራሉ፡፡ ምክንያታቸው የቀለብ ጉዳይ የህፃናትን ጥቅሞችና መብቶች የማስከበር ጉዳይ በመሆኑ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ይመለከተዋል የሚል ነው፡፡ ይህ መከራከሪያቸው አያስኬድም ሊባል አይችልም፡፡

በሌላ በኩል ሌሎች የህግ ባለሙያዎች ፍቺና የፍቺ ውጤቶችን ተቀብሎ እንዲወስን ስልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤት ነው አቤቱታው መቅረብ ያለበት በማለት ይከራከራሉ፡፡ መከራከሪያቸውም የህግ መሠረት ያለው ይመስላል፡፡ የተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ፍርድ ቤት የፍቺ አቤቱታ ሲቀርብለት የልጅ ቀለብን ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥቶ ሊወስን እንደሚገባ ተደንግጎ መገኘቱን ማንሳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የልጅ ቀለብ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ከፍቺ ውጤት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው፡፡ ይህም ማለት በፌደራል ደረጃ ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፤ በክልል ደረጃ

ደግሞ ለክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ለወረዳ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችል ይሆናል ማለት ነው፡፡

ሆኖም ግን የቀለብ ጥያቄ የግድ ከፍቺ አቤቱታ ጋር ተያይዞ ብቻ ሊቀርብ የሚችል አይደለም፡፡ የቀለብ ጉዳይ እራሱን ችሎ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከፍቺና ከፍቺ ውጤት ወይም ከልጅነት አቤቱታዎች ጋር አብሮ ሊቀርብ የሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ ሳይኖር ልጅ ሊወለድ ይችላልና ነው፡፡ ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ልጆችም በጋብቻ ከተወለዱት ልጆች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ የፍቺም ሆነ የንብረት ክፍፍል አቤቱታ ሳይቀርብ የቀለብ ጥያቄ ብቻ ለፍርድ ቤት እራሱን ችሎ ወይም ከልጅነት፣ ከአባትነት፣ ከእናትነት (ከተወላጅነት) አቤቱታ ጋር አብሮ ሊቀርብይችላል፡፡ ስለሆነም የቀለብ ጥያቄ ብቻውን በቀረበ ጊዜ ፍቺና የፍቺ ውጤቶችን ተቀብሎ እንዲወስን በህግ ስልጣን ለተሰጠው ፍርድ ቤትለማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህ አንደኛው አማራጭ ነው፡፡ አለበለዚም በተጠየቀው የቀለብ ገንዘብ መጠን ልክ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት (ለምሳሌ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት) ከመቅረብ የሚከለክል ህግ የለም፡፡

አሁን ባለው አሰራር የቀለብ አቤቱታ በአብዛኛው የሚቀርበው ለፌድራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን የፌድራል ከፍተኛው ፍርድ ቤትም በመጀመሪያ ደረጃ ቀጥታ ክስነት ተቀብሎ ሲያስተናግደው ይታያል፡፡ በይግባኝ ስልጣኑ ተቀብሎ የሚመለከታቸውን ሌሎች ጉዳዮች እየተመለከተ ባለበት ሁኔታ በክርክር ሂደት ከተነሳ ሌላኛው ወገን መልስ እንዲሰጥበት አድርጐ ውሳኔ ሲያሳርፍበት ይታያል፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ፍርድ ቤት የቀለብ ጥያቄ ይመለከተኛል የሚል አቋም መያዙ ክፋት የለውም፡፡ እንዲያውም ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ የሰጡትን ትኩረትና ክብደት የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በእርግጥም ቀለብ ለልጆች በህይወት መኖር ወሳኝነት አለውና፡፡

### 3.3. የቀለብ አወሳሰን መርሆች

ቀለብ የሚወሰነው በዘፈቀደ አሰራር ሳይሆን የባለጉዳዮቹን ዓይነትና የአካባቢውን ልማድ መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡ የቀለብ ተቀባዩን መሠረታዊ ፍላጎትና ጥቅም ለማሟላት ይቻል ዘንድ የቀለብ ከፋዩን የመክፈል አቅምና ሌሎች በርካታ ነጥቦችንም ከግምት ውስጥ በማስገባት

በተቻለ መጠን ወላጆቻቸው ከመለያየታቸው በፊት ልጆቹ ያገኙት የነበረውን ጥቅም ለማስቀጠል በሚያስችል መልኩ ነው፡፡[8] ስለዚህ የተለመደው መርህ ልጆቹ ያገኙት የነበረውን ጥቅም በተቻለ መጠን ለማስቀጠል በሚያስችል መልኩ ቀለብ መወሰን አለበት የሚል ነው፡፡ ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ ህፃናትን በተመለከተም የአካባቢውን ልማድ፣ የኑሮ ሁኔታውንና የህፃናቱን ፍላጐት መሠረት በማድረግ በአግባቡ ሊያኖራቸው የሚያስችል ቀለብ እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡ ሞግዚትነት ካልተሰጠኝ ቀለብ አልከፍልም ማለት የማይቻል መሆኑ ሌላኛው ፍርድ ቤቶች የሚሰሩበት መርህ ነው፡፡ ቀለብ ካልተከፈለኝ ልጅን አላሳይም የሚለው መከራከሪያም ከመጀመሪያዉኑ ተቀባይነት እንደሌለው ግንዛቤ የተያዘበት ነው፡፡ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላም ቢሆን በስምምነት የቀለቡን ጉዳይ ለመጨረስ ከተስማሙ በስምምነት ለመጨረስ እድሉ ይሰጣቸዋል፡፡

አባትና እናት ገቢያቸውን ማዕከል ባደረገ መልኩ ለልጆቻቸው ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በተግባር ማሳየት ሌላው የአወሳሰን መርህ ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በእርግጥ ህፃናቱን በሞግዚትነት ኮትኩቶ ማሳደግ በገንዘብ የማይተመን ከፍተኛ ኃላፊነትን እንደሚጠይቅ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ልጆቹን በሞግዚትነት የሚያሳድገው ወገን በገንዘብ የማይተመን ከፍተኛ ኃላፊት ያለበት መሆኑ እውቅና ሊሰጠው የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀለብ ገንዘቡን ሲወስን ሞግዚት የሆነውን ወገን በገንዘብ ሊተመን የማይችል ኃላፊነት በአንክሮ በመመልከትና በማመዛዘን መሆን አለበት፡፡ ተመሳሳይ ገቢ ያላቸው ቢሆንም እንኳን በምንም ዓይነት ሁኔታ ሞግዚት ያልሆነው ወገን የሚከፍለው የቀለብ ገንዘብ ሞግዚት ከሆነው የላቀ መሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡ የገቢ ሁኔታቸው የተለያየ ከሆነ ደግሞ መጠኑ የበለጠ ከፍ ማለቱ አይቀርም፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ አባትም ሆነ እናት ልጆቻቸውን በማሳደግ ረገድ የገቢ ሁኔታቸውን መሠረት ባደረገ መልኩ ተመሳሳይ ግዴታ እንዳለባቸው በህጉ ላይ ተቀምጧል፡፡ እየተሰራበት ያለውም በዚህ መልኩ እንደሆነ የፍርድ መዛግብት ያመለክታሉ፡፡

---

[8] የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን ማኗልን በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ነው፡፡ እንዲሁም ቀለብ የሚወሰነው ልጆች ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት ያገኙት የነበረውን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል መነሻነት እንደሆነ በተሻሻለው የፌድራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከአንቀጽ 197 ቀጥሎ ያሉትን ድንጋጌዎች ይመለከቷል፡፡

ከዚህ አኳያ በፍርድ ቤቶች እየተወሰነ የሚገኘው የቀለብ ገንዘብ የህፃናቱን ጥቅሞች የሚያስከብር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ብር 110,000 (መቶ አስር ሺህ) ወርሃዊ ገቢ ካለው የውጪ ድርጅት ተቀጣሪ ሰራተኛ ለሁለት ልጆች በወር ብር 30,000 እንዲከፍል ተወስኖበታል፡፡ ወላጆቻቸው አብረው በአንድ ላይ ሲኖሩ በነበረበት ጊዜ ልጆች በየሳምንቱ ለመዝናናት ተብሎ ከአዲስ አበባ ውጪ የሚወጡ ከሆነ ከተለያዩም በኋላ ይህ ነገር እንዳይቋረጥባቸው መደረግ አለበት፡፡ ሲያገኙ የነበሩትን ጥቅም በተቻለ መጠን ማስጠበቅ ማለትም እነዚህን ሁሉ ነገሮች የሚያጠቃልል ነው፡፡ ወላጆች በመለያየታቸው የተነሳ ልጆች ያገኙት የነበረውን ጥቅም ማጣት የለባቸውም፡፡ በመሆኑም እየተወሰነ የሚገኘው የቀለብ ገንዘብ ልጆችን በአግባቡ የሚያኖራቸው መሆኑን ማረጋገጥ ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል፡፡

### 3.4. ገቢ የሌለው ሰውና ቀለብ የመክፈል ግዴታ

ከላይ እንደተመለከተው ቀለብ የመክፈል ግዴታ የሚመነጨው ከህግ ነው፡፡ አንድ ሰው ቀለብ የሚከፍለው ከአብራኩ ለተወለደውልጅ ወይም ለጉዲፈቻ ልጁ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በርካታ ሰዎች በችሎት ቀርበው ቀለብ እንዲቆርጡ ሲጠየቁ "ቀለብ ልቆርጥ አይገባም ምክንያቱም ገቢ (ሥራ) የለኝም" የሚል መከራከሪያ ያቀርባሉ፡፡ ይህ መከራከሪያቸው ተቀባይነት አለውን? ለመሆኑ ጤነኛ የሆነ ሰው ገቢ የለኝም በማለቱ ብቻ ቀለብ አይከፍልም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ ብዙ ሰዎችም ስለ ስራ ያላቸው አመለካከት በራሱ ችግር ያለበት ይመስላል፡፡ በርካታ ገቢ የሚያስገኙ ህጋዊ የስራ ዘርፎች እንዳሉ ያለመገንዘብ ችግር አለ፡፡ አንድ ሰው ጤነኛ ከሆነና ሌላ ሞያና ገቢ ባይኖረውም እንኳን የቀን ስራ በመስራት ገቢ እንደሚያገኝ ይታወቃል፡፡

ሌላው ደግሞ የቀለብ ውሳኔ ከተወሰነበት በኋላ ለልጆቹ ቀለብ ላለመክፈል በማሰብ ስራውን የሚለቅ ያጋጥማል፡፡ "ክቡር ፍርድ ቤቱ ስራዬን ለቅቄያለሁና ቀለብልከፍል አልችልም" የሚል ባለጉዳይ ያጋጥማል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፡፡ የጡረታ ገቢ በእዳ ወይም በመያዣ ምክንያት አይያዝም ስለሚባል ከመደበኛው የጡረታ መውጫ ዘመን አስቀድመው በፍላጐታቸው በጡረታ ይገለሉና ይህንኑ ለፍርድ ቤት በማሳወቅ ቀለብ መክፈል የለብኝም ወይም ይህ የሚታለፍ ከሆነ መጠኑ ይቀነስልኝ የሚሉ

አቤቱታዎች በተደጋጋሚ ለፍርድ ቤት ይቀርባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ አባባላቸው የህግም ሆነ የፍሬ-ነገር ምክንያት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡ ማንኛውም ሰው ጤነኛ እስከሆነ ድረስ ማንኛውንም ገቢ የሚያስገኝ ስራ በመስራት ቀለብ እንዲከፍል ይደረጋል፤ በህግም ይገደዳል፡፡ መስራት የሚችል ጤነኛ እስከሆነ ድረስ የቀን ስራ ቢሰራ ሊያገኝ የሚችለው ገቢ በወቅቱ የገበያ ዋጋ መሠረት ታስቦ ለልጅ ቀለብ እዲከፍል ይደረጋል፡፡ መስራት የማይችል ቢሆንም እንኳን ያፈራው ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለ ተሸጦ ወይም በአይነት ተገምቶ ለቀለብ መክፈያ እንዲውል ለማዘዝ የሚቻልበት የህግ መሠረት አለ፡፡

በተለይ ለልጅ ቀለብ ላለመክፈል በማሰብ ስራውን የለቀቀ መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነበት የቀለብ ገንዘብ ሊቀነስለት መቻል የለበትም፡፡ በፍርድ ቤቶች በኩል ያለው አሰራርም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ቀለብ ላለመክፈል በማሰብ አስቀድሞ በጡረታ ስለተገለለም ቀለብ ሊቋረጥ ቀርቶ ሊቀነስ መቻል የለበትም፡፡ እዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ የጡረታ አበል በእዳ ወይም በመያዣ የተነሳ አይያዝም ማለትና ጡረተኛው ከአብራኩ ለተወለዱት ልጆች ቀለብ የመቁረጥ ህጋዊ ግዴታ የለበትም ማለት ሁለት የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው ነው፡፡ ያለበለዚያ የጡረተኛ ልጅ የመኖር መብት የለውም እንደማለት መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አንዲያውም አንዳንድ ሰው ለብዙ ጊዜ ሳይወልድ ይቆይና በጡረታ መውጫ ዘመኑ ላይ አከታትሎ በመውለድ የበርካታ ልጆች አባት ሲሆን ይታያል፡፡ እናም ጡረታ በመውጣቱ ብቻ ልጆቹን የማሳደግ ግዴታ የለበትም ለማለት እንዴት ይቻላል?!! የህግ መሠረትስ ይኖረዋል?! የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጣቸው የህግ ትርጓሜዎች በበታች ፍርድ ቤቶችና ችሎቶች ላይ ተመሳሳይ የክርክር ጭብጥን በተመለከተ አስገዳጅ እንደሆነበአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (5) ላይ ተመልክቷል፡፡በዚሁ አግባብ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ከጡረታ አበል ላይ ተቀንሶ ለልጅ ቀለብ እንዲከፈል ማድረግ የሚቻል መሆኑን በማመልከት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡[9]

---

[9] የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአምስት ባለነሱ ዳኞች ስለህፃናት ቀለብ አከፋፈል በተመለከተ የሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች መመልከት ይቻላል፡፡ በተለይ የሰበር መዝገብ ቁጥር 34387 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተጠቃሽ ነው፡፡

ስለዚህ የጡረታ አበል ለልጅ ቀለብ ክፍያ የመዋሉ ጉዳይ ምንም አሻሚነት የለውም፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ከጡረታ አበል ላይ ለልጅ ቀለብ እንዲውል ትዕዛዝ እንደሚሰጡ ተረጋግጧል፡፡ ሌላው ደግሞ ጡረተኛው አስቀድሞ ከስራው በፍላጎቱ የተገለለው ሆንብሎ ለልጅ ቀለብ ላለመክፈል መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠም የቀለብ መጠኑን መቀነስ ተገቢ አይሆንም፡፡ ይሁን እንጂ ጡረታ የወጣው ጊዜው ደርሶ ወይም ጊዜው ባይደርስም በአሳማኝ ምክንያት መሆኑ ከተረጋገጠና ሌላ ምንም ዓይነት የገቢ ምንጭ የሌለው ወይም ሌላ ስራ የማይሰራ ከሆነ እንደ ሁኔታው ታይቶ የቀለብ ገንዘቡን መቀነስ ፍትሃዊ ይመስላል፡፡ ፍርድ ቤቶችም የሚወስኑት በዚሁ መልኩ ነው፡፡

## 3.5. የቀለብ ጉዳይ በፈጣን የፍትህ ሥርዓት መታየት ያለበት ስለመሆኑ

የቀለብ አቤቱታ የቀረበው እራሱን ችሎም ሆነ ከሌሎች አቤቱታ ጋር ተጣምሮ የሚታየውና የሚወሰነው በተቻለ መጠን በፈጣን የፍትህ ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ ለምሳሌ ከፍቺ አቤቱታ ጋር የልጅ ቀለብ ተጠይቆ እንደሆን ጋብቻውን ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ማፍረስ አይጠበቅበትም፡፡ ቢያንስ ከሶስት ወር ያላነሰ የማሰላሰያ ጊዜም ሊሰጥ ይገባል፡፡ ባልና ሚስቱ እንዲስማሙም ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ቀለብ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም፡፡ ስለዚህ አቤቱታው ለፍርድ ቤት እንደቀረበ ወዲያኑ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ውሳኔ ማግኘት ይገባዋል፡፡

የሚሠጠውም ቀጠሮ በአማካኝ ከ15 ቀናት በላይ የበለጠ አይደለም፡፡ በጋብቻው ላይ ተጠሪ (ተከሳሽ የሆነው ሰው) መልሱን እንዲያቀርብ ረዘም ያለ ቀጠሮ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የቀለብ አቤቱታ አብሮ ተጠይቆ ከሆነ ግን አጭር ቀጠሮ መስጠት በፍርድ ቤቶች የተለመደ አሰራር እየሆነ መጥቷል፡፡ ለፍርድ ቤት ከሚቀርቡት የቀለብ ጉዳዮች ተጠሪ የሆነው ሰው ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ከተደረገ በኋላ ወዲያኑ በመጀመሪያው ቀጠሮ እልባት የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት ከ97 በመቶ በላይ የሆኑት የቀለብ ጉዳዮች ለፍርድ ቤት በቀረቡ በመጀመሪያ ቀጠሮ (እስከ 15 ቀናት ባለው

ጊዜ ውስጥ) ውሳኔ እንደሚያገኙ መገንዘብ ይቻላል፡፡[10] በመሆኑም ቀለብ የፍተሐብሄር የአር.ቲ.ዲ (Real Time Dispatch) ጉዳይ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ሌሎቹ 3 በመቶ የቀለብ ጉዳዮች ለሁለት ጊዜና ከዚያ በላይ የተቀጠሩ ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው ተጠሪ (ተከሳሽ) ለሆነው ሰው በአግባቡ መጥሪያ ባለመድረሱ ወይም አድራሻው ባለመታወቁ ወይም ልጅነት፣ አባትነት ወይም እናትነት የተካደ እንደሆን ወ.ዘ.ተ... በመሳሰሉ ምክንያቶች ብቻ ነው፡፡ በዚህ መልኩም ተጨማሪ ቀጠሮ ተሰጥቷቸው የሚቀጠሩት የቀለብ ጉዳዮች በድምሩ ከ30 እስከ 45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንደሚወሰኑ የተዘጉና በቀጠሮ ላይ የሚገኙ መዛግብት ያመለክታሉ፡፡ እናም የቀለብ ጉዳይ በተፋጠነ የፍትህ ሥርዓት አግባብ እየታየ ነው ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ይህም ሁኔታ በጥቅሉ ሲታይ የሚያበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን በሚፈለገው ደረጃ ላይ ደርሷል ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡

የቀለብ መጠን አወሳሰን ከፍርድ ቤት ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ተከራካሪዎችን በተመለከተ ወጥነት ይጎድለዋል፡፡ ለምሳሌ በወር ብር 10,000 ገቢ ያለው አንድ ሰው ለአንድ ልጅ በወር 3000 ብር ቀለብ እንዲከፍል ሲወሰንበት ተመሳሳይ ወርሃዊ ገቢ ያለው ሆኖ ለሶስት ልጆች ግን 3000 ብር ወይም ከዚያ በታች ሲወሰንበት ይታያል፡፡ በእርግጥ በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ከወጣ በኋላ በመጠኑም ቢሆን የሚታየውን ወጥ ያልሆነ አሰራር ችግር እየቀረፈው ይገኛል፡፡

በዋናነት ችግሩ ያለው በቀለብ ጉዳይ አመልካች (ከሳሽ) የሆነው ወገን የቀለብ ከፋዩን ገቢ በሚገባ ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት አለመቻሉ ላይ ነው፡፡ በፍርድ ቤትም በኩል ቢሆን እውነትን በማጣራት ረገድ የተወሰኑ ችግሮች መኖራቸው አያጠያይቅም፡፡ በአንደኛው ወገን ቢጠየቅም ባይጠየቅም የገቢ ምንጭና መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ በሚመለከተው አካል አማካኝነት ተጣርቶ ይቀርብለት ዘንድ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት በሚል ትእዛዝ መስጠት እየተቻለ የሚሰጡ ትዕዛዞች ግን አናሳ መሆናቸው አንዱ ችግር ነው፡፡ የሚታዘዘውም አንደኛው ወገን ባመለከተ ጊዜ ሆኖ ያውም ውሱን

---

[10] በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ በ1ኛ በ2ኛውና በ3ኛው የቤተሰብ ችሎቶች የተዘጉ መዛግብትና በቀጠሮ ላይ ያሉ የቀለብ ክርክሮችን በማየት ማረጋገጥ የተቻለው የቀለብ ጉዳይ በተፋጠነ የፍትህ ሥርዓት እየተስተናገደ የሚገኝ ስለመሆኑ ነው፡፡

በሆኑ ጉዳዮች አልፎ አልፎ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የቀለብ ከፋዩን ትክክለኛ የመክፈል አቅም ባገናዘበ መልኩ መክፈል የሚገባውን ያህል ቀለብ ሳይከፍል ሊቀር ይችላል፡፡

ለምሳሌ ያህል ፍርድ ቤት ቀርቦ ምንም ዓይነት ቋሚ ገቢ የለኝም ያለ አንድ አባት ለሁለት ልጆቹ በወር ብር 400 ብቻ እንዲከፍል በመዝገብ ላይ ሊታዘዝ ችሏል፡፡ በዚሁ መልኩም ለሁለት ዓመት ያህል ሲከፍል ከቆየ በኋላ እናት የቀለብ ይሻሻልልኝ አቤቱታ አቅርባ አባትም መልስ እንዲሰጥበት ተደርጐ ሲያበቃ ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የገቢው ሁኔታ ተጣርቶ መቅረቡ ጠቃሚ ሆኖ ስለተገኘ ይኸው የታዘዘ ሲሆን ተጣርቶ በቀረበው ምላሽ ላይ የግለሰቡ ገቢ ላለፉት ሶስት ዓመታት በተከታታይ በአማካኝ በወር 12,000 በዓመት ደግሞ 144,000 እንደነበር ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ ለአንድ ልጅ ብር 1,500 ሂሳብ ለሁለት ልጆች በወር በድምሩ ብር 3,000 ቀለብ አባት እንዲከፍል ተሻሽሎ የተወሰነበት ሲሆን ይግባኝ ጠይቆም ውሳኔው በበላይ ፍርድ ቤቶች በተከታታይ ፀንቷል፡፡ ፍርድ ቤቱ በመጀመሪያው የቀለብ ክርክር ላይ የገቢው ሁኔታ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ሰጥቶበት ቢሆን ኖሮ ትክክለኛ የመክፈል አቅሙን በማየት ተመጣጣኝ የቀለብ ገንዘብ ሊወሰን በተቻለ ነበር፡፡

አንድ ፍርድ ቤት ውጤታማና ብቃት ያለው መሆኑ በተሟላ መልኩ ሊገለፅ የሚችለው እውነትን ፈልጎ በማግኘት ችሎታው ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ እውነት ላይ ለመድረስ ከሚቻልባቸው ዘዴዎች አንደኛው የተከራካሪ ወገኖችን ሚና ሳይተካ ፍርድ ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ጭምር ትክክለኛ ፍትህ[11] ለመስጠት ጠቃሚ ነው ብሎ ባመነባቸው ጭብጦች ላይ ሁሉ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ በመስጠት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በተለይ በቀለብ ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤቶች የሚወሰነው መጠን የልጆችን የመኖርና የደህንነት መብቶች የሚያረጋግጥ መሆኑን በአንክሮ መመልከት ይገባቸዋል፡፡ እርግጥ ነው ፍጥነት በቀለብ ጉዳይ ላይ ወሳኝ ነገር ነዉ፡፡ ግን ለፍጥነት ተብሎ የውሳኔው ጥራት ጥያቄ ውስጥ እንዳይወድቅ መጠንቀቅም ተገቢ ነው፡፡ ጥራት ዋንኛው የእርካታ ምንጭ መሆኑንም

[11] በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ ፍርድ ቤት የተከራካሪ ወገኖችን ሚና ሳይተካ በእራሱ አነሳሽነት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ጠቃሚ ነው ብሎ ባመነባቸው ጭብጦች ላይ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብለት ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል መሆኑ በፍትሐብሔር *ሥነ-ሥርዓት* ህጉ በአንቀጽ 257 እና በአንቀጽ 345 (1) ሰፍሮ ይገኛል፡፡

ማጤን ይገባል። ለዚህም ነው የውሳኔ ፍጥነትና ጥራት አንዱ ሌላውን ሳይተካ አብረው በእኩልነት መሻሻልና መዳበር አለባቸው የሚባለው። ጊዜያዊ ቀለብ ወስኖ ሲያበቃ ትክክለኛ የመክፈል አቅምን በማስረጃ አረጋግጦና አጣርቶ ቋሚ ውሳኔ መስጠትም አንደኛው አማራጭ መንገድነዉ።

### 3.6. የተፀነሰ ልጅ እና የቀለብ ይቆረጥ ጥያቄ

ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ መቁረጥ ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ በህግ ባለሞያዎች መካከል የቆየ ክርክር ነዉ። ቀለብ ሊቆረጥ አይገባም የሚሉ የህግ ባለሞያዎች የሚያነሱት መከራከሪያ ስለሰውና ስለሰዎች መብቶች በህጉ ላይ የተቀመጠውን አጠቃላይ አነጋገር በማንሳት ነው። ይኸውም አንድ ሰው በህግ ላይ መብት አለው ተብሎ የሚገመተው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ብቻ ነው። በፅንስ ውስጥ ያለ ወይም ያልተወለደ ህፃን በህጉ መሠረት ሰው የሚለውን መብት ገና አልተጐናፀፈም። ህፃኑ በህይወት ኖሯል የሚባለውም በህይወት ተወልዶ ለ48 ሰዓት ያህል መኖር ከቻለ ብቻ ነው።[12] ስለሆነም ህፃኑ ገና በህይወት ተወልዶ ለ48 ሰዓት ያህል መኖሩ ያልታወቀ ስለሆነ ቀለብ ሊቆረጥለት አይገባውም ይላሉ። በዓለም አቀፍ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተዉ ድንጋጌ የተፀነሰ ልጅን የሚመለከት አለመሆኑን በመጥቀስም ቀለብ ሊከፈል እንደማይገባ ክርክራቸውን ያቀርባሉ።

ቀለብ ሊቆረጥለት ይገባል የሚሉ የህግ ባለሙያዎች የሚያነሱት መከራከሪያ ደግሞ በፅንስ ውስጥ ያለ ህፃንም ሰው ነው የሚለውን ነው። በተለይ በፍትሐብሔር ህግ ስለ ሰውና ስለ ሰዎች መብት በሚደነግገው የህግ ክፍል በአንቀጽ 2 ላይ የተፀነሱ ልጆችን አስመልክቶ የተቀመጠውን አጠቃላይ ድንጋጌ በማንሳት አጥብቀው ይከራከራሉ። በዚህ ህግ ላይ የተመለከተው ድንጋጌም የተፀነሰ ልጅ በህይወት ከተወለደና የሚኖር ከሆነ የራሱ ጥቅም በሚያሻበት ጊዜ ሁሉ እንደተወለደ ይቆጠራል ይላል። የተፀነሱ ልጆችም ጥቅማቸው ጥያቄ ውስጥ በገባ ጊዜ ሁሉ እንደተወለዱ ስለሚገመት መብት አላቸው። እናም ቀለብ መቆረጥ አለበት ይላሉ።

---

[12] 'ሰው' ለሚለዉ ቃል የተሰጠው ህጋዊ ትርጉም በ1952 ዓ/ም የወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 1 እና ተከታዮቹ አንቀጾች ላይ ተመልክቷል።

ሌላው መከራከሪያቸው ቀለብ ከሚቆረጥበት መሠረታዊ ዓላማ ይነሳል፡፡ ይኸውም ቀለብ የሚቆረጠው የህፃኑን መሠረታዊ ጥቅምና የተሻለ አስተዳደግ ለማስጠበቅ በሕይወት እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡ ህፃኑ ጤናው ተጠብቆ አካሉ ተስተካክሎ ይወለድ ዘንድ የግድ ምግብ ያስፈልገዋል፡፡ የተፀነሱ ልጆች ምግብ የሚያገኙት በእናታቸው እትብት በኩል ነው፡፡ እንዲያውም ለተወለዱ ህፃናት ከሚከፈለው የቀለብ መጠን የበለጠ ቀለብ ለተፀነሱ ልጆች መከፈል አለበት የሚል አቋም አላቸው፡፡ ምክንያቱም ነፍሰ ጡር እናቶች ጤነኛ የሆነ ህፃን ይወልዱ ዘንድ የህክምና አገልግሎት፣ በየጊዜው ምርመራ እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ በእጅጉ ያስፈልጋቸዋልና ነው፡፡ በቤታቸውም ምቾታቸው ተጠብቆ መያዝ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ለተፀነሱ ልጆች የሚወሰነው ቀለብ ለነፍሰ-ጡሯ ሴት ለህክምናና ለምርመራ የሚያስፈልገውን ወጪም ጭምር ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባዋል ይላሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በዓለም አቀፉ የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መግቢያ ላይ ህፃናት በአካልና በአእምሮ ያልዳበሩ መሆናቸው የተመለከተ ስለሆነና ይህም አነጋገር የተፀነሰ ልጅን የሚመለከት መሆኑን በማንሳት ቀለብ ሊከፈል እንደሚገባ አጥብቀው ይሞግታሉ፡፡[13]

በብዙ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች በተግባር ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ እንደሚቆርጡ ታውቋል፡፡ በአንዳንድ ችሎቶችም ለነፍሰ-ጡሯ እናት ለህክምናና ለምርመራ የሚያስፈልገውን ወጪ ጭምር ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ቀለብ ይቆርጣሉ፡፡ በሌሎቹ ደግሞ በሚሰጠው ትዕዛዝ ላይ ለተፀነሰው ልጅ የሚቆረጠው የቀለብ መጠን በግልፅ ከሰፈረ በኋላ ለጤና ምርመራና ለህክምና የሚያስፈልገውን ወጪ እስከ ብር ይህን ያህል ድረስ ወይም በደረሰኝ መሰረት እንዲሸፈን ሲሉ የሚያዙበት ሁኔታ አለ፡፡ ቀጥሎ ያሉትን በመዝገብ ላይ የተሰጡ ሁለት የፍርድ ቤት ትዕዛዞችን ለአብነት መመልከት ይቻላል፡፡

1. *"ተጠሪው ከአብራካቸው ለተወለዱት ሁለት ልጆችና ለተፀነሰው(ችው) ልጅ ከግንቦት ወር 2007 ዓ/ም ጀምሮ ለአንድ ልጅ በወር ብር 1,200 ሂሳብ በድምሩ ለሶስት ልጆች 3,600 (ሶስት ሺህ ስድስት መቶ ብር)*

---

[13] ህፃናት በአካልና በአእምሮ ያልዳበሩ መሆናቸው በታህሳስ 20 ቀን 1989 ዓ/ም የፀደቀው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መግቢያ ላይ ተጠቅሷል፡፡

*በየወሩ ቀለብ ለአመልካች እንዲከፍሉ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡ የቀለብ ገንዘቡንም በየወሩ መጨረሻ ከ22ኛው ቀን ጀምሮ እስከ 30ኛው ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ተጠሪው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአመልካች ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ሳያቋርጡ ገቢ እንዲያደርጉላቸው ታዟል፡፡"*

2. *"አመልካች ነፍሰጡር መሆናቸው በተጠሪው የታመነ ጭብጥ ነው፡፡ በፅንስ ውስጥ ላለው ልጅም ተጠሪው ቀለብ ሊከፍሉ እንደሚገባ ፍርድ ቤቱ አምኖበታል፡፡ ስለዚህ ተጠሪው በአትሌትነታቸው በወር የሚያገኙትን ገቢ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከሚያዚያ ወር 2005 ዓ/ም ጀምሮ በወር ብር 7,000 (ሰባት ሺህ ብር) ቀለብ ሳያቋርጡ እንዲከፍሉ ታዟል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አመልካች በየሳምቱ ላለባቸው የሐኪም ክትትል ምርመራና ለህክምና ወጪዎች፣ ለጤና መጠበቂያቸው፣ ለሰራተኛና ተያያዥ ወጪዎች በድምሩ ብር 6,500 (ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) በድምሩ 13,500 በየወሩ እንዲከፍሉ የማዋለጃ ወጪያቸውንም በደረሰኝ መሰረት (ተጠሪ) እንዲሸፍኑ በማለት ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡ የትራንስፖርት አገልግሎትም ለመስጠት ተጠሪ ፍቃደኛነታቸውን የገለፁ በመሆኑ ይኸው እንዲፈፀም ታዟል፡፡"*

ከምሳሌዎቹ በመነሳት የቤተሰብ ችሎቶች አሰራር በጥቅሉ ሲታይ ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ በመቁረጥ ረገድ ብዙም ችግር እንደሌለባቸው ለመገንዘብ ያስችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ፅሁፍ በሁሉም ችሎቶች ያለውን የእለት ተእለት አሰራር የሚወክል ባለመሆኑ ከዚህ የተለየ ሁኔታ የለም ለማለት አያስደፍርም፡፡ ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ ሊቆረጥ አይገባም የሚለዉ ክርክር አሁንም ድረስ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ መኖሩ በእራሱ የሚያመለክተው ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ የማይቆርጡ ችሎቶች ሊኖሩ መቻላቸውን ነው፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተግባር ያለው ችግር የተፀነሰው ልጅ አባት ነው የተባለው ሰው አባትነቱን በካደ ጊዜነው፡፡ በጋብቻ ዘመን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ በጋብቻው ባል የተባለው ሰው ነው፡፡ እንዲሁም ጋብቻን በመሰለ የግንኙነት ዘመን አንድ ወንድና አንዲት ሴት አብረው ሲኖሩ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ በግንኙነቱ ውስጥ ያለው ወንድ ነው፡፡[14]

[14] በተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 126 እና አንቀጽ 130 (1)ን መመልከት ይቻላል፡፡

በእነዚህ ሁኔታዎች የህጉ ግምት ግልፅና አስገዳጅ ስለሆነ የመካድ ሁኔታዎች ብዙም አያጋጥሙም፡፡ ቢያጋጥሙም ቀለብ እንዲከፍል የመወሰን እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀለብ እንዲከፈለው የሚጠይቀው ወገን ማስረዳት የሚጠበቅበት ልጁ የተፀነሰው በጋብቻ ዘመን (ወይም እንደባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ በነበረበት ዘመን) መሆኑን ብቻ ስለሚሆን ነው፡፡

ነገር ግን ልጁ የተፀነሰው ከዚህ በላይ ከተገለፁት ሁኔታዎች ውጪ ከሆነና አባት ነው የተባለው ሰው አባትነቱን በካደ ጊዜ ፈታኝ ሁኔታ መፈጠሩ አይቀርም፡፡ በተለይ ልጅነትን የዲ.ኤን.ኤ. (DNA) ምርመራ በማድረግ ካልሆነ በቀር በሌሎች መንገዶች ተጠቅሞ ለማስረዳት በማይቻል ጊዜ ጥያቄው የበለጠ አወዛጋቢና አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ፅንሱ እስከሚወለድ ድረስ ቀለብ መቆረጥ የለበትም ማለት ፍትሃዊ አይመስልም፡፡ ምን እየበላስ በህይወት ሊወለድ ይችላል?! የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ልጅነት ሊረጋገጥ ይችላል እንዳይባል የተወለደ ልጅ የለም፡፡ አባት ነው የተባለው ሰው ቢክድም እንኳን አባትነህ እስከተባለ ድረስ ብቻ የግድ ቀለብ ሊቆርጥ ይገባል ለማለት ከቶውኑ የሚቻል አይሆንም፤ ህጋዊ መሠረትም አይኖረውም፡፡

ስለዚህ ቢያንስ ቢያንስ እናት ከማን እንዳረገዘች ማስረዳት ከቻለች ቀለብ መክፈል አለበት ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ፡፡ ለምሳሌ የጠለፋ ተግባር፣ የመድፈር ተግባር አባት ነው በተባለው ሰው የተፈፀመባት መሆኑን ወይም የወንድና የሴት ጓደኛሞች መሆናቸውን ወይም ጓደኛሞች ተብለው እንደሚታወቁ ማስረዳት ከቻለች ቀለብ መወሰን ተገቢ ነው የሚሉ አሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን ለተፀነሰ ልጅ ቀለብ ሊከፈል የሚገባው ልጅነት እስከታመነ ጊዜ ድረስ ወይም ልጅ ነው የሚያስብል ህጋዊ ግምት እስከኖረ ጊዜ ድረስ ብቻ ነው የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ በዚህ ረገድ ላለው ውዝግብ መልሱ ቀላል አይደለም፡፡ ከችሎት ችሎት ወጥ የሆነ አሰራርም የለም፡፡

ሌላው ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነጥብ የተፀነሰ ልጅ ከመወለዱ በፊት አባቱ ቢሞት አባቱን የመውረስ መብት ያለው በመሆኑ ህፃኑ እስከሚወለድ ድረስ የውርስ ሀብቱ ተጣርቶና ተከብሮ ሊጠብቀው የግድ መሆኑ ነው፡፡ ፅንሱ በህይወት ተወልዶ መኖሩ በህግ አግባብ እስከሚታወቅና የውርስ ሃብቱም እስከሚከፋፈል ድረስ ለተፀነሰው ልጅ ከውርስ ሀብቱ እየተቀነሰ ቀለብ ለእናት መከፈል አለበት፡፡ የተፀነሰ ልጅ በህይወት ሊወለድ

የሚችለው በፅንሱ ውስጥ እያለ ተገቢውን ምግብና መጠጥ በእናቱ አማካኝነት ማግኘት እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ቀለብ የመቁረጥ አንገብጋቢነትም መታየት ያለበት ከዚህ መሠረታዊ ነጥብ አኳያ ነው፡፡

### 3.7. ቀለብ አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ እንደገና ሊሻሻል የሚችል ስለመሆኑ

ቀለብ አንድ ጊዜ በፍርድ ቤት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ 'አንሶኛል' ወይም ደግሞ 'በዝቶብኛል' የሚል ወገን ካለ ወይም በውሳኔው ቅር የተሰኘ ወገን ካለ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታውን የማቅረብ መብት አለው፡፡ ከዚያም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን አይቶ የሥር ፍርድ ቤት የወሰነዉን የቀለብ መጠን ሊቀንሰው፣ ሊያሻሽለው ወይም ደግሞ ሊያፀናው የሚችልበት አግባብ አለ፡፡ ይህ አካሄድ በማንኛውም የፍትሐብሄር ክርክር ያለ አሰራር ነው፡፡ ለተከራካሪ ወገኖችም የተሰጠ መብት ነው፡፡

ይህ የተለመደ አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ ምክንታዊ ሊባል የሚችል ጊዜ ጠብቆ ሲያበቃ የቀለብ ውሳኔውን ለወሰነው ፍርድ ቤት 'የቀለብ ይሻሻልልኝ' አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ 'የቀለብ ይሻሻልለኝ' አቤቱታ የሚያጠቃልለው የተወሰነው ቀለብ ሊጨመርልኝ ይገባል ወይም ደግሞ በዝቶብኛልና ሊቀነስለኝ ይገባል የሚሉትን ሊሆን ይችላል፡፡ የተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 203 ይህን በግልፅ ያመለክታል፡፡ በዕርግጥ በፍትሐብሄር ክርክር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ውሳኔ ባረፈበት ጉዳይ ተከራካሪ ወገኖቹና የተያዘው ጭብጥ ተመሳሳይ ወይም አንድ ዓይነት ከሆነ በዚያው ጉዳይ ላይ ዳግመኛ ሊከሰስና ዳኝነት ሊጠየቅበት አይችልም፡፡

ይህ አጠቃላይ የህጉ አነጋገር ግን በቀለብ ጉዳይ ላይ አይሰራም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የልጅ ቀለብ እጅግ አንገብጋቢ ከመሆኑም በተጨማሪ ህፃናት በየጊዜው ፍላጐታቸው እየጨመረና እያደገ እንደሚሄድ ይታመናል፡፡ ይህንን ሁኔታ የአገሪቱ የህግ አውጪ አካል ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀለብ በአንድ ፍርድ ቤት አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ በሌላ ጊዜ ተመልሶ ሊታይ እንደሚገባ አቋም ወስዶበታል፡፡ እናም የልጆችን ፍላጐትና በየጊዜው የሚከሰተውን የኑሮ ሁኔታ በመመልከት እንዲሁም የቀለብ ከፋዩን ገቢ መጨመር ከግምት ውስጥ በማስገባት የቀለብ ይጨመርለኝ አቤቱታ ሊቀርብ ይችላል፡፡ የቀለብ ይሻሻልልኝ አቤቱታ ተቀባይነት የሚያገኘውም

ፍርድ ቤቱ አዲስ የተፈጠረውን ሁኔታ ቢያውቅ ኖሮ ውሳኔው የተለየ ሊሆን የሚችል መሆኑን ካመነበት ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩል ቀለብ እንዲከፍል የተወሰነበት ሰው ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ገቢው ሊቀንስ አለበለዚያም ከነ-አካቴው ሊቆም ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ሁኔታ ገልፆና ማስረጃውንም አይይዞ የተወሰነበት ቀለብ እንዲቀነስለት የቀለብ ይሻሻልልኝ አቤቱታ ለማቅረብ መብት አለው፡፡ ግን የተወሰነብኝ ቀለብ ሙሉ በሙሉ ሊነሳልኝ ይገባል የሚል አቤቱታ ሊቀርብ አይችልም፤ ቢያቀርብም ከህግ አንፃር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም አባት ለወለደው ልጅ ቀለብ የመክፈል ግዴታ አለበትና ነው፡፡ ማናቸውንም ህጋዊ ሥራ በመስራት ከአብራኩ ለተወለደው ልጅ ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በእርግጥ ገቢው መቀነሱ ከተረጋገጠ የሚከፍለው ቀለብም በተመሳሳይ መልኩ ሊቀንስ ይችል ይሆናል፡፡ ከነጭራሹ ግን ቀለብ ከመክፈል ግዴታው ነፃ ሊሆን የሚችልበት የህግም ሆነ የፍሬነገር ምክንያት የለም፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በፍርድ ቤት የሚጋጥመው ችግር የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 5 መሠረት እንደማይታገድ እየታወቀ አቤቱታው በቀረበ ጊዜ ሁሉ ሌላኛው ወገን ይህንኑ የህግ አንቀጽ በመጥቀስ የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ የሚያቀርብ መሆኑ ነው፡፡ ቀለብ አንድ ጊዜ ከተወሰነ በኋላ ይሻሻልልኝ የሚል አቤቱታ ጉዳዩን መጀመሪያ ላየው ፍርድ ቤት በሌላ ጊዜ ሊቀርብ እንደሚችል በህጉ ላይ ተመልክቶ ይገኛል፡፡ ህጉም በዚህ ረገድ አሻሚነት ያለው አይመስልም፡፡ በተጨማሪም የፍርድ ቤቱ ህጋዊ አቋምና ብይን ምን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኛነት እየታወቀ ጭምር መቃወሚያው ይቀርባል፡፡ ይህ የሚሆነውም መቃወሚያውን በማቅረብ ተጨማሪ ቀጠሮ ለማሰጠት (ጉዳዩን ለማጓተት) ታስቦ እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የብዙ ዓመት የስራ ልምድና የህግ ችሎታው ያላቸው ጠበቆችም ሳይቀሩ በተደጋጋሚ ይህንን መቃወሚያ በማንሳት ሲከራከሩ ይስተዋላልና ነው፡፡

### 3.8. የቀለብ ውሳኔ አፈፃፀም

የቀለብ ውሳኔ የሚፈፀመው ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ ቀለብ ከፋዩ የመንግስት ሰራተኛ ከሆነ ተቀጥሮ በሚሰራበት መስሪያ ቤት በኩል ከደመወዙ ላይ ከፔይሮል እየተቀነሰ ለቀለብ ተቀባዩ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ፡፡ ቀለብ ከፋዩ በቀለብ ተቀባዩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር አማካኝነት ገንዘቡን እንዲያስገባ የሚደረግበት ሁኔታም አለ፡፡ አለበለዚያም ቀለብ ከፋዩ ለቀለብ ተቀባዩ በአካል ወይም በሶስተኛ ወገን አማካኝነት ገንዘቡን እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ወይም በፍርድ ቤቱ ፋይናንስ ክፍል በአደራ በሲ.ፒ.ኦ.(C.P.O.) ገንዘቡን እንዲያሲዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሆኖም ግን በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሠረት ቀለብ ከፋዩ ለቀለብ ተቀባዩ መክፈል ካልቻለ (ፍቃደኛ ካልሆነ) ምን ሊደረግ ይቻላል? የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ይፈፀም ዘንድ አቤቱታው የሚቀርበው ለማን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ እንደሚታወቀው የቀለብ ውሳኔ እንደማናቸውም የፍትሐብሄር ውሳኔ የሚታይ ነው፡፡ ስለዚህ ቀለብ ተቀባዩ ውሳኔውን ይዞ እንደፍርዱ እንዲፈፀምለት አቤቱታውን ለፍርድ አፈፃፀም ችሎት ወይም ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቀለብ ከፋዩም በህግ ተገዶ አስፈላጊ ከሆነም ታስሮ ቀለቡን እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ አለ ማለት ነው፡፡ ጉዳዩ በክርክር ላይ የሚገኝ ከሆነ ብዙ ጊዜ የቀለብ ውሳኔውን የሚያስፈፅመው ፍርዱን (ውሳኔውን) የሰጠው ፍርድ ቤት እንደሆነ ተግባራዊ አሰራሩ ያሳያል፡፡ ለቀለብ ተቀባዩ የበለጠ አመቺና ቀልጣፋ የሚሆነውም ፍርዱን (ውሳኔውን) የሰጠው ፍርድ ቤት ቢያስፈፅመው ነው፡፡ ከፍርድ አፈፃፀም ችሎቱ ጋር ሊፈጠር የሚችለውን አላስፈላጊ መጓጓትም ያስቀራል፡፡

ገቢ የሌለው ሰው የተወሰነበትን የቀለብ ገንዘብ አልከፍልም ካለም እንደማንኛውም የፍርድ ባለእዳ እንዲከፍል ሊገደድ የሚችልበት የህግ መሠረት አለ፡፡ ፍርድ ቤት ቀርቦ ሀብት የለኝም በማለቱም መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመላሽ ሊደረግ አይገባውም፡፡በፍትሐብሄር ክርክር የፍርድ ባለእዳ የሆነ ሰው ሀብት የለኝም ካለና የፍርድ ባለመብቱም የባለእዳውን ንብረት አጣርቶ ሊያቀርብ ካልቻለ ባለእዳው ሀብት ባገኘ ጊዜ መዝገቡ የሚንቀሳቀስ ሆኖ ለጊዜው መዘጋቱ አይቀርም፡፡ እስከ አስር ዓመት

ባለው የጊዜ ገደብም ባለእዳው ሐብት ያገኘ እንደሆነ የፍርድ ባለመብቱ መዝገቡን የማንቀሳቀስ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡[15]

በቀለብ ጉዳይ ግን ይህ የተለመደው መከራከሪያ አይሰራም፡፡ ባለእዳው ገንዘቡን እስከሚከፍል ወይም እየሰራ እንደሚከፍል ማረጋገጫ ለፍርድ ቤቱ እስከሚሰጥ ወይም ፍቃደኛነቱን እስከሚያሳውቅ ድረስ መታሰር እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም የልጅ ቀለብ ጊዜ የማይሰጥ አንገብጋቢ ስለሆነ ነው፡፡ በተግባርም ሲታይ ሁሉም የፌደራል ቤተሰብ ችሎቶች (የአፈፃፀም ችሎቱን ጨምሮ) አሰራራቸው ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ያለማጋነን ሁሉም ችሎቶች የቀለብ ገንዘብን በማስከፈል ረገድ ጥብቅ አቋም አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ የፍርድ ባለእዳው ቀለቡን አልከፍልም በማለቱ የተነሳ እንደሚታሰር ሲነገረው ወዲያዉኑ በሚያስገርም ፍጥነት የእስራት ማዘዣዉ ከፍርድ ቤቱ ከመውጣቱ በፊት ገንዘቡን ተበድሮም ቢሆን ይከፍላል፡፡ እንዲሁም ባለእዳው ለተወሰኑ ቀናት ያህል ከታሰረ በኋላ ቀጠሮው ሳይደርስ ወይም በቀጠሮው ቀን ይከፍላል ወይም ለመክፈል ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ይህ ሁኔታ በግልፅ የሚያመለክተው የቀለብ ውሳኔ በአግባቡ እየተፈፀመ የሚገኝ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በዚህ ረገድ የፍርድ ቤቶች አቋም አስቀድሞ ተገማች እየሆነ መምጣቱን ጭምር ነው፡፡

እዚህም ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነጥብ ቀለቡን እየሰራ ከሚከፍል ይልቅ መታሰርን የሚመርጥ የፍርድ ባለእዳ አልፎ አልፎ የሚያጋጥም መሆኑ ነው፡፡ ቁጥሩ ቀላል የማይባል ሰው ከአብራኩ ለተወለደው ልጅ አስቀድሞ ሳይጠየቅ በእራሱ ፍላጎት የተወሰነበትን የቀለብ ገንዘብ (ከዚያም በላይ ጨምሮ) እንደሚከፍል ይታወቃል፡፡ ከዚህ አለፍ ያለ ነገር ሲያጋጥምም ሰው በተፈጥሮው ነፃነትን አብዝቶ የሚሻ ፍጡር በመሆኑ ቀለብ ከመክፈል መታሰርን ስለማይመርጥ ወዲያዉኑ ወይም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ይፈፅማል ወይም ለመፈፀም ይስማማና ዋስትና ይሰጣል፡፡ ለወለደው ልጅ ቀለብ አልከፍልም በማለቱ ምክንያት ታሰረ መባልንም ብዙ ሰው በእጅጉ አይፈልግም፡፡ ነገር ግን የሚያጋጥመው

[15] በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር የሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 384 ላይ እንደተመለከተው አንድ የተወሰነ ፍርድ ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ እንደፍርዱ ይፈፀም ዘንድ ለፍርድ ቤት ካልቀረበ በአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ይታገዳል፡፡ ሆኖም ግን የፍርድ ባለእዳው የተወሰነበትን ገንዘብ ለመክፈል አቅም ከሌለውና ባለመብቱም ሀብቱን አጣርቶ ለመቅረብ ካልቻለ መዝገቡ ለጊዜ ባለእዳው ሀብት እስከሚያገኝ ድረስ ይዘጋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ቢሆንም "መታሰር እኮ ለእኔ አዲስ ነገር አይደለም" የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡ እንዲያውም በየቀጠሮው እለት ፍርድ ቤት ቀርበው ሲጠየቁ ምንም የአቋም ለውጥ የማያሳዩ ይባስ ብሎም ከጊዜያዊ ማረፊያ ቤት (ፖሊስ ጣቢያ) ወደ ማረሚያ ቤት እንዲላኩ የሚጠይቁ ሆነው ይገኛሉ፡፡[16]

ይህን አስመልክቶ የተወሰኑ ዳኞች ባለእዳው የሚፈለግበትን የቀለብ ገንዘብ እስካልከፈለ ወይም እየሰራ ለመክፈል ፈቃደኛ እስካልሆነ ወይም ማረጋገጫ እስካልሰጠ ድረስ መታሰሩ መቀጠል አለበት ብለው ሲከራከሩ፣ ሌሎች ደግሞ እስከመቼ ድረስ ነው ሊታሰር የሚገባው የሚል ተገቢነት ያለው ጥያቄ ያነሳሉ፡፡ በወንጀልም ጉዳይ ቢሆን ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ሰው የሚታሰርበት ጊዜ ገደብ አለው፡፡ "ቀለብ ክፈል ከምትሉኝ እሰሩኝ" የሚል ባለእዳ ግን እስከመቼ ድረስ ነው ሊታሰር የሚችለው? የሚለው ጥያቄ በአንክሮ መታየት የሚገባው ነው፡፡ የልጁስ የመኖር መብት አደጋ ላይ አልወደቀም ወይ? ሊባል ይችላል፡፡ ሁለቱም አቋሞች አግባብነት ያላቸው ይመስላሉ፡፡ ጥያቄዎቹም ቀላል መልስ የላቸውም፡፡ እንዲህ ዓይነት አስቸጋሪ ባለጉዳዮች (ተከሳሾች) ሲያጋጥሙ ለፍርድ ቤቶች ፈታኝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ቁም ነገሩ ያለው የዳኝነት ስራ ለችግሮች መፍትሄ መስጠት መሆኑን በውል ተገንዝቦ ሚዛናዊና ህጋዊ አቋም በመያዝ እልባት መስጠት መቻሉ ላይ ነው፡፡ በዚህ መሀልም ህፃናት እንዳይጐዱ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በተቻለ መጠን ማፈላለግ አግባብነት ይኖረዋል፡፡ ባለእዳውም ቢሆን ያለገደብ እንዳይታሰር መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

### *3.8.1. ሳይከፈል የቆየ ውዝፍ ቀለብ እንዲከፈል ስለመጠየቅ*

በመርህ ደረጃ ቀለብ ጠያቂው ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር ለሶስት ወር ያህልና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ሳይከፈል የቆየ ውዝፍ ቀለብ እንዲከፈል ለመጠየቅ እንደማይቻል በህጉ ላይ ተመልክቶ ይገኛል

[16] በዚሁ የሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 386 (4) እና አንቀጽ 387 (1) ሥር እንደተጠቀሰው ማንኛውም የፍርድ ባለእዳ አቅም እያለው እንደፍርዱ ለመፈፀም ፍቃደኛ ካልሆነ ወይም አፈፃፀሙን በማኛቸውም መንገድ ካሰናከለ ወይም ንብረቱን ወይም ከፍርድ ቤቱ ስልጣን ክልል ውስጥ ለማሸሽ ከሞከረ ወይም እራሱን ለመሰወር ማቀዱን የሚያመለክት በቃለ-መሃላ የተደገፈ ማመልከቻ ከቀረበለት ፍርድ ቤቱ ባለእዳው እንዲታሰር ትዕዛዝ ለመስጠት የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀለብ ጉዳይ ባለእዳው የተወሰነበትን ገንዘብ ለመክፈል ካልቻለ ወይም ፍቃደኛ ካልሆነ በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ስድስት ወር በሚደርስ ቀላል እስራት ሊታሰር እንደሚችል በወንጀል ህግ አንቀጽ 458 ላይ ተመልክቷል፡፡

(የተሻሻለው የፌድራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 206 ይመለከቷል)፡፡ ምክንያቱም ቀለብ አንገብጋቢ ስለሆነ በየጊዜው ሳይቋረጥ መጠየቅ አለበት ከሚል እሳቤ በመነሳት ይመስላል፡፡ ድንጋጌው ቀለብ ተቀባዩም በየጊዜውና በየወሩ ሊጠይቅ እንደሚገባው አመላካች ነው፡፡ ስለዚህ በእራሱ ቸልተኛነት ወይም ጥፋት ምክንያት ሳይጠይቅ ቀርቶ ለሶስት ወር ያህልና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ተጠራቅሞ የቆየን ውዝፍ ቀለብ እንዲከፍል ሊጠየቅ እንደማይችል በህጉ ላይ ተደንግጓል፡፡

ነገር ግን ይህ ድንጋጌ ቀለብ ከፋዩ ፈቃደኛ ባለመሆኑ የተነሳ ወይም አድራሻውን ሆን ብሎ በመደበቁ ምክንያት ሊገኝ ስላልቻለ የተጠራቀመ ውዝፍ ቀለብን የሚመለከት አይመስልም፡፡ በዚህ መልኩ የተጠራቀመ ውዝፍ የቀለብ ገንዘብ ከሆነ ሊከፈል መቻል የለበትም ወይ? የሚል ጥያቄ ማንሳት ፍትሃዊነት ያለው ነው፡፡ ቁምነገሩ ያለው ቀለብ ጠያቂው ውዝፍ ገንዘቡ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በማስረዳትና ባለማስረዳቱ ላይ ነው፡፡ ውዝፉ የቀለብ ገንዘብ የተጠራቀመው ጠያቂው መጠየቅ እየቻለ በእራሱ ጥፋት ከሆነ ወይም ስላልቸገረው ከሆነ ሊጠየቅ የሚችልበት ሁኔታ ያለ አይመስልም፡፡ በተግባር ያለው አሰራርም የሚያመለክተው ከሶስት ወር በላይ የተጠራቀመ ውዝፍ የቀለብ ገንዘብ እንዲከፈል የሚጠየቅ መሆኑን ነው፡፡

የፍርድ ቤቶች አቋም በዚህ ረገድ ወጥነት ያለው አይመስልም፡፡ አንዳንዴ ውዝፉን አስገድደው ሲያስከፍሉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ህጉን ጠቅሰው ውድቅ የሚያደርጉበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይሁን እንጂ የተጠየቀው ውዝፍ ገንዘብ የሚፈለገው የልጆችን ትምህርት ቤት ክፍያ ለመክፈል ከሆነና ውዝፉ ካልተከፈለ በቀር ልጆቹ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ የሚገደዱ ከሆነ ባለእዳው ተገዶ እንዲከፍል ማድረግ የልጆቹን መሠረታዊ ጥቅም ማስከበር ነው፡፡ ውዝፉ የሚያስፈልገው የቤት ኪራይን ለመክፈል፣ ህፃናቱን ለማሳከም፣ የተጠራቀመ የመብራትና የውሃ ክፍያ ለመፈፀም ወ.ዘ.ተ.... ከሆነም በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲከፈል ማድረግ የህፃናቱን ጥቅም ከማስከበር ጋር የተያያዘ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል፡፡ ውዝፉ የተጠየቀው ህፃናቱ መጉብኘት የነበረባቸውን ታሪካዊ ቦታ እንዲጉበኙ ለማድረግ ወይም በከተማው ውስጥ ወይም ወጣ ብለው እንዲዝናኑ ለማስቻል ነው ከተባለስ ሊከፈል ይገባል? አይገባም? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ሊያከራክር የሚችል ነዉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ወጪዎች የግድ መከፈል አለባቸው

ለማለት ጉብኝት ወይም መዝናናት ለኑሮ አስፈላጊ መሆናቸውን ቀለብ ጠያቂው ማስረዳትና ዳኞችም በዚህ ማመን ያለባቸው በመሆኑ ነው። በፍርድቤቶችም የሚወሰደውም አቋም ወጥነት የለዉም።

## 4. የህፃናት አስተዳደግና ጉብኝት

### 4.1. ሞግዚትና አሳዳጊነት

የልጆችን አስተዳደግና ጉብኝት አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮችለፍርድ ቤት የሚቀርቡት ከፍቺ አቤቱታ ጋር አብረው እንደሆነ ተግባራዊ አሰራሩ ያመለክታል። አልፎ አልፎ ቢሆንም ከጋራ ንብረት ዝርዝር የክፍፍል አቤቱታጋር ሲቀርብ ይስተዋላል፡ ለዚህም ነው ልጆች የተወለዱት በጋብቻ ወይም ጋብቻን በመሠለ የግንኙነት ዘመን በሆነ ጊዜ ሁሉ የልጆች አስተዳደግና ጉብኝት ጉዳዮች ከፍቺ ውጤት ክርክሮች ውስጥ የሚመደቡት። በቋሚነት ውሳኔ የሚሰጥባቸውም ጋብቻው በፍርድ ቤት ውሳኔ ከፈረሰ በኋላ ወይም የግንኙነቱን መቋረጥ ተከትሎ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም ተመሳሳይነት ካላቸው የልጅነት፣ የአባትነት፣ የቀለብ አቤቱታዎች ወ.ዘ.ተ.... ጋርም አብሮ ሊቀርብ የሚችል ነው። ስለሆነም ከዚህ ቀጥሎ የልጆችን አስተዳደግና ጉብኝት ጉዳዮች በተመለከተ በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች እንዴት እንደሚወሰን አጠር ባለ መልኩ ይቀርባል።

### 4.2. አንደኛው ወላጅ በሌለ ወይም ባልታወቀ ጊዜ የሞግዚትነት አወሳሰን

ልጆች የተወለዱት ከጋብቻ ውጪ ባለ ግንኙነት (በአንድ ጊዜ አጋጣሚ፣ በመደፈር፣ በጠለፋ ወ.ዘ.ተ.... ተግባር ከሆነ) የአባትነት ጥያቄውም ብዙጊዜ ስለሚካድ የአባትነት (የልጅነት) ጭብጡ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ታይቶና በማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስም ልጆችን የመጠበቅ ኃላፊነቱ ወዲያዉኑ በእናት ላይ ማረፉ አያጠራጥርም። በዚህ መልኩ የተወለደ ልጅ ወላጅነት የሚረጋገጠውም በፍርድ ቤት ነው። በሌላ በማንኛቸውም ሁኔታ አባት ባልታወቀ (በተካደ) ጊዜ እናት የህፃኑ ጊዜያዊ ተንከባካቢ፣ ጠባቂና አሳዳጊ ትሆናለች ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ህፃን ከወላጆቹ አንደኛው በህይወት የሌለ ከሆነ ወይም በህግ ችሎታ ካጣ (ብቃት የሌለው ከሆነ) ሌላኛው ወገን

የሞግዚትነትና የአሳዳጊነት ስልጣን ይሰጠዋል፡፡[17] ምክንያቱም ከወላጆች አንደኛው በህይወት ባለበትና ልጆቹንም ለማሳደግ ፍላጐቱና አቅሙ እያለው ለሌላ ሶስተኛ ወገን የአሳዳጊነት ስልጣን ሊሰጥ የሚችልበት ሁኔታ የህጉን መንፈስ የተከተለ አይሆንምና ነው፡፡ የህፃናቱንም ጥቅም ከማስከበር አኳያም የሚደገፍ አይደለም፡፡

ነገር ግን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ለህፃኑ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የሞግዚትነት ስልጣን ከወላጆች ውጪ ለሆነ ግለሰብ ሊሰጥ እንደሚችል በሰበር መዝገብ ቁጥር 23632 ጥቅምት 26 ቀን 2000 ዓ/ም በዋለው የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ እንዲሁም ስለልጆች አስተዳደግ በሚመለከት በወላጆች የተደረገ ኑዛዜም ቢሆን ጥቅማቸውን የማያስጠብቅ ሆኖ ከተገኘ ሊሻር እንደሚገባ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰበር መዝገብ ቁጥር 35710 ውሳኔ የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡ የበታች ፍርድ ቤቶችም ለህፃናት ጥቅም እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ሲታመንበት በተግባር ከወላጆች ውጪ ለሆነ ሰው የሞግዚትነት ስልጣን አልፎ አልፎ እንደሚሰጡ ታውቋል፡፡

### 4.3. በጋራ የሞግዚትነት (የአሳዳጊነት) ስልጣን መስጠት

በጋብቻ ዘመን ወይም እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው ሲኖሩ የተወለዱ ልጆች ሆነው ይህ ጋብቻም ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ (ወይም በግንኙነቱ እስካሉበት ጊዜ ሁሉ) ልጆቹን የማሳደግ ኃላፊነት የሁለቱም ወላጆች የጋራ ስልጣን ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን ፍቺ በተፈፀመ (በተለያዩ) ጊዜ ልጆቹን ማን ሊያሳድጋቸው ይገባል የሚለው ጥያቄ አብሮ የሚነሳና እልባት የሚሻ ነው፡፡ ባልና ሚስት በስምምነት ከተፋቱ (ከተለያዩ) የልጆቻቸውን አሳዳጊነትና ሞግዚትነት ጉዳይም በስምምነት እንዲወስኑ የተሻሻለው የፌድራል የቤተሰብ ህግ በአንቀጽ 221 (1) ላይ መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ

[17] ስለሞግዚትነትና አሳዳጊነት በተሻሻለው የፌደራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 220 እና ተከታዮቹን መመልከት ይቻላል፡፡ ከወላጆች አንደኛው የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ ከቤተሰብ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ፣ ወ.ዘ.ተ.እንደሆነ ሌላኛው ወላጅ የሞግዚትነቱን ስልጣን ይዞ ይቆያል፡፡ ወይም በማኛቸውም ሌላ ሁኔታ የልጁ አባት ያልታወቀ እንደሆን እናት ሞግዚት እንደምትሆን ያመለክታል፡፡

ረገድ የህጉ ግምት የተፋቱት (የተለያዩት) ባልና ሚስት የልጆቻቸው ጉዳይ በቀጥታ ይመለከታቸዋል የሚለውን ነው፡፡

ስለዚህ ብዙ የተለመደ አይደለም እንጂ የተሻለው አማራጭ ሁለቱም ወላጆች የወለዷቸውን ልጆች በጋራ እንዲይዟቸው (እንዲያሳድጓቸው) [joint custody] መፍቀድነው፡፡ መግባባት የሰፈነበት የህፃናት አጠባበቅ ስምምነት ሲኖር ተግባራዊ የሚሆን ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እያንዳንዱ ወላጅ እኩልና ህጋዊ የሆነ ልጆቹን የመያዝ (የማሳደግ) ወይም የመጠበቅ ስልጣንና መብት ይኖረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም ህፃናቱ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ከአንደኛው ወገን ጋር ሆነው እንዲኖሩ እንዲሁም የተወሰነውን ጊዜ ደግሞ ከሌላኛው ወገን ጋር ሆነው እንዲኖሩ በማድረግ የሚያዝበት አግባብ ይኖራል ማለት ነው፡፡ የህፃናቱን መሠረታዊ ጉዳዮች ሁለቱም ወላጆች በጋራ የሚወስኑበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ይህ ዓይነቱ የአሳዳጊነት ሥርዓት ሊሰራ የሚችለው አባትም ሆነ እናት በጋራ ለመስራትና ህፃናቱን ለማሳደግ በተስማሙ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በፍቺ ውሳኔውም ላይ ወላጆቹ በአንድ አገር ውስጥ እንዲኖሩ ማዘዝ የግድ ተገቢ ይሆናል፡፡ ያለበለዚያ አንደኛው ወገን ህፃናቱን ይዞ ሌላው ወገን ሳያውቅ ከአገር ሊወጣ ይችላል፡፡ በመሠረቱ ልጆችን በጋራ የመጠበቅ (የማሳደግ) አማራጭ የበለጠ ተወዳጅ/ተመራጭ/ የሚሆነው ጋብቻው ከፈረሰ በኂላም ቢሆንም የቤተሰቡን አንድነት (Family integrity) በተቻለ መጠን ይዞ የመቀጠል ባህሪ ስላለው ነው፡፡ ወላጆቻቸውን በእኩልነት ያገኟቸዋል፡፡ ለህፃናቱም የወላጆቻቸው መለያየት ብዙም እንዳይሰማቸው ያደርጋል፡፡

### 4.4. ስምምነት በሌለ ጊዜ ሞግዚት አሰያየም

በባልና በሚስት መካከል ተመስርቶ የነበረው ጋብቻ እንዲፈርስ አቤቱታ በሚቀርብ ጊዜ የፍቺው ጉዳይ ታይቶ ከመወሰኑ በፊት ፍርድ ቤቱ ቅድሚያ መመልከት የሚጠበቅበት መሠረታዊ ነጥብ ህፃናቱ ቀለብ እንዲያገኙ ማድረግ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከቀለቡ ጉዳይ ቀጥሎ አለበለዚያም ጐን ለጐን አብሮ የሚታየው አንኳር ጭብጥ ከአብራካቸው የሚወለዱት ወይም ጉዲፈቻ ያደረጓቸዉ ህፃናት በቋሚነት (ወይም በጊዜያዊት) ከማን ጋር ሆነው ቢያድጉ ይሻላል የሚለውን የአስተዳደጋቸውን ሁኔታ በተመለከተ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ህፃናት የነገው አገር ተረካቢ (አምራች ዜግነታቸው) የሚመሰረተው በዛሬው አያያዛቸውና አስተዳደጋቸው ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች አስተዳደጋቸውን በመወሰን ረገድ በህግ የተጣለባቸው

ኃላፊነት ከፍተኛ ነው፡፡ ውሳኔ ሰጪ አካላት የልጆችን አስተዳደግ በተመለከተ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ለደህንነታቸውና ለመልካም አስተዳደጋቸው በሚበጅ መልኩ ብቻ ነው፡፡[18]

እንደሚታወቀው ዳኞች የህግ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ልጆች ከማን ጋር ሆነው ቢያድጉ ይሻላል የሚለውን ጭብጥ አይቶ ለመወሰን የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የሙያ እገዛና አስተያየት ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የህፃናት አስተዳደግ በፍርድ ቤቶች ሲወሰን የነበረው አልፎ አልፎ የሚደረጉ ውስን ጥረቶች የነበሩ ቢሆንም በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ተደግፎ አልነበረም፡፡ በእርግጥ ዳኞች ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት አስፈላጊዉን መረጃና ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ ሆኖም ግን ማስረጃው በዋናነት የሚገኘው ተከራካሪ ወገኖቹ በችሎት ከሚያቀርቡት የቃልና የፅሁፍ ክርክርና ማስረጃ በመነሳት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ሲሰጡ የነበሩት ውሳኔዎች የህፃናቱን መሠረታዊ ጥቅሞችና መብቶች በማስከበር ረገድ የተዋጣላቸው ነበሩ ለማለት አያስደፍርም፡፡

ከ1997 ዓ/ም ወዲህ ግን የህፃናት አስተዳደግ በፌደራል የቤተሰብ ችሎቶች በዋናነት የሚወስነው በማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያዎች የሙያ አስተያየት እየታገዘነው፡፡ በተለይ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን አስፈላጊነት ከፍተኛ ግምት በመስጠት የስራ መደብ በማስከፈት የፍርድ ቤት አካል ሆነው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰው ኃይል አደረጃጀትና አወቃቀር ላይ ተካትተው የማይተካ ሚናቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በባለሞያ እንዲታገዝ በማድረግ የህፃናትን የተሻለ ጥቅም በማስከበር ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡፡

ህፃናት ከማን ጋር ሆነው ሊያድጉ ይገባል የሚል ጭብጥ በፍርድ ቤት በተነሳ ጊዜ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየታቸውን

---

[18] ውሳኔ ሰጪ አካላት የልጅ አስተዳደግን በሚመለከት ውሳኔ ለመስጠት መነሻ ማድረግ ያለባቸው መርህ በተሻሻለው ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 218 ሥር የተመለከተ ሲሆን ይህም ለደህንነታቸውና መልካም አስተዳደግ በሚበጅ መልኩ ታይቶ መሆን ይገበዋል የሚለው ነው፡፡

እንዲሰጡበት ማድረግ የተለመደ አሰራር ሆኗል፡፡ ባለሞያዎቹም ግራ ቀኙን አስቀርበው የሙያው ሥነ-ምግባር በሚጠይቀው አግባብ የመግባቢያ ሰነድ ይፈራረማሉ፤ ገቢያቸውን እንዲገልፁ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም ጉዳዩን በሰፊው በማጥናት ግራ ቀኙንና ህፃናቱን በማነጋገር የቤት ለቤት የዳሰሳ ጥናትም አድርገው የኑሮ ሁኔታቸውን በአይናቸው አይተው ቃለ-መጠይቃቸውን አቅርበው የሚሰጠውን ምላሽ ሞልተው በመጨረሻ ሪፖርታቸውን ለፍርድ ቤቱ በፅሁፍ ያቀርባሉ፡፡ በዚህ የተነሳም የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ክፍል የማይተካ ሚናውን በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ በባለሙያዎቹ ሪፖርት ላይ የሚቀርበው ተቃዉሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ የሙያውን አስፈላጊነት በግልፅ ያሳያል፡፡ አሰራሩ በዘፈቀደ እንዳይሆን አሳታፊና ውጥረትን የሚቀንስ እና ተገማች ዉጤት ያለዉ እንዲሆን በማድረግም ረገድም ጉልህ ድርሻ ያበረክታል፡፡

በአጠቃላ ይህፃናት ከማን ጋር ሆነው ይደጉ የሚለውን ጭብጥ በመወሰን ረገድ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ነጥቦችም የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነዚህም፡- ተደጋጋሚ ግንኙነት የመፍጠር (የቅርርቦሽ መጠንና ሁኔታ)፣ ለህፃናቱ ተገቢውን እንክብካቤ የመስጠት ችሎታ (መልካም ወላጆች የሚባሉ የመሆናቸው ጉዳይ)፣ የባህሪ ሁኔታ፣ የህፃናቱ ምርጫ (ፍላጐታቸው)፣ ለትምህርታቸው ያለው ቀረቤታና አመችነት፣ ተስማሚ አካባቢያዊ ሁኔታ፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ሁኔታ (ወላጆቻቸው ከሱስና ከአላስፈላጊ ነገሮች እንዲሁም ህፃናትን አግባብነት በሌለዉ መንገድ ከመያዝ ነፃ የመሆናቸው ነገር)፣ የወላጆች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታወ.ዘ.ተ... የመሳሰሉት ናቸው፡፡[19] በወላጆች መካከል ስምምነት በሌለ ጊዜ የሞግዚትነት ስልጣን የሚሰጠው የህፃናቱን ጥቅም የበለጠ ለሚያስጠብቀው ወገን ይሆናል፡፡

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መመዘኛዎች የህፃናቱን መሠረታዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚጠቅሙና በብዙ አገራትም በስፋት የሚሰራባቸው ቢሆንም የተዋጣላቸው ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት የሚገባው ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ በርካታ የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዳሉ ሊታወቅ ይገባል፡፡ መመዘኛዎቹንም ነጥብ በነጥብ ለማየትም ሰፋ ያለ ዝግጅትና አቀራረብን የሚጠይቅ በመሆኑ ለዚህ ፅሁፍ ዓላማ አልተመረጠም፡፡ ስለሆነም የህፃናቱን

[19] በ2005 ዓ/ም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የወጣው የስራ መመሪያና የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ላይ በግልፅ የተመለከተው አስተዳደግን በሚመለከት ጠቃሚ ናቸው የሚባሉና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰፊው የሚሰራባቸው መስፈርቶቹን የያዘ መሆኑ ነው፡፡

ተሳትፎ በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ የሆነውንና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ የሚስተዋለውን ነጥብ ብቻ ከዚህ ቀጥሎ ገለፃ ተደርጐበታል፡፡

### *4.4.1. የህፃናትን ምርጫና ፍላጐት ከግምት ማስገባት*

ህፃናት ከማን ጋር ሆነው ሊያድጉ ይገባል የሚለውን የክርክር ጭብጥ አይቶ ከመወሰን በፊት የህፃናቱን ምርጫና ፍላጐት ከግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢነት አለው፡፡ ህፃናቱንም በእራሳቸው ጉዳይ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል፡፡ የመናገር፣ የመደመጥና ሀሳባቸውን በነፃነት የመግለፅ መብታቸውንም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል፡፡ "ልጅ ያቦካው ለእራት አይበቃም" የሚለው የቆየ አገራዊ ብሂልም ቦታ የለውም፡፡ ከህፃናት እጅግ ጠቃሚ መረጃ ይገኛል፡፡ ስለ ወላጆቻቸውም ትክክለኛ ባህሪ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ለህፃናት የመሰማት መብት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ወሳኝነት አለው፡፡

በተግባር ያለውን አሰራር ስንመለከተውም አንዳንድ ፍርድ ቤቶች ህፃናቱን በጽ/ቤት በማስቀረብ ወላጆቻቸው ባሉበት ወይም በሌሉበት ሁኔታ ያዳምጧቸዋል፡፡ ለብቻቸው በማነጋገርም ከማን ጋር መሆን እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸዋል፡፡ ምርጫቸውንም በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተከትለው ውሳኔ ሲሰጡ ይታያል፡፡ የህፃናትን የትምህርት ሰዓት በማይጋፋ ሁኔታ አገልግሎት ለመስጠት በየወሩ አንድ ቀን ቅዳሜ እለት የቤተሰብ ችሎቶች በፍላጐታቸው አገልግሎት እየሠጡ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በየአስራ አምስት ቀናት እረቡ እለት ከመንግስት የስራ ሰዓት ውጪ እስከ ማታ 12፡30 ድረስ አምሽተው የሚሰሩ ችሎቶች አሉ፡፡ ይህ የተደረገውም በዋናት የህፃናቱን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ እነዚህ ተሞክሮዎች መስፋፋትና መዳበር ያለባቸው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል በተግባር ያለው ችግር የጋብቻውን መፍረስ ወይም የወላጆቻቸውን መለያየት ህፃናት እንዳያውቁት በሚስጥር እንዲያዝላቸው የሚፈልጉ ወላጆች ቁጥር ቀላል አለመሆኑ ነው፡፡ መለያየታችን ልጆቻችን መስማት የለባቸውም ብለው በችሎት የሚከራከሩ ወላጆች በስፋት ያጋጥማሉ፡፡ በተለይ በስምምነት በሚፋቱ ወላጆች ላይ ይህ ሁኔታ በሰፊው ይከሰታል፡፡ ይህ ግን እራስን ማታለል ነው ማለት ይቻላል፡፡ በማንኛውም የህግ መመዘኛ ቢታይም የሚደገፍ አይደለም፡፡ የወላጆቻቸው መለያየት

የማይካድ፣ ያገጠጠና ያፈጠጠ እውነት ሆኖ እያለ ህፃናት እንዳያውቁት ማድረግ የሚቻል አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ በቀጥታ የሚመለከታቸው እንደመሆኑ መጠን ጉዳዩን እንደ እድሜ ሁኔታቸው እየታየ በሚገባቸው ቋንቋ በግልፅ ማሳወቅ ይገባል፡፡ እውነታውን አውቀዉትም ከማን ጋር መሆን እንደሚፈልጉ መጠየቃቸው ተገቢነት አለው፡፡ የትምህርት ሰዓታቸውን እንዳይጋፋ በመጠንቀቅ፣ የወላጆቻቸውን እሰጣገባ እንዳያዳምጡ በማድረግ በጽ/ቤት በማስቀረብ ህፃናቱን ማነጋገር ተመራጭ ነው፡፡

ሌላው መሠረታዊ ነጥብ ህፃናት በችሎት (በዳኛ ፊት) መቅረባቸው የግድ አለመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ስለሆነ የመሰማት መብታቸውን ማክበር አማራጭ ያለው አይመስልም፡፡ በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ዘንድ ቀርበው ወይም ባለሙያዎቹ ወደ ህፃናቱ ሄደው ፍላጐታቸውን ማዳመጥ ተገቢነቱ አያጠያይቅም፡፡ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ህፃናቱን አግኝተው እንደሚያነጋግሯቸው ለየፍርድ ቤቶቹ በየጊዜው ከሚቀርቡት ሪፖርቶች ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በሥነ-ልቦና ባለሙያዎች በኩል የመሰማት መብታቸው እየተተገበረ ይገኛል፡፡

በእርግጥ በዚህ ረገድ የሚያጋጥሙ ችግሮች ምንድን ናቸው ከተባለ ህፃናት የሚመርጡት ሁል ጊዜ የተሻለ ቅርርቦሽ ያለውን ወይም አብልጠው የሚወዱትን ወላጃቸውን መሆኑ ነው፡፡ ይህን ፍላጐታቸውን ተከትሎ ብቻ ሞግዚትነትን መወሰን ተገቢ አይሆንም፡፡ ፍላጐታቸውን ማዳመጥ ማለት ፍርድ ቤቶች ህፃናቱ የሚያቀርቡትን ጥያቄ ሁሉ መከተል አለባቸው ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ እውነተኛ ፍላጐታቸውን ላይገልፁ የሚችሉባቸው በርካታ አጋጣሚዎች እንዳሉ ስለሚታወቅ ነው፡፡ በአንደኛው ወገን 'ይህን በሉ' የተባሉትን ፍርድ ቤት ቀርበው ሳያቅማሙ የሚደግሙበት ሁኔታም እንዳለ የቤተሰብ ችሎት ዳኞች የሚያውቁት እውነታ ነው፡፡ ይህንንም በሰከነ ሁኔታ ቀስ በቀስ እያዝናኑ አውጣጥቶ ከእውነቱ ላይ መድረስ መቻል እንጅ ገና ለገና በሉ የተባሉትን ይላሉ በሚል ጥርጣሬ መነሻነት እንዳይቀርቡ ማድረግም ፍትሃዊ አይደለም፡፡

ህፃናት በአንደኛው ወላጃቸው ላይ የሚያሳዩት ፍቅር ደካማ (አነስተኛ) የሚሆነው በብዙ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ከአንደኛው ወገን ጋር አስቀድሞውኑ አብረው ባለመኖራቸው ሊፈጠር የሚችለው ክፍተት ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ችግር ብዙ ጊዜ የሚከሰት (የተለመደ) ዓይነት ሲሆን መፍትሔውም ከባድ አይደለም፡፡ ሌላኛውና

ምናልባትም ዋነኛው ችግር ግን ወላጆች ወይም በህግ የሞግዚትነት ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ለህፃናት አንዱ ስለሌላው መጥፎነት፣አላስፈላጊነት ወ.ዘ.ተ.... የመሳሰሉትን ተገቢነት የሌላቸውን ነገሮች በተደጋጋሚ ጊዜያት በመናገራቸው የተነሳ የሚመጣው ክፍተትና መቃቃር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በህፃናቱ አእምሮ ላይ አላስፈላጊ ጥላቻና የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ እርግጥ ነው ይህ ዓይነቱ ክፍተት አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው፡፡ ይሁን እንጅ ችግሩ ከተከሰተ አደገኛ ሲሆን መፍትሄውም በቀላሉ ሊመጣ የሚችል አይደለም፡፡

ህፃናት የሚነገራቸውን ሁሉ በቶሎ ይይዛሉ፤ አንድ ጊዜ የተነገራቸውንም ነገር በቀላሉ አይረሱትምም፡፡ በተለይ እንደ እድሜያቸው ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም ህፃናት በለጋ እድሜያቸው እያሉ የተነገራቸውን ነገር ትክክለኛነት ሳያመዛዝኑ የመቀበል እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ በእርግጥ በርካታ ወላጆች በአንደኛው ወገን እውነተኛ የሆነ በደል ደርሶባቸው እያለም እንኳን ለህፃናት ልጆቻቸው የሚያስተላልፉት መልዕክት ግን ፍፁም ኃላፊነት የተሞላበት ዝምድናቸውን የሚቀጥል እንዲሆን የሚያድርግ ነው፡፡ አንዳንድ ወላጆች ግን በሚያስገርም ሁኔታ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ከዚህ በተቃራኒው ለህፃናቱ የሚነግሯቸው ነገሮች ጥላቻን ከዚያም አለፍ ሲል ጠላትነትን የሚዘራ ሆኖ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ ያህል "አባትህ እኮ አንተን አርግዤ እያለ ከነፅንሱ እገልሻለሁ እያለ የዛተብኝን መቼም ጊዜ ቢሆን አልረሳውም፡፡ ይህንንም የተናገረው ሁላችንንም ስለማይወደን ሊገድለን አስቦ ነው፡፡" እየተባለ በተደጋጋሚ ሲነገረው የቆየ ህፃን ወላጁን ቢጠላ ሊያስገርም አይችልም፡፡

ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ከነመንስኤያቸው ጭምር በማጥናት ሰፋያለ ስራ በወላጆች፣ በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችና በፍርድ ቤቶች ጭምር መሰራት ይገባል፡፡ በወላጆችና በህፃናት መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሻሻል፣ እንዲጠገንና ወደ ሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ ጊዜ ተወስዶ በርካታ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡ ግንባር ቀደም ኃላፊነቱ ያለው ግን በወላጆች ዘንድ ነው፡፡ አንዱ ወገን ስለሌላኛው የሚናገረው ነገር የተመረጠ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት፣ ውዴታንና ፍቅርን የሚጨምር ብቻ ነው መሆን የሚገባው፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ግንኙነቱን በማጠናከር ረገድ የማይናቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በመዝገብ ላይ የሚሰጡ ትዕዛዞችም የሚያረጋግጡት ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

## 4.5. የመጎብኘት መብት

ህፃናት በወላጆቻቸው፣ በህግ የአሳዳጊነት ወይም የሞግዚትነት ስልጣን በተሰጣቸው ሰዎች፣ በቤተሰቦቻቸው ወይም በዘመዶቻቸው የመጐብኘት መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ወላጆቻቸው፤ አሳዳጊዎቻቸው ወይም ሞግዚቶቻቸው ህፃናቱን የመጐብኘት መብት አላቸው፡፡ መብቱ የሁለትዮሽ ነው፡፡ የህፃናቱም የወላጆቻቸውም ነው፡፡ ይህን ህገ-መንግስታዊ መብት ማስከበር የሚቻለው በፍርድ ቤት ነው፡፡ ይህ መብት እንዲከበር አቤቱታ ለብቻው፣ በፍቺ ወቅት ወይም ከአሳዳጊነትና ከሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎች ጋር ሊቀርብ ይችላል፡፡ ወላጆች ለልጃቸው ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ያለባቸውን ያህል እነሱንም የመጠየቅና የመጐብኘት መብት አላቸው፡፡ ህፃኑ የወላጆቹን (የአሳዳጊዎቹን) ፍቅር በእኩልነት የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡[20]

ስለዚህ እናት ልጁን እንድታሳድግ የሞግዚትነት ስልጣን ተሰጥቷት ከሆነ ህፃኑ በወላጅ አባቱ የመጐብኘት መብት እንዳለው አባቱም ህፃኑን የመጠየቅ መብት እንዳለው መገንዘብና በተግባር እንዲፈፀም የመተባበር ግዴታ አለባት፡፡ በዚህ ረገድ በተግባር ያሉት ችግሮች በርካታ ናቸው፡፡ ሞግዚት የሆነው ወገን ለሌላኛው ወገን ህፃኑን ለማሳየት ፍቃደኛ ያለመሆን፤ በተቃራኒው በልጁና በወላጁ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲዳከምና እንዲላላ ማድረግ፣ ወይም የቦታ መራራቅና የወጪ ሁኔታ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ ሆነው በሁለት የተለያዩ ከተሞች የሚኖሩ ወላጆች ህፃናቱን በማስጐብኘት ረገድ የወጪ ጥያቄ ብዙጊዜ የሚያጋጥም ሌላኛው ችግር ነው፡፡ ልጁን የሚያሳድገው ወገን ሌላኛውን ወገን በራሱ ወጪ መጥቶ ይጠይቅ ይላል፡፡ ልጁን ማየት የሚፈልገውም ወገን ሞግዚቱ በራሱ ወጪ አምጥቶ ያሳየኝ ይላል፡፡

በዚህም የተነሳ ይህንን መብት ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አለመግባባት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶች ግን ጉብኝቱ በምን መልኩ መካሄድ እንዳለበት፣ ወጪያቸውንም እንዴት መሸፈን እንዳለባቸው፣ በመዝገብ ላይ በማስቀመጥ በተቻለ መጠን በማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች

[20] ኢትዮጵያ ባፀደቀችውና የሀገሪቱ የህግ አካል ባደረገችው ዓለምአቀፍ የህፃናት ኮንቬንሽን ላይ ህፃናት በወላጆቻቸው (አሳዳጊዎቻቸው) የመጐብኘት መብት እንዳላቸው ተደጋግሞ የተገለፀ ነጥብ ነው፡፡ ለተጨማሪ መረጃም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት አንቀጽ 36 (1) (ሐ) በቀጥታ አግባብነት አለዉ፡፡

እየታገዙ መብቱን ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ የህፃናት የጉብኝት መብት መተግበር ያለበት ትምህርታቸውን በማያስተጓጉል መልኩ ነው፡፡ የጉብኝት ቦታው ደግሞ ለሁለቱም ወገን የሚያመች፣ ህፃናቱ በተቻለ መጠን ሊወዱት የሚችሉት እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ የጉብኝት ስርዓቱ በአካል፣ በስልክ ወይም እንደአመቺነቱ በሌላ ቴክኖሎጂ ለምሳሌ ስካይፕና ቫይበር በመጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡ ጉብኝቱ የሚካሄድበት ጊዜ የተገደበ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የህፃናቱን ትምህርት በማይጋፋ መልኩ፣ እንደሚኖሩበት የቦታ ርቀትና የትራንስፖርት አመቺነት በየቀኑ ለተወሰነ ደቂቃ ወይም ሰዓት ሊፈፀም ይችላል፡፡ የሚከተሉትን ትዕዛዞች በምሳሌነት ማየት ይቻላል፡፡

1. *"አባት ህፃኑን በየቀኑ ከ10፡00 ሰዐት ጀምሮ እስከ 12፡00 ሰዓት ድረስ እናትና ህፃን በሚኖሩበት ቤት ፊትለፊት በሚገኘው የህፃናት መዝናኛ ማእከል እንዲጉበኝ ተፈቅዷል፡፡"*
2. *"አባት በሳምንት አንድ ቀን እለተ ቅዳሜ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ላይ ህፃኑን ተረክበው አውለውና አሳድረው በማግስቱ እሁድ እለት ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ላይ በተረከቡበት ሁኔታ ለእናት እንዲመልሱ ታዟል፡፡"*

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ችግር ህፃናቱ የሚገኙት በሌላ ሀገር በሆነ ጊዜ ነው፡፡ ለምሳሌ ህፃናቱ ከእናታቸው ወይም ከአባታቸው ጋር በአሜሪካን ሀገር ቢሆኑ ከወላጆቻቸው አንዱ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ይሆንና እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ወገን ጥያቄ ቢያነሳ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ነው፡፡ ጥያቄው የወጪና የቪዛ ጉዳዮችንም የሚመለከት ስለሆነ ችግሩ ከባድ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖረው ወላጅ ወጪ አሜሪካን ሀገር የሚኖረው ወላጅ ልጆችን ይዞ ወይም ልጆቹን ለታማኝ ሰው ልኮ እንዲያስጉበኝ ማድረግ አንደኛው አማራጭ ነው፡፡ አለበለዚያም እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ወላጅ በራሱ ወጪ ወይም በአሜሪካን ሀገር ባለው ወላጅ ወጪ ሄዶ እንዲጎበኝ ማድረግ ነው፡፡ ወይም ደግሞ የሁለቱም አቅም ተመጣጣኝ ከሆነ ለሁለቱም ወላጆች በሚመች መልኩ ሶስተኛ ሀገርን በመምረጥ በየራሳቸው ወጪ ጉብኝቱ እንዲፈፀም ማድረግ ይቻላል፡፡

ዞሮ ዞሮ ሊሰመርበት የሚገባው ጉዳይ የጉብኝት ጥያቄውን ተግባራዊ ማድረግ በተግባር ፈታኝ መሆኑ ነው፡፡ የገንዘብና ሌሎች ሁኔታዎች ተሟልተው እያለ ቪዛ ሊከለከል ይችላል፡፡

ሌላው ችግር ጉብኝቱ ሲፈፀም የአሳዳጊነት ስልጣን የተሰጠው ወላጅም ከልጆች ጋር አብሮ መቅረብና ማግኘት አለብኝ የሚለው ተደጋጋሚ ጥያቄ ነው፡፡ ምክንያቱም ጥያቄውን ሞግዚቱ ላይቀበለውና ላይስማማ ስለሚችል ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ተለያይተው የቆዩ የቀድሞ ባልና ሚስት ፍርድ ቤትን ሆንብለው እንደመተያያ ቦታ ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ ፍርድ ቤትም አንደኛውን ወገን ያለፍላጐቱ ጉብኝቱ በሚካሄድበት ስፍራ እንዲገኝ ለማዘዝ የህግ መሠረት አለው ወይ? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በአንዳንድ ፍርድ ቤቶች የሞግዚቱን መገኘት አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ሞግዚቱም አብሮ በጉብኝት ስፍራው እንዲገኝ የሚያዙ ሲሆን ሌሎቹ ግን መገኘቱ የግድ የሚያስብል አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በቀር እንዲቀርብ ትእዛዝ አይሰጡም፡፡

የጉብኝት ውሳኔ ፍርድ ቤት ከመስጠቱ በፊት የሥነ-ልቦና ባለሙያዎች ሙያዊ አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ይደረጋል፡፡ የባለሞያዎቹ ሪፖርት ሞያዊ አስተያየት እንደመሆኑ መጠን አስገዳጅነት የሌለው የውሳኔ ሀሳብ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን ሪፖርት ተመልክቶ የውሳኔ ሀሳቡን እንዳለ ሊቀበለው፣ ሊያሻሽለው ወይም ውደቅ ሊያደርገውና እንደገና በድጋሚ እንዲሰራ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ብዙጊዜ ግን በተግባር ያለው ሁኔታ የባለሞያዎችን የውሳኔ ሀሳብ እንዳለ ተቀብሎ ወይም ከመጠነኛ ማስተካከያ ጋር ማፅደቅ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ውደቅ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ይህን ፅሁፍ ለማዘጋጀት በተደረገው ጥናት ውድቅ የተደረገ የውሳኔ ሀሳብ አልተገኘም፡፡ ይህም የሚያሳየው የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የውሳኔ ሀሳቦች ተቀባይነት እያገኙ መምጣታቸውን ነው፡፡ በሪፖርቶቹ ላይም ብዙጊዜ ቅሬታ ሲቀርብባቸው አይታይም፡፡ ህፃናቱ ለምን ከአባት ወይም ከእናት ጋር እንዲያድጉ እንደተደረገ ገብቶኛል ወ.ዘ.ተ… የሚሉ አስተያየቶች ናቸው የሚቀርቡት፡፡ ስለዚህ የሚሰጡትን የውሳኔ ሀሳቦች ውድቅ ለማድረግ አሳማኝ የህግና ፍሬ-ነገር ምክንያት ማስፈለጉ አይቀሬ ነው፡፡

ዳኛ የውሳኔ ሃሳቡን የመሻር ወይም የማሻሻል ስልጣን ስላለው ብቻ መሻር ወይም ማሻሻል ፈፅሞ አግባብነት ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ነገር ግን የሥነ-ልቦና ባለሙያዎችም ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ሆንተብሎ ወይም በግዴለሽነት ስህተት ሊፈፅሙ ይችላሉ፡፡ ለአብነት ያሕል የሙያውን ሥነ-ምግባርና ደንብ በሚቃረን ሁኔታ የፈፀሙት ግልፅ ስህተት መኖሩ ከተረጋገጠ ወይም ለአንደኛው ወገን ወገንተኝነት ካሳዩ ወይም

የአንደኛውን ወገን ማስረጃና ሁኔታ በአግባቡ ካልያዙለት ወ.ዘ.ተ… የውሳኔ ሃሳቡ ላይፀድቅ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ መግለፅ ይቻላል፡፡

# 5. ልጅነትና ውርስ

## 5.1. የልጅነት (የተወላጅነት) ጥያቄ

የልጅነት ጥያቄ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ከሚችሉ አቤቱታዎች አንዱ ነዉ፡፡ የልጅነት፣ የአባትነት፣ እናትነት ወይም የተወላጅነት ወ.ዘ.ተ… አቤቱታዎች በማንኛውም ጊዜ ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡ ሆኖም ግን የህፃናት ተወላጅነት ወይም ልጅነት አቤቱታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ የሚችለው በእራሳቸው በህፃናቱ አማካኝነት አይደለም፡፡ የክስ አቤቱታውም የሚቀርበው በወላጆቻቸው፣ በህግ የሞግዚትነት ስልጣን በተሰጣቸው ሰዎች ወይም በተወካዮቻቸው አማካኝነት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የፍትሐብሄር ህጋችንም ሆነ የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ እድሜያቸው ከአስራ ስምንት ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ህጋዊ ተግባራትን መፈፀም እንደማይችሉ ደንግገው ስለሚገኙ ነው፡፡

እድሜያቸው ከአስራ ስምንት አመት በታች የሆኑ ህፃናት በመርህ ደረጃ ህጋዊ ተግባራትን መፈፀም የሚችሉት በሞግዚቶቻቸው ወይም በአስተዳዳሪዎቻቸው አማካኝነት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ቀድሞ ነገር እድሜው ከአስራ ስምንት አመት በታች የሆነ ህፃን በነፃነት ፈቃዱን ይሰጣል ተብሎ በህግ አይገመትም፡፡[21] ለምሳሌ የውሉን ህጋዊነት ጥያቄ ውስጥ ከሚያስገቡ ምክንያቶችም አንዱ በህግ ችሎታ ማጣት ነው፡፡ በዚህ ረገድ በማወቅም ሆነ ባለማዎቅ እድሜዉ ከ18 አመት በታች በሆነ ሰዉ የተፈፀመ ህጋዊ ግንኙነት መኖሩ ከተረጋገጠ ህጋዊ ዉጤት እንደማይኖረው በመርህ ደረጃ

[21] የጋብቻ መፈፀሚያ እድሜ ለወንድም ሆነ ለሴት 18 ዓመት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በተለየ ሁኔታ በፍትሕ ሚኒስቴሩ ካልተፈቀደ በቀር ከዚህ እድሜ በታች የሚገኙ ህፃናት ጋብቻ ፈፅመው ቢገኙ ፍቃዳቸውን በነፃነት ሰጥተዋል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ስለዚህ ጋብቻው እንዲፈርስ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል/ግለሰብ በህጉ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም ከችሎታ ማጣት ጋር በተያያዘ በፍትሐብሄር ህጉ ከአንቀጽ 1696 ጀምሮ የተደነገጉት ድንጋጌዎች የሚያስረዱት ከተዋዋዮች መካከል አንደኛው ውሉን የፈፀመው በፍቃድ ጉድለት ምክንያት መሆኑን በማንሳት ውሉ እንዲፈርስለት የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን ነው፡፡

መግባባት ይቻላል፡፡ ይህ ማለት ግን እድሜው ከ18 በታች የሆነው አንድ የጎዳና ተዳዳሪ ህፃን ያቀረበው አቤቱታ ክሱን በእራሱ ቆሞ ለመከራከር ተቀባይነት ባይኖረውም ህፃኑ የህግ ድጋፍ እንዲያገኝ ፍርድ ቤቱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ትዕዛዝ ከመስጠት አያግደውም፡፡ ምክንያቱም የፍርድ ቤት ዋንኛ ሥራ እውነትን ማፈላለግ እንደመሆኑ መጠን ህፃኑ ፍትሕ እንዲያገኝ መርዳት ከፍርድ ቤቶች የሚጠበቅ ስለሆነ ነው፡፡

የሕፃናት የልጅነት አቤቱታ ለፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የሚመለከቱትና የሚወስኑት በተፋጠነ ሁኔታ ነው፡፡ ህፃናት የወላጆቻቸውንና የአሳዳጊዎቻቸውን ፍቅር፣ እንክብካቤና ድጋፍ የማግኘት መብቶቻው ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው በቅድሚያ እነሱን የማወቅ መብታቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ብቻ ነው፡፡ የአንድ ህፃን ልጅነት ጥያቄ ውስጥ በገባ ጊዜ ሁሉ የህፃኑን መብት በተሟላ መልኩ የማስከበር ጉዳይ አደጋ ላይ እንዳለ በመገንዘብ ጉዳዩ በአስቸኳይ ታይቶ እልባት እንዲያገኝ ማድረግ ከፍርድ ቤቶች ይጠበቃል፡፡ ለአብነት ያህል የልጅ ቀለብ የማግኘት ጥያቄ ጊዜ የማይሰጥ አንገብጋቢ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ መብት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ሲታወቅ ብቻ ነው፡፡ ልጅነት ተክዶ እያለ ቀለብ ቁረጥ ለማለት የሚቻልበት የህግ መሠረት የለምና በቅድሚያ ይኸው መሠረታዊ ጭብጥ መረጋገጥ ይገባዋል፡፡

ከፍርድ ቤቶች በተገኘ መረጃ መሠረት የልጅነት ጥያቄ በቀረበ ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በአብዛኛው እልባት ይሰጥበታል፡፡ እንዲያውም አቤቱታው ተጠሪ ወይም ተከሳሽ ያለው ከሆነና ጉዳዩ በተጠሪው የታመነ እንደሆን በአብዛኛው የቤተሰብ ችሎቶች በመጀመሪያው ቀጠሮ ውሳኔ እንደሚያገኝ የተዘጉ መዛግብት ያመለክታሉ፡፡ ማስረጃ መስማት የግድ አስፈላጊ በሆነ ጊዜም በልደታ ምድብ በአንደኛና በሁለተኛ የፍተሐብሄር ችሎቶች ጥያቄው ለፍርድ ቤቱ በቀረበ በመጀመሪያው ቀጠሮ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ እንዳለ ተረጋግጧል፡፡ ይህም አበረታች እንደሆነ መግባባት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ በዚሁ ምድብ በ3ኛው የፍተሐብሄር ችሎት ግን አንድ ተጨማሪቀጠሮ ይወስዳል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የህፃኑ ወላጆች ናቸው የተባሉት ግለሰቦች በህይወት የሌሉ ከሆነና ሌላ ተከሳሽ የሚሆን ሰው እንደሌለ በቃለመሃላ ተረጋግጦ በቀረበ ጊዜ ተቃዋሚ ካለ በጋዜጣ እንዲጠራ ስለሚደረግ ነው፡፡ በእርግጥ ተቃዋሚ ካለ በጋዜጣ ለመጥራት ለምን አስፈለገ? ህጋዊ መሠረቱስ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ በየችሎቶቹ ግን የተለመደ አሰራር ነዉ፡፡

የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግም ከልጅነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ መወሰን የሚገባበትን አግባብ ደንግጎት ይገኛል፡፡ ህጉ የሚከተለው መርህ በግልፅ የተቀመጠ ባይሆንም ከድንጋጌዎቹ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው በተቻለ መጠን ህፃናት አባት እንዲኖራቸው የማድረግን መርህ ይመስላል፡፡ ለአብነት ያህል በጋብቻ ላይ እያለ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ህፃን አባቱ በጋብቻው ላይ ያለው ወንድ ነው፤ እንደባልና ሚስት በመሆን ሲኖር የተወለደ ወይም የተፀነሰ ህፃን ወላጅ አባቱ በግንኙነቱ ውስጥ ያለው ወንድ ነው ወ.ዘ.ተ... የሚሉ የቤተሰብ ህጉ ድንጋጌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በጋብቻ ወቅት የተፀነሰ (የተወለደ) ልጅ አባቱን በመልክ መሠለ አልመሰለ ባል የሆነው ሰው አባት መሆኑ አይቀርም፡፡ ማስረዳት የሚጠበቀውም ህፃኑ የተፀነሰው ወይም የተወለደው በጋብቻ ላይ እያሉ አለበለዚያም እንደባልና ሚስት በመሆን አብረው ሲኖሩ በነበረበት ጊዜ መሆኑን ብቻ ነው፡፡ የፌድራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 12 ቀን 2002 ዓ/ም ባስቻለው ችሎት በመዝገብ ቁጥር 40624 የሰጠው ውሳኔ የሚያመለክተውም አንድ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተወለደ ልጅ አባት ባልዬው ነው በሚል ህጉ የወሰደው ግምት አስገዳጅ መሆኑን ነው፡፡ አባት ነው የተባለውም ሰው ይህን ድንገጋጌ የሚቃረን ኑዛዜ ቢተው ኑዛዜው የህጉን ግምት ለማስተባበል በቂ ማስረጃ አለመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁም ይኸው የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 54024 ጥር 10 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የተወለደ ልጅ አባት ባልዬው ነው የሚለው የህጉ ግምት ከሌሎች ማስረጃዎች ይልቅ አባትነትን በማረጋገጥ ረገድ በፍርድ ቤቶች እውቅና ሊያገኝ የሚገባው ማስረጃ መሆኑን አስምሮበታል፡፡

በግልፅ እንደሚታወቀው አባት ወይም እናት የሆነ ሰው የልጁ አባት እገሌ የሚባለው ሰው ነው በማለት የልደት የምስክር ወረቀት በማቅረብ ብቻ ልጅነት ሊረጋገጥ እንደሚችል በህጉ ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የልደት የምስክርነት ወረቀት ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በተግባር እንዳሉ የሚታወቅ ቢሆንም በህግ አግባብ የተሠጠ የልደት ሰርተፊኬት በተመለከተ ልጅነት ከሚረጋገጥባቸው አንዱ መሆኑ ግን መዘንጋት የለበትም፡፡ በተሻሻለው የፌድራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 154 መሰረት የልደት ሰርቲፊኬት ቀርቦ እያለ ሌላ

የሰውም ሆነ የሰነድ ማስረጃ መመልከትና መስማት ያንያህል አስፈላጊነት የለውም ለማለት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን የልደት የምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ***የልጅነት ሁኔታ*** መኖሩን በማስረጃ በማስረዳት ልጅነት ሊረጋገጥ እንደሚችል የተሻሻለው የፌድራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 155 እና ተከታዮቹ አንቀጾች ይደነግጋሉ፡፡ እንዲህ በሆነ ጊዜም ***የልጅነት ሁኔታ*** መኖሩን ማስረዳት የሚጠበቅበት ወገን በቅድሚያ ሊያስረዳ የግድ ይለዋል፡፡ በተግባር ያለው አሰራር ሲፈተሽ በቅድሚያ ማስረዳት ያለበት ማነው በሚለው ጉዳይ ላይ ከችሎት ችሎት ወጥ የሆነ አረዳድ የለም፡፡ በአንዳንድ ችሎቶች የካደው ወገን ነው ቅድሚያ ሊያስረዳ የሚገባውየሚሉ ዳኞችአሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን የልጅነት ጥያቄም እንደሌላው የፍትሐብሔር ክስ የሚታይ በመሆኑ በቅድሚያ ማስረዳት የሚገባው ምንጊዜም ቢሆን ከሳሽ ነው የሚሉ ዳኞች ይገኛሉ፡፡ የዚህፅሁፍ አዘጋጅ የማስረዳት ሸክሙ የከሳሹ እንደሆነ በአንክሮ ያምናል፡፡ የአብዛኛው የችሎቶች አሰራርም ይህንኑ መርህ የተከተለ ነው፡፡

የልደት ሰርተፊኬት ልጅነትን በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ ማስረጃ ነው፡ ፡ ነገር ግን በልደት ሰርተፊኬቱ ላይ ስሙ በአባትነት የተጠቀሰው ሰው ስሙ በሰርተፊኬቱ ላይ መመዝገቡን ላያውቅ የሚችልበት ሁኔታ እንዳለ ግልፅ ነው፡፡ እኔ ሳላውቅ ነው ስሜ በአባትነት ሊመዘገብ የቻለው ቢል ሊያዋጣው ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ ወጥነት የሚጎድለው ነው፡፡ ሆኖም ግን የፌድራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሚያዚያ 21 ቀን 2001 ዓ/ም በሰበር መዝገብ ቁጥር 33440 ላይ የሰጠው ውሳኔ የልደት ሰርተፊኬት በሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል እንደሚችል ነው፡፡ ስለሆነም በተወሰኑ ችሎቶች የልደት ሰርተፊኬት ማስረጃ ልጅነትን በማረጋገጥ ረገድ በሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ሊስተባበል የሚችል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንዲሁም አባትነት በማኛቸውም መልኩ የታመነ ከሆነ ልጅነት ሊረጋገጥ እንደሚችል በተሻሻለው የፌድራል ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 125 (2) እና 131 (1) ተደንጎ ይገኛል፡፡

## 5.2. የውርስ የጥያቄና የህፃናት ደህንነት እና ጥቅም መርህ አተገባበር

ህፃናት የወላጆቻቸው የመጀመሪያ ደረጃ ወራሾች ናቸው፡፡[22] ህፃናት ወላጆቻቸው ወይም ከወላጆቻቸው አንዱ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩ ጊዜ ይህ መብታቸው ይከበርላቸው ዘንድ በሞግዚቶቻቸው ወይም በአሳዳጊዎቻቸው አማካኝነት ጥያቄው ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል፡፡ በመሆኑም የህፃናት ወራሽ የመሆን መብት የሚረጋገጠዉ የውርስ አቤቱታ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ነዉ፡፡ በዚህ ጊዜ የቀረበው የውርስ ጥያቄ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናትን በሚመለከት ከሆነ የውርሱን አቤቱታ በተቻለ ፍጥነት ማስተናገድ የሚገባ ይሆናል፡፡ የህፃናትን የውርስ መብት ጥያቄ በተቻለ ፍጥነት እልባት እንዲያገኝ ማድረግ የህፃናቱን በህይወት የመኖር መብት በተሟላ ሁኔታ ማስከበር ማለት ነው፡፡

የውርስ ክርክሩ የተጓተተ የሙግት ሥርዓትን የሚከተል ከሆነ በዋናነት ተጎጂ የሚሆኑት ህፃናትናቸው፡፡ በተለይ የወላጆቻቸው የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በሶስተኛ ወገን እጅ ሆነው ያለአግባብ እየተጠቀሙባቸው እያለ ህፃናቱ ግን በከፍተኛ ችግር ላይ የሚወድቁባቸው ሁኔታዎች ያጋጥማሉ፡፡ የውርስ ጉዳይ በእራሱ ለኪራይ ሰብሳቢ አመለካከት የተጋለጠ መሆኑ ብዙዎችን ያግባባል፡፡ ከሟች ጋር ዝምድና ያለውም ሆነ የሌለው ወገን ሃብቱን በእጅ ለማስገባት ከፍተኛ ግብ ግብ የሚካሄድበትሁኔታ ነው፡፡ ያለ የሌለ የዝምድና ሃረግ እየተመዘዘ ክርክር የሚጧጧፍበት፣ የማይመለከታቸው ሰዎች ሳይቀሩ የሕፃናቱን የውርስ ሀብት ያለአግባብ ይዘው ለመጠቀምና ያለአግባብ ለመበልፀግ ሰፊ ጥረት የሚያደረጉበት ሁኔታ ይታያል፡፡ የማይመለከታቸው ወገኖች የውርስ ሀብቱን ይዘው እየተጠቀሙበት መሆኑ ሳይበቃቸው ይባስ ብሎ በሀሰተኛ የሰነድ ማስረጃ፣ ምስክርነት፣ ኑዛዜ፣ ወይም ሀሰተኛ ውሳኔ ወ.ዘ.ተ.... በመጠቀም ህፃናቱን ከንብረቱ ከነጭራሹ ለመንቀል ሙከራ ሲደረግም ይስተዋላል፡፡

በተግባር እንደሚታየው የውርስ ጉዳይ በጠቅላላው ሰፋ ያለ ችግር የሚስተዋልበት የክርክር ዘርፍነው፡፡ የህጉ ግልፅ አለመሆን ጋር በተያያዘ

[22] በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 842 ላይ የሟች ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡

የህግ አተረጓጎሙ ከፍርድ ቤት ፍርድ ቤት፣ ከችሎት ችሎት ወጥነት ያለው አይደለም፡፡ የወራሽነትም ሆነ የልጅነት ማስረጃ (ውሳኔ) አሰጣጡ የሚወስደው ጊዜ እንዳለ ሆኖ የውርስ አጣሪ አመራረጡ፣ አሰያየሙ፣ የሪፖርቱ አቀራረብና አፀዳደቁ ወ.ዘ.ተ… የሚወስደው ጊዜ ሁሉ እራሱን የቻለ ከፍተኛ መጓተትን ያስከትላል፡፡ በመጨረሻም ሁሉም ነገር ተጠናቆ ካበቃ በኋላ ወራሾች እንደየ ድርሻቸው የውርስ ንብረቶቹን እንዲከፋፈሉ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ እንኳን ሳይቀር ክፍፍሉ በአፈፃፀም ደረጃ ላይ እያለ ታግዶ ለበርካታ ዓመታት እንዲቆይ የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡ ለአብነት በአፈፃፀም ችሎት የተዘጉ መዛግብትን ብቻ መመልከት ይበቃል፡፡ በዚህ የተነሳም የህፃናቱ ህልውና አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል፡፡

"የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል" ነውና መዘግየትን ማስቀረት ጊዜ ሊሰጠው አይገባም፡፡ ምንጊዜም ቢሆን በፍትህ አሰጣጥ ሥርዓት ውስጥ መዘግየት የፍትሕ ፀር ነው፤ የብቃትና የውጤታማነት ማነቆ ነው፡፡ ወራሾች ተለይተው የውርስ ሀብቱ ተጣርቶ እስከሚከፋፈሉ ድረስም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆኑት ወራሾች ቢያንስ ከወደፊት ድርሻቸው ሊታሰብ የሚችል ሆኖ ከውርስ ሀብቱ ላይ ቀለብ ሊቆረጥላቸው የግድ ነው፤ ቀለብ የህፃናት የህልውና ጉዳይ ስለሆነ፡፡ በተግባር ግን የውርስ ሀብቱ እስከሚከፋፈል ድረስ ለህፃናት ቀለብ ፍርድ ቤቶች እየቆረጡ ነው ወይ? የሚለው ጉዳይ አነጋጋሪ ነው፡፡ የውርስን ጉዳይ በተቻለ ፍጥነት አይቶ ውሳኔ መስጠት እንዳለ ሆኖ እስከዚያው ድረስ ቀለብ የመቁረጡ ነገር መዘንጋት አይገባውም፡፡

የህፃናት የውርስ ሃብት በሶስተኛ ወገን እጅ ሆኖ ያለአግባብ እየተጠቀሙበት ሳለ ህፃናቱ ግን ችግር ላይ የሚወድቁባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ፍርድ ቤቶች በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የችግሩን መንስኤ በአግባቡ መረዳት መቻል በራሱ የመፍተሄውን ግማሽ ያህል ማግኘት በመሆኑ ፍርድ ቤቶች መንስኤውንና የጉዳዩን አሳሳቢነት በአግባቡ መገንዘብ ይገባቸዋል፡፡ በፍርድ ቤቶች ውስጥ ከሚስተናገዱ ጉዳዮች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የውርስ ጉዳይ ነዉ፡፡ በሚበዛው የውርስ ክርክርም ላይ የህፃናት መብት ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ ዳኞችም ሆኑ በየደረጃው የሚገኙት የፍርድ ቤቶች አመራር አካላት የውርስን ጉዳይ ብቻ የሚመለከቱ ችሎቶችን በየምድብ ችሎቶቹ ማደራጀት አንገብጋቢ የሆነ የወቅቱ ጥያቄ መሆኑን ልብ ማለት ይኖርባቸዋል፡፡

የህብረተሰቡን እርካታ ለማረጋገጥም ሲባል የውርስ ክርክሮችን ብቻ ተቀብለው የሚያስተናግዱ ችሎቶችን ማደራጀት አስፈላጊ ነዉ፡፡

## ዋቢ መፅሐፍቶች፣ ህጐችና ፅሁፎች


1. በታህሳስ 20 ቀን 1989 ዓ/ም የፀደቀው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የህፃናት መብቶች ኮንቬንሽን፤
2. የተባበሩት መንግስታት የህፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር፤
3. በ1987 ዓ/ም የፀደቀው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት፤
4. በ1952 ዓ/ም የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ህግ፤
5. በ1958 ዓ/ም የወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ፤
6. በ1997 ዓ/ም የወጣውየኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ፤
7. በ1992 ዓ/ም የወጣው የተሻሻለው የፌደራል የቤተሰብ ህግ፤
8. በ2004 ዓ/ም በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የተዘጋጀውና የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳኖችን የያዘው ጥራዝ፤
9. ጉዲፈቻ በኢትዮጵያ በ2004 ዓ/ም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋጀው ጥራዝ፡፡
10. በ2005 ዓ/ም በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የወጣው የስራና የቀለብ አወሳሰን መመሪያዎች፤
11. በ2002 ዓ/ም የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ያዘጋጀው ወሲባዊ ትንኮሳ የሴቶች መብት ጥሰት ናቸው የሚል ጥናታዊ ፅሁፍ፤
12. ስለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የወጣው ህግ አዋጅ ቁጥር 454/1997 እና ችሎቱ ከህፃናት መብቶች ጋር በተያያዘ በተለያዩ ጊዜያት የሰጣቸው አስገዳጅ ውሳኔዎች፣ በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት የቤተሰብ ችሎቶች የሰጧቸው ውሳኔዎች፣ ብይኖች እና ትዕዛዞች እንዲሁም የተዘጉ መዛግብትና ቃለ-መጠይቆችም ይገኙበታል፡፡

# PART II:

# WORKSHOP PROCEEDING

# Proceeding of the National Workshop on the Judicial Application of the Best Interest of the Child Principle

*Organized by the Center for Human Rights of Addis Ababa University in Collaboration with Federal First Instance Court of Ethiopia*

*June 17 – 18, 2015*

*- Addis Ababa -*

## 1. Introduction

As an academic institution the Center for Human Rights of Addis Ababa University (the Center) has the responsibility to nurture a multidisciplinary discourse on broader human rights issues through its academic and community service programs. In pursuance of this responsibility, the Center organized a national workshop on the judicial application of the 'best interest of the child' principle in mid-2015. The workshop brought together different stakeholders – academicians, practitioners, government and CSOs representatives – to make nuanced deliberations on the theoretical and practical aspects of the 'best interest of the child' principle and other principles related to the protection of the rights of the child.

The main theme of the Workshop was reviewing contemporary theoretical understanding and normative framework as well as practice of implementing the best interest principle in judicial proceedings, with special emphasis on the works of the Federal First Instance Court of Ethiopia. During the Workshop review of international and comparative standards, rules and practices relating to implementation of the 'best interest of the child' principle and their relevance to the Ethiopian context was made; best practices as well as inconsistencies and challenges in implementing the 'best interest of the child' principle in judicial proceedings in the Federal First Instance Court were identified and ways of enhancing the judicial application of the principle were suggested; and the need to develop working procedures, manuals, guidelines and standards as well as cooperation among institutions to promote the full and effective implementation of the 'best interest of the child' principle was recommended.

This proceeding summarizes the major points raised during the presentations and the discussion at the Workshop.

## 2. Opening Speech

The Workshop was formally opened with opening speech made by H. E. Mr. Desalegn Berhe, President of Federal First Instance Court. In his speech Mr. Desalegn noted that the principle of the 'best interest of the child' should be the concern of everyone and it is with this in view that the Federal First Instance Court and Addis Ababa University Center for Human Rights organized the Workshop so that all stakeholders can familiarize themselves on the theoretical, normative and practical aspects as well as best ways of giving effect to the 'best interest of the child' in their respective works.

working on the area of child rights. He said that the proposed committee can be organized at the national and regional level. He then went on to propose committee members from participants of the Workshop. Finally, a national steering committee to facilitate collaborative work on child rights was constituted comprising of the following members.

1. Ato Abdulahi Shafi (East Shewa Zone High Court President)
2. Ato Girma Guye (Sidama Zone High Court President)
3. Ato Amsalu Olani (West Shewa Zone High Court President)
4. Ato Elias Alemayehu (Ministry of Women, Youth and Children Affairs - Expert)
5. Leulesilassie Liben (Federal First Instance Court - Judge)
6. Feleke Jembere (Ministry of Labour and Social Affairs – Director)
7. W/ro Selamawit Girmay (Fderal Supreme Court Child Justice Project Office)

The attendees expressed their support for the proposed committee members with applause. Further agreement was also reached for the establishment of similar facilitative committees at West Shewa Zone, East Shewa Zone, and at Hawassa, comprising the high court, women, youth and children affairs offices and labour and social affairs offices, in each area

Finally, Ato Fasil thanked participant for their valuable contribution. He then called on Ato Leuleselasse, judge at the Federal First Instance Court, to make concluding remarks.

## Concluding remark

Ato Leulseged thanked all participants for being helpful and cooperative for the fruitful discussion at the Workshop and declared the workshop concluded.

# PART III:

# ANNEXES

**(Directives & Guidelines from the Federal First Instance Court)**

# የቀለብ አወሳሰን እና ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ቤት አንደኛው ተጋቢ ስለሚለቅበት ሁኔታ

## <u>መግቢያ</u>

ቤተሰብ የህብረተሰብ መሰረት በመሆኑ ነው ህብረተሰብ እና መንግስት ጥበቃ የሚያደርጉለት፡፡ መንግስት ለቤተሰብ ጥበቃ ከሚያደርግበት መንገድ አንዱ የቤተሰብን ግንኙነት በህግ መደንገጉ ነው፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አላማ አድርጎ የተነሳባቸው ዋና ዋና ቁምነገሮች በተጋቢዎች መካከል ሊኖር የሚገባውን የእኩልነት መብት ማክበርና ማስከበር፤ በቤተሰብ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ፍትሀዊና በተቀላጠፈ ሁኔታ መፍታት እንዲሁም ልጆችን የሚመለከቱ ጉዳዮችጥቅምና ደህንነት ባስቀደመ ሁኔታ እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ነው፡፡ እነዚህን እጅግ በጣም ጠቃሚ ግን ጥቅልየሆነ የቤተሰብ ህግን ለማሻሻል ዋና ምክንያት የሆኑ አላማዎችን ማሳካት የሚቻለው በህጉ ውስጥ የተካተቱ መብቶችና መርሆዎችን ዘርዘር ብለው ለአጠቃቀም በሚያመች ሁኔታ ሲዘጋጁ ነው፡፡

የዚህ ጽሁፍ አላማም የልጆችን ቀለብ አወሳሳን፣ የልጆች ጥቅምና ደህንነት በሚያስቀድም ሁኔታ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል እንዲሁም የፍች ጥያቄ ፍርድ ቤት እንደቀረበ ከባልና ሚስት አንዱ ከጋራ መኖሪያ መውጣት ካለባቸው የትኛው መውጣት እንዳለበት ለመወሰን የሚያስችል ማብራሪያ ለማቅረብ ነው፡፡

ተመሳሳይ ይዘት ያለው ማብራሪያ ለማቅረብ በ1999 ተዘጋጅቶ በስራ ላይ ለማዋል የተሞከረ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈለገውን ያህል ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ ማብራሪያ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ የነበረውን ማብራሪያንና ማብራሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ አጋጥመው የነበሩ ችግሮችን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

በማብራሪያው ረቂቅ ላይ የቤተሰብ ችሎት ዳኞች በሰፊው ተወያይተውበታል፡፡ ማብራሪያው ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠትም ሆነ የፍርድ ቤቱን ስራ ተገማች ከማድረግ አኳያ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የቤተሰብ ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ ደንብ ለማውጣት ስልጣን የተሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲሁም መመሪያ ለማውጣት የተሰጣቸው የከተማ መስተዳድሮች (አዲስ አበባ እና ድሬደዋ) ለወደፊት ለሚያወጡት ደንብና መመሪያ ለማውጣት እንዲሁም በጉዳዩ ላይ ጥናት ለማካሄድ ለሚሹ ግለሰቦችና ተቋሞች መነሻ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

*ደሳለኝ በርሄ*

*የፌደራል መጀመሪያ ደረጃፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት*

## ክፍል 1፡ የቀለብ አወሳሰን

### መግቢያ

ለልጆች የሚቆረጥ የቀለብ ጥያቄ ጋብቻ በፀናበት ጊዜ፤ የፍቺ ጥያቄ ሲቀርብና የፍቺ ውሣኔ ከተሰጠ በኋላ በፍርድ ቤቶች ይስተናገዳል፡፡ የቀለብ ጥያቄን የምናስተናግድበት ሁኔታ በውል የተጠና እና መሠረታዊ መርሆዎችን ያገናዘበ ካልሆነ በልጆች አስተዳደግ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

ሕፃናት የመኖር እና የእድገት መብት አላቸው፡፡ ይህን መብት ለማስከበር በፍርድ ቤት ከሚወሰዱ እርምጃዎች አንዱ ቀለብ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወገን ግዴታውን እንዲወጣ ማድረግ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው አለምአቀፋዊ ስምምነቶች፤ ሕገ-መንግስታችን እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ሕፃናትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ሲያስተናግዱ የሕፃናትን ደህንነት በቀደምትነት ማሰብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ቀለብን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎች መስተናገድ ያለባቸው በዚሁ መንፈስ ነው፡፡

የቤተሰብ ሕጋችን እንዲሻሻል ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱ ሕጉ የሕፃናትን ደህንነት በሚያስቀድም መልኩ መሻሻል በማስፈለጉ መሆኑን ከሕጉ መግቢያ ላይ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ተቀርጾ በመውጣቱ ብቻ የሚፈለገውን ግብ ማምጣት አይቻለውም፡፡ ሕጉ የታሰበለትን ግብ የሚያስገኘው የፍርድ ቤቶች አሰራር የሕጉን የፍልስፍና መሰረቶች እና ትክክለኛ መንፈስ የተከተለ ሲሆን ነው፡፡

የጽሁፉ አላማ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ከቀለብ ውሳኔ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ጉዳይ አመራሩ ዙሪያ ያሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት የልጆችን ጥቅም ያስቀደመ የቀለብ ጉዳይ አወሳሰን ሥርዓት ምን መምሰል እንዳለበት ማመላከት ነው፡፡

ልጆችን አስመልክቶ የሚሰጡት ውሳኔዎች የልጆች መብቶች የፍልስፍና መሰረት የሆኑትን ልዩነት አለማድረግ፣ የልጆች ጥቅም ቀደምትነትንመኖርና የእድገት መብቶችን እንዱሁም የተሳትፎ መብቶችን ታሰቢ ማድረግ አለባቸው፡፡

### 1. ጥናቱ ያተኮረባቸው ነጥቦች

ከቀለብ አውሳሰን ጋር በተያያዘ ተስፋ ሰጭ የሆኑ አሰራሮች ቢኖሩም በተቃራኒው የጉዳይ አመራራችን እና የምንሰጣቸው ትዕዛዞች/ ውሣኔዎች/ ላይ ከፍትሐዊነት እና ተገማችነት ጋር በተያያዘ ቅሬታዎች ይሰማሉ፡፡

ለቅሬታዎቹ መነሻዎች በርካታ የመሆናቸውን ያህል መፍትሄዎቹም ያንን ያህል ናቸው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ላይ ማተኮር የተፈለገው ተደጋግመው ቅሬታ በሚሰማባቸው

የተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው፡፡ እነሱም የቀለብ እና የገቢ ትርጉም እንዲሁም የቀለብ መጠን አወሳሰን ገቢ የሌለው ሰው ቀለብ የመክፈል ግዴታ ሊጣልበት ይገባል ወይስ አይገባም በሚሉትና የቀለብ መጠን ለማሻሻል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን የሚመለከት ነው፡፡ እንዲሁም ለተጠቀሱት ችግሮች የመፍትሄ ሀሳቦች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ከላይ የተመለከቱትን አከራካሪ ነጥቦች እንደ ቅደም ተከተላቸው እንመለከታቸዋለን፡፡

## 2. ቀለብ ማለት ምን ማለት ነው?

ስለቀለብ መስጠት ግዴታ የሚደነግገው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጋችን ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዩ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልምድ የሚስማማውን በተመለከተ ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፤ መኖሪያ፤ እና ልብስ ጤናውን የሚጠብቅበትንና እንደ ሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊውን ነገር መስጠት ያለበት መሆኑን ይደነግጋል፡፡ አንቀጽ 197(ን) ይመለከታል፡፡ በተለይም ለልጆች አጠባበቅ አያያዝ የሚደነግገው አንቀጽ 113 ላይ ስለልጆች ለቀለብና ፍላጎታቸውን የሚያስጠብቅ መሆን እንዳለበት በግልጽ ተደንግጓል፡፡

ለልጅ የሚቆረጥ ቀለብ ማለት ምን ማለት ነው ለሚለው ቀጥተኛና ሁሉን የሚያስማማ ትርጉም ማግኘት ያስቸግራል፡፡ ሆኖም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ስለቀለብ የተደነገጉትን የተለያዩ ድንጋጌዎች እንዲሁም በተለያዩ ሀገራት ለቀለብ ከተሰጡ ትርጉሞች በመነሳት ለዚህ ጽሁፍ አላማ ቀለብን በሚከተለው ሁኔታ ለመተርጎም ተሞክሯል፡፡

የልጅ/ጆች ማሳደጊያ ቀለብ /Child support/ ወላጆች ልጆቻቸው አካለ መጠን እስከሚደርሱ ድረስ ለልጃቸው ማሰደጊያ የሚያውጡት (የሚያዋጡት) ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ ከፍች ጋር በተያያዘ ሁኔታ ደግሞ የልጅ/ጆች ቀለብ ልጅ ለማሳደግ በህግ የተወሰነለት ወገን ለልጁ አስተዳደግ ለሚያወጣው ገንዘብ ሌላኛው ወላጅ እንዲከፍል ወይም እንዲያዋጣ የሚገደደውን የገንዘብ መጠን የሚመለከት ነው፡፡ ቀለብ የመክፈል ግዴታ ያለበት ወላጅ የሚከፍለው ቀለብ የሚቆረጥለት ልጅ የተስተካካለ (አካላዊ፣ አእምሮአዊ እና ስሜታዊ) ጤንነትና እድገት እንዲኖረውየሚያስችሉ ሁኔታዎች ለማሟላት የሚያስችል ምክንያታዊና አስፈላጊውን ያህል (reasonable and necessary) መሆን አለበት፡፡

ከተለያዩ ሀገራት በተለይም በአሜሪካ/የተለያዩ ግዛቶች/፣ በካናዳ እና በአውስትራሊያ ቀለብን ለመወሰን የተዘጋጁ መመሪያዎች (child support guidelines) ለመገንዘብ የሚቻለው ከፍቺ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የቀለብ ጥያቄዎች ልጆች ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት ያገኙት የነበረውን ጥቅም ማግኘት እንዲቀጥሉ በሚያስችል መልኩ ሰፍቶ ነው የሚተረጎመው፡፡ እንደሚታወቀው አብዛኞቹ ወላጆች ለልጆቻቸው አይሰስቱም፡፡ ፍቅራቸውን ከሚገልጽበት መንገድ አንዱ ለልጆቻቸው ያላቸውን በመስጠት ነው፡፡ ይህ ለጋስነታቸው ይበልጥ የሚታየው ጋብቻው በጸናበት ወቅት ነው፡፡ ለዚህም ነው የቀለብ ውሳኔ ሲወሰን ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት ያገኙት

የነበረውን ጥቅም ማግኘት እንዲቀጥሉ በሚያስችል መልኩ መተርጎሙ በበርካታ ሀገሮች ተቀባይነት ያለው፡፡ ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ሲያገኙት የነበረው ጥቅም በሙሉ መዘርዘር አይቻልም ይሆናል፡፡

ሆኖም ዋና ዋናዎቹን መዘርዘር አይከብድም ተብሎ ይታመናል፡፡ ለልጆች የላቀ አካላዊ እና አእምሮአዊ እድገት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ዋና ዋና ተብለው በተለምዶ የሚታወቁት ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ ትምህርት እና ህክምና በተጨማሪ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ለልጆች እድገት አስፈላጊ መስለው ከሚታዩና በቀለብ ውሣኔዎች ላይ ታሳቢ አድርገናቸው ለማናውቃቸው ግን በጣም ጠቃሚ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ የመጫወትና የመዝናናት መብት ነው፡፡ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 12 ልጆች የመጫወት መብት እንዳላቸው በግልጽ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ይህን መብት ታሳቢ ያደረገ ጥያቄም ሆነ ውሳኔ በመዝገቦች ፍርድ ቤት ቀርቦ የማያውቅ መሆኑን ለጥናት ከተጠቀምንባቸው መዝገቦችም ሆነ ከዳኞች ጋር በተደረገ ውይይት መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህን መብት ማረጋገጥ ሌሎችን መብቶች ከማረጋገጥ የሚከብድ አይደለም፡፡ ይህን መብት ልጆች በልጆች ቋንቋ እንዴት በጨዋታ እንደሚገልጹ ማስታወሱ የመብቱን ፋይዳ ለመግለጽ ይጠቅማል -- ከማር ከወተት ይሻለል መጫወት፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቀለብን  አስመልክቶ የደነገጋቸው ድንጋጌዎች የልጆችን ጥቅም እና ፍላጎት ለማሟላት አስበው የተቀረፁ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የቀለብ ጥያቄንም ሆነ ማናቸውንም ሕፃናትን የሚመለከት ጉዳይ ፍርድ ቤት ሲወስን የልጆችን ጥቅም ማስቀደም እንዳለበት ሕገ-መንግስታችንም ሆነ ኢትዮጵያ ፈራሚ የሆነችባቸው አለምአቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች የሚደነግጉ መሆኑን ማስታወሱ የቀለብጉዳይን ለልጆች አስተዳደግ በሚጠቅም መልኩ ለመተርጎም ይረዳል፡፡ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 36(3)፤ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3 እና የአፍሪካ የሕፃናት መብት ቻርተር አንቀጽ4(1) ይመለከቷል፡፡

በአጭሩ ቀለብ የሚለው ቃል ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ልጆች በአካላቸውና በአእምሮአቸው እንዲጎለብቱ የሚያስችልና ቢያንስ ጋብቻው ከመፍረሱ /ቀለብ ጠያቂው ከጋብቻ መፍረስ ጋር በተያያዘ ከቀረበ/ በፊት ሲያገኙ የነበረውን የአኗኗር ሁኔታ ማስቀጠል የሚያስችል ተደርቶ መተርጎም አለበት፡፡

ከቀለብ ትርጉም ጋር የሚነሱት ነጥቦች አንድ ነፍሰጡር ሴት በማህፀኗ ውስጥ ላለው ልጅ ቀለብ የማግኘት መብት አላት ወይስ የላትም የሚለው አከራካሪ ነጥብ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በየእለቱ የሚገጥም ጉዳይ ባይሆንም ጥያቄው ሲቀርብ መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን የሚነካካ በመሆኑ በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡ ሰው የመብት ባለቤት መሆን የሚጀምረው ከተወለደ ነው ወይስ ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለው ጥያቄ መልስ ካላገኘ የሕግ ክርክሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የቀለብ ውሳኔን

ለመተርጎም ሲባል ግን የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽኑን መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ከሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መግቢያ መገንዘብ የሚቻለው ሕፃናት ከመወለዳቸው በፊትም ሆነ በኋላ ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን ነው፡፡

> *"ሕፃኑ በአካልና በአእምሮም ያልዳበረ በመሆኑ ምክንያት ከመወለዱ በፊትም ሆነ በኋላ ልዩ ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያስፈልገው በማስተዋል"* የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው ነፍሰጡር እናቶች በማሕፀናቸው ላለው ልጅ ደሕንነት ቀለብ የማግኘት መብት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የቀለብ ትርጉም ሕፃናት በማህፀን ውስጥ እያሉ ለማደረግላቸው እንክብካቤ የሚደረግ ክፍያንም እንደሚጨምር ይታሰባል፡፡

### 3. የገቢ (Income) ትርጉም

የገቢ መጠን ቀለብ ለመወሰን ከሚረዱ ዋና መስፈርቶች አንዱ ነው፡፡ ገቢ የሚለው ቃል ትርጉም ላይ ግልጽነት ከሌለ ትክክለኛ የቀለብ መጠን መወሰን አይቻልም፡፡ የቀለብ መቁረጥ መሠረት የሚሆን ገቢን በተመለከተ በፍርድ ቤቶች የተዘጋጀ እና በስራ ላይ የዋለ ምንም አይነት ሰነድ ማግኘት አልተቻለም፡፡ የሰበር ችሎትም ከቀለብ ጋር በተያያዘ ገቢን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም የለም፡፡ የሌሎች ሀገራት ልምዶችም የሚያሳዩን ይህንኑ እውነታ ነው፡፡ ከማናቸውም ህጋዊ ምንጭ የተገኘ ገቢ ለቀለብ ውሳኔ መሠረት እንደሚሆን ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካን ሀገር በማሳቹተስ ግዛት የቀለብ አወሳሰን መመሪያ (child support guidelines) ገቢን አስመልክቶ የሰጠው ትርጉም "…gross income from whatever source" የሚል ነው፡፡ ይህ ትርጉም ለመልካም ስራ አፈፃፀም የሚሰጡ ጉርሻዎች (tips)የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ጨምሮ ሌሎች ማናቸውንም ገቢ ይመለከታል፡፡

ከዳኞች ጋር በተደረገው ውይይት እና ከተበተኑ መጠይቆች ከተገኙ መልሶች መረዳት የተቻለው ገቢን በተመለከተ አንድ ወጥ የሆነ አረዳድ አለመኖሩን ነው፡፡ በቀለብ መጠን አወሰሰንም ሆነ አፈፃፀም ዳኞች ገቢን መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ብለው ይከፍሉታል፡፡

መደበኛ ገቢ ተብለው የሚወሰዱት የቀለብ ገንዘብ ለመወሰንምሆነ ለማስፈፀም አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ምቹ ናቸው ተብለው የሚወሰዱት ከቋሚ ተቀጣሪዎች፤ ከቤት ኪራይ፤ ከኩባንያ ትርፍ ድርሻ እና ከመሳሰሉት የሚገኙ ገቢዎች ናቸው፡፡

ኢ-መደበኛ ገቢ የሚባሉት የቀለብ መጠንን ለመወሰንም ሆነ ለማስፈፀም አስቸጋሪ ናቸው ተብለው የሚወሰዱት ሲሆን፤ በዚህ ውስጥ ከድለላ ሥራ፤ ቋሚ ካልሆኑ ስራዎች፤ አነስተኛ ንግድና ከመሳሰሉት ሥራዎች የሚገኙ ገቢዎች የሚመለከት ነው፡፡ በእነዚህ የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች ገቢን ማረጋገጡም ሆነ ማስፈፀሙ አስቸጋሪ ነው፡፡

ከንግድ ስራ ጋር በተያያዘም የታክስ ባለስልጠን የወሰነውን ገቢ መሠረት በማድረግ የቀለብ መጠንን ለመወሰን መሠረት ማድረግ ይቻል ይሆናል፡፡ ሆኖም ከታክስ ስርአታችን ችግር ጋር በተያያዘ ትክክለኛውን የገቢ መጠን ማወቁ አስቸጋሪ ነው፡፡ በዚህ ሂደት የልጆችን ጥቅም በተሟላ መልኩ ማስከበር መቻሉ ያጠራጥራል፡፡

የገቢ መጠንን ማወቅ ለበርካታ ሀገሮች ቀላል አይደለም፡፡ የሌሎች ሀገራት ልምዶችም የሚያሳዩን ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

ምንም እንኳን እስካሁን ባለው የፍርድ ቤቶች ልምድ በቀለብ መሠረት አይሆኑም የተባሉ ገቢዎች ስለመኖራቸው ማስረጃ ባይኖርም ገቢ የሚለው ትርጉም **ማናቸውም ገቢና ንብረትን** የሚመለከት መሆኑን ማስታወሱ አመልካቾችም ሆኑ ዳኞች ጉዳዩን ሰፋ አድርገው እንዲመለከቱና በሚወሰነው የቀለብ ገንዘብ ተጠቃሚ የሚሆኑ ልጆች ከወላጆቻቸው ሊያገኙት የሚችሉትን የገንዘብ ድጋፍ በተሟላ መልኩ እንዲያገኙ ይረዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም እውቀቱም ሆነ ገንዘብ የሌላቸው እና የህግ ድጋፍ ማግኘት የማይችሉ በርካታ የቀለብ ጥያቄ አቅራቢ ሴቶች ባሉበት ሁኔታ ዳኞች ምንም ያህል ሕጉ እና አሰራሩ የሚፈቅደውን ያህል ቢሄዱ ቀለብ የተጠየቀለት/ላት ልጅ ጥቅም የሚያስጠብቅ ውሣኔ መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ ችግሩን ከሚያወሳስቡት ነገሮች ውስጥ አንዱ ቀለብ እንዲከፍል የሚጠየቀው ሰው ገቢን ማወቅ አስቸጋሪ መሆን ነው፡፡ **ይህን ችግር ለማስወገድ በማስረጃ አሰባሰብም ሆነ በምዘና ሂደት የልጆችን ጥቅም ማስከበር እንዲቻል ከተለመደውየማስረጃ አሰባሰብና ምዘና ሂደት ሰፋ ያለ አያያዝን መከተል ተገቢእንደሆነ የተለያዩ ሀገሮች ልምድ ያስረዳል፡፡** ከአንዳንድ ሀገሮች ልምድ መገንዘብ የሚቻለው ቀለብ ጠያቂው አለው የተባለውን ያህል ገቢ የሌለው መሆኑን የማስረዳት ሸክም እንዲጣልበት ማድረጉ ትክክለኛውን የገቢ መጠን ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ እነዚሁ የሕግ ሥርአቶች በአመልካቾች ላይ የሚጥሉት ግዴታ ቀለብ እንዲከፍል የተጠየቀው ሰው ገቢ ያለው መሆኑን የማሳመን ግዴታ ነው፡፡

### 4. የቀለብ መጠን አወሳሰን

የቀለብ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂውን ወይም ቀለብ የሚጠየቅለት/ላት/ ልጅ ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን መሆን እንዳለበት፤ እንዲሁም ቀለብ የመስጠት ግዴታ የአካባቢውን ልምድ በመከተል ለምግብ ፣ ለመኖሪያ፣ ለልብስ እና ለጤና መጠበቂያ እና እንደነገሩ ሁኔታ በትምህርት የሚወጣ ወጪን የሚሸፍን መሆኑ እንዳለበት ስለቀለብ በአጠቃላይ በሚደነግገው የሕግ ክፍል ላይ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል አካለ መጠን ያልደረሱ ወይም አካለ መጠን ቢደርሱም በአካላዊና በአእምሮአዊ ችግሮ ምክንያት የራሳቸው ገቢ የሌላቸው ልጆችን አስመልክቶ የቀለብ መጠን ፍርድ ቤቶች ሲወስኑ የልጆቹን አድሜ ጥቅም እና ፍላጎት ማገናዘብ እንዳለበት በአንቀጽ 113 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከእነዚህ የሕጋችን ድንጋጌዎች

መገንዘብ የሚቻለው የቀለብ መጠን የሚወሰነው የቀለብ ሰጪውን የገቢ መጠን እና ቀለብ የሚጠየቅላቸውን ልጆች እድሜ፣ ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን የሚያመዛዝን መሆን አለበት፡፡

በፍርድ ቤቶቻችን ያለውን አሰራር በዚህ ጥናት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ለጥናቱ መሠረት ከሆኑ መዝገቦች መገንዘብ የተቻለው ዳኞች የቀለብ ውሣኔ ሲወስኑ እንዴት እና ለምን የተወሰነውን የገንዘብ መጠን እንደወሰኑ የሚጠቁም ነገሮች በውሣኔው /ትዕዛዝ/ ላይ ተመልክተው አልተገኙም፡፡ ለምሣሌ በመ/ቁጥር 31876 ተጠሪ ለሁለት /2/ ልጆች ቀለብ ብር 120 እንዲከፍል ሲታዘዝ የቀለቡን መጠን እንዴት እንደተወሰነም ሆነ ቀለብ የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰው የገቢ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ከመዝገብ ውስጥ አልተመዘገበም፡፡ የመ/ቁጥር 28249፤ 28581 እና 28249 በተመሳሳይ ሁኔታ ውሳኔ የተሰጠባቸው መዝገቦች ናቸው፡፡ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት ከተሸፈኑት ውስጥ በአንዳቸውም ዳኛው ለቀለብ የተቆረጠውን የገንዘብ መጠን እንዴት እንደተሰላ የሚያመለክት ፍንጭ አልተገኘም፡፡ ዳኞች የቀለብ መጠኑን ለመወሰን የተጠቀሙበት ስሌት የማይገለጽበት ምክንያት ባመዛኙ ጉዳዩን ግራ ቀኙን በመስማት ለመፍታት ጥረት በማድረጋቸው እንደሆነ ቃለ-መጠየቅ ከተደረገላቸው ዳኞች መገንዘብ ተችሏል፡፡

መደበኛ ገቢ ያለቸው ባለጉዳዮችን በተመለከተ በተለይም የገቢው ምንጭ ደመወዝ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የገቢውን መጠን ከገለፀ በኂላ በምን ስሌት እንደተሰራ የማይታወቅ የቀለብ መጠን ተወስኖ ይገኛል፡፡ በበርካታ መዝገቦች የሚወሰነው ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ ያለበት ገቢ እና ጥያቄው ወደ ፍርድ ቤቱ ከመቅረቡ በፊት ተጠሪው ሲከፍል የነበረው መጠን ለሚሰጠው የቀለብ ውሣኔ መሠረት የተደረገ መሆኑን ነው፡ ፡ በዚህ ረገድ የመ/ቁጥር 34731 እና 30834 ተጠቃሽናቸው፡፡

በሌላ በኩል መደበኛ ያልሆነ ገቢ ያላቸው ወይም ገቢያችን ተቋርጧል በማለት የሚከራከሩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ተከራካሪዎች በተመለከተ ዳኞች ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወገን የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት ቀለብ የሚቆረጥለት/ላት ልጅ ይኖርበት የነበረውን የኑሮ ሁኔታ በማገናዘብ ቀለብ እንደሚቆርጡ ከዳኞች ጋር በተደረገ ውይይት መገንዘብ ተችሏል፡፡

ከቀለብ መጠን አወሳሰን ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው አከራካሪ ነጥብ ተቀናናሾችን የሚመለከት ነው፡፡ የቀለብ መጠን የሚወሰነው ከአጠቃላይ ገቢ ሳይሆን ከተጣራው ገቢ ነው፡፡ የተጣራ ገቢ የሚባለው ተቀባይነት ያላቸው ተቀናናሾች ከተቀነሱ በኂላ ወደ እጁ የሚገባ የገንዘብ መጠን ነው፡፡ አከራካሪው ነጥብ ተቀባይነት ያላቸው ተቀናናሾች የትኞቹ ናቸው የሚለው ነው፡፡ ከደመወዝ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚቀርቡትና አከራካሪ የሆኑት ጋብቻ ከመፍረሱ በፊት ከትዳር ጓደኛው እውቅና ውጭ ለተገባ ግዴታ የሚቀነስ ገንዘብ፤ ለገንዘብ ቁጠባ ማሕበር በየወሩ የሚደረግ መዋጮንና የመሳሰሉት የሚመለከት ነው፡፡ በሌላ በኩል ቀለብ የመቁረጥ ግዴታ የተጣለበት ወገን ለአባት እና ለእናቱ መጦሪያ (ፍርድ ቤት ያልተወሰነም ቢሆን) እንዲሁም አካለ መጠን ለደረሱ ልጆች ማስተዳደሪያ አወጣለሁ የሚለው ገንዘብ

የቀለብ መጠንን ለመወሰን ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው ወይም የለባቸውም የሚለውም ሌላው አከራካሪ ነጥብ ነው፡፡

ከዳኞች እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች ባለሙያዎች ጋር ከተደረገ ውይይት መገንዘብ የተቻለው በጉዳዩ ላይ ሰፊ ልዩነት ያለ ቢሆንም ልጆችን በተመለከተ የሚሰጡ ውሣኔዎች የልጆችን ጥቅምና ደሕንነት ማስቀደም ስላለባቸው ሌሎች ወጪዎች ለልጆች ከሚሰጥ ቀለብ ቅድሚያ ሊያገኝ አይገባም የሚል መግባባት ያለ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ ምንምእንኳን የታወቁ እዳዎች በተለይም በፍርድ የተረጋገጡ ቀድመው መቀነሳቸው የግድ ቢሆንም ቀለብ ሲሰላ ተቀናሽ ናቸው የተባሉት እዳዎች ወይም መዋጮዎች በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በሌሎች ሀገራት ያለው አሰራር የሚያሳየው የቀለብ መጠን የቀለብ ሰጪን ገቢ እና የቀለብ ተቀባዩን ፍላጎቶች ለማመዛዘን የሚሞከር ቢሆንም በዋና መስፈርትነት የሚወሰዱት ግን ልጆች ጋብቻው ከመፍረሱ በፊት ያገኙት የነበረውን ጥቅም ሳይጓደል እንዲቀጥል ማስቻልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካን ሀገር ኤሊኖይ ግዛት የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ስንመለከት በዋና መስፈርትነት ከተቀመጡት ውስጥ ልጆች ጋብቻው ባይፈርስ ኖሮ ይኖሩት የነበረው ህይወት(the standard of living the child would have enjoyed had the marriage not been dissolved)፤ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው አቅም እና ቀለብ የሚቀረጥለት/ላት ልጅ ፍላጎት ይገኙበታል፡፡ በርካታ ያደጉ አገሮች ይህን ታሳቢ ያደረገ የቀለብ መጠን ለመወሰን የሚረዳ መመሪያ (child support guidelines) አላቸው፡፡ ይህን መመሪያና በዚሁ መሰረት የተዘጋጀውን የሂሳብ ማስሊያ መጠቀም ባለጉዳዮች በቀለብ ረገድ ያለባቸው መብት እና ግዴታ ዳኛው ሳይነግራቸው መገመት የሚችሉበት አሰራር አላቸው፡፡ ሆኖም ይህን አሰራር ተግባራዊ ለማድረግ አስተማማኝ የታክስ ስርአትና የንብረት ምዝገባ መኖር የግድ ይላል፡፡ ይህ ማለት ግን ቀለብ ለመወሰን የሚረዳ ማስሊያ ቀመር ማዘጋጀት አያስፈልግም ወይም አይቻልም ማለት አይደለም፡፡

የቀለብ ጥያቄ ከጋብቻ መፍረስ ጋር በተያያዘ ሲቀርብ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ**ዋናው መስፈርት መሆን ያለበት ጋብቻው ባይፈርስ ኖሮ ልጆች ይኖሩት የነበረው ህይወት ለማስቀጠል የሚያስችል ስሌት መስራት ነው፡፡** ሆኖም ይህ አማራጭ የልጆችን ጥቅም ሊያስከብር አይችልም ተብሎ ሲታመን፤ እንዲሁም ለሌሎች ጥቅም ላይ ይውል ዘንድ የተዘጋጀ የቀለብመጠን ማስሊያ ማጣቀሻ ተሰራጭቷል፡፡ ይህ “ለልጅ ቀለብ የመስጠት ግዴታን ለመወሰን የሚያግዝ ረቂቅ ማጣቀሻ” ሰነድን አግባብነት ባላቸው ጉዳዮች መሞከሩ ለወደፊት ለሚዘጋጁ ተመሳሳይ ሰነዶች ትልቅ ፋይዳ አለው ተብሎ ያታመናል፡፡

የቀለብመጠን መወሰኛ ማጣቀሻው በርካታ ጥቅም ያለው ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ጥቅሞች ፍትሐዊና ተገማችነት ያለው አሰራር እንዲኖር ማስቻልና የዳኞችና ተከራካሪ ወገኖችን ድካምና ጊዜን መቆጠብ ነው፡፡

## 5. ገቢ የሌለው ሰው ቀለብ ሊከፍል ይገባል?

በዚህ ዙሪያ ሚነሱ አከራካሪ ነጥቦች

1. ገቢ ከሌለው ቀለብ የመክፈል የሕግ ግዴታ አለበት ወይስ የለበትም?
2. ግዴታ አለበት ቢባል እንኳን የገቢው መጠን ካልታወቀ እንዴት የቀለብ መጠን ማስላት ይቻላል?እና
3. ገቢ ከሌለው እንዴት ማስፈፀም ይቻላል የሚሉት ናቸው፡፡

ከዳኞች ጋር በተደረገ ውይይት መገንዘብ የተቻለው በጉዳዩ ላይ የተለያዩ አቋም ያለ መሆኑን ነው፡፡ በአንድ በኩል የቀለብ ግዴታ ከገቢ መጠን ጋር የሚያያዝ ስለሆነ ገቢ ከሌለው ቀለብ የመክፈል ግዴታ ሊኖር አይችልም የሚል ትርጉም ያለ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የገቢ መጠን ከቀለቡ መጠን ጋር የሚያያዝ እንጂ የቀለብ መክፈል ግዴታ አያስቀርም የሚል አረዳድ ያለ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ጥናቱ ካተኮረባቸው መዝገቦችም ሆነ ከተደረጉት ዉይይቶች ላይ መገንዘብ የተቻለው ቀለብ የሚጠይቀው/የምትጠይቀው/ሰው ገቢ አለው/አላት ብለው ማሳየት ካልተቻለ የቀለብ መስጠት ግዴታ መሠረት ተደረጎ የተሰጠ ትዕዛዝ የሌለ መሆኑን ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕጋችን ስለቀለብ በሚደነግገው ምዕራፍ ወላጆች ለልጆቻቸው ቀለብ የመስጠት ግዴታ እንዳለባቸው በግልጽ ተደንግጓል (አንቀጽ 198/ን/ ይመልከቷል)፡፡ ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብ እንዲሁም የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ ፍርድ ቤቱ የልጆችን ቀለብ አስመልክቶ መወሰን እንዳለበት ተመልክቷል (የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 82 እና 113 /ን/ ይመልከቷል)፡፡ ከዚህ በተጨሪም ልጅ የማሳደግ ግዴታን አለመወጣት ወንጀል ነው (የወ/መ/ሕ/ቁጥር 659 ይመለከቷል)፡፡ ከእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው ልጆቻቸውን የማሳደግ ግዴታን አለመወጣት የወንጀልን እና የፍትሀብሄር ሀላፊነትን ያስከትላል፡፡

ወላጆች ሙሉ ጤንነት እያላቸው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሥራ ባለመያዛቸው ወይም በማናቸውም መልኩ ገቢ ለማግኘት ባለመቻላቸው የወላጅነት ግዴታቸውን ላለመወጣት ተቀባይነት ያለው ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ ለምሳሌ ሁለት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በጓደኝነት ዘመናቸው በትምህርት ላይ እያሉ ልጅ ቢወልዱ ሁለቱም ስራ ስለሌላቸው የተወለደው ልጅ ቀለብ የማግኘት መብት የለውም ማለት አይደለም፡፡ የልጁ ወላጆች ትምህርታቸውን እየተማሩ በትርፍ ጊዜያቸው በመስራት ልጃቸውን መርዳት ግዴታቸው ነው፡፡ የልጁ አባት እኔ ተማሪ ስለሆንኩ ገቢ የለኝም ቀለብ ልከፍል አይገባም የሚል ክርክር ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ሆኖም ትምህርቱን እየተማረ መስራት ካልቻለ ትምህርቱን አቋርጦም ቢሆን በሕግ የተጣለበትን ልጅ የማሳደግ ግዴታ ይወጣል እንጂ ስራ ስለሌለው ቀለብ ሊከፍል አይገባም የሚል ውሳኔ መስጠት ከህጉ መንፈስ ውጭ ነው፡፡ ህገ-መንግስታችን፣ በአለም አቀፍ

ስምምነቶች እንዲሁም በቤተሰብ ሕጋችን የልጆችን የመኖርና የማደግ መብት እንዲሁም የልጆችን ጥቅምና መብቶች እንድናከብርና እንድናስከብር ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ልጅን የማሳደግ ግዴታን አለመወጣት የወንጀልም የፍትብሔርም ሀላፊነት የሚያስከትል መሆኑን ካየን ቀጥሎ መታየት ያለበት የገቢው መጠን ባልታወቀበት ሁኔታ የቀለብ መጠኑን እንዴት መወሰን ይቻላል የሚለው ነው፡፡ የገቢው መጠን ሳይታወቅ የሚከፈለውን የቀለብ መጠን መወሰን አስቸጋሪ መሆኑ የገንዘብ መጠኑን መወሰን አይቻልም ማለት አይደለም፡፡

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ዳኞች ሶስትመንገዶችን ሊከተሉ ይችላሉ፤

**1ኛው፡-** ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለቀለብ ጥያቄ ምክንያት የሆነው ነገር ከመፈጠሩ በፊት ይሰጥ የነበረውን ገንዘብ ወይም የልጁን የኑሮ ሁኔታ መነሻ ማድረግ (ወይም)

**2ኛው፡-** ያለውን ሙያ፣ የትምህርት ደረጃ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት በዝቅተኛ ደሞዝ ቢቀጠር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ መገመት (ወይም)

**3ኛው፡-**በቀን ስራ ላይ የተሰማራ ሰው የሚያገኘውን ዝቅተኛ ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት ቀለብ መጠኑን መወሰን ይቻላል፡፡

ይህ አሰራርና የህግ ትርጉም ጠቃሚ በመሆኑ እንደነገሩ ሁኔታ እየታየ ተገቢውን አማራጭ መውሰዱ ይመከራል፡፡

የቀለብ መጠኑ መወሰኑ ግዴታው የተጣለበት ሰው ግዴታውን እንዲወጣ የሚያተጋው ከመሆኑም በተጨማሪ አፈፃፀሙን በተመለከተ ማናቸውም የፍትሐብሄር ጉዳዮች በሚፈፀሙበት ሁኔታ ሊፈፀምየሚችልበት ሁኔታ ማመቻቸት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ይህንኑ ግዴታ ካልተወጣ የወንጀል ኃላፊነት እንዳለበት ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የቀለብ ውሣኔ ላይ ማስፈሩም የቀለብ መክፈል ግዴታ ያለበት ሰው ኃላፊነቱን ተግቶና ተጠንቅቆ እንዲወጣ ያስገድደዋል፡፡

### 6. የቀለብ ውሣኔ ስለማሻሻል

የቀለብ ውሣኔ እንዲሻሻል ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ በርካታ ጉዳዮች አለመኖራቸውን በተደረገ ጥናት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ለጥያቄዎቹ አለመቅረብ የተለያዩ ግምቶች ቢኖሩም አንዱ እና ዋናው ምክንያት በርካታ ባለጉዳዮች በጠበቃ ስለማይከራከሩ ይህ መብት ያላቸው መሆኑን አለማወቃቸው እንደሆነ ይገመታል፡፡ የቀለብ ውሳኔን ለማሻሻል ከሚቀርቡ አቤቱታዎች ጋር በተያያዘ ከሚነሱ ችግሮች ውስጥ አንዱ የቀለብ ጥያቄን

ለማስለወጥ የሚቀርብ አቤቱታ ፍርድ ቤቱ የሚቀርበው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው የሚል ነው፡፡

የቀለብ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ሁኔታ እና የቀለብ ሰጭውን አቅም በማመዛዘን ነው (የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 202/2/ ይመለከቷል)፡፡ ፍርድ ቤት የቀለብ መጠን የሚወስነው ይህንኑ መነሻ አድርጎ ነው፡፡ የቀለብ መጠን ይሻሻልልኝ ጥያቄም ተቀባይነትሊያገኝ የሚችለው ለቀለብ ውሳኔ መሠረት ከሆኑት ነገሮች (ቀለብ የተጠየቀላቸው ልጆች ፍላጎት ወይም/ እና የቀለብ ሰጭው ገቢ ሲለወጥ) አንዱ ወይም ሁሉም ተለውጠው ሲገኙ ነው፡፡

ለምሳሌ ቀለብ እንዲቆርጥ የተወሰነበት ሰው ከሥራ ቢቀነስ ወይም ተጨማሪ ገቢ ቢያገኝ እንደነገሩ ሁኔታ ቀለብ ሰጭው ወይም ተቀባዩ የቀለብ መጠኑ እንዲጨመርለት ወይም እንዲቀነስለት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይህ ግን በልጁ ሕይወት ላይ ለውጥ ሊያመጡ የማይችል ቀለብ ሰጭው ያገኛቸውን ውስን ገቢዎች በመያዝ ፍርድ ቤቱ ቀለብ እንዲጨምር ማመልከት ይቻላል ማለት አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተለያይተው የነበሩት ቤተሰቦች በጋራ መኖር ከጀመሩ ለቀለብ ውሳኔ መለወጥ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም በጋራ መኖር ስለጀመርን የቀለብ ውሳኔው ይነሳልን የሚል ማመልከቻ እንደቀረበ ወዲያው መወሰኑ ተገቢ ላይሆን ይቻላል፡፡ የአብሮ መኖር ውሳኔው የቀለብ ውሳኔውን ለማስነሳት ያህል ብቻ የተደረገ ስምምነት አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ለተወሰኑ ወራቶች ውሳኔው ሳይለወጥ ባለበት ሁኔታ ማቆየቱ ተመራጭ ነው፡፡

የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄን ፍርድ ቤት የሚያስተናግደው የቀለብ መጠኑ ሲወሰን ዳኛው አዲስ የተፈጠሩትን ሁኔታዎች አውቆ ቢሆን ኖሮ የቀለብ መጠኑን በወሰነው መልኩ አይወስንም ነበር የሚል ግምት የሚያሰጥ ነገር ሲኖር ብቻ ነው፡፡

የቀለብ መጠን ይሻሻልልኝ ጥያቄን በተመለከተ የሚነሳው ሌላው ነጥብ የቀለብ ውሣኔ ከተሰጠ ከምን ያህል ጊዜ በኂላ ነው ማመልከቻ መቅረብ የሚቻለው የሚለው ነው፡፡

የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 113/3/ ና 202 የቀለብ ጥያቄን ሁኔታዎች በተለወጡ በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ በአንዳንድ ሀገሮች በተለይም በተለያዩ የአሜሪካን ግዛቶች የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄን ለማቅረብ የሚቻለው በሕግ የተመለከተው ጊዜ ሲያልፍ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ የሚቀርበው ምክንያትም የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ የሚቀርብ ከሆነ በፍርድ ቤቶች ላይ ተጨማሪ ጫና ይፈጥራል የሚል ነው፡፡

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ መብቱን አውቆ በተደጋጋሚ አቤቱታ በማቅረብ የፍርድ ቤቱን ጊዜያጣብባል የሚል ስጋት ስለመኖሩ ጠቋሚ ነገሮች ካለመኖራቸውም በላይ የቀለብ ይሻሻልልኝ አቤቱታ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ማስቀመጡ የልጆች መብት ያጣብባል፡፡ አሁን ካለው እውነታ በመነሳት የቀለብ ይሻሻልልኝ ጥያቄን ሁኔታዎች

መለወጣቸውን አመልካቹ እስካስረዳ ድረስ በማናቸውም ጊዜ አቤቱታቸውን መቀበሉ ተገቢ ነው የሚል እምነት አለ፡፡

### 7. የልጅ ቀለብ አወሳሰን መርሆዎች

1. የልጆች ቀለብ አወሳሰን በዋናነት የልጆች ጥቅምን ቀዳሚ ማድረግ አለበት፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን የማሳደግ እና የመንከባከብ ሕጋዊ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ኢኮኖሚያዊ ኃላፊነትን የሚወጡት እንደገቢያቸው መጠን ለልጆች መልካም አስተዳደግ ተገቢው መዋጮ ሲያደርጉ ነው፡፡
2. የልጆች ቀለብ በሚወሰንበት ሂደት ወላጆች ለመኖር የሚያስፈልጋቸውንና ሌሎች ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያስችሉ መሠረታዊ ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም በማናቸውም ሁኔታዎች እንዲወጡ የሚያስችሉ መሰረታዊ ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም በማናቸውም ሁኔታ ግን ታሳቢ የሚደረጉ ነገሮች ለልጁ ቀለብ የመስጠት ግዴታን የሚያስቀርና በእጅጉ የቀለቡን መጠን የሚቀንስ መሆን የለበትም፡፡
3. እያንዳንዱ ልጅ የወላጆቹን ገቢ ተጠቃሚ መሆን አለበት፡፡ የቀለብ መጠን ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ የልጆችን እድሜ፤ ብዛት፤ የጤና (አካላዊና ስነ-ልባናዊ) እና የመጫወቻና መዝናናት መብታቸውን እንዲሁም ሌሎች የልጆች እድገት ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡
4. የልጆች ጥቅም የሚያስቀድም እስከሆነ ድረስ የቀለብ መጠኑን ወላጆች በስምምነት እንዲጨርሱ ማድረጉ ይመረጣል፡፡
5. ልጆች ጋብቻው ችግር ላይ ሳይወድቅ ወይም ከመፍረሱ በፊት ያገኙትየነበረውን ጥቅም ሳይጎደል እንዲቀጥል ማስቻል መሠረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡

### 8. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

የቀለብ አወሳሰን ሥርዓታችን በርካታ ችግሮች ያሉበት መሆኑ መፍትሄውም ያንኑ ያህል ውስብስብ ነው፡፡ የዳበረ የታክስ መክፈል ባሕልና የንብረት ምዝገባ ስርዓት በሌለበት አገር የተከራካሪ ወገኖችን ትክክለኛ ገቢ ማግኘት ቀላል አይደለም፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እውቀቱም ሆነ ገንዘቡ የሌላቸው እና የህግ ድጋፍ ማግኘት የማይችሉ በርካታ የቀለብ ጥያቄ አቅራቢ ሴቶች ባሉበት ሁኔታ ዳኞች ምንም ያሕል ሕጉ እና አሰራሩ የሚፈቅደውን ያህል ቢሄዱ ቀለብ የተጠየቀለት/ላት ልጅ ጥቅም የሚያስጠብቅ ውሣኔ መስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ዳኞች የሕግ አተረጓጎማችን እና አሰራራችን የሕጉን ትክክለኛ መንፈስ እንዲከተል በማድረግ ዘመናዊ አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ለውጥ ማምጣት አንችልም ማለት አይደለም፡፡

በመሆኑም የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ በቅርብርቀት ሊታይ የሚችል ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡ የመፍትሄ ሀሳቦች የተመረጡት ፍርድ ቤቱ በራሱ እና

ከፍርድ ቤቱ ጋር ለመስራት ፈቃደኛ በሆኑ አካላት ጥረት ያለብዙ ወጪ መተግበር የሚችሉ በመሆናቸው ነው፡፡

### 8.1 የአመለካከት ለውጥ ማምጣት

ሕገ-መንግስታችን፣ ሀገራችን ፈራሚ የሆነባቸው አለምአቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በግልጽ እንዳስቀመጠው ፍርድ ቤቶች የልጆችን ጉዳይ ሲመለከቱ የልጆችን የመኖርንና የእድገት መብትን ያረጋገጠ እንዲሁም የልጆችን ጥቅም ያስቀደመ ውሣኔ የመስጠት ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ ግዴታችንን ለመወጣት በምንሰጠው ውሣኔ ሁሉ ይህንን እንደመሰረታዊ መርሕ አድርገን ልንወስድ የግድ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአመለካከት ለውጥ ከመጣ ከቀለብ ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ትዕዛዞች እና ውሣኔዎች የሕፃናት መብት ያስከበሩ ይሆናሉ፡፡

### 8.2 የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት

ያደጉ ሀገሮች የሚጠቀሙበት የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ከታክስ ስርአቱ እድገት ጋር የተያያዘ መሆኑን ከመመሪያዎቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በእነዚህ ሀገሮች የእያንዳንዱ ሰው ንብረትና ገቢ ያለብዙ ድካም ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት አለ፡፡ ይህ ስርዓት በመኖሩ ከገቢ ጋር በተያያዘ የሚነሱ በርካታ ክርክሮች አይኖሩም፡፡ በሌላ በኩል ሕብረተሰቡ ከመካከለኛ ገቢ በላይ በመሆኑ ገቢ የለኝም የሚልም ክርክር የሚያነሱበት ሁኔታ ጠባብ ነው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች በሀገራችን የተሟሉ ባለመሆናቸው ባደጉት ሀገሮች በተግባር ላይ የዋለውን አይነት የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት አይቻልም፡፡ የምናዘጋጀው የቀለብ አወሳሰን መመሪያ የተጠቀሱት ሁለት ሁኔታዎች በሌሉበት ሁኔታ በመሆኑ የኛን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ለተወሰኑ ጉዳዮች ተግባራዊ እንዲሆን የተዘጋጀና ለሙከራ ተግባራዊ የሆነ ቀለብ አወሳሰን ማጣቀሻ ለዳኞች ተሰራጭቷል፡፡ የቀለብ አወሳሰን መመሪያ ማዘጋጀት በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡

**ከእነዚህም ውስጥ፡-**

ሀ/ ልጆች ጋብቻው ባይፈርስ ኖሮ ይኖሩ የነበረውን ኑሮ/ሕይወት/ እንዲኖሩ ለማድረግ ያስችላል፡፡

ለ/ ለተመመሳሳይ ጉዳዮች ተመመሳሳይ ውሳኔ/ትዕዛዝ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ሐ/ ተከራካሪ ወገኖች የቀለብ መብት ምን ያህል እንደሆነ መገመት ስለሚችሉ ወደ ሙግት ውስጥ ሳይገቡ ጉዳያቸውን በስምምነት ለመጨረስ ይደፍራሉ፡፡

መ/ የፍርድ ቤቱ የስራ ጫና ይቀንሳል፡፡

ሠ/ የፍርድ ቤቱ አሰራር ተገማች እና ፍትሐዊ እንዲሆን ይረዳል፡፡

ረ/ ሕብረተሰቡ በፍርድ ቤቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው ይረዳል፡፡

## 8.3 ለችግረኛ ሴቶች የሕግ እርዳታ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት

በርካታ ባለጉዳዮች በተለይም ሴቶች በገንዘብ እጥረት ምክንይት የህግ ባለሙያ ይዘው መቅረብ ስለማይችሉ ተገቢውን ክርክር እና ማስረጃ ባለማቅረባቸው የሚሰጠው ውሣኔ የልጆችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ የቤተሰብ ጉዳይ በሚታይባቸው አካባቢዎች መረጃዎችን የሚሰጥ፤ የመጠይቅ ፎርሞችን በመሙላት የሚያግዝ፤ በምክር እና እንደነገሩ ሁኔታም ችሎት ቀርቦ የሚከራከርላቸው ባለሙያ እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**<u>በቀለብ ጠያቂው የሚሞላ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

**<u>የቀለብ ጠያቂ የገቢ ምንጭ</u>**

1. የግል ከሆነ፦ የሥራው ዓይነት------------------------------ ገቢ/በዓመት/---------------------
2. ተቀጣሪ/

*ሠንጠረዥ 1*

| ተ. ቁ | የሥራው አይነት | የሚሠራበት መ/ቤት | ገቢ በወር | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | ብር | ሣ |
| 2 | | | | |
| ድምር | | | | |

3. ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ፡ የገቢው ምንጭ---------------------- የገቢው መጠን /በወር/----------
4. ከገቢዎ ምን ያህል ገንዘብ መስጠት ይችላሉ---------------
5. የሕክምናና ኢንሹራንስ አበል አለዎት? ካለዎት መጠኑ ምን ያህል ነው?--------------
6. ቀለብ የሚቆረጥላቸው ልጆች ሁኔታ (ችግር ከመፈጠሩ በፊት ሲወጣ የነበረውን ወጭ ታሳቢ ያደረገ)

*ሠንጠረዥ 2*

| ተ. ቁ. | ስም | ዕድሜ | የወጪ አይነቶች በወር | | | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለልብስና ለጫማ ለሽንት ጨርቅ ሌሎች…….. | | ለት/ቤት | | ለትራንስፖርት | | ለምግብ | | ለሰራተኛ (ሞግዚት) | | |
| | | | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | |
| 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | |

* በሠንጠረዥ 2 ለብስና ለጫማ የሚወጣ ወጪ የሚለው የአመቱን ወጪ ለ 12 ተካፍሎ መቅረብ አለበት።ቀለብ ከሚጠየቀው ሰው ውጭ የሚወለዱ ልጆች ሁኔታ፤

ሠንጠረዥ 3

| ተ. ቁ. | ስም | ዕድሜ | የወጪ አይነቶች በወር | | | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለልብስና ለጫማ ለሽንት ጨርቅ ሌሎች…….. | | ለት/ቤት | | ለትራንስፖርት | | ለምግብ | | ለሰራተኛ (ሞግዚት) | | |
| | | | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | |
| 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | |

7. በሰንጠረዡ ያልተመለከቱ ሌሎች ወጪዎች

| ተ.ቁ | የወጪው አይነት | መጠን |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| | **ድምር** | |

8. የሚጠየቀው የቀለብ መጠን አጠቃላይ ድምር………………………
9. የቀለብ ተጠያቂው የገቢ ሁኔታ /የሚያውቁ ከሆነ የሚከተለውን ይሙሉ!

**የገቢ ምንጭ**

1. የግል ከሆነ፡- የሥራው ዓይነት-------------------- ገቢ /በዓመት/------------------
2. ተቀጣሪ/

ሠንጠረዥ 4

| ተራ ቁ. | የሥራው አይነት | የሚሠራበት መ/ቤት | ገቢ በወር | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | ብር | ሣ |
| 2 | | | | |
| **ድምር** | | | | |

3. ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ፡ የገቢው ምንጭ -------------------------- የገቢው መጠን /በወር/-------------------

ከላይ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች እውነት መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ፊርማ----------------------

**<u>በቀለብ ተጠያቂው የሚሞላ ቅፅ</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት

**<u>የቀለብ ተጠያቂው የገቢ ምንጭ</u>**

1. የግል ከሆነ፡- የሥራው ዓይነት----------------------------- ገቢ/በዓመት/----------------------
2. ተቀጣሪ ከሆነ

***ሠንጠረዥ 1***

| ተ.ቁ. | የሥራው አይነት | የሚሠራበት መ/ቤት | ገቢ በወር | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | ብር | ሣ |
| 2 | | | | |
| ድምር | | | | |

3. ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ፡ የገቢው ምንጭ---------------------- የገቢው መጠን /በወር/----------
4. ከገቢዎ ምን ያህል ገንዘብ መስጠት ይችላሉ---------------
5. የሕክምና ኢንሹራንስ አለዎት? ካለዎት መጠኑ ምን ያህል ነው?-----------------
6. ቀለብ የሚቆረጥላቸው ልጆች ሁኔታ (ጋብቻው ችግር ውስጥ ከመውደቁ በፊት ሲወጣ የነበረውን ውጪ)

***ሠንጠረዥ 2***

| ተ.ቁ. | ስም | ዕድሜ | የወጪ አይነቶች በወር | | | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለልብስና ለጫማ ለሸንት ጨርቅ ሌሎች…….. | | ለት/ቤት | | ለትራንስፖርት | | ለሠራተኛ /ለሞግዚት/ | | ለምግብ | | |
| | | | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | |
| 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | |

* በሠንጠረዥ 2 ለልብስና ለጫማ የሚወጣ ወጭ የሚለው የአመቱን ወጪ ለ 12 ተካፍሎ መቅረብ አለበት፡፡

**በሰንጠረዡ ያልተመለከቱ ሌሎች ወጪዎች**

| ተ.ቁ | የወጪው አይነት | መጠን |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| | **ድምር** | |

7. ከቀለብ ጠያቂው ሰው ውጭ የሚወለዱና ከ 18 አመት በታች የሆናቸው ልጆች አሉ? ካሉ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ይሙሉ፤

*ሠንጠረዥ 3*

| ተ.ቁ. | ስም | ዕድሜ | የወጪ አይነቶች በወር | | | | | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለልብስና ለጫማ ለሽንት ጨርቅ ሌሎች…….. | | ለት/ቤት | | ለትራንስፖርት | | ለሠራተኛ /ለሞግዚት/ | | ለምግብ | | |
| | | | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | ብር | ሣ | |
| 1 | | | | | | | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | |

8. የቀለብ ጠያቂው የገቢ ሁኔታ /የሚያውቁ ከሆነ የሚከተለውን ይሙሉ/

**ገቢ ምንጭ**

1. የግል ከሆነ፡- የሥራው ዓይነት----------------------------- ገቢ/በዓመት/--------------
2. ተቀጣሪ ከሆነ

*ሠንጠረዥ 4*

| ተ. ቁ. | የሥራው አይነት | የሚሠራበት መ/ቤት | ገቢ በወር | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | ብር | ሣ |
| 2 | | | | |
| ድምር | | | | |

9. ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ፡ የገቢው ምንጭ -------------------------------- የገቢው መጠን /በወር/---------------------

ከላይ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮች እውነት መሆናቸውን አረጋግጣለሁ፡፡

የተጠሪ ፊርማ-----------------

## ክፍል 2፡ ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ቤት አንደኛው ተጋቢ ስለሚለቅበት ሁኔታ

### መግቢያ

ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብ ፍርድ ቤት ተጋቢዎች የፍቺ ሀሳባቸውን እንዲተዉ እና አለመግባባታቸውን በስምምነት እንዲፈቱ ለማድረግ ጥረት ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፍርድ ቤቱ የማስማማት ጥረቱ ውጤት ካላስገኘ ወይም ውጤት የሚያስገኝ መስሎ ካልታየው ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካኝነት ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው እንደሚችል በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ላይ ተመልክቷል፡፡

የማስማማት ጥረቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤት የፍች አቤቱታ እንደቀረበለት ወዲያው ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩበትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ፤ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ፣ ስለሚኖሩበት ስፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለንብረት አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይገባል፡፡ በተለይም ተጋቢዎቹ አብረው መኖር የማይችሉ ሲሆንና ከተጋቢዎች አንዱ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ መውጣት ካለበት ፍርድ ቤቱ ከተጋቢዎቹ አንዱ የጋራ መኖሪያቸው ለቆ እንዲወጣ ያዛል፡፡ የፍቺ ጥያቄ በመነሳቱ ምክንያት ከጋራ መኖሪያቸው አንደኛው ወገን የግድ መውጣት የለበትም፡፡ ይልቁንም በጋራ ቤታቸው ተቀምጠው ክርክሩን ይመራሉ ተብሎነው የሚታመነው፡፡

ሆኖም በተለያዩ ምክንያቶች በአንድ ቤት ውስጥ መኖር የማይችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን አንደኛው ተጋቢ ሌላኛው ወገን ከጋራ መኖሪያቸው እንዲወጣ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ከጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ያለበት ተጋቢን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ በዋነኝነት የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ሊያይ እንደሚገባ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 82 (6) ላይ ተመልክቷል፡፡

1/ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ ይበልጥ የሚጎዳው የትኛው ነው?

2/ የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመች የሚሆነው የትኛው ነው?

እነዚህ ሁለት ሁኔታዎች በሕጉ ላይ የተቀመጡት በአጠቃላይ በሆነ አገላለጽ ነው ፡ ፡ የመስፈርቶቹ አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ መቀመጥ ለተለያዩ ትርጉሞች የተጋለጡ መሆኑ በሕጉ አፈፃፀም ዙሪያ ችግር ፈጥሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ዳኞች ተመሳሳይ ይዘት ባላቸው ጉዳዮች የተለየዩ ትዕዛዞች ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ በተለይም በባሕላችን በባልና ሚስት መካከል ያለው አለመግባባት በስምምነት ወይም በእርቅ መፍታት ካልቻሉ የፍች ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት ወይም ጥያቄውን እንዳቀረቡ በራሳቸው ፍቃድ መኖሪያ ቤታቸውን ለቀው የሚወጡበት ሁኔታ መኖሩና የጋራ መኖሪያ ቤት ምን ማለት ነው? የሚለው ጥያቄ ዙሪያ የሚስተዋሉ የትርጉም ልዩነቶች ጥያቄውንና አፈፃፀሙን ይበልጥ አወሳስበውታል፡፡

ስለሆነም የፍርድ ቤቶች አሰራር የህጉን ትክክለኛ መንፈስ የተከተለ እንዲሆንና የሚሰጡት ውሳኔዎች ተገማች እንዲሆኑ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ከጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ያለበት ተጋቢን ለመወሰን የሚረዳ ማጣቀሻ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ይህንን ታሣቢ በማድረግ ይህ ማጣቀሻ ወይም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ የማጣቀሻው ዋና መሠረት የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቢሆንም ማብራሪያ የሚሹ ነጥቦችን ለማብራራትና ክፍተቶችን ለመሙላት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. ሕገ መንግስት፤ የፍትሐብሄር ሕግ፤ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለምአቀፋዊ ሕጎች እንዲሁም በቤተሰብ ችሎት ልምድ ያላቸው ዳኞች ጋር በመወያየት የተገኙ ሀሳቦች እና የሌሎች ሀገሮች ልምዶች በጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

ይህ ማጣቀሻ እንደማብራሪያ እና ክፍተት መሙያ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው የሚገመት ሲሆን ወደፊት ሁኔታዎች እየታዩ የሚዳብርና የሚለወጥ ይሆናል፡፡ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያታ የተገለፀበት ሀሳቦች ለሴቶችም የሚያገለግሉ ሆነው ይነበባሉ፡፡

## 1. አንድ ተጋቢ ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ቤት መልቀቅ ካለበት የሚለቀው ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው?

በመርህ ደረጃ ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ሁኔታ ላይ ባልና ሚስት በጋራ መኖሪያቸው ቤታቸው ይኖራሉ (የተሻሻላው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 53/1/)፡፡ ነገር ግን የፍቺ አቤቱታ በፍርድ ቤት ቀርቦ ፍ/ቤቱ የፍቺ ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት ወዲያውኑ ትእዛዝ ከሚሰጥባቸው ሁኔታዎች መካከል ተጋቢዎቹ ስለሚኖሩበት ሁኔታ እና የልጆች አጠባበቅ ለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 82/5/ ይገልፃል፡፡

ከተጋቢዎቹ አንዱ የግድ ከባልና ሚስቱ የጋራ መኖሪያቸው ቤት መውጣት ካለበት የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ የሚጎዳው ተጋቢ ወገን ማን ነው የሚለውን እና የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመች የሚሆነውን ሁኔታ ፍ/ቤቱ ከግምት በማስገባት የፍች ውሣኔ ፍ/ቤቱ ከመስጠቱ በፊት ወይም ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ፍርድ ቤቱ አንደኛውን ተጋቢ ወገን ከባልና ሚስቱ የጋራ ቤት ሊያስወጣው እንደሚችል በልዩ ሁኔታ ተደንግጓል (የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 82/6/)፡፡

### 1.1. የተጋቢዎች የጋር መኖሪያ (marital residence) ማለት ምን ማለት ነው?

በርካታ ዳኞች ከጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ጋር በተያያዘ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ በሚሰጡት ብይን ላይ የጋራ መኖሪያ ቤት ጽንሰ ሀሳብ ከባለቤትነትና ባለይዞታነት መብት ጋር የማቀላቀል ሁኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ መታየት ያለበት ነጥብ የተጋቢዎች መኖሪያ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለው ነው፡፡

*የተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ* (marital residence) *ማለት የግድ ባልና ሚስቱ በትዳራቸው ያፈሩት የጋራ መኖሪያ ቤት* (common property) *ወይም በጋር የተከራዩት ቤት መሆን የለበትም፡፡*

*የተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ማለት የፍቺው ጥያቄ ከመቅረቡ በፊት ባልና ሚስቱ ይኖሩበት የነበረው ቤት ሲሆን የቤቱ ባለቤት ተጋቢዎቹ ራሳቸው፤ መንግስት፤ ግለሰብ፤ ባልና ሚስቱ ወይም አንዳቸው ሊሆኑ ይችላል፡፡ ቤቱ የተገኘው ከተጋቢዎች በአንዳቸው የስራ ሁኔታም ሊሆን ይችላል፡፡ ተጋቢዎቹ በቤቱ ላይ ያላቸው መብት ምንም ይሁን ምን በትዳር ውስጥ እያሉ በቋሚነት ይኖሩበት የነበረ የመኖሪያ ቤት እስከሆነ ድረስ የተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ነው፡፡ የጋራ መኖሪያ ቤት መሆኑን ለማስረዳት የሚያስፈልገው በቤቱ ውስጥ በቋሚነት በጋራ ሲኖሩ የነበረ መሆኑን ብቻ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ በተለያያ የማስረጃ አይነቶች ማስረዳት ይቻላል፡፡ አለመስማማት በመፈጠሩና በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰነ ጊዜ ከጋራ መኖሪያ ቤት አንደኛው ተጋቢ መውጣቱ የጋራ መኖሪያ ቤታቸው መሆኑን አያስቀረውም፡፡*

*ተጋቢዎች በጋብቻቸው ጊዜ በኖሩበት የጋራ መኖሪያ ቤታቸው የፍቺው ጥያቄ እና የንብረት ክፍፍል ላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ለመኖር መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት ቀሪ የሚሆነው ተጋቢዎቹ ባንድ ጣሪያ ስር መኖር መቀጠላቸው የሚያስከትለው ጉዳት ከባድ ሲሆን ብቻ ነው፡፡*

## 1.2. *አንድ ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲወጣ ፍ/ቤት ትዕዛዝ የሚሰጠው በምን ያህል ጊዜ ነው?*

*የፍቺ ጥያቄ ለፍ/ቤት ቀርቦ አንደኛው ተጋቢ ሌላኛው ተጋቢ ከጋራ መኖሪያቸው ለቆ እንዲወጣ ሲጠየቅ ፍርድ ቤቱ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ያለበት ወገን አለ ወይስ የለም? መውጣት ካለበትስ ማነው? የሚለው ላይ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት ጥያቄው እንደቀረበለት ወዲያውኑ ለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ* 82/5/ *ይገልፃል፡፡ ስለዚህ ወዲያውኑ ሲባል ምን ማለት ነው? የሚለው ጉዳይ መታየት አለበት፡፡*

*በእርግጥ እንደዚህ አይነት ጥያቄ ላይ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚፈጀው ጊዜ እንደ ጉዳዩ የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዱ ጉዳይ የፍቺው ጥያቄ እንደቀረበ በእለቱ ትዕዛዝ ሊሰጥባቸው ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው የፍቺው ጥያቄ ላይ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ አንደኛው ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ መውጣቱ ግድ መሆኑ ጠያቂው ወገን ባቀረበው ማስረጃ ያስረዳ ከሆነ እና ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ ለመስጠት ተጨማሪ ማስረጃ መስማት ሆነ ማስቀረቡ አስፈላጊ ሆኖ ባላገኘበት ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ጥያቄው ላይ በዕለቱ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከተጋቢዎቹ አንደኛው በሌላኛው ተጋቢ ወገን የተደበደበ ለመሆኑ ከፖሊስ የቀረበ ማስረጃ ወይም የፍርድ ቤት ውሣኔ ተያይዞ የቀረበ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በእለቱ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ግን ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ማጣራት ያለበት ጉዳይ ሲኖር ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ጥያቄ በቀረበበት እለት ጥያቄው ላይ*

ትዕዛዝ ላይሰጥ ይችላል፡፡ ይህም ቢሆን የነገሩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥያቄው ላይ ፍርድቤቱ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

ስለሆነም ፍርድ ቤቱ የፍቺ ጥያቄው እንደቀረበለት ሕጉ ላይ በተመለከቱት መስፈርቶች ከግምት በማስገባት ከጋራ መኖሪያቸው አንደኛው ተጋቢ ለማስወጣት ወዲያውኑ ትዕዛዝ ይሰጣል ሲል የነገሩን ውስብስብነት ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ (በአዳሪ ጉዳዮችን ይዞ በቅርብ ክትትል ማድረግን ይጠይቃል) ውስጥ ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ ይሰጣል ማለት ነው፡፡

## 2. የፍቺ ጥያቄ እንደቀረበ ከተጋቢዎቹ ማንኛቸው ከጋራ መኖሪያ ቤት (marital residence) መውጣት አለባቸው የሚለው ለመወሰን የምንጠቀምባቸው መስፈርቶች

### 2.1. ከጋራ መኖሪያ አንደኛው ተጋቢ እንዲወጣ ማዘዝ የመጨረሻ አማራጭ ስለመሆኑ

የመስፈርቶችን ባህሪና ምንነት ከመመልከታችን በፊት በቅድሚያ አንደኛው ተጋቢ ከጋራ መኖሪያ ቤት እንዲወጣ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚሰጠው መቼ ነው የሚለውን ማየቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ተጋቢዎቹ የፍች ጥያቄ ቢያቀርቡም በጋራ መኖሪያቤታቸው ሆነው ክርክራቸውን ማካሄድ አለባቸው፡፡ አንደኛው ተጋቢ ከጋራ መኖሪያቸው እንዲወጣ የሚደረገው ባንድ ጣሪያ ስር ለመኖር የማያስችል ሁኔታ መፈጠሩን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በሚከተለው ሁኔታ በአንቀጽ 82 (6) ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡

> በአማርኛ "ከሁለቱ ተጋቢዎች ያንደኛው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ.." ሲል የእንግሊዘኛው ቅጂ ደግሞ፡-"where circumstances absolutely require that one of the spouses leave their common………" ይላል፡፡

ከድንጋጌው ቅርብ ንባብ መገንዘብ የሚቻለው የአስገዳጁ ሁኔታ መኖር የግድ መሆኑን ነው፡፡ ከአማርኛው ቅጂ በጠነከረ ሁኔታ የእንግሊዘኛው ቅጂ በግልጽ እንደሚያያስረዳው አንደኛው ተጋቢ ከጋራ መኖሪያ ቤቱ እንዲወጣ የሚደረገው ፍፁም አስገዳጅ ሁኔታ መኖሩን ፍርድ ቤቱ ሲያምን ነው፡፡ ሌላው መመለስ ያለበት ጥያቄ ህጉ አስገዳጅ ሁኔታ ሲል ታሳቢ ያደረገው ምንድን ነው? ምን አይነት ሁኔታዎችን ነው? የሚለው ነው፡፡ አስገዳጅ ሁኔታ የሚለውን መዘርዘር ባይቻልም ለህጉ አፈጻጸም ጥሩ ምሳሌ ተደርጎ ሊወሰድ ከሚችሉት አንዱና ዋናው የሀይል ተግባር መፈጸም ነው፡፡ ከተጋቢዎቹ አንዱ የጥቃት ተግባር በሌላኛው ተጋቢ ወይም በልጃቸው/ልጆቻቸው መፈጸሙ ወይም ሊፈጽም መሆኑ ከተረጋገጠ ይህን ችግር ለማስወገድ ወይም ችግሩ እንዳይደገም ለማድረግ የችግሩ ባለቤት ከጋራ መኖሪያ

ቤታቸው እንዲወጣ ብቻ ሳይሆን ወደ የጋራ መኖሪቸው እንዳይደርስም ማድረግ ይቻላል፡፡

## 2.2. ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ቤት (marital residence) አንደኛው ተጋቢ እንዲወጣ ለማዘዝ መስፈርቱ ምንድን ነው?

ከጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ያለበት ተጋቢን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይገባል ተብሎ በህግ የተጣለበት ግዴታ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1/ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ ይበልጥ የሚጎዳው የትኛው ነው?

2/ የልጆቻቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነው ማን ከጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ ነው?

እነዚህ መስፈርቶች እጅግ አጠቃላይ በሆነ አገላለጽ የተቀመጡ በመሆኑ እያንዳንዱን መስፈርት በተናጠልና በአንድነት ዘርዘር አድርጎ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት የጋር መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ ይበልጥ የሚጎዳው የትኛው ነው የሚለው የሚያጠነጥነው በተጋቢዎች እና በልጆቻቸው ሁኔታ ነው፡፡ ከመኖሪያ ቤታቸው ያንደኛው ወገን መልቀቅ የግድ ሲሆን በመልቀቁ ይበልጥ የሚጎዳው ማን ነው? የልጆችን ጥቅምና ደህንነት ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነው የትኛው ወላጁ ከመኖሪያ ቤቱ ቢወጣ ነው የሚለውን መመርመር ይጠይቃል፡፡ መታየት ካለባቸው በርካታ ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የልጆችን ጥቅምና ደህንነት በቀደምትነት ማስጠበቅ
- ተጋቢዋ ሴት ነፍሰጡር በሆነች ጊዜ
- አካላዊና የጤና ሁኔታ
- ጾታ

እነዚህን መስፈርቶች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

### 2.2.1. የልጆችን ጥቅምና ደህንነት በቀደምትነት ማስጠበቅ (the best interest of the child)

> "ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡"

> "ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች የሚወሰዱበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ሕፃናትን ደህንነት በቀደምትነት በማሰብ ውሳኔ መስጠት አለባቸው፡፡"

ይህ መብት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት፤ በዝርዝር ሕጎቻችን እንዲሁም ሕፃናትን የሚመለከቱ አለምአቀፋዊ ስምምነቶች ላይ ተመልክቷል፡፡

ከላይ የተመለከተው ሕገ-መንግሰታዊ ድንጋጌ ኢትዮጵያ በአዋጅ ቁጥር 10/1984 ባፀደቀችው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 3/1/ እና በአዋጅ ቀጥር 283/92

ባፀደቀችው የአፍሪካ የሕፃናት መብቶች ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 4/1/ በተመሳሳይ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

የሕፃናት መብቶች የፍልስፍና መሰረት ተብለው ከሚወሰዱት ውስጥ አንዱ የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቀደምትነት ነው፡፡ በመሆኑም የፍች ጥያቄ ሲቀርብ ከተጋቢዎቹ አብራክ የተገኙሕፃናት ካሉ የልጆቹ ደህንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ይልቁንም ጥቅም ቅድሚያ እንዲያገኝ ፍርድ ቤት በሚሰጠው ትእዛዝ ሁሉ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ፍ/ቤት ከፍቺ ጥያቄ ጋር የልጆች አስተዳደግን የተመለከተ ጥያቄ ሲቀርብለት ልጆች ለጊዜው ከማን ጋር መሆን እንዳለባቸው ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ስለልጆች አጠባበቅ ስለሚኖሩበት ስፍራ እና ስለ አኗኗራቸው ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

ፍ/ቤቱ ትዕዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ የልጆችን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡ የልጆችን ጥቅም ለማስቀደም የልጆችን የመደመጥ መብት እንዲሁም የመኖር መብትን ማክበር ይጠይቃል፡፡ የሕፃናት የመኖር መብት በተለያዩ ሕጎች ተደንግጓል፡፡ የመኖር መብት ሕፃናቱ ለእድገታቸው እና ለህልውናቸው አስፈላጊ የሆነ እንደ ምግብ፤ የጤና አገልግሎት፤ ልብስ መጠለያ ለኑሮ ምቹ የሆነ አካባቢ የማግኘት መብትን ይጨምራል፡፡

ሰለዚህ ልጆችን አብረውት እንዲኖሩ ፍርድ ቤቱ ያዘዘለት ተጋቢ ከተጋቢዎች መኖሪያ ቢወጣ የልጆች ደህንነት እና ጥቅም ሊከበር አይችልም፡፡ ይልቁንም የልጆች ጥቅም የሚከበረው በመሆኑም በልጆቹ እና በተጋቢው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል ይገመታል፡፡ ስለሆነም በቤቱ ውስጥ መቆየት ያለበት ልጆች አብረውት እንዲኖሩ የተወሰነለት ተጋቢ መሆን አለበት፡፡

### 2.2.2. ተጋቢዋ ሴት ነፍሰጡር በሆነች ጊዜ

ነፍሰጡር እናት ልዩ እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋት አከራካሪ አይደለም፡፡ በእርግዝና ወቅት ለአካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ ችግሮች እንዳትጋለጥ ጥበቃ ሊደረግላት ይገባል፡፡ ለእናት የሚደረገው እንክብካቤ በመህጸኗ ላለው ልጅም ይበጃል፡፡

የሰው ልጅ መብት ከውልደት ይጀምራል ቢባልም ሁኔታዎች አስፈላጊ ሲያደርጉት ጽንሱም እንደተወለደ ሰው ይቆጠራል፡፡ የሕግ ጥበቃም ይደረግለታል፡፡ በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መግቢያ/preamble/ ላይ ጽንስ ከመወለዱ በፊት ልዩ የህግ ጥበቃ እና እንክብካቤ የሚያስፈልገው መሆኑ ተገልጿል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እናቶች ልዩ እንክብካቤና ድጋፍ የማግኘት መብት እንዳላቸው በሰብዓዊ መብቶች ሁሉን አቀፍ መግለጫ አንቀጽ 25/2/ እንዲሁም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 35/9/ ተደንግጓል፡፡

ስለሆነም ተጋቢዋ ሴት ነፍሰጡር በሆነች ጊዜ ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ብትወጣ የበለጠ ጉዳት የሚደርስባት በመሆኑ እና ጽንሱም መጠበቅ ስላለበት እርሷ በተጋቢዎች መኖሪያቸው ብትወጣ የበለጠ ጉዳት በእርሷ እና በጽንሱ ላይ ስለሚደርስ ባልየው ከተጋቢዎች የጋራ መኖሪያ ቤት ቢወጣ ይመረጣል።

## 2.2.3 አካላዊና አእምሮአዊ የጤና ሁኔታ

በአለማችን በርካታ የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኞች በተለያየ የሥራ መስኮች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ እንዲሁም አቅም በፈቀደ መጠን ወደ ማሕበራዊ ኑሮ ተቀላቅለው የተሻለ ኑሮ እንዲመሠርቱ በአካልና በአእምሮ ተጎጂ የሆኑትን ሰዎች መብት መጠበቅ የኑሮ ደህንነታቸውን ማረጋገጥና ማቋቋም አስፈላጊነት በተባበሩት መንግስታት አጽንኦት ተሰጥቶበት ስለአካል ጉዳተኞች መብቶች ድንጋጌ (Declaration on the rights of disabled person) 1995 እ.ኤ.አ ወጥቷል:: በዚህ ድንጋጌ መሠረት አካል ጉዳተኞች ማለት አብሮ በሚወለድ በሽታ ወይም በአካሉ ወይም በአንዱ ላይ በሚደርስ ጉድለት ችሎታውን በማጣቱ አስፈላጊ የሆኑትን የግል እና/ወይም ማህበራዊ ኑሮ ተግባሮችን በሙሉም ሆነ በከፊል በራሱ ለማሟላት የማይችል ማንኛውም ሰው ነው ይላል።

የተለያዩ አገሮችም የኢኮኖሚ አቅማቸው እና አካል ጉዳተኞችን በሚመለከት ባላቸው ፖሊሲ እና ስትራተጂ የአካል ጉዳተኞችን ችግር ለመፍታት የተለያዩ አሰራሮችን ይዘረጋሉ።

በሀገራችንም በኤ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት ለአካልና የአእምሮ ጉዳተኞች አስፈላጊው የድጋፍ አገልግሎት እንደሚሰጣቸው ደንግጓል። ለመብቱ አፈፃፀም ከመጡት አዋጆች አንዱ የአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት አዋጅ ቀጥር 568/2000 ነው።

በዚህ አዋጅ መሠረት አካል ጉዳተኞች ማለት በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ ምክንያት ማየት፤ መስማት ወይም መናገር የተሳናቸው፤ በእጅ፤ በእግር ወይም በሌላ ወይም የአእምሮ ዝግመት ያለበት ሰው እንደሆነ ተተርጉሟል።

በመሆኑም የኤ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት እንዲሁም ሌሎች ከላይ የተጠቀሱት ሕጎች ጥበቃ ያደረጉለት የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኞች መብት ከመጠበቅ እና ከማስፈፀም አንፃር ከተጋቢዎቹ አንዳቸው የአካል፤ የአእምሮ ጉዳተኛ ከሆነ ወይም ሌላ ከባድ የውስጥ የጤና ችግር ያለበት ወገን ከተለመደው መኖሪያ እንዲወጣ ሊደረግ አይገባም። ሁለቱም ጤናቸው የተጓደለ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው በሆነ ጊዜ የትኛው ተጋቢ ወገን ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት አለበት? የሚለው ጥያቄ ሲነሣ በጤናው መጓደል ምክንያት ወይም በአካል መጉደል ምክንያት ከጋራ መኖሪያቸው ቢወጣ የጤናው ሁኔታ ሌላ ቤት ለማግኘት የሚያስቸግራቸው ወይም ከቤቱ ወይም እርዳታ በቅርብ ሊሰጡት ከሚችሉት ከለመዳቸው ጎረቤቶቹ ቢለይ የበለጠ ይጎዳል የተባለው ሰው በጋራ መኖሪያ ቤታቸው እንዲቆይ ማድረጉ ይመረጣል።

በዚህ ረገድ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ከተጋቢዎች አንዱ ማየት የተሳነው ከሆነ ነው። ማየት የተሳነው ሰው በጋራ መኖሪያ ቤቱንም ሆነ አካባባውን በመቆየቱ ምክንያት በቀላሉ ወደ ቤቱ ለመግባታና ለመውጣት እንዲሁም ቤቱ ውስጥ ያሉትን መገልገያዎች በቀላሉ ሊጠቀምባቸው ይችላል። ማየት የተሳነው ሰው ከለመደው የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲወጣ ቢደረግ አካባቢውን እስከሚለምድ እንደሚቸገር አያጠያይቅም። በመሆኑም ማየት የተሳነው ሰው በጋራ መኖሪያ ቤት እንዲቆይ ማድረጉ ይመረጣል። በተመሳሳይ አንደኛው ተጋቢ የአካል ጉዳተኛ በመሆኑ የተነሳ በዊልቸር የሚሄድ ከሆነ እና የተጋቢዎች መኖሪያ ቤት በዊልቸር ያለው ወይም ለዚሁ አላማ እንዲያመች ተደርጎ የተዘጋጀ ከሆነ ይህ የአካል ጉዳተኛ ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ቢወጣ ከሌላኛው ተጋቢ ወገን የበለጠ ጉዳት የሚደርስበት ስለሆነ ሌላኛው ተጋቢ ወገን ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት አለበት።

እንደዚሁም ጤናው የተጓደለ ተጋቢ በጤነው መጓደል ምክንያት የአካባቢው ሰው እገዛ የሚያገኝ በሕመሙ ጊዜ ሮጦ የሚደርስለት ሁኔታ ካለ እና ይህ ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ወጥቶ ሌላ አዲስ ሰፈር ይኑር ቢባል በጤናው ምክንያት ለጉዳት በጣም የተጋለጠ ስለሚሆን ይኸኛው ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ቢወጣ የበለጠ ስለሚጎዳ ሌላኛው መውጣት አለበት።

ከላይ እንደተገለፀው የጤናው መጓደል ደረጃ ከግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለሆነ ከጉዳይ ጉዳይ ይለያያል። ስለሆነም ዝርዝር ሁኔታው ለፍርድ ቤት የተተወ ነው።

### 2.2.4. ፆታ

ሰዎች ሁሉ እኩል ናቸው የሚለው ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ቢሆርም በተለያዩ ምክንያቶች ወንዶች እና ሴቶች እኩል የመብት ተጠቃሚ አልነበሩም። በጾታ ምክንያት ብቻ በሴቶች ላይ የሚደርስ አድሎአዊ ልዩነት ነበር፣ አሁንም አለ። ይህም የሴቶችን እኩል የመሆን መርህ የሚጥስ ከመሆኑም ባሻገር ሴቶች ከወንዶች እኩል በአገሮቻቸው ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባሕላዊ ሕይወት ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለው ተሳትፎ የሚያሰናክል፤ ሴቶች ለሕብረተሰባቸው እና ለአገሮቻቸው አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው አቋም እና ችሎታ እንዳይጎለብት የሚያደናቅፍ ነው። ይህን በመገንዘብ የተባበሩት መንግስታት እ.ኤ.አ 1981 ሴቶች ላይ የሚደረግ ማንኛውንም አድሎአዊ ልዩነት ለማስወገድ የሚያስችል ስምምነት (Convention on the Elimention of all forms of Discrimination Against Women (CEDAW/) አጽድቋል።

ወደ አገራችን ነባሪዊ ሁኔታ ስንመጣ በነበረው የፆታ ልዩነት ምክንያት አብዛኛዎቹ ሴቶች ያልተማሩ እንዲሁም የራሳቸው ገቢ የሌላቸው በመሆናቸው በወንዱ ላይ የኢኮኖሚ ጥገኛ ናቸው። በዚህም ምክንያት ከአንዲት ሴት ትዳር መያዝ ስራ እንደመያዝም የሚቆጠርበት ሁኔታ አለ።

ይህን ሀሳብ የሚያጠናክረው ለምሳሌ በፍርድ ቤቶች አካባቢ ሥራ የሌላቸው ባለትዳር ሴቶች ለምስክርነት ወይም ለሌላ ጉዳይ መጥተው ሥራዎ ምንድ ነው? ተብለው ሲጠየቁ ባለትዳር ብለው ይመልሳሉ፡፡

ስለሆነም ሴቶች ስር በሰደደው ባህልና ወግ ምክንያት ከወንዶች እኩል መብታቸውን ያልተጠቀሙበትና መጠቀም ያልቻሉበት ሁኔታ መኖሩ ይህን የሥርዓተ-ፆታ ክፍተት ለመቅረፍ የሴቶች መብት ሕገ-መንግስታዊ እውቅና አግኝቷል፡፡ የሴቶችን መብት የሚያስከበር ሕግ ወጥቷል፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግስት ሴቶች ልዩ ድጋፍ (affirmative action) ሊያገኙ እንደሚገባ በሚከተለው ሁኔታ ተመልክቷል፡፡ ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡

በጉዳዩ ዙሪያ በተደረጉ ውይይቶች እና በስራ አጋጣሚ ከበርካታ ፍርድ ቤት ከቀረቡ ጉዳዮች መገንዘብ እንደሚቻለው በርካታ ሚስቶች የጋራ ንብረታቸውንም ሆነ የባል የግል ንብረቶችን ምን ያህል እንደሆኑና የት እንደሚገኙ አያውቁም፡፡ በዚህም ምክንያት በበርካታ ሁኔታዎች በተለይም ኢኮኖሚያዊ በሆኑ ጉዳዮች ሚስቶች በጣም ሲቸገሩ ይስተዋላል፡፡ በአጠቃለይ ሴቶች ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከወንዶች በበለጠ ለጥቃት የተጋለጡ መሆኑም ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ሁኔታዎች ተመሳሳይ ሲሆኑ እንደነገሩ ሁኔታ ሕገ-መንግስቱ ለሴቶች የሚሰጠው ልዩ ድጋፍ ታሳቢ በማድረግ ባል ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት አለበት፡፡

### 3. የመስፈርቶቹ አጠቃቀምን በተመለከተ

የፍርድ ቤት አሰራር ተገማች እንዲሆን እንዲሁም የሕጉን ፍትሕ የማስፈን አላማ ለማሳካት ፍርድ ቤት የፍቺ ጥያቄ እንደቀረበለት የግድ አንዱ ተጋቢ ከጋራ መኖሪያቸው ለቆ ካልወጣ በተጋቢዎች ወይም/እና/ በልጆች ደህንነት ላይ አካላዊ ወይም/እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ይደርሳል ብሎ ፍርድ ቤቱ ካመነ፣ የልጆቹን ጥቅምና ፋላጎት የተጋቢዎቹን የጤና ሁኔታ እንዲሁም ለሴቶች የተሰጠውን ልዩ ድጋፍ መሠረት ባደረገ መልኩ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ቢወጣ የበለጠ ጉዳት የሚደርስበት ተጋቢ በተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲኖርበት ማድረግ ሌላኛው ተጋቢ የፍቺ ጥያቄ ላይ እና የንብረት ክፍፍል ላይ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት እንዲወጣ የጉዳዮቹን ውስብስብነትና የእያንዳንዱ መስፈርት ክብደት ከግምት ውስጥ አስገብቶ በተቻለ አጭር ፍጥነት ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

ከጋራ መኖሪያ ቤት መውጣት ያለበትን ተጋቢ ለመወሰን በርካታ መስፈርቶች ተዘርዝረዋል፡፡ በዝርዝር ከተመለከቱት ውጪም ሌሎች መነዛሪያ መስፈርቶች

ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህን መስፈርቶች እንዴት ነው መጠቀም ያለብን? እያዳንዱ መስፈርት ምን ያህል ክብደት ሊሰጠው ይገባል? እንዲሁም ከአንድ በላይ መስፈርቶች ሲኖር እንዴት ይመዘናል? የሚሉትን መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ አንድ መስፈርት ብቻ ተግባራዊ ሲሆን፤ በአብዛኛው ጊዜ መስፈርቶቹ ተደራርበው ይገኛሉ፡፡

የልጆችን ጥቅም ማስከበር በተመለከተ በተለያዩ አለምአቀፋዊ ስምምነቶች እንዲሁም የአገር ውስጥ ሕጎች ቅድሚያ የተሰጠው ጉዳይ በመሆኑ በምንም መልኩ ሊጣስ የሚችል ነገር ባለመሆኑ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ለምሳሌ አንድ አይነ ስውር ነፍረጡር ሴት የፍቺ ጥያቄ ጠይቃ ባሏ ከጋራ መኖሪያቸው እንዲወጣ በተጨማሪ የጠየቀች ከሆነ አካል ጉዳትን፤ ነብሰጡርነትን እንዲሁም ሴትነትን የተመለከቱት መስፈርቶች በድምር መታየት አለባቸው፡፡ ከላይ ከተመለከቱት መስፈርቶች ውስጥ ሶስቱ ተሟልተዋል፡፡ እነዚህ መስፈርቶች ሚስት ከጋራ መኖሪያ ቤት እንድትቆይና ባል ከቤት መውጣት እንዳለበት ለመወሰን በቂ ምክንያት ነው፡፡ የተመለከትናቸው የጋራ መኖሪያ ማስወጣት መስፈርቶች ውስጥ ሶስት የሚያሟላ በመሆኑ ሚስት ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ትውጣ ቢባል የበለጠ ጉዳት የሚደርስባት በመሆኑ ከጋራ መኖሪያ መውጣት ያለበት ባል ነው፡፡ ስለሆነም ዝርዝር ሁኔታው ለዳኛው የተተወ ሆኖ የመስፈርቶችን ክብደትና ተደራራቢነት ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ማን ከጋራ መኖሪያ ቤት ይውጣ የሚለው ጥያቄ ላይ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሊስጥ ይገባል፡፡

### 4. ማጠቃለያ ሀሳቦች

የፍቺ ጥያቄ ለፍርድ ቤት እንደቀረበ ወዲያው ትዕዛዝ ከሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ ተብሎ የሚታመነው ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ማን መውጣት አለበት የሚለው ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 82/6/ ላይ ፍ/ቤት ማንኛው ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ መውጣት አለበት? የሚለውን ለመወሰን የልጆችን ጥቅም እና ከጋራ መኖሪያ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደረስበት ተጋቢ ማን ነው የሚለውን በማየት ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ መስጠት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

ይህ የሕግ አንቀጽ ለትርጉም የተጋለጠ ስለሆነ በፍርድ ቤት ውስጥ ለተመሳሰይ ጉዳይ የተለያዩና የህጉን መንፈስ ያልተከተሉ ትዕዛዞች ሲሰጡ ተስተውሏል፡፡ ይህን ችግር ለመቅፈርና የፍርድ ቤታችንን አሰራር ተገማች እንዲሁም የህጉን ትክክለኛ መንፈስ (አላማ) ለማሳካት ሕገ-መንግሰቱን፤ ዝርዝር ሕጎችን እንዲሁም አለምአቀፍ ስምምነቶችን መሰረት ያደረገ መስፈርቶች በማዘጋጀት ዳኛው በእለት ተእለት ተግባሩ እንደ ማጣቀሻ እንዲጠቀምበት ተዘጋጂቷል፡፡

መስፈርቶቹ ተግባሪዊ የሚሆኑት ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት የፍቺ ጥያቄ እንደቀረበለት የግድ አንዱ ተጋቢ ከጋራ መኖሪያቸው ለቆ ካልወጣ በተጋቢዎቹ

ወይም/እና/ በልጆች ደህንነት ላይ አካላዊ ወይም/እና ስነ-ልቦናዊ ጉዳት ይደርሳል ብሎ ፍርድ ቤቱ ካመነ ብቻ ነው፡፡ ዳኛው በእርግጥም ይህ መስፈርት መሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ነው ለጊዜው መውጣት ያለበት ማን ነው? ለሚለው መልስ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ያለበት፡፡

ለማስወጣት ሁኔታዎች ግድ ይላሉ ወይ? በሌላ አገላለጽ አንደኛው ተጋቢ ከተጋቢዎቹ የጋራ መኖሪያ ቤት ካልወጣ በተጋቢዎቹ እና/ወይም በልጆች ደህንነት ላይ አካላዊ እና/ወይም ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት ይደርሳል ወይ? የሚለውን ጥያቄ መርምሮ ጥያቄው ላይ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚከተሉት መስፈርቶችን ማየት ይጠበቃል፡፡

1. የልጆችን ጥቅም እና ደሕንነት ከማስከበር አኳያ
2. ሚስት ነፍሰጡር በሆነች ጊዜ
3. የጤና ሁኔታ
4. ያታን መሠረት ያደረጉ በማየት

ዝርዝር ሁኔታው ለዳኛው የተተወ ሆኖ የመስፈርቶችን ተደራራቢነት እና ቀደምትነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት በተቻለ ፍጥነት በጥያቄ ላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይገባል፡፡

<u>**ዋቢ ጽሁፎች**</u>

1. የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን (CRC)፡፡
2. የተባበሩት መንግስታት የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር፡፡
3. የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት፡፡
4. በሴቶች ላይ የሚደረጉ ማንኛውም ዓይነት ተጽዕኖዎችን ለማስወገድ የወጣየተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስምምነት (CEDAW)፡፡
5. የተባበሩት መንግስታት የአካል ጉዳተኛ ሰዎች መብቶች ድንጋጌ እ.ኤ.አ. 1995፡፡
6. የፍትሐብሄር ሕግ 1952፡፡
7. የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ 1992፡፡
8. የአካል ጉዳተኞች የስራ ስምሪት መብት አዋጅ ቁጥር 568/2000፡፡

# የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የስራ መዘርዝር

## <u>መግቢያ</u>

ሕፃናት ልዩ አያያዝ ከሚጠይቁ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚመደቡ ስለሆኑ ለሕፃናት የሚደረግ አያያዝ ለመብቶቻቸው እውቅናና ጥበቃ የሚያደርግ እንዲሁም አካላዊና አዕምሮአዊ እድገታቸውን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የሕፃናት መብቶች መሠረታዊ መርሆች የሆኑት አድሎ ያለማድረግ፣ የሕፃናት መብት ደህንነት ቀደምትነት፣ የመኖር እና የዕድገት መብት በኢ.ፌ.ድ.ሪ ሕገ-መንግስት፣ በአለማቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም በዝርዝር ሕጎቻችን ተካተዋል፡፡

እነዚህን ከሕፃናት መብቶች ጀርባ የሚገኙ የፍልስፍና መሰረቶችን መሰረት በማድረግ ላለፉት አስር ዓመታት በርካታ የማሻሻያ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተሰሩት የማሻሻያ ስራዎች ፍርድ ቤታችን የህጻናት ጉዳይ አያያዝ የህፃናትን የአሁኑንና የወደፊቱን ስብዕናቸውን የማይጎዳ እንዲሁም የሚሰጠው ውሳኔ የልጆችን ጥቅምና ደህንነት የሚስቀድም እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ ከተሰሩት የማሻሻያ ስራዎች ውስጥ አንዱ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የዳኝነት ስራውን እንዲያግዙ ማድረግ ነው፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን ፍርድ ቤታችን መጠቀም የጀመረው በ1997 ዓ.ም ነው፡፡ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ያልሆኑ የፍርድ ቤት ሰራተኞችን መሰረታዊ ስልጠና በመስጠት የወንጀል ጥቃት ሰለባ የሆኑ ልጆች ለነሱ በልዩ ሁኔታ እንዲያገለግል በተዘጋጀ ክፍል ውስጥ በመገኘት እንደ አገናኝ ባለሙያ (intermediary) ሆነው እዲያገለግሉ በማድረግ የተጀመረው ስራ ዛሬ የማህበራዊ ሳይንስ ስራ በዋና ክፍል ደረጃ ተደራጅቶ ከሀያ በላይ የመጀመሪያ ድግሪ እና ሁለተኛ ድግሪ ያላቸው ባለሙያዎችን ይዞ በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

እነዚህ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ፡-

(1) የህፃናት አስተዳደግ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍች ጋር በተያያዘ ከቤተሰብ ችሎት የልጆችን አስተዳደግ አስመልክቶ የሚመራላቸውን ጉዳዮች የልጆችን ጥቅምና ደህንነት መሰረት በማድረግ ልጆች ከየትኛው ቤተሰባቸው ጋር ማደግ እንዳለባቸውና ቀሪው ወላጅ ልጆቹን የሚገኝበትን ሁኔታ ሙያዊ ጥናት በማድረግ የውሳኔ ሀሳብ ለዳኞች ያቀርባሉ፡፡

(2) የጥቃት ሰለባ እና የወንጀል ምስክር የሆኑ ሕፃናትን በተመለከተ ለምስክርነት ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ልጆች ሳይፈሩ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ያግዛሉ እንዲሁም፤

(3) በወንጀል ነክ ጉዳይ ውስጥ ህፃናት ገብተው ሲገኙም ዳኞች ለውሳኔ አሰጣጥ የሚጠቅማቸውን መረጃ በማሰባሰብና የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ለልጆች ጥቅም የሚያስቀድም ውሳኔ ዳኞች እንዲሰጡ ያደርጋሉ፡፡

ባለሙያዎቹ የልጆችን ጥቅም የሚያስቀድም ውጤታማ ስራ መስራት ይቻላቸው ዘንድም እንደየስራ ዘርፉ ባህሪ የተለያዩ የስራ መዘርዝሮች በተለያዩ ጊዜያት ተዘጋጅተው ባለሙያዎቹ እንዲጠቀሙባቸው ተደርጓል፡፡

እነዚህን የስራ መዘርዝሮች አሰባስቦ በዚህ መልኩ ለህትመት ማብቃቱ የስራ መዘርዝሮቹ ለባለሙዎቹ በቀላሉ ተደራሽ እነዲሆኑ ከማስቻሉም በላይ የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ስለስራውና ስለ አሰራሩ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ከዚህ በተጨማሪ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለበትን አሰራር ለማስፈን ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በመስኩ ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚሹ ባለሙያዎችም ሆኑ የምርምር ተቋሞች የስራ መዘርዝሮቹን በቀላሉ እንዲያገኙና መዘርዝሩንም ሆነ የፍርድ ቤቱን አሰራር በመፈተሽ ጠቃሚ ግብረ-መልስ እንዲሰጡን ይረዳል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡

*ደሳለኝ በርሄ*
*የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት*

## <u>ክፍል 1</u>፡ የሕፃናትን አስተዳደግ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሙያ አስተያት እንዲያቀርቡ ለሚጠየቁ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የስራ መዘርዝር

<u>*መግቢያ*</u>

የፍች ውጤቶች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የልጆች አስተዳደግን ይመለከታል፡፡ ልጆች ከማን ጋር መኖር አለባቸው የሚለውን ጉዳይ በተመለከተ ወላጆች ስምምነት ላይ መድረስ ካልቻሉ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት የሚያገኘው በፍርድ ቤት ውሳኔ ነው፡፡

ልጆች ከየትኛው ቤተሰባቸው ጋር ማደግ እንዳለባቸው ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲሰጥ የሚጠይቅ ክርክር ሲነሳ ዳኞች ጉዳዩን ለማህበራዊ ሳይንስ ወይም ለሥነ-ልቦና ባለሙያዎች በመላክ ባለሙያዎቹ ተገቢውን ጥናት አካሂደው የልጆቹን ጥቅምና ደህንነት ያስቀደመ የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡ የሚያደርግ አሰራር በበርካታ ሀገሮች የተለመደ ነው፡፡ ይህ አሰራር በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ የሆነው በ2000 ዓ.ም ሲሆን በተደጋጋሚ በተደረጉ ጥናቶች ስራ ውጤታማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ይህ የስራ መዘርዝር (መመሪያ) በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚገኙ የቤተሰብ ችሎት ላይ የሚቀርቡ የሕፃናት አስተዳደግ ጥያቄዎች ላይ ባለሞያው ጥናት የሚያደርግበትን እና ሙያዊ አስተያየት የሚሰጥበትን አሰራርና የስነምግባር ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ የዚህ ስራ መዘርዝር ግብ የሞያ ሥነ-ምግባሩን የጠበቀ እና ብቃት ያለው አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

### 1. የስራ መዘርዝሩ መጠሪያ

ይህ የስራ መዘርዝር ህፃናት ከየትኛው ወላጃቸው ጋር ማደግ እንዳለባቸው በሚቀርብ ጥያቄ የሞያ አስተያየት እንዲያቀርብ የተመራለት ባለሙያ ሊከተለው የሚገባ የስራ መዘርዝር ነው፡፡

### 2. የስራ መዘርዝሩ ዓላማ

የስራ መዘርዝሩ ዓላማ ባለሞያው የሕፃናትን ጥቅምና ደህንነት ያስቀደመ፤ ብቃት ያለውና የሞያ ሥነ-ምግባሩን የተከተለ አስተያየት እንዲያቀርብ ማስቻል ነው፡፡

### 3. ባለሞያው ስራውን ሲሰራ ሊከተለው የሚገባ መርህ

ባለሙያው ስራውን ሲሰራ የሚከተሉትን የሕፃናትን መብቶች የፍልስፍና መሰረቶች ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

1 አድሎ አለማድረግ
2 የሕፃናት ጥቅምና ደህንነት ቀደምትነት
3 የሕፃናት የመኖርና እድገት መብት
4 የተሳትፎ መብት

## 4. ስለ ባለሞያው

### 4.1 የሞያ ብቃትን ማሳደግ

4.1.1. ባለሞያው ከሥነ-ልቦና ወይም ከማህራዊ ሳይንስ ዕውቀቱ በተጨማሪ ስለሕፃናት እድገት ሁኔታ (child development) ፣ ስለመሰረታዊ የህፃናት መብቶች፣ስለ ሕፃናት ጥቃቶችና በመሳሰሉ በስራው ላይ ያለውን ብቃት የሚያጎለብቱለትን ስልጠናዎች መውሰድ አለበት።

4.1.2. ባለሙያው በኬዝ ሪቪው ፕሮግራም የመገኘትና የመሳተፍ ግዴታ አለበት።

### 4.2 ገለልተኝነት

ባለሙያው ሁለቱንም ወገኖች በእኩል ሁኔታ ማስተናገድ አለበት። ከየትኛውም ወላጅ ሆነ ከሕፃናቱ ጋር ከስራ ውጪ የተለየ ቅርበት ወይም ግኑኙነት አይኖረውም። በሙያ ስራው የራሱን ወይም የሌሎችን አካላት እምነትና አመለካከት ማንፀባረቅ የለበትም።

### 4.3 ከያዘው ጉዳይ ስለመነሳት

ጉጋዩን በገለልተኝነት ለማየት የማያስችለው ነገር ካለ ባለሙያው ይህንኑ በመጥቀስ ጉዳዩን የማያይ መሆኑን ለቅርብ አለቃው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት። በተለይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ከሀላፊነቱ መነሳት አለበት።

4.3.1. ከባለጉዳዮች ወይም ከጠበቃቸው ጋር ዝምድና ወይም ልዩ ቅርበት ካለው፤

4.3.2. ጉዳዩን በግልም ሆነ በሙያው ምክንያት ቀደም ብሎ በስፋት የሚያውቀው ከሆነ። ባለሙያው በራሱ ፍቃድ ካልተነሳና ከክፍሉ ሀላፊ አቤቱታ ከቀረበ ሀላፊው ሁኔታውን መዝኖ ሌላ ባለሙያ እንዲተካ ሊያደርግ ይችላል። ይህ ሂደት ባለጉዳዮቹ ለችሎት የሚያቀርቡትን ቅሬታ አይከክልም።

## 5. የስራው ሂደት በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል።

1 የመግቢያ ኮንፍረንስ
2 መረጃ ማሰባሰብ
3 እውነቱን ማፈላለግ
4 የመውጫ ኮንፍረንስ
5 ሪፖርት ማዘጋጀት

## 6. የመግቢያ ኮንፍረንስ

6.1. ባለሙያው ትዕዛዙ እንደደረሰው ተከራካሪ ወገኖች በጋራ በክፍሉ የሚያገኙበትን ቀጠሮ ትዕዛዙን ይዞ ለመጣው ባለጉዳይ ያሳውቃል፡፡

6.2. ሁለቱም ወገኖች ሲቀርቡ ስራውን የሚጀምረው በቅድሚያ ራሱን በማስተዋወቅ ሲሆን በመቀጠልም ስለስራው ምንነትና ሂደት እንዲሁም ስለመብትና ግዴታቸው ማብራሪያ በመስጠት ነው፡፡ ማብራሪያው የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡፡

6.2.1. የባለሙያው ስራና የመጨረሻው ውጤት የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት ያስቀደመ ውሳኔ ዳኛው እንዲሰጥ የሚያስችል መረጃ ማሰባሰብና የባለሙያ ሀሳብ ማቅረብ መሆኑን፤

6.2.2. ተከራካሪ ወገኖች የሚሞሉት መጠይቅና በቃል የሚሰጧቸው አስተያየቶች እንዲሁም ያቀረቡት ማስረጃ እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን፤የተሰጠው ቃልና የቀረበው ማስረጃ ለፍርድ ቤት የሚቀርብ በመሆኑ ተጠያቂነት እንደሚያስከትልባቸው፤

6.2.3. የሚናገሩትና የፃፉት ነገር በማስረጃነት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ መሆኑንና በሚስጥርነት የማይያዝላቸው መሆኑን፤

6.2.4. ሂደቱ ሊወስድ የሚችለውን ጊዜና ከተከራካሪዎች ስለሚጠበቅ ግዴታ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ማካተት አለበት፡፡

## 7. መረጃ ማሰባሰቢያና ፍሬ ነገርን ማጣሪያ መንገዶች

ባለሙያው ጥናቱን ለማካሄድ የተለያዩ መረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥናት ከዚህ በታች በተመለከቱት ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ እንደ ነገሩ ሁኔታ ሊጠቀም ይችላል፡፡

- ቃለ መጠይቆች
- የባለሙያው ምልከታ (Observation)
- የቤት ውስጥ ጉብኝት
- መረጃ ይገኝባቸዋል ተብለው ለተጠቆሙ ተቋሞች ማለትም ከፍርድ ቤት፣ ከትምህርት ቤት፣ ከሆስፒታሎች እና ከፖሊስ ጣቢያዎች የሚገኙ መረጃዎች እንዲሁም፤
- ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

## 8. የፅሁፍና የቃል መጠይቆች

በዚህ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ስር የሚሞላ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ ማንበብና መፃፍ ለማይችሉ ወላጆች /አሳዳጊዎች/፣ መጠይቁን መሙላት ለማይችሉ ወይም በአካላዊ

ሁኔታቸው ምክንያት በራሳቸው መጠይቁን ለመሙላት ለሚቸገሩ ሰዎች ባለሙያው መጠይቁን በመሙላት ራሱ ሊያግዛቸው ወይም እርዳታ የሚያገኙበትን ቦታ ሊያመላክታቸው ይችላል፡፡ በተሞሉት መጠይቆች ግርጌ መጠይቁን የሞሉት ሰዎች ፊርማቸውን ማስፈራቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለሕፃናቱ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች ባለሙያው ለሕፃናቱ ያቀርባል፡፡ ሕፃናቶች በራሳቸው መጠይቁን መሙላት የሚችሉ ከሆነም ይህንኑ ባለሙያው ያበረታታል፡፡ በእድሜና በትምህርት ደረጃቸው ምክንያት መጠይቁን ሊሞሉ የማይችሉ ከሆነ ባለሙያው ራሱ እየጠየቀ ይመዘግባል፡፡

ከሕፃናቱ ለሚገኙ መረጃዎች የተዘጋጁት ጥያቄዎች የአብዛኛዎቹን ሕፃናት የእድሜ ደረጃ ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን አለባቸው፡፡ የሚመዘኑትም ይህንኑ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡

## 8.1. እውነቱን ማፈላለግ

የፍርድ ቤት ስራ እውነትን ማግኘት ነው፡፡ የማሕበራዊ ሳይንስ ክፍል ባለሙያዎች ዋና ስራም ይኸው የፍርድ ቤቱ ስራ የልጆችን ጥቅም ባስቀደመ ሁኔታ እንዲሳካ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ባለሙያው በቃለ-መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሙያው የሚፈቅደው የእውነት ማፈላለጊያ መንገዶች መጠቀም አለበት፡፡

እውነቱን ለማፈላለግ በዋነኛነት የሚከተሉትን ዘዴዎች እንደነገሩ ሁኔታ በአንድነት ወይም በተናጥል ሊጠቀምባቸው ይችላሉ፡፡

## 8.2. የባለሙያው ምልከታ (Observation)

ይህ መንገድ ባለሙያው በጥናቱ ውስጥ ከሚካተቱ አካላት ጋር በሚኖረው ቆይታ እና በሚያደርጋቸው ውይይቶች ወቅት የሚወስደው ግንዛቤ ነው፡፡ ወላጆች/አሳዳጊዎች ከህፃናቱ ጋር ያላቸው ቅርበት እና ትስስር በዋነኛነት በዚህ መንገድ ሊታወቅ ይችላል፡፡

## 8.3. የቤትና የመኖሪያ አካባቢ ጉብኝት

የሕፃናቱን አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ እድገት ከመጠበቅ አንፃር የመኖሪያ ቤታቸው እና አካባቢው ለዕድረታቸው የሚኖረውን አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት ወላጆች/አሳዳጊዎች ሕፃናቱን ለማሳደግ የሚያቅዱበት የመኖሪያ ቦታና የአኗኗር ሁኔታ በባለሙያው መታየቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ያስችላል፡፡ በቤት ውስጥ የሚደረግ ጉብኝት የቤት ውስጥ ሁኔታ ለልጆች አስተዳደግ ምቹ

ስለመሆን አለመሆኑ ከማረጋገጥ በተጨማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሕፃናቱ በእለት ተዕለት ኑሯቸው ላይ ያለውን ባህሪ ለማየት ያስችላል፡፡

8.4. ከሌች ተቋሞች ማለትም ከትምህርት ቤቶች፣ ከሆስፒታሎች እና ከፖሊስ ጣቢያዎችና ከመሳሰሉት የሚገኙት መረጃዎች ባለሙያው ስለሕፃናቱ ባህሪ እንዲሁም ወላጆቻቸው /አሳዳጊዎቻቸው ከትምህርት ቤቶች ጋር ስላላቸው ግኑኝነት ከትምህርት ቤቶች መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡ በተመሳሳይ በጥናቱ ውስጥ የሚነሱ ጤናን የተመለከቱ ጉዳዮች ከሆስፒታሎች በሚገኙ መረጃዎች ሊረጋገጡ ይችላሉ፡፡ ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲሁም ህፃናት በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከፖሊስ ጣቢያዎች ጋር ግንኙነት ኖሯቸው የሚያውቁ ከሆነ በተጨማሪነት ባለሙያው ግንዛቤውን የሚያሰፉ መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡

8.5. ከሌሎች የቤተሰቡ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶች በሕፃናቱ ህይወት ውስጥ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ የቤተሰቡ አካላት (አያቶች፣አክስቶች፣አጎቶች እና የመሳሰሉት) እንደ አስፈላጊነታቸው በጥናቱ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ ይህም ወደፊት ስለሚደረጉ የህፃናቱ የአስተዳደግ እና ተያይዘው በሚመጡ ሁኔታዎች ላይ የባለሙያውን የግንዛቤ መጠን ለመጨመር ይረዳሉ፡፡ ባለሙያው እነዚህን አካላት በቢሮው ወይም በቤት ውስጥ ጉብኝት በሚያደርግበት ጊዜ ሊያነጋግራቸው ይችላል፡፡

## 9. የውሳኔ ሀሳብ ሲዘጋጅ ታሳቢ ሊሆኑ የሚገቡ ነጥቦች

የሕፃናቱን ጥቅም ያስጠበቀ የውሳኔ ሀሳብ ለማዘጋጀት ባለሙያው የሚከተሉትን ነጥቦች በተገቢው መጠን ሊመዝን ይገባል፡፡

### 9.1 ጠንካራና ጤናማ የግኑኝነት ሁኔታ (Healthy Attachment)

በወላጅ/በአሳዳጊዎችና በሕፃኑቱ መካከል ያለውን የግኑኝነት ሁኔታ ማጥናት የባለሙያው ዋና ተግባር ነው፡፡ ባለሙያው የትኛው ወላጅ/አሳዳጊ ከሕፃናቱ ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳዳበረ እና ይህ የትስስር ሁኔታ ምን ያህል ጤናማ እንደሆነ በጥናቱ ያካትታል፡፡ በአብዛኛው በሕፃናት የመጀመሪያ ዓመታት ሕፃናቱን ይንከባከብ የነበረው ወላጅ/አሳዳጊ ከሕፃናቱ ጋር የጠበቀ ትስስር ለመመስረት ዕድሉ የሰፋ ቢሆንም ይህ እንደቅድመ ሁኔታ መወሰድ የለበትም፡፡ ይልቁንም የወላጆች/አሳዳጊዎች ጤናማ የሆነ ግኑኝነት የመፍጠር ብቃት ደረጃቸውን ከግምት ውስጥ የማስገባት ድርሻ የባለሙያው ይሆናል፡፡

### 9.2 ወላጆች/አሳዳጊዎች ህፃናትን የሚይዙበት መንገድ (Parenting Style)

ይህ የጥናት ክፍል ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ለማሳደግ በሚጠቀሟቸው መንገዶች ላይ ያተኩራል፡፡ ህፃናትን መልካም ዜጋ አድርጎ ለማብቃት ጥቅም ላይ የሚውሉ መንገዶች በባለሙያው ይዳሰሳሉ፡፡ ባለሙያው ወላጆቹ/ አሳዳጊዎቹ

የነበራቸውን እና ህፃናቱን በአንድነት በሚያነጋግርበት ግዜ ስለወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ የልጅ አስተዳደግ ባህሪ ማወቅ ይቻላል፡፡

## 9.3 እሴቶች (Values)

ወላጆች/አሳዳጊዎች ለልጆቻቸው የመጀመሪያዎቹ አርአያ እንደመሆናቸው መጠን በህይወታቸው ውስጥ ዋጋ የሚሰጧቸውና የሚያከብሯቸው እንዲሁም የሚጠብቋቸው መመሪያዎች፤ የሞራል ግዴታዎች ፣ያሏቸው እንዲሁም ለማህበራዊ ህይወት ያላቸውን አመለካከት እና እነዚህ እሴቶቻቸው በልጆቻቸው ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ባለሙያው ይመለከታል፡፡ የእነዚህ እሴቶች አለመኖርም በህፃናቱ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንዳለው ባለሙያው በተመሳሳይ ሁኔታ ይመለከታ፡፡ ይህን በሚያደርግበት ወቅት ባለሙያው የግሉ አመለካከት በጥናቱ ላይ ተፅዕኖ እንዳያደርግ ይጠነቀቃል፡፡

## 9.4 መገኘት (Availability)

ሕፃናቱ የወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸውን አብረዋቸው መሆን የሚፈልጉባቸው ለምሳሌ ወደ ት/ቤት ሲሄዱ ፤ ከት/ቤት ወደ ቤት ሲመለሱ እንዲሁም ከት/ቤት ተመልሰው ቤት ውስጥ የሚያሳልፏቸውን ጊዜና ህመም በሚገጥማቸው ግዜ አጠገባቸው መገኘት የመቻላቸውን ሁኔታ ይዳስሳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናት ክፍል ህፃናቱን በትምህርታቸው የሚያግዘውን ወላጅ/አሳዳጊ በመለየት ላይ ያተኩራል፡፡

## 9.5 ለትምህርት ያላቸው አመለካከት

ወላጆች /አሳዳጊዎች በህፃናቱ ህይወት ውስጥ ለትምህርት መሟላት ያላቸው አመለካከት እና ይህንንም ለማሟላት የሚያደርጉት ጥረት በባለሙያው ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ ወላጆች /አሳዳጊዎች በህፃናቱ ት/ቤት ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ የተመለከቱ ቦታዎችን በመዳሰስ ሊታወቅ ይችላል፡፡

## 9.6 የሌላኛውን ወላጅ በህፃኑ ህይወት ውስጥ ያለውን ሚና ማወቅ እና መቀበል

ባለሙያው በጥናቱ ወቅት አንደኛው ወላጅ/አሳዳጊ ከህፃናቱ ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲቀጥል የማድረግ ፍላጎት እንዳለውና እንደሌለው ያጣራል፡፡ የዚህ ሁኔታ አለመኖር በህፃናቱ እና በሌላኛው ወላጅ/አሳዳጊ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻከር ህፃናቱ የጥላቻ መንፈስ እንዲያዳብሩ ክፍተት የሚሰጥ መሆኑን ያሳያል፡፡

### 9.7 የትብብር መጠን

በጥናቱ ወቅት ወላጆች/አሳዳጊዎች ከሌላኛው ወገን ጋር በስምምነት ለመስራት የሚያደርጉትን የትብብር መጠን ባለሙያው ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡ ምንም እንኳን የራሳቸውን ጉዳይ ወደ ጎን ትተው አብሮ ለመስራት ቢከብዳቸውም ይህ ሁኔታ የህፃናቱ ህይወት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር አይገባውም፡፡

### 9.8 የሕፃቱም መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት

ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን መሰረታዊ ፍላጎት /የምግብ፣ ልብስ እና መጠለያ የማሟላት አቅማቸው /የገንዘብ አቅም/ እና አቅማቸውን ምን ያህል ጥቅም ላይ እንደሚያውሉት ባለሙያው ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባል፡፡

### 9.9 አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጤና

በወላጆች/አሳዳጊዎች ላይ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ የጤና ችግር መኖር አለመኖራቸው ትኩረት ተሰጥቶት ይዳሰሳል፡፡ ማንኛውም የጤና ችግር በወላጆች/አሳዳጊዎች እና በህፃናቱ መካከል ያለው ግኑኝነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው እና እንደሌለው ባለሙያው ጥናት ያደርጋል፡፡

ባለሙያው ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች መኖር አለመኖራቸውን በወላጆች/አሳዳጊዎች ላይ የሚታዩ የባህሪ ችግሮች ፣ ለሱስ ተገዥ መሆን አለመሆናቸውን ፣ አካላዊ ሥነ- ልቦናዊና ፆታዊ ጥቃት ለማድረስ ያላቸውን ዝንባሌ /tendency/ እና የመሳሰሉትን እንደጠቋሚ ሁኔታዎች በመውሰድ ጥናቱን ያደርጋል፡፡

### 9.10 ህፃናቱን በአለመግባባቶች ውስጥ ማካተት

አንዳንድ ወላጆች ህፃናትን እንደመሳሪያ በመጠቀም ሌላኛውን ወላጅ ለማጥቃት ሲሞክሩ ይታያል፡፡ ህፃናትን እንደሰላይ /መረጃ እንደማግኛ መንገድ/ መጠቀም ለህፃናት መልካም ሥነ-ምግባርን አለማሳየት መሆኑ ታውቆ ባለሙያው እነዚህ አይነት ባህሪያት በወላጆች/ አሳዳጊዎች ላይ መኖር አለመኖራቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ህፃናቱ ስለወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻው አለመግባባት ባላቸው የግንዛቤ መጠን ሊታወቅ ይችላል፡፡

### 9.11 ሌሎች የቤተሰብ አባላት

ሕፃናት ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች ከሚያገኙት ፍቅርና እንክብካቤ በተጨማሪ ሌሎች የቤተሰቡ አባላት በቅርብ በሚያገኙበት ሁኔታ ማደጋቸው በተለይ በማህበረሰባችን ውስጥ ያለውን በጠንካራ የቤተሰብ ትስስር ላይ የተመሰረተ አኗኗራችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለህፃናቱ የተሟላ ዕድገት ያለውን አዎንታዊ አስተዋፅኦ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ስለሆነም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸው ቅርበት

በባለሙያው ከግንዛቤ ውስጥ ይገባል፡፡ ይህ ሲባል ግን ሰፊ ቤተሰብ ያለው ወላጅ ህፃናቱን ለመያዝ ቅድሚያ ይሰጠዋል ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንደ የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የቤተሰቡ አባላት የትምህርትና የስራ ደረጃ፣ በቤተሰቡ መካከል ያለው ቅርበትና ተመሳሳይ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡

## 9.12 የህፃናቱ ፍላጎት

የህፃናት ፍላጎት ከዕድሜያቸውና ከአስተሳሰባቸው ደረጃ አንፃር ዋጋ የሚሰጠው ቢሆንም ከዚህም በዘለለ ትክክል ያልሆነ መረጃ ሊገኝበት የሚችል መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ስለሆነም ባለሙያው የህፃናቱን ፍላጎት ከዕድሜና ከአስተሳሰብ ብስለት ደረጃቸው ጎን ለጎን ተፅዕኖ የሌለበት መሆን አለመሆኑን ይመዝናል፡፡

## 9.13 ልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት (Children with special needs)

ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው (የአእምሯቸው ሁኔታ ያልተስተካከለ፤ ማየት የተሳናቸውና በአካላቸው የተለያየ ደረጃ ጉዳት ያለባቸው (Handicapped) ህፃናትን ለማሳደግ የሚጠይቀውን ኃላፊነት ለመቀበል ወይም ለመሸሽ ጥረት የሚያደርጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች በባለሙያው አማካይነት በጥናቱ ወቅት ሊታወቁ ይችላሉ፡፡ እነዚህን መሰል ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥም ሌሎች ነገሮች እንዳሉ ሆነው ባለሙያው ህፃናቱን ለማሳደግ እውነተኛ የሆነ ፍላጎት ያለውን ወላጅ/አሳዳጊ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

## 10. የልጆችን ጥቅም አስመልክቶ ሊወሰዱ የሚገባቸው ህሊናዊ ግምቶች (Presumptions)

10.1. **በጋራ ለማሳደግ (Shared parenting)** የሚደረጉ ስምምነቶች የልጆችን ጥቅም የሚያስቀድሙ ናቸው ተብሎ ይገመታል፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን በጋራ ለማሳደግ ስምምነት ማድረጋቸው ልጆች ከፍች በፊት ያገኙት የነበረውን የሁለቱንም ወላጆቻቸውን እንክብካቤ የማግኘት ሁኔታ እንዲቀጥል ስለሚያደርግ የልጆች ጥቅምና ደህንነትን የበለጠ ያረጋግጣል ተብሎ ይታመናል፡፡

10.2 ተመራጭ አሳዳጊ ዋና እንክብካቤ እያደረገ ያለ ወላጅ ስለመሆኑ ግምት ይወስዳል፡፡ ሕፃናቶችን በተመለከተ (በተለይ እድሜያቸው ከሰባትና ከሰባት አመት በታች ለሆኑ) በመመገብ፤ ሥነ-ሥርአት በማስያዝ፤ በማዝናናትና ትምህርታቸውን በመከታተል ከፍተኛ ሚና የነበረው ወላጅ የማሳደጉን ሀላፊነት ይዞ እንዲቀጥል ቢደረግ የልጆች ጥቅም ይበልጥ ይጠበቃል የሚል ግምት ይወሰዳል፡፡ ይህ ግምት እድሜያቸው ከፍ ላሉት ህፃናትም ይሰራል፡፡

ሆኖም ግምቱ የተሳሳተ መሆኑን በማሳየት ግምቱን ዋጋ ማሳጣት ይቻላል፡፡ በተለይም እድሜያቸው ከሰባት ዓመት በላይ የሆኑ ህፃናትን በተመለከተ ግምቱን በቀላሉ ማፍረስ ይቻላል፡፡

## 10.3 ያደጉ ልጆች ፍላጎት (Wishes of older children)

እድሜያቸው ከአስራ አራት ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ጥቅማቸውን ይበልጥ የሚያስጠብቅላቸውን ወላጆች ለመምረጥ አይቸገሩም ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ለፍላጎታቸው በቂ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ሆኖም ይህ ግምት በሁለት ምክንያቶች ከሌሎች ግምቶች ያነሰ ግምት ይሰጠዋል፡፡ አንደኛው በቤተሰቦቻቸው ውዝግብ ህፃናትን እንዲገቡ ተፅዕኖ ማሳደሩ ተገቢ ባለመሆኑ ሲሆን ፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የልጆች ፍላጎት እንዴትና ከምን እንደመነጨ በውሳኔ ሰጪው አካል መመዘን መቻል ስላለባቸው ነው፡፡

## 11. የመውጫ ኮንፍረንስ

ባለሙያው ሪፖርቱን ከማጠናቀቁ በፊት ባለጉዳዮቹን በመጥራት የደረሰበትን ድምዳሜና ምክንያቶችን በማስረዳት በስምምነት ሊጨርሱ የሚፈልጉት ነገር ካለ እንዲጨርሱ ሀሳብ ሊቀርብላቸው ይችላል፡፡ ተከራካሪዎች ለመውጫ ኮንፍረንስ ተጠርተው ካልቀረቡ ወይም የተከራካሪ ወገኖች አጠቃላይ ሁኔታ ለዚህ ሂደት አስቸጋሪ ሆኖ ከተገኘ ግን የመውጫ ኮንፍረንስ ማድረግ ሳያስፈልግ ሪፖርቱ ለችሎት በወቅቱ መላክ አለበት፡፡

## 12. ሪፖርት ማዘጋጀት

12.1 የሚዘጋጀው ሪፖርት የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡፡ የልጆች ሁኔታ (Child factor) ፤ የወላጆች ሁኔታ(Parents factor) ፤ በወላጆች መካከል ያለው ግኑኝነት(Inter-parental factor) እንዲሁም አካባቢያዊ ሁኔታዎች (Situational factors)፤እንዲሁም ሪፖርቱ ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን በዝርዝር ማስቀመጥ አለበት፡፡ እንዲሁም እያንዳንዱ ተከራካሪ ወገን ልጅ የማሳደግ መብት ቢሰጠው ያለውን ጥቅም እና ጉዳት ሪፖርቱ ማሳየት አለበት፡፡ በመጨረሻም ሪፖርቱ የማጠቃለያ (Conclusion) ሀሳብና የመፍትሔ ሀሳብ (Recommendation) መያዝ አለበት፡፡

12.2 የባለሞያው አስተያየት ልጆች ከማን ጋር ማደግ እንዳለባቸውና ልጆችን የማሳደግ መብት ያልተሰጠው ወላጅ ያለው የመጎብኘት መብት እንዲሁም የጉብኝቱ ሁኔታ መቼ ፤ እንዴትና በምን ሁኔታ ቢፈፀም ተመራጭ እንደሆነ በዝርዝር መያዝ አለበት፡፡

## 13. ሪፖርቱን ለችሎት መላክ

ሪፖርቱ ጉዳዩን የላከው ችሎት ከሰጠው የጊዜ ቀጠሮ በፊት ለችሎቱ ይደርሳል፤ በተሰጠው ጊዜ ሪፖርቱ መቅረብ ካልቻለ ባለሙያው ምክንያቱን በመግለፅ ችሎቱን ተጨማሪ ቀጠሮ እንዲሰጠው ከቀጠሮ ቀን በፊት በፅሁፍ ይጠይቃል፡፡

*ይህ የተሻሻለ የማህበራዊ ሳይንስ ክፍል ሰራተኞች የስራ መዘርዝር ከሰኔ 12 ቀን 2004 ዓ፣ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡*

## ክፍል 2፡ የጥቃት ሰለባ እ የወንጀል ምስክር ከሆኑ ህፃናት ጋር ለሚሰሩ የማህበዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የስራ መዘርዝር

### መግቢያ

ህፃናት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ፍትህ ስርዓቱ ይመጣሉ፡፡ ከእነዚህም ምክንያቶች ውስጥ ህፃናቱ የጥቃት ሰለባ እንዲሁም የወንጀል ምስክር ሆነው የሚመጡበት ሁኔታ ተጠቃሽ ምክንያት ነው፡፡ የጥቃት ሰለባ ሆነው የመጡ ህፃናት ወይም የወንጀል ምስክር ህፃናት የሚለው ስያሜ የሚያካትተው እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑትን ህፃናት ሲሆን እነሱም ጥቃት የተፈፀመባቸው የግል ተበዳዮችን፣ ወንጀል ስለመፈፀሙ ሊያስረዱ የሚችሉ ህፃናትን እና ለተከሳሽ የመከላከያ ምስክር የሆኑ ህፃናትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ክፍሉ ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ግለሰቦችን በደረሰባቸው የሥነ-ልቦና ጉዳት የተነሳ እና ከባህላቸው አንፃር የደረሰባቸውን ጥቃት ችሎት ቀርበው መመስከር የሚቸገሩ ሲሆኑ ችሎቱ ኔታውን በማገናዘብ በክፍሉ እንዲስተናገዱ ይሆናል፡፡

ይህ አሰራር ህፃናት ምስክርነታቸውን ተረጋግተው እና በምቹ ሁኔታ የሚሰጡበትን መንገድ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ በክፍሉ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ እገዛ ያገኛሉ፡፡ በዚህ ክፍል የሚሰራው ባለሙያ የስራ መጠሪያው አገናኝ ባለሙያ (Intermediary) ይባላል፡፡ ይህን ስራ የሚሰራው ባለሙያ ህፃናቱ ከችሎቱ የሚጠየቀው ጥያቄ ገብቷቸው በተረጋጋ ሁኔታ ምስክርነታቸውን እንዲሰጡ በማድረግ የማገናኘት ስራ ይሰራል፡፡

ይህ የስራ መዘርዝር(መመሪያ) በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚገኙ የህፃናት ጥቃት የሚታይባቸው ችሎቶች ውስጥ የሚሰሩ አጋዥ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎችን የአሰራ ሂደትና የሥነ-ምግባር ሁኔታን የሚያመለክት ነው፡፡ የዚህ የስራ መዘርዝር ግብ ባለሞያው የሙያ ሥነ-ምግባሩን የጠበቀ እና ብቃት ያለው አሰራር ተግባራዊ እንዲያደርግ ለመርዳት ነው፡፡

### 1. የስራ መዘርዝሩ መጠሪያ

ይህ የስራ መዘርዝር "ህፃናት የጥቃት ሰለባ እና የወንጀል ምስክር ሆነው ሲመጡ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያ ሊከተለው የሚገባ የስራ መዘርዝር" ነው፡፡

### 2. የስራ መዘርዝሩ አላማ

የስራ መዘርዝሩ አላማ የምስክርነት መስማት ሂደቱ የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን ውጤታማነት በሚያጠናክር መልኩ ምስክርነት ለመስጠት የመጡ ህፃናት ሥነ-ልቦና እንዳይጎዳ በሚያደርግ ሁኔታ የወንጀል ጥቃት ሰለባ የሆኑ ህፃናት የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡

## 3. ባለሙያው ስራው ሲሰራ ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆች

ባለሙያው ስራውን ሲሰራ የሚከተሉትን የህፃናት መብቶችና የፍልስፍና መሰረቶችን ታሳቢ ማድረግ አለበት፡፡

1 የህፃናት ጥቅምና ደህንነት ቀደምትነት
2 የህፃናት ተሳትፎ መብት
3 አድሎ አለማድረግ
4 የህፃናት የመኖርና የማደግ መብት

## 4. ስለባለሞያው

### 4.1 የሞያ ብቃትን ማሳደግ

- ባለሙያው ከሥነ-ልቦና እና ከማህበራዊ ሳይንስ እውቀቱ በተጨማሪ ስለህፃናት መብቶችና መርሆቻቸው፤ የህፃናት ምስክሮችን አያያዝ በተመለከተ እና ለምስክሮች በሚቀርቡ ጥያቄዎች አቀራረብ ዙሪያ ስላሉት የሥነ-ሥርዐት ህጎች በአጠቃላይ ስለችሎት ሂደት እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ስለጥቃት ምንነት እና አይነቶች በተለይም በህፃናት ላይ የሚያደርሰውን የአጭር ጊዜም ሆነ የረጅም ጊዜ ተፅዕኖ የህፃናት እድገት ደረጃ በተለይም የማስታወስ እና ትኩረት የመስጠጥ ችሎታን በተመለከተ እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡
- ባለሙያው ከህፃናት ጋር የመግባቢያ መንገዶችንና በዚህ ረገድ ሊኖረው የሚገባውን ክህሎት ሊያውቅ ይገባል፡፡
- ስለ ህፃናት እና ፍላጎቶቻቸው በተለይም በምስክር ወቅት ህፃናት ከተፅዕኖ ወይም ከአደጋ ውጪ መሆናቸውን ሊያረጋግጥም የሚችልበትን ችሎታ ማዳበር ይገባዋል፡፡

### 4.2 ገለልተኝነት

ባለሙያው ተጠሪነቱ ለፍርድ ቤቱ ሲሆን በጉዳዩ ውስጥ ከሚካተቱ አካላት ማለትም ከከሳሽ (ዐቃቢ ህግ)፣ ከተበዳይ ነን ባዮች እና ከተከሳሽ ወገን ገለልተኛ በመሆን በታማኝነት ማገልገል አለበት፡፡ ከየትኛውም ወላጅ ሆነ ከህፃናቱ ጋር ከስራ ውጪ የተለየ ቅርበት ወይም ግንኙነት ሊኖረው አይገባም፡፡ በሞያ ስራው የራሱን ወይም የሌሎችን አካላት አመለካከት ማንፀባረቅ የለበትም፡፡

### 4.3 ከያዘው ጉዳይ ስለመነሳት

ጉዳዩን ለማየት የማያስችለው ነገር ካለ ባለሙያው ይህንኑ በመጥቀስ ጉዳዩን የማያይ መሆኑን ለቅርብ አለቃው ማሳወቅ አለበት፡፡ በተለይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ከኃላፊነቱ መነሳት አለበት፡፡

4.3.1 ከባለጉዳዮችም ሆነ ከጠበቃቸው ጋር ዝምድና ወይም ልዩ ቅርበት ካለው፣

4.3.2 ጉዳዩን በግልም ሆነ በሙያው ቀደም ብሎ በስፋት የሚያውቀው ከሆነ፣

4.3.3 ባለሙያው በራሱ ፍቃድ ካልተነሳና ለክፍሉ ኃላፊ አቤቱታ ከቀረበ ኃላፊው ሁኔታውን መዝኖ ሌላ ባለሙያ እንዲተካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4.3.4 ይህ ሂደት ባለጉዳዮቹ ለችሎት የሚያቀርቡትን ቅሬታ አይከለክልም፡፡

### 5. የስራው ሂደት በ6 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል

1 መግቢያ
2 ቅርርብ መፍጠር
3 ህፃናቱን ለማስመስከር ቅድመ ዝግጅት
4 የባለሞያው ህፃናቱን የማስመስከር ሂደት
5 መዝጊያ
6 ህፃናቱን ተጨማሪ እገዛ ሊያገኙ ከሚችሉበት አካል ጋር ማገናኘት (Referral)

### 5.1. የመግቢያ ንግግር

ህፃናቱ ወደ ክፍሉ ሲገቡ ባለሙያው በቅድሚ ራሱን በማስተዋወቅ የሚጀምርበት ሲሆን ባለሞያው ከህፃናት እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚሰራ ባለሞያ ስለመሆኑና ህፃናቱ በቢሮው ውስጥ ሊገኙ የቻሉት ጥቅምና ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ ሲባል እንደሆነ ለህፃናቱ እንደ እድገት ደረጃቸው በማስረዳት ይጀምራል፡፡

### 5.2. ቅርርብ መፍጠር (Rapport building)

በቀጣይ ህፃናቱ ስለደረሰባቸው ጥቃት ወይም ስላዩት ወንጀል የሚናገሩ በመሆኑ ተረጋግተው ምቾት ተሰምቷቸው እና በባለሞያው ላይ እምነት አድሮባቸው መናገር እንዲችሉ ባለሙያው ከህፃናቱ ጋር ቅርርብ ሊፈጥር ይገባል፡፡ ስለ ህፃናቱ የግል ሁኔታ ለምሳሌ የት እንደሚኖሩ፣ የስንተኛ ክፍል ተማሪዎች እንደሆኑ፤ የሚያስደስታቸው ምን እንደሆነ በመጠየቅ እና የሚያስደስታቸውን ነገር እንዲያወሩ እና እዲጫወቱ መንገዱን በማመቻቸት በአጠቃላይ ስርዓትን በተከተለ መልኩ ህፃናቱን ሊያዝናኑ የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ባለሙያው ቅርርብ መፍጠር ያስፈልገዋል፡፡ ከህፃናቱ ጋር ቅርርብ ለመፍጠር ባለሙያው

የሚጠቀምባቸውን ዘዴዎች እንደ ህፃናቱ እድሜ፣ የአእምሮ ሁኔታ፣ ስሜት እና የእድገት ደረጃ ሊቀያይራቸው ይገባል።

## 5.3 ህፃናቱን ለምስክርነት የማዘጋጀት ስራ

ባለሙያው ከህፃናቱ ጋር ቅርበት ከፈጠረ በኋላ በክፍሉ ስለሚስተናገዱ ህፃናት፣ ህፃናቱ ስለሚቀርብላቸው ጥቄዎች እና በፍርድ ቤት ስርዓቱ ከነሱ ስለሚጠበቁት ሁኔታዎች ህፃናቱ ማወቅ እንዲችሉ በቅድሚያ የማዘጋጀት ስራ ያከናውናል። ህፃናቱ የምስክር አሰጣጥ ሂደቱ ምን ሊመስል እንደሚችል ወይም ምን እንደሚጠበቅባቸው ግልፅ እንዲሆንላቸው ባለሙያው ህፃናቱ ሊረዱት በሚችሉበት መንገድ በመጠቀም መረዳታቸውን ያረጋግጣል።

## 5.4 የባለሙያው ህፃናቱን የማስመስከር ሂደት

ህፃናት የጥቃት ሰለባ እና የወንጀል ምስክር ሆነው በሚመጡበት ወቅት በዋነኛነት የሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች የዋና ጥያቄ፣ የመስቀለኛ ጥያቄ እና የማጣሪያ ጥያቄዎች ሲባሉ እነዚህም ጥያቄዎች በምስክር መስማት ሂደቱ ላይ ተሳታፊ በሆኑት አካላት በዓቃቢ ህግ፣ በተከሳ (በተከሳሽ ጠበቃ) እና በችሎቱ ዳኛ እንደ ቅደም ተከተላቸው ይቀርባሉ። በቅድሚያ ህፃናቱ የግል ሁኔታ ማለትም ስም ፣ ዕድሜ ፣ የትምህርት ወይም የስራ ሁኔታ፣ የመኖሪያ አድራሻ ከተጠየቁ በኋላ ስለተከሳሽ ማንነት፤ ስለወንጀሉ ምንነት፤ ከተከሳሽ ጋር ዝምድና ወይም ፀብ ካለ እና ምን ለማድረግ እንደቀረቡ የሚጠየቁበት ሂደት ይቀጥላል። በመቀጠል የዋና ጥያቄ ሂደት ሲሆን በዚህ ወቅት በዋነኛነት ህፃናቱ ስለደረሰባቸው ጥቃትና ስለአጠቃላይ ሁኔታው ማለትም ድርጊቱ የተፈፀመበትን ቦታ፣ ጊዜና ሰዓት የድርጊቱን አፈፃፀም ሁኔታ እና የመሳሰሉትን፣ ድርጊቱ ስለመፈፀሙ እንዲያስረዱ የሚጋብዛቸውን ጥያቄዎች ይጠየቃሉ። በመስቀለኛ ጥያቄ የሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በተከሳሽ ወይም በተከሳሽ ጠበቃ የሚቀርቡ ሲሆን በዚህ ሂደት ተከሳሹ ራሱን ከጥፋተኝነት ሊያድን የሚችልባቸውን መረጃዎች ለማግኘት ወይም ህፃናት በሚሰጡት የምስክርነት ታማኝነት ታጥቶባቸው እንዲያጠራጥሩ የሚያደርጉ ናቸው። ዓቃቤ ህግ በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት በህፃኑ የተመለሱ አጠራጣሪ መልሶች ካሉ በድጋሚ ጥያቄ ጊዜ መልሶቹን በግልፅ ሊያስረዳ እንዲችል በድጋሚ ይጠይቃል። በመጨረሻም የችሎቱ ዳኛ በማጣሪያ ጥያቄ የቀረ ወይም ግልፅ ያልሆኑለት መረጃዎች ካሉ ለህፃኑ ጥያቄ የሚያቀርብበት ሂደት ይከተላል።

### 5.4.1 የህፃናቱ ሁኔታ

ባለሙያው ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በሙሉ ለህፃናቱ የሚያቀርብ በመሆኑ የህፃናቱ እድሜ፣ የዕድገት ደረጃ እና የሥነ-ልቦና ሁኔታ ታሳቢ ማድረግ አለበት ።

**የህፃናቱ ዕድሜ**

በየትኛውም የዕድሜ ደረጃ የሚገኙ ህፃናት በምስክርነት የሚመጡበት ሁኔታ ስላለ ባለሙያው ለመግባቢያ የሚጠቀምበትን ዘዴ እንደ ህፃናቱ እድሜና የብስለት ደረጃቸው ሊቀያይር ይገባል፡፡

**የህፃናቱ የዕድገት ደረጃ**

ህፃናት እድሜያቸው ብቻ ሳይሆን ያሉበትም የዕድገት ደረጃ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡ ፡ አንዳንድ ህፃናት ባሉበት እድሜ ሊያሳዩዋቸው የሚገባቸው እድገቶች ላይ ሊዘገዩ ወይም ሊፈጥኑ ይችላሉ፡፡ስለሆነም በእድሜያቸው ብቻ ሳይሆን እንደ እድገት ደረጃቸው ዝቅ ወይም ከፍ ብለን መግባባት አለብን ፡፡

**የሕፃናቱ የሥነ-ልቦና ሁኔታ**

ከዚህ በተጨማሪ ህፃናት ለመመስከር በሥነ-ልቦናቸውና በስሜታቸው ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ አንድ ህፃን ለመመስከር ቀርቦ በተለያየ ምክንያት የመረበሽ ወይም የመጨነቅ ስሜት ውስጥ ያለ እንደሆነ ባለሙያው ተጨማሪ ግዜ በመውሰድ ህፃኑ ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ አለበት፡፡ ይህ ሁኔታ በምስክር ሂደቱ ወቅት ከተከሰተ ህፃኑ እንዲረጋጋ የምስክር ሂደቱ ለተወሰነ ግዜ እንዲቋረጥ ወይም ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ለችሎቱ ያሳውቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባለሙያው ህፃኑ ላይ ሌሎች የሥነ-አዕምሮ ችግሮች ማለትም የአዕምሮ ውስንነት፣ የሀሳብ ቶሎ ቶሎ መሰረቅ እና ያለመረጋጋት (ADHD) ወ.ዘ.ተ ችግሮች መኖራቸውን የሚያመላክቱ ነገሮች ካገኘ ሙያው የሚፈቅደውን ጥንቃቄ እንዲሁም በቂ ጊዜ በመውሰድ ሊያስተናግዳቸው ይገባል፡፡

**5.4.2 የመግባቢያ ክህሎቶችና መንገዶች**

ባለሙያው ህፃናት ተረጋግተው እና ገብቷቸው እንዲመሰክሩ የሚከተሉትን የመግባቢያ ክህሎቶች ሊያደርግ ይገባዋል፡፡

- ቃላት አጠቃቀም
- የድምፅ አጠቃቀም
- አካላዊ ሁኔታ
- ጥያቄ አቀራረብ
- ሌሎች የሀሳብ መግለጫ ወይም የመግባቢያ መንገዶች

**5.4.2.1. ቃላት አጠቃቀም**

መግባባትን ከሚያሰናክሉ ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የቃላት አጠቃቀም ነው፡፡ ስለሆነም ለመግባባት ያሰብነውን ሰው እድሜና የዕድገት ደረጃ እንዲሁም የባህል ሁኔታ ልናውቅ ይገባል፡፡ ህፃናት ማለትም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ በተለያየ የእድገት ደረጃ ውስጥ የሚገኙ እና የተለያየ የህብረተሰብ ክፍል ባህል ውጤት እንደመሆናቸው መጠን ባለሙያው ለህፃናቱ የሚያቀርባቸውን ጥያቄዎች በዚህ መልኩ መጥኖ እና አስተካክሎ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ለምሳሌ የአስገድዶ

መድፈር ጥቃት ደርሶባት በመመስከር ላይ ያለች ከአምስት አመት በታች የሆነች ህፃን በብልት ክፍሏ ላይ ስለደረሰባት ጥቃት እንድትገልፅ የምትጠየቅ ከሆነ በቀላሉ ግልፅ እንዲሆንላት በሽንት መሸኚያሽ ላይ ምን አይነት ጉዳት ደረሰብሽ በሚል ልትጠየቅ ትችላለች፡፡

#### 5.4.2.2. የድምፅ አጠቃቀም

ባለሙያው ህፃናቱን በሚያነጋግርበት ወቅት የሚጠቀመው ድምፅ ህፃናቱን በማይረብሽና በተረጋጋ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ እንደዚሁም ባለሙያው ሁኔታዎች በሚፈቅዱለት ጊዜ ድምፁን ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ እየቀያየረ ከህፃናቱ ጋር የሚያደርገውን መግባባት ውጤታማ ሊያደርገው ይችላል፡፡

#### 5.4.2.3. አካላዊ ሁኔታ

ባለሙያው ከህፃኗ/ኑ ጋር በሚነጋገርበት ወቅት ሊኖር የሚገባው የአካል አቀማመጥ ማለትም ከህፃኗ/ኑ ያለው ቅርበትና አቅጣጫ እንዲሁም የአይን አትኩሮት የህፃኑን ምቾት በማይረብሽ ሁኔታ መሆን አለበት፡፡ ከሁሉም በላይ በአካላዊ ሁኔታ የሚተላለፉ መልዕክቶች በቃላት ከሚገለፁ መልዕክቶች በላይ ያላቸውን ተፅዕኖ በቅጡ መገንዘብ አለበት፡፡

#### 5.4.2.4 ጥያቄ አቀራረብ

ህፃናት እድሜያቸው እያነሰ በመጣ ቁጥር ውስብስብ ሀሳቦች በቀላሉ የመረዳት ችሎታቸው እየቀነሰ ስለሚመጣ የሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች በአጭርና በግልፅ ሊቀመጡ ይገባል፡፡ ይህም ማለት በአንድ ግዜ ከአንድ በላይ ጥያቄ ሊቀርብላቸው አይገባም፡፡ ባለሙያው ውስብስብ ሆነው ግልፅ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በመነጣጠል ለህፃኑ ሊያቀርብ ይገባል፡፡ የሚቀርቡት ጥያቄዎች ደግሞ የሚመሩ ወይም መልሱን የሚጠቁሙ ሳይሆኑ ክፍት ጥያቄዎች መሆን አለባቸው፡፡

#### 5.4.2.5. ሌሎች ሀሳብ መግለጫ ወይም መግባቢያ መንገዶች

በተጨማሪም በእድሜ አነስ ያሉት ህፃናት የተፈፀመውን ድርጊት ለመግለፅ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡ ለምሳሌ በጨዋታ መልክ አሻንጉሊት በመጠቀም ወይም ስዕል በመሳል ይገልፃሉ፡፡ ስለሆነም ባለሙያው በእነዚህን የአገላለፅ መንገዶች ህፃናቱ እንዲጠቀሙ ማመቻቸት ይጠበቅበታል፡፡

### 5.4.2.6. የህፃናቱ የምስክር ሂደት መቋረጥ ወይም መተላለፍ

ባለሙያው ከህፃናቱ ጋር የሚኖረውን የምስክር ማሰማት ሁኔታ ለተወሰነ ግዜ አቋርጦ የሚቀጥልበት ወይም ለሌላ ግዜ ሊተላለፍ የሚችልበት ሁኔታዎች ይኖራሉ፡ ፡ ከእነዚህም ውስጥ ባለሙያው ለዳኛው ማሳወቅ የሚገባቸው ነገሮች ፡-

- ባለሙያው ህፃናቱ በተፅዕኖ ምክንያት ሀሳባቸውን መቀየራቸውን የተረዳ እንደሆነ፤
- ባለሙያው በተሰጠው ሰዓት ከህፃናቱ ጋር ቅርበት መፍጠር የተቸገረ ከሆነ፤
- ሂደቱ ከተጀመረ በኋላም በህፃናቱ በኩል በተለያየ ምክንያት የመጨነቅ፣ የማልቀስ ወይም የመሰልቸት ወ.ዘ.ተ. ሁኔታዎች ከተከሰቱ ወይም ከክፍሉ የመውጣትና ሽንት ቤት ለመሄድ ፍላጎት ያሳዩ እንደሆነ፡፡

### 5.5. መዝጊያ

የምስክር ሂደቱ እንዳለቀ ባለሙያው የምስክር ሂደቱ መጠናቀቁን ገልፆ ህፃናቱን ካመሰገነ በኋላ ህፃናቱ በቀረቡላቸው ጥያቄዎች በአብዛኛው ስለተፈፀመባቸው ጥቃት በድጋሚ እንዲያስታውሱና እንዲሰማቸው የሚያደርግ በመሆኑ ህፃናቱ የመረበሽ፣ የመደንገጥ፣ የመናደድ እና የጥፋተኝነት ስሜት እንዲቀሰቀስባቸው ሊያደርግ ስለሚችል ባለሙያው ህፃኗን/ኑን ከመሸኘቱ በፊት ደስታን ሊፈጥሩላቸው የሚችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ለምሳሌ በጨዋታ፤ በተረቶች፣ (መዝሙር) ወይም ስዕል በመሳል የህፃናቱን ስሜት ለመቀየር መሞከር አለበት፡፡

### 5.6 ህፃናቱን ተጨማሪ እገዛ ሊያገኙ ከሚችሉበት አካል ጋር ማገናኘት (Referal)

በቀጣይ ጥቃት የደረሰባቸው ምስክር ህፃናት ለማህበራዊና ስነ- ልቦናዊ ችግር የተዳረጉ ከሆነ ወደ ጤናማ ወይም የተሻለ ሁኔታ እንዲመለሱ ባለሙያው ህፃናቱን እና/ወይም ቤተሰባቸውን ተቀብለው ሊያስተናግዱ ከሚችሉ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ የማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ማገናኘት አለበት፡፡ ይህ ሂደት እንደ ህፃናቱ ጉዳት መጠን፤ የቤተሰብ ሁኔታ እና እንደ ፍላጎት ልዩነታቸው ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ብሎ ለሚያስባቸው ቅድሚያ በመስጠት ድርጅቶች እንዳላቸው አቅም ተጠቃሚዎችን ሊያገናኝ ይገባል፡፡

*ይህ የስራ መዘርዝር ከታህሳስ 17 ቀን 2005 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡*

## ክፍል 3፡ በወንጀል ነክ ጉዳይ ውስጥ ገብተው የተገኙ ወጣቶች ላይ ለሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የስራ መመሪያ

### መግቢያ

ሕፃናትና ወጣቶች የወንጀል ህግን በመተላለፍ ወደ ወንጀል ድርጊት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በርካታ ፅሁፎች ህፃናት/ወጣቶች ለምን እና እንዴት ወደ ወንጀል ነክ ድርጊቶች ውስጥ እንደሚገቡ የተለያየ መረጃዎችን ያትታሉ፡፡ ሆኖም ግን ጠቅለል ባለ መልኩ ከሚያስሚሟቸው ምክንያቶች ውስጥ ድህነት፣ የትምህርት እድል ማጣት፣ ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት፣የጓደኛ ግፊት የከተሞች ስልጣኔ፣ የቤተሰብ መፍረስ፣ የሥነ-ልቦና ችግር፣ በቂ የሆነ የወላጆች/የአሳዳጊ ክትትል አለመኖር እና ልዩ ልዩ ማህበራዊ ነክ ተፅዕኖዎች በዋነኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በዚህም መሰረት በወንጀል ነገር ገብተዋል ተብለው ተጠርጥረው የተያዙ ወጣቶች በምርመራና በክስ ሂደት የሚያልፉባቸው በርካታ ሂደቶች ያሉ ሲሆን እነዚህ ሂደቶችና በመጨረሻም የሚሰጡ ውሳኔዎች የልጆችን ጥቅምና ደህንነት ማስቀደም እንዳለባቸው በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት፤ ሀገራችን በፈረመቻቸው አለምአቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲሁም በዝርዝር ህጎቻችን ላይ ተመልክቷል፡፡

ፍርድ ቤታችን በህግ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ወጣቶችና ህፃናት በወንጀል ነገር ገብተዋልተብለው ተጠርጥረው ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ለህፃናት/ለወጣቶች ምቹ የሆነ የችሎት ሥነ-ስርዓትና አደረጃጀት በመከተል የልጆችን ጥቅም ያስቀደመ አሰራር ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የችሎቱ ዳኛ የሚሰጠው ውሳኔ የልጆችን ጥቅምና ደህንነት ያስጠበቀ እንዲሆን በመስኩ ባለሙያዎች የተጠናቀረ በቂና ብቁ መረጃ ማግኘት አለበት፡፡ ይህን ስራ የሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ከችሎቱ ጋር እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

ይህ የስራ መዘርዝር/መመሪያ/ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚገኙ በወንጀል ጉዳይ ተጠርጥረው ፍርድ ቤት የቀረቡ ወጣቶችን ጉዳይ በሚያየው ችሎት የሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች ስለሚሰሩት ስራ (ጥናት የሚደረግበትን እና ሙያዊ አስተያየት የሚሰጥበትን አሰራር) ምንነትና አሰራር የሚዘረዝር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የስራ መዘርዝሩ ወጥ የሆነ አሰራር እንዲዘረጋ እንዲሁም የባለሙያውን ሙያዊ ሥነ-ምግባር እንዲሁም የስራ ብቃት ለማሳደግ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

### 1. የሥራ መዘርዝሩ መጠሪያ

የሥራ መዘርዝሩ "በወንጀል ነገር ገብተው የተገኙ ወጣቶችን ጉዳይ በሚያየው ችሎት ለሚሰሩ የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የስራ መዘርዝር" ነው፡፡

### 2. የስራ መዘርዝሩ አላማ

የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያዎች በችሎቱ ውስጥ የሚኖራቸው ሚና የወንጀል ፍትህ አስተዳደሩን ውጤታማ በሚያደርግና የልጆችን ጥቅም እና ደህንነት ባስቀደመ ሁኔታ ስራቸውን እንዲሰሩ ማስቻል ነው።

### 3. ባለሙያው ስራውን ሲሰራ ሊከተለው የሚገባ መርህ

ባለሙያው ስራውን ሲሰራ የሚከተሉትን የህፃናት መብቶች የፍልስፍና መሰረቶች ሊከተል ይገባል።

1 የህፃናት ጥቅምና ደህንነት ቀደምትነት
2 የህፃናት የመኖርና የእድገት መብት
3 የተሳትፎ መብት
4 አድሎ አማድረግ

### 4. ስለባለሙያው

#### 4.1 የሙያ ብቃት ማሳደግ

4.1.1 ባለሙያው ከስነ ልቦና ወይም ከማህበራዊ ሳይንስ ዕውቀቱ በተጨማሪ ስለህፃናት የእድገት ደረጃዎች (Child development) እና ፍላጎቶቻቸው፣ ስለሀገር አቀፍና አለም አቀፍ መሰረታዊ የህፃናት መብቶች፣ ስለወጣት ጥፋተኞች፣ ለወጣት ጥፋተኝነት ስለሚያጋልጡ ሁኔታዎች እና የመከላከያ ዘዴዎች፣ ስለህፃናት ጥቃቶችና ስለመሳሰሉት በስራው ላይ ያለውን ብቃት ሚያጎለብቱለትን ስልጠናዎች መውሰድ አለበት።

4.1.2 ባለሙያው በየወቅቱ በሚከናወኑ የጉዳዮች የቡድን ውይይት ላይ የመገኘትና የመሳተፍ ግዴታ አለበት።

#### 4.2 ገለልተኛነት

ባለሙያው ባለጉዳዮችን በእኩል ሁኔታ ማስተናገድ አለበት። እንዲሁም ከባለጉዳዮችም ሆነ ከባለጉዳዮቹ ወላጆች ጋር ከስራው ውጪ የተለየ ቅርበት ወይም የሌሎችን አካላት እምነትና አመለካከት ማንፀባረቅ የለበትም።

#### 4.3 ከጉዳይ ስለመነሳት

ባለሙያው ጉዳዩን በገለልተኝነት ለማየት የማያስችለው ነገር ካለ ባለሙያው ይህንኑ በመጥቀስ ጉዳዩን የማያይ መሆኑን ለቅርብ አለቃው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት። በተለይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ከጉዳዩ መነሳት አለበት።

4.3.1 ከባለጉዳዮች ወይም ከጠበቃቸው ጋር ዝምድና ወይም ልዩ ቅርበት ካለው፤
4.3.2 ጉዳዩን በግልም ሆነ በራሱ ምክንያት ቀደም ብሎ በስፋት የሚያውቀው ከሆነ ባለሙያው በራሱ ፍቃድ መነሳት አለበት፡፡
4.3.3 ባለጉዳዮቹ ምክንያታቸውን ዘርዝረው ባለሙያው እንዲነሳ ከጠየቁ ባለሙያው ወዲያው ለክፍሉ ሃላፊ ስለሁኔታው በማሳወቅ የክፍሉ ኃላፊ ውሳኔ እንዲሰጥበት ማድረግ አለበት፡፡
4.3.4 የክፍሉ ኃላፊ አቤቱታው እንደቀረበለት ሁኔታውን መዝኖ ሌላ ባለሙያ እንዲተካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4.3.5 ይህ ሂደት ባለጉዳዮቹ ለችሎት የሚያቀርቡትን ቅሬታ አይከለክልም፡፡

**5. የስራው ሂደት በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡**

1 የመግቢያ ንግግር
2 መረጃ ማሰባሰብ እና ማጣራት
3 የመውጫ ንግግር
4 ሪፖርት ማዘጋጀት
5 ተጨማሪ አገልግሎቶች/Referal/
6 ክትትል/Follow up/

**5.1 የመግቢያ ንግግር**

5.1.1 ባለሙያው ትዕዛዙ እንደደረሰው ለባለጉዳዩ ህፃን እና ቤተሰቦች /አሳዳጊዎች የመወያያውን ቀጠሮ ያሳውቃቸዋል፡፡
5.1.2 ባለሙያው ባለጉዳዮች ሲቀርቡ ስራውን የሚጀምረው በቅድሚያ ራሱን በማስተዋወቅ ሲሆን በመቀጠልም ስለስራው ምንነትና ሂደት፤ ስለመብትና ግዴታቸው ማብራሪያ በመስጠት ስለሂደቱ መረዳታቸውን ያረጋግጣል፡፡ የባለሙያው ማብራያ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች ያካተተ መሆን አለበት፡፡

- የባለሙያው ስራና የመጨረሻው ውጤት የሕፃናቱን ጥቅምና ደህንነት ያስቀደመ ውሳኔ ዳኛው መስጠጥ የሚችልበትን መረጃ ማሰባሰብና የባለሙያ ሀሳብ ማቅረብ መሆኑን፤
- የተናገሯቸው ሀሳቦችና በማስረጃነት ያቀረቧቸው መረጃዎች ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ መሆናቸውን እና በሚስጥርነት የማይያዝላቸው መሆኑን፤
- ስለሂደቱ፣ ሂደቱ ሊወስድ ስለሚችለው ጊዜና ከባለጉዳዮች ስለሚጠበቅ ግዴታ እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ማካተት አለበት፡፡

### 5.2 መረጃ ማሰባሰብና ማጣራት

ባለሙያው ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው ሙያዊ አስተያየት በተለያዩ መንገዶች በተገኙ መረጃዎች መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም እንደጉዳዩ አይነት በሚከተሉት የመረጃ ማሰባሰቢያ እና ማጣሪያ መንገዶች አማካይነት መረጃዎችን ያጠናቅራል፡፡

- ቃለ-መጠይቆች
- የባለሙያው ምልከታ(Observation)
- የቤት ውስጥ ጉብኝት
- መረጃ ይገኝባቸዋል ተብሎ ከተጠቆሙ ተቋማት ማለትም ከፍርድ ቤት፣ ት/ቤት፣ ከሆስፒታሎች፣ ከፖሊስ ጣቢያዎችና ከማሳደጊያ ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋሞች የሚገኙ መረጃዎች እንዲሁም ከሌሎች የቤተሰብ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን ሊጠቀም ይችላል፡:

#### 5.2.1 መረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶች

**ቃለ መጠይቅ**

በዚህ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ስር ባለሙያው የህፃናቱን እድሜና የእድገት ደረጃ ግምት ውስጥ በማስገባት ከህፃናቱ እና ከቤተሰብ/አሳዳጊ ጋር በመሆን የቃለ-መጠይቅ ዘዴን በመጠቀ ከህፃኑ ስለግልና የቤተሰብ ሁኔታው መረጃ ያሰባስባል፡፡ ከዚህ ባሻገር ሰፋ ባለ መልኩ ስለህይወቱና ለምን ወደ ወንጀል ድርጊት ሊገባ እንደቻለ ከህፃኑ እና ከቤተሰቡ ጋር በመሆን መረጃ ይሰበስባል፡፡

**የባለሙያው እይታ (Observation)**

መረጃ በማሰባሰብ ወቅት ከቃለ-መጠይቅ በተጨማሪ ባለሙያው ከባለጉዳዩ ጋር በሚኖረው ቆይታ የእይታ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴን በመጠቀም መረጃ ያገኛል፡፡ በዚህ ሂደት ላይ ባለጉዳዩ የሚያንፀባርቃቸው የሚታዩ ባህሪያትን እና ባለጉዳዩ (ወጣቱ) ከቤተሰቡ ጋር ስላለው አቀራረብ የሚያገኘውን ግንዛቤ ባለሙያው በመረጃነት ይይዛል፡፡

#### 5.2.2 መረጃ ማጣሪያ መንገዶች

የፍርድ ቤት ስራ እውነተኛ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ውሳኔ መስጠት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የሚሰራው የማህበራዊ ሳይንስ ባለሙያም የሚያቀርበው አስተያየት እውነተኛነታቸው በተረጋገጠ መረጃዎች የህፃናትን ጥቅምና ደህንነት ማስጠበቅ ነው፡ ፡ ስለሆነም ባለሙያው የመረጃ ማሰባሰቢያ መንገዶችን ተጠቅሞ ያገኛቸውን ቅድመ መረጃዎች እውነተኛነት ሊያረጋግጡ ከሚችሉ ግለሰቦች ወይም ተቋማት ተጨማሪ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል፡፡

ባለሙያው ቅድመ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚጠቀምባቸው መንገዶች እንደሚከተው ተዘርዝረዋል፡፡

**በጉብኝት የሚገኝ መረጃ**

የዚህ አይነቱ መረጃ ባለሙያው እንደአስፈላጊነቱ ባለጉዳዩ በሚኖርበት መኖሪያ እና በአካባቢው በአካል በመገኘት ያለውን ሁኔታ በመመልከት ሊያገኘው የሚችለው የመረጃ አይነት ነው፡፡ ባለሙያው ይህን መንገድ በመጠቀም ባለጉዳዩ (ወጣቱ) በእለት ተእለት እንቅስቃሴው ላይ ድጋሚ ወደ ጥፋት እንዲገባ ወይም እንዳይገባ የሚያመቻቹ ሁኔታዎችን ለማየት ወይም ለመለየት ይቻላል፡፡

**ከተቋማት የሚገኙ መረጃዎች**

ባለሙያው ባለጉዳዩ ከገለፀለት መረጃ በመነሳት እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ያገኛቸውን መረጃዎች ከትምህርት ቤት፣ ከጤናና ተቋማት፣ ከፖሊስ ጣቢያ፣ ከፍርድ ቤት፣ ከማሳደጊያ ተቋማትና ከመሳሰሉት ሊሰበስብ ይችላል፡፡

**ከባለጉዳዩ (ከወጣቱ) የቤተሰብ አባላትና በቅርብ ወጣቱን ሊያውቁ ከሚችሉ ግለሰቦች የሚገኙ መረጃዎች**

የባለጉዳዩን የቤተሰብ አባላት፣ ወጣቱ በሚኖርበት አቅራቢያ ስለወጣቱ ባህሪ ለማወቅ አጋጣሚው ያላቸውን ጎረቤቶች፣ የት/ቤት ጓደኞቹን፣ የቅርብ አስተማሪዎቹን እንዲሁም ተበዳይን እና የተበዳይ ወገኖችን በማነጋገር ስለባለጉዳዩ ተጨማሪ ግንዛቤ እንዲኖረው ይረዳል፡፡ ባለሙያው እነዚህን አካላት በሚገኙበት ቦታ በመሄድ፣ በጽ/ቤቱ በመጥራት ወይም በጉብኝት ወቅት ሊያነጋግራቸው ይችላል፡፡

**5.3 የመዝጊያ ንግግር**

ባለሙያው ውይይቱን ከማጠናቀቁ በፊት ለህፃኑ/ለወጣቱ ወላጆች/ አሳዳጊዎች በአስተዳደግ ዙሪያ፣ ህፃኑን/ወጣቱን ለወንጀል የሚያጋልጡ ሁኔታዎችን እና ወደ ወንጀል እንዳይገባ ሊወስዱ የሚገባቸውን ጥያቄዎች በተመለከተ ሙያዊ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡

**5.4 ሪፖርት ማዘጋጀት**

የሚዘጋጀው ሪፖርት የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፡- የባለጉዳዩ(ወጣቱ) የግል ሁኔታ፣ የወላጅ ሁኔታ፣ ስለልጅና ወላጅ ግኑኝነት፣ የባለሙያውን እይታ እንዲሁም ከሌሎች የተገኙ ተጨማሪ መረጃዎችን ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ሀሳቦች በዝርዝር መቀመጥ አለባቸው፡፡ በመጨረሻም ሪፖርቱ የተገኙትን መረጃዎች መሰረት ያደረገ ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ መያዝ አለበት፡፡

ሪፖርቱ ጉዳዩ የላከው ችሎት ከተሰጠው የጊዜ ቀጠሮ በፊት ለችሎት ያደርሳል፡፡ በተሰጠው ግዜ ሪፖርቱ መቅረብ ካልቻለ ባለሙያው ምክንያቱን በመግለፅ ችሎቱን ተጨማሪ ቀጠሮ እንዲሰጠው ከቀጠሮው ቀን በፊት በፅሁፍ ይጠይቃል፡፡

### 5.5 ተጨማሪ እገዛ ማግኘት

ባለሙያው ለያዘው ባለጉዳይ መረጃ ከመሰብሰብ ባሻገር እንደ ጉዳዩ ክብደትና እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ አገልግሎት ከሚሰጡ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግኑኝነት በመፍጠር አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያመቻቻል፡፡

## 6. ለጥንቃቄ እርምጃ ሙያዊ አስተያየት ለማቅረብ ታሳቢ ሊደረጉ የሚገቡ ነጥቦች

ባለሙያው መረጃ ካሰባሰበና ካጣራ በኋላ ሪፖርቱን አጠናክሮ ለጥንቃቄ እርምጃ የሚሆን የባለጉዳዩን ጥቅምና ደህንነት ያስጠበቀ ሙያዊ አስተያየት ለማቅረብ የሚከተሉትን ነጥቦች ያመለክታል፡፡

6.1 **የጥፋተኛው ወቅታዊ የወንጀል አፈፃፀም ግንዛቤ፡-** ባለሙያው ከአጥፊው ጋር በሚያደርገው ውይይት ወይም የመረጃ ማሰባሰብ እና እውነትን የማፈላለግ ሂደት ህፃኑ/ወጣቱ ጥፋቱን በተፈፀመበት ወቅት የነበረው የትምህርት እና የእድገት ደረጃ ከጥፋቱ ጋር በተያያዘ ስላለው መረጃ እና ጥፋቱን ለመፈፀም ምክንያት የሆነው ምን እንደነበር እንዲሁም ሌሎችንም ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ ባለሙያው ህፃኑ/ወጣቱ ለፈፀመው ወንጀል ግንዛቤ ኖሮት መሆን አለመሆኑን በመመዘን አስተያየቱን ያጠናክራል፡፡

6.2 **የህፃኑ/ወጣቱ የቀድሞ የጥፋተኝነት ታሪክ፡-** ተከሳሹ አሁን ከተከሰሰበት ክስ ሌላ በየትኛውም ፍርድ ቤት ተከሶ የሚያውቅ ከሆነ የተከሰሰበትን የጥፋት አይነት ጭምር መጠየቅ፣ በተጨማሪም በተከሰሳቸው የጥፋት አይነቶች ጥፋተኛም ተብሎ ከነበረም አያይዞ ይህንኑ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህ መረጃ ባለሙያው ህፃኑ ድጋሚ ወንጀል እንዳይገባና የቅርብ ክትትል እና እገዛ የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲኖር ይረዳል፡፡

6.3 **የህፃኑን/ወጣቱን ለጥፋት ተጋላጭነት መለየት፡-** ተከሳሹ ወደ ጥፋት የገባው በቂ የሆነ የቤተሰብ ክትትል /ቁጥጥር/ ያለመኖር፤ የትምህርት እድል ማጣት፤ ወላጅ/አሳዳጊ መለያየት/አለመኖር፤ የጓደኛ ግፊት፤ በአካባቢው የሚገኙ ለጥፋት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ተቋማት/ቦታዎች ወዘተ...የሚሉትን ምክንያቶች መኖራአቸውን በአግባቡ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

6.4 **ጥፋተኛውና ቤተሰቡ ከተፈፀመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ያላቸው አስተያየት፡-** ተከሳሹም ሆነ ወላጅ/አሳዳጊ በተፈጸመው ጥፋት ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅ፤ ለምሳሌ ከጥፋቱ ጋር በተያያዘ ከከሳሽ/ከተበዳይ ቤተሰብ ጋር እንደ

ጉዳዩ ክብደት መጠን የጥፋተኝነት ስሜት ተሰምቷቸው በመፀፀት ይቅርታ በመጠየቅ በስምምነት ለመጨረስ ያሳዩትን ፍላጎት መጠየቅና ማወያየት ይገባል፡፡

6.5 **የጥፋተኛው አካላዊና ስነ-ልቦናዊ የጤና ሁኔታ፡-** ባለሙያው ከባለጉዳዩ ወይም ከቤተሰቡ ጋር በሚኖረው ቆይታ ሙያዊ እውቀቱን መሰረት በማድረግና በዚህ ረገድ ያለውን ግንዛቤ ሊያጠናክሩለት የሚችሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ የጥፋተኛውን የአካል ወይም የሥነ-ልቦና ጤንነት በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

*ይህ የስራ መዘርዝር ከታህሳስ 17 ቀን 2005 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡*

# የውርስ ማጣራት ስራን እንዲሰሩ በፍርድ ቤት ለተሾሙ ባለሙያዎች የተዘጋጀ የስራ መዘርዝር

*ታህሳ 2007 ዓ. ም.*

<u>**መግቢያ**</u>

በፍትሐብሄር ህጉ ላይ የውርስ ሀብት ማጣራት ስራ ሟች በመረጠው ወይም ያለኑዛዜ በወራሾች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ የአጣሪነት መብት እንዳላቸው፤ በዚህም መሰረት የውርስ ሀብቱን ማጣራት እንደሚችሉ፤ በኑዛዜ የተመረጠው ሰው ፈቃደኛ ካልሆነ እና ወራሾች በራሳቸው ተስማምተው የውርስ ሀብት አጣሪውን መምረጥ ካልቻሉ በማንኛውም ባለጉዳይ አመልካችነት ፍርድ ቤት ውርስ ሀብት አጣሪ እንደሚሾም ይደነግጋል። በዚህም መሰረት የውርስ ሀብት የማጣራት ስራው ፈቃደኛ በሆኑ ሰዎች ቢሰራ የተሻለ መሆኑ ይታመናል። ሆኖም በህጉ እና በተግባሩ መካከል ልዩነት መኖሩን ማወቅ ተችሏል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ ባለጉዳዮቹ በራሳቸው ተስማምተው የውርስ ሀብት አጣሪ ለመምረጥ ሳይስማሙ ቀርተው ችሎቱ በፍርድ ቤት በኩል አጣሪ እንደሚሾምላቸው ትዕዛዝ ሲሰጥ የማጣራት ስራውን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል በፍርድ ቤቱ የሚሰሩ ባለሙያዎች እንዲሰሩ ተደርጓል።

በዚህም መሰረት የውርስ ሀብት አጣሪዎችን ስራ ግልፅነት፣ ተደራሽነት እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መስራቱን ለመቆጣጠር እንዲቻል ፍርድ ቤቱ ይህንን የስራ መዘርዝር አዘጋጅቷል።

## 1. የስራ መዘርዝሩ አላማ

የስራ መዘርዝሩ የውርስ ማጣራት ስራው የህጉን አላማ ተከትሎ እንዲተገበር ማስቻልን እና ሂደቱም ተደራሽ፣ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን ማስቻል ነው።

## 2. የውርስ ሀብት አጣሪ ተግባራት እና ግዴታዎች

2.1. የውርስ ሀብት አጣሪው የማጣራት ስራውን ከፍርድ ቤቱ ውጪ እና ከስራ ሰዓት ውጪ መስራት ፤
2.2. የውርስ ሀብት አጣሪው በቅድሚያ ስለራሱ እና ስለ ስራው ሁኔታ አጠቃላይ ማብራሪያ መስጠት፤
2.3. በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ መነሻነት በህጉ አግባብ ገለልተኛ፤ ቀልጣፋ በሆነ መልኩ እና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ግራ ቀኙን ማስተናገድ፤
2.4. የማጣራት ስራውን በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰርቶ ሪፖርቱን እንዲያጣራ ትዕዛዙን ለሰጠው ችሎት ማቅረብ፤

2.5. በማጣራ ሂደት ከተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች ግራ ቀኙ በራሳቸው ወጪ ኮፒ አድርገው ወስደው አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፤
2.6. የውርስ ሀብት አጣሪው ክርክር የተነሳበትን ቤት፤ የቤት ቁሳቁስ፣ ቦታ እና ሌሎች ለውርስ ማጣራት ስራው ሊጠቅሙ የሚችሉ ነገሮችን ለማየት ወይም ለመቁጠር ሲሄዱ ግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች ባሉበት መሆን ይኖርበታል፡፡
2.7. ሪፖርቱን ሰርቶ ለግራ ቀኙ በሚሰጥበት ጊዜ ስለ ሪፖርቱ ጠቅለል ያለ መግለጫ በመስጠት በሪፖርቱ ላይ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ካለ ቅሬታውን ለችሎት ማቅረብ እንደሚችል መግለፅ፣
2.8. የውርስ ሀብት አጣሪው ለባለጉዳዮች ተገቢውን ክብር መስጠት ይኖርበታል፡፡

## 3. ገለልተኝነት

3.1. ባለሙያው ሁለቱንም ወገኖች በእኩል ሁኔታ ማስተናገድ አለበት፡፡ ከየትኛውም ባለጉዳይ ሆነ ከጠበቃው ጋር ከስራው ውጪ የተለየ ቅርበት ወይም ግንኙነት ሊኖረው አይገባም፡፡ በሙያ ስራው የራሱን ወይም የሌሎችን እምነትና አመለካከት ማንፀባረቅ የለበትም፡፡

### 3.2. ከያዘው ጉዳይ ስለመነሳት

3.2.1. ጉዳዩን በገለልተኝነት ለማየት የማያስችለው ነገር ካለ ባለሙያው ይህንኑ በመጥቀስ ጉዳዩን የማያይ መሆኑን ለሬጅስትራር አለቃው በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ በተለይ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ከሀላፊነቱ መነሳት አለበት፡፡
3.2.2. ከባለጉዳዩ ወይም ከጠበቃቸው ጋር ዝምድና ወይም ልዩ ቅርበት ካለው፤
3.2.3. ጉዳዩን በግሉም ሆነ በሙያው ምክንያት ቀደም ብሎ በስፋት የሚያውቀው ከሆነ፤
3.3.4. ባለሙያው በራሱ ፍቃድ ካልተነሳ ለዋና ሬጅስትራር አቤቱታ ከቀረበ ሬጅስትራር ሁኔታውን መዝኖ ሌላ ባለሙያ እንዲተካ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ሂደት ባለጉዳዮቹ ለችሎት የሚያቀርቡትን ቅሬታ (አቤቱታ) አይከለክልም፡፡

## 4. የባለጉዳዮች ግዴታ

4.1. ለውርስ ሀብት አጣሪ ተገቢውን ክብር መስጠት፤
4.2. የውርስ ሀብት ማጣራት ስራው "በነፃ አገልግሎት" ካልሆነ በቀር የውርስ ሀብት አጣሪውን አበል በመመሪያው እና በስምምነታቸው መሰረት መክፈል፤
4.3. ግራ ቀኙ ከውርስ ሀብት አጣሪው ጋር በያዙት ቀጠሮ፣ ቀንና ሰዓት አክብሮ መገኘት፤

4.4. ለውርስ ማጣራት ስራው ሊጠቅሙ የሚችሉ ማስረጃዎችን ለውርስ ሀብት አጣሪው ማቅረብ፤

4.5. የውርስ ሀብት አጣሪው ከማጣራት ስራው ጋር በተያያዘ የሚሰጣቸውን ትዕዛዞች በቀጠሮው መሰረት ወጪ አድርጎ ምላሻቸውን ተከታትሎ ማምጣት፤

4.6. የውርስ ማጣራት ሂደቱን እንዲሁም የውርስ ሀብት አጣሪውንና የባለጉዳዮቹን መብትና ግዴታ የሚያሳየውን ከዚህ መመሪያ ጋር የተያያዘውን ፎርም ባለጉዳዮች የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## 5. ከውርስ ሀብት አጣሪ አበል አከፋፈል ጋር በተያያዘ

5.1. የውርስ አጣሪ አበል አከፋፈልን በተመለከተ የግራ ቀኙን የመክፈል አቅምና የጉዳዩን ውስብስብነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከባለጉዳዮች ጋር በሚደረግ ስምምነት የውርስ ሀብት ማጣራት ስራው "በነፃ አገልግሎት" ካልሆነ በቀር ለግራ ቀኙ ተከራካሪዎች እኩል በሆነ አተማመን የሚከፈል በድምሩ እስከ ብር 5,000.00 (አምስት ሺ) ማስከፈል ይችላሉ፡፡

5.2. የውርስ ሀብት አጣሪው አበል በዋናው መዝገብ ላሉ እና በውርስ ሀብት አጣሪው መዝገብ ውስጥ ለሚገቡ ጣልቃገቦች ለእያንዳንዳቸው እኩል በሆነ አተማመን የሚከፍሉት ይሆናል፡፡

5.3. የውርስ ሀብት አጣሪ ከስራው ውስብስብነት፤ ስራውን ለመስራ ከሚወስደው ጊዜና ከንብረቱ ብዛት በመነሳት ከ5000 (አምስት ሺ) ብር በላይ ሊከፈለኝ ይገባል ብሎ ሲያምን የውርስ ማጣራት ስራው ከአምስት ሺ ብር በላይ የሚያስከፍለው መሆኑ እና በዚህም መሰረት ከአምስት ሺ ብር በላይ ሊጠይቅ መሆኑን ለባለጉዳዮቹ እና ለዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤት በፅሁፍ ካሳወቀ በኂላ ተጨማሪ የአበል መጠኑን አስመልክቶ ከባለጉዳዮቹ ጋር ሳይደራደር ቀጥታ በክፊውያው መጠን ላይ ትዕዛዝ እንዲሰጥበት ለችሎት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5.4. ከተከራካሪ ወገኖች የመክፈል አቅም የተነሳ ወይም ከሚያጣራው ንብረት አይነት ችሎቱ በነፃ እንዲያጣራ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5.5. የሚያጣራው ንብረት በባንክ ያለ ገንዘብ ብቻ ሆኖ በዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤት በነፃ እንዲጣራ ትዕዛዝ የደረሰው የውርስ ሀብት አጣሪ የሚጣራው የገንዘብ መጠን ከሀምሳ ሺ ብር በታች ከሆነ እስከ 500 ብር ፤ ከሀምሳ ሺ ብር በላይ ከሆነ ደግሞ ከአንድ ሺህ ብር የማይበልጥ ገንዘብ እንዲከፈለው መጠየቅ ይችላል፡፡

5.6. በነፃ እንዲያጣራ ትዕዛዝ የደረሰው የውርስ ሀብት አጣሪ ምንም አይነት ክፍያ መጠየቅ የለበትም፡፡ ሆኖም በነፃ እንዲያጣራ ትዕዛዝ ደርሶት ስራውን እየሰራ ባለበት ጊዜ የሚጣራውን ንብረት ብዙ ሆኖ ሲገኝ እና ባለጉዳዮቹ የመክፈል አቅም አላቸው ብሎ ሲያምን የውርስ ሀብቱ በነፃ ሊጣራ አይገባም ወይም አበል ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ለዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤት እና ለችሎት በፅሁፍ ማመልከት ይችላል፡፡

5.7. የውርስ ሀብት አጣሪው ስራውን ሰርቶ ሲጨርስ ከዋና ሬጅስትራር ቢሮ የአበል አከፋፈልን አስመልክቶ የደረሰውን ፍርም ሞልቶ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

5.8. ቀደም ብሎ የሰራቸውን ስራዎች አስመልክቶ የተሞላ ሪፖ`ርት ላላቀረበ ውርስ አጣሪ የዋና ሬጅስትራር ቢሮ ተጨማሪ የማጣራት ስራ አይልክም፡፡

## 6. ውርስ ሀብት አጣሪው ስራውን ሊያጠናቅቅበት ስለሚገባው ጊዜ

6.1. የውርስ ሀብት አጣሪው ተግባሩን የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ማጠናቀቅ ይኖርበታል፡፡

6.2. የውርስ ሀብት አጣሪው በማንኛውም የውርስ ሀብት ክርክር ለተከታታይ አስራ አምስት ቀናት ማስታወቂያ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

6.3. የውርስ ሀብት አጣሪው በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1018(2) ላይ እንደተቀመጠው ገንዘብ ጠያቂዎች አሉ ብሎ የሚያምን ከሆነ ለሶስት ወር የሚቆይ ማስታወቂያ ከለጠፈ በኂላ ለችሎቱ ገንዘብ ጠያቂዎች አሉ ብሎ እንዲያምን ያደረገውን አሳማኝ ምክንያት ጠቅሶ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

6.4. የውርስ ሀብት አጣሪው የሚያጣራው ንብረት ብዛት የተነሳ ወይም ግራ ቀኙ ከሚያቀርቡት ክርክር ውስብስብነት የተነሳ የውርስ ማጣራት ስራው ከሁለት ወር ጊዜ በላይ የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ ይህንኑ ለችሎቱ በማስረዳት ከዚያ በላይ ጊዜ እንዲሰጠው መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

## 7. ይህንን መመሪያ ተላልፎ የተገኘ ውርስ ሀብት አጣሪ ላይ ሊወሰድ የሚችል እርምጃ

7.1. በአንድ ውርስ አጣሪ ላይ ከውርስ ማጣራት ስራው ጋር በተያያዘ አቤቱታ ሲቀርብበት እንደ አቤቱታው ሁኔታ ታይቶ አቤቱታው ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥበት ድረስ ለውርስ ሀብት አጣሪው አዲስ የውርስ ማጣራት ሳይላክለት እንዲቆይ ሊደረግ ይችላል፡፡

7.2. የውርስ ሀብት አጣሪው ከተፈቀደለት የአበል ክፍያ መጠን በላይ በፅሁፍ ለባለጉዳዮች እና ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤት ሳያሳውቅ እንዲሁም ከ5000 ብርበላይ ስለሚጠይቀው አበል ከባለጉዳዮቹ ጋር የተደራደረ ወይም ችሎቱን ሳያስፈቅድ ከባለጉዳዮቹ የተቀበለ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከውርስ ሀብት ማጣራት ስራ ለተወሰነ ጊዜ ወይም እስከመጨረሻው የመታገድ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፤

7.3. ባለጉዳዮችን በእኩልነትና ገለልተኛ በሆነ መልኩ፤እንዲሁም ሰብአዊ መብታቸውንና ክብራቸውን በመጠበቅ ባለመስራቱ ምክንያት አቤቱታ የቀረበበት እና የቀረበበት አቤቱታ ትክክል ሆኖ የተገኘበት የውርስ ሀብት አጣሪ እንደጥፋቱ ክብደት ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ እስከ ከውርስ ሀብት ማጣራት ለተወሰነ ግዜ ወይም እስከመጨረሻው የመታገድ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

7.4. የውርስ ሀብት አጣሪው ሪፖ`ርቱን ሰርቶ ለመጨረስ የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ያለበቂ ምክንያት ለማሳለፍ የውርስ ማጣራት ስራውን እንዲጓተት በማድረጉ በተደጋጋሚ አቤቱታ የቀረበበት እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ ከውርስ ማጣራት ስራው ለተወሰነ ግዜ ወይም እስከመጨረሻው እንዲታገድ ሊደረግ ይችላል፤

8. ማኛውም የውርስ ሀብት አጣሪ በዚህ መመሪያ ላይ የተዘረዘሩትን በመተላለፍ ምክንያት ቅሬታ ያለው ባለጉዳይ ቅሬታውን በፅሁፍ ለዋና ሬጅስትራር ቢሮ ማቅረብ ይችላል፡፡
9. ማንኛውም የውርስ ሀብት አጣሪ ዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤት በሚወስደው እርምጃ ላይ ያለውን አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ፕሬዝዳንት ማቅረብ ይችላል፡፡
10. ይህ መመሪያ ለንብረት ማጣራትም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
11. በዚሁ መመሪያ ላይ የተገለፁት የውርስ ሀብት አጣሪና የባለጉዳዮች መብትና ግዴታ በአጭሩ የሚገልፅና በውርስ ሀብት አጣሪ ተሞልቶ ለዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤት የሚላከው 2 ገፅና ለባለጉዳዮች የሚሰጥ 1 ገፅ አባሪ የዚህ መመሪያ አካል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

*ይህ የስራ መዘርዝር ከታህሳስ 7 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡*

**የተከራካሪ ወገኖች የውርስ ሀብት አጣሪ መብትና ግዴታ እና ውርስ ሀብት አጣሪነት በሚመደብ ባለሙያ ተሞልቶ ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤት መቅረብ ያለበት ቅፅ**

**<u>የተከራካሪ ወገኖች ግዴታ</u>**

1. ተከራካሪ ወገኖች በቀጠሮ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ሳያረፍዱ ከመቅረብ ጀምሮ በውርስ አጣሪ የሚሰጡ ህጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን በተገቢው ፍጥነት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በተጨማሪም የውርስ አጣሪ ባለሞያው ከታች የተገለፁትን ግዴታዎች የጣሰበት ሁኔታ ሲፈጠር ለችሎትና ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤቱ የማሳወቅ ግዴታና ስራው ሲጠናቀቅም በዚህ ቅፅ ላይ የተቀመጡትን የሚመለከታቸውን ባዶ ቦታዎች በመሙላትና ለዋና ሬጅስትራር ፅ/ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

**<u>የባለሙያው ግዴታ</u>**

1. በቅድሚ ስለሚሰራው ስራ ለግራ ቀኙ ተገቢ የሆነ ማብራሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
2. ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት በህጉ አግባብ ገለልተኛ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ግራ ቀኙን ማስተናገድ አለበት፡፡
3. ባለሙያው ስራውን ከስራ ሰዓትና ከስራ ቦታ ውጭ ማከናወን አለበት፡፡
4. የግራ ቀኙን የመክፈል አቅምና የጉዳዩን ውስብስብነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ በመዝገቡ ላይ ግራ ቀኝ ወገኖች እኩል በሆነ አተማመን በድምሩ እስከ ብር 5000.00 (አምስት ሺ ብር) የባለሙያ ክፍያ እንዲከፈለው መስማማት ይችላል፡፡
5. ከዚህ የክፍያ ጣሪያ በላይ የሆነ ማናቸውም አይነት የበለጠ ዋጋ ሊከፈለው የሚገባ ስራ ሲያጋጥመው ስለተጨማሪው ክፍያ ከባለጉዳዮቹ ጋር ሳይደራደር አቤቱታን ቀጥታ ለችሎቱ በማቅረብ በክፍያ መጠኑ ላይ መመሪያ እንዲሰጥበት ባለሙያው አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡
6. የማጣራው ንብረት በባንክ ያለ ገንዘብ ከሆነ የማጣራት ስራው የሚሰራው በነፃ ሆኖ የሚጣራው ገንዘብ እስከ 50,000(ሀምሳ ሺ) ብር ከሆነ እስከ 500 (አምስት መቶ ብር)፤ ከ 50,000 (ሀምሳ ሺ) ብር በላይ ከሆነ ደግሞ እስከ 1000 (አንድሺ) ብር ድረስ ለማፃፊያና ለአንዳንድ ወጪዎች ግራቀኙ ወገኖች እንዲከፍሉ መስማማት ይቻላል፡፡
9. በአበል አተማመንም ላይ ሆነ በፍትሀዊነት እንዲሁም በቅልጥፍና ዙሪያ ቅሬታ ሲቀርብበት ባለሙያው ለግራ ቀኙ በፍጥነት መፍትሔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግራ ቀኙ በችሎት በሚያቀርቡት አቤቱታ መነሻነት መፍትሔ ማግኘት ይችላሉ፡፡
10. ባለሙያው የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ከተቀበለ አንስቶ በ2 ወር ጊዜ ውስጥ ስራውን አጠናቆ ሪፖርቱን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ተጨማሪ ግዜ ለመጠየቅ በቂ ምክንያት የሚኖር ከሆነ ይህንኑ ባለሙያው ለችሎት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
11. ይህን የስራ አፈፃፀም መከታተያ ፎርም ባለሙያው የተመደበበትን ስራ ሲያበቃ በሶስት ኮፒ አባዝቶ በራሱና በግራ ቀኙ እንዲሞላ አድርጎ ሪፖርቱን ለችሎት

**በሚቀርብበት ቀን ለዋና ሬጅስትር ጽ/ቤት በግራ ቀኙ በኩል ማቅረብ ይኖርበታል።**

**<u>ማሳሰቢያ</u>**

***ከላይ በተገለፀው መመሪያ መሰረት ስራን አከናውኖ ሪፖርት ያላደረገ ባለሙያ እንደነገሩ ሁኔታ ከውርስ አጣሪ ባለሙያነት ለጊዜው ወይም በቋሚነት የሚታገድ መሆኑን ዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤቱ ያሳታውቃል።***

አመልካቾች ________________________________________
ተጠሪ/ዎች__________________________________________
አድራሻ__________ክ/ከ/ካ______________የቤት ቁ.____________________
አድራሻ___________ክ/ከ/ካ___________የቤት ቁ._____________________
ስልክ_________________________________________________
ስልክ_________________________________________________
ለባለሙያው የከፈሉት የገንዘብ መጠን ብር_________________________
ለባለሙያው የከፈሉት የገንዘብ መጠን ብር_________________________
በአሀዝ____________________________________________________________
በአሀዝ____________________________________________________________
የጣልቃ-ገብ/ገቦች ________________________________________________
አድራሻ_________ክ/ከ/ወ______________የቤት ቁ.___________________
ስልክ_________________________________________________
ለባለሙያው የከፈሉት የገንዘብ መጠን ብር_________________________
በአሃዝ____________________________________________________________
ስሜ ከታች የተገለፀው ባለሙያ እና ስማችን ከላይ የተገለፀው ተከራካሪ ወገኖች የሰጠነው መረጃ እውነት መሆኑን እናረጋግጣለን።
በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት___________________________ምድብ__________________________ፍ/ብ/ችሎት በኮ/መ/ቁጥር ______________________ላይ በተሰጠ ትዕዛዝ መነሻነት በመዝገቡ ላይ የውርስ ሀብት አጣሪ ሆኜ በመመደብ ለሰጠሁት አገልግሎት ከአመልካች/ቾች ብር_________________ ከተጠሪ/ዎች ብር____________________ ከጣልቃ-ገብ/ገቦች ብር_________________ ተከፍሎኝ የማጣራት ስራውን በ_____________ወራት ውስጥ አጠናቅቄ ሪፖርት ለፍ/ቤቱ ማቅረቤን አረጋግጣለሁ።

የውርስ ሀብት አጣሪ ስም__________________________________________
ፊርማ______________________ ቀን_____________________________________

የአመልካች/ቾች
ስም______________________________________
ፊርማ_____________________________ ቀን___________________________
የተጠሪዎች ስም________________________________________
ፊርማ_____________________________ ቀን___________________________
የጣልቃ-ገብ/ገቦች ስም______________________________________________
ፊርማ_____________________________ ቀን___________________________

**ለባለጉዳዮች የሚሰጥ የተከራካሪ ወገኖችና የውርስ ሀብት አጣሪ መብትና ግዴታ የሚያሳይ ፎርም**

1. ተከራካሪ ወገኖች በቀጠሮ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ሳያረፍዱ ከመቅረብ ጀምሮ በውርስ አጣሪ የሚሰጡ ህጋዊ የሆኑ ትዕዛዞችን በተገቢው ፍጥነት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በተጨማሪም የውርስ አጣሪ ባለሙያዎች ከታች የተገለፁትን ግዴታዎች የጣሰበት ሁኔታ ሲፈጠር ለችሎቱና ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤቱ የማሳወቅ ግዴታና ስራው ሲጠናቀቅም በዚህ ቅፅ ላይ የተቀመጡትን የሚመለከታቸውን ባዶ ቦታዎች በመሙላት ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤቱ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. በቅድሚያ ስለሚሰራው ስራ ለግራ ቀኙ ተገቢ የሆነ ማብራሪያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
4. ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መነሻነት በህጉ አግባብ ገለልተኛ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ግራ ቀኙን ማስተናገድ አለበት፡፡
5. ባለሙያው ስራውን ከስራ ሰዓትና ከስራ ቦታ ውጪ ማከናወን አለበት፡፡
6. አበልን በተመለከተ የግራ ቀኙን የመክፈል አቅምና የጉዳዩን ውስብስብነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የማጣራት ስራው በአበል የሚሰራ ከሆነ በመዝገቡ ላሉ ግራ ቀኝ ወገኖች እኩል በሆነ 5000.00 (አምስት ሺህ ብር) የባለሙያው ክፍያ እንዲከፈለው መስማማት ይችላል፡፡
7. ከዚህ የክፍያ ጣሪያ በላይ የሆነ ማናቸውም አይነት የበለጠ ዋጋ ሊከፈለው የሚገባ ስራ ሲያጋጥመው ስለ ተጨማሪው ክፍያ ከባለጉዳዮቹ ጋር ሳይደራደር አቤቱታውን ቀጥታ ለችሎቱ በማቅረብ መክፍያ መጠኑ ላይ መመሪያ እንዲሰጥበት ባለሙያው አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡
8. የሚጣያራው ንብረት በባንክ ያለ ገንዘብ ከሆነ የማጣራት ስራው የሚሰራው በነፃ ሆኖ የሚጣራው ገንዘብ እስከ 50000 ከሆነ እስከ 500 ብር፣ ከ 50000 ብር በላይ ከሆነ እስከ 1000 ሺ ብር ድረስ ለማፃፊያና ለአንዳንድ ወጪዎች ግራቀኙ ወገኖች እንዲከፍሉ መስማማት ይቻላል፡፡
9. አበል አተማመንም ላይ ሆነ በፍትሀዊነት እንዲሁም በቅልጥፍና ዙሪያ ቅሬታ ሲቀርብለት ባለሙያው ለግራ ቀኙ በፍጥነት መፍትሔ ሊሰጥ ይገባል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግራ ቀኙ ለችሎት በሚያቀርቡት አቤቱታ መነሻነት መፍትሔ ማግኘት ይችላሉ፡፡
10. ባለሙያው የፍ/ቤቱን ትዕዛዝ ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ በ2 ወር ግዜ ውስጥ ስራውን አጠናቆ ሪፖርቱን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ተጨማሪ ግዜ ለመጠየቅ በቂ ምክንያት የሚኖር ከሆነ ይህንኑ ባሙያው ለችሎት ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
11. ይህን የስራ አፈፃፀም መከታተያ ፎርም ባለሙያው የተመደበበትን ስራ ሲያበቃ በሶስት ኮፒ አባዝቶ በራሱና በግራ ቀኙ እንዲሞላ አድርጎ ሪፖርቱን ለችሎት በሚያቀርብበት ቀን ለዋና ሬጅስትራር ጽ/ቤት በግራ ቀኙ በኩል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**Advice for Divorcing Parents: - by Judge Michael Haas**

*"Your children have come into this world because of the two of you. Perhaps you two made lousy choices as to whom you decided to be the other parent. If so, that is YOUR problem and YOUR fault.*

*"No matter what you think of the other party — or what your family thinks of the other party — these children are one-half of each of you. Remember that, because every time you tell your child what an 'idiot' his father is, or what a 'fool' his mother is, or how bad the absent parent is, or what terrible things that person has done, you are telling the child half of HIM is bad.*

*"That is an unforgivable thing to do to a child. That is not love! That is possession. If you do that to your children, you will destroy them as surely as if you had cut them into pieces, because that is what you are doing to their emotions.*

*"I sincerely hope that you do not do that to your children. Think more about your children and less about yourselves, and make yours a selfless kind of love, not foolish or selfish, or your children will suffer."*

Judge Michael Haas retired in December 2002 after 26 years of service as a Judge in Cass County, Minnesota. He wrote this advice in a letter written to advice columnist Abigail Van Buren in October 1994.

ISBN 978-99944-947-0-5

9 789994 494705 >

Design + Print @ Eclipse +251-115-572222 / 23 Addis Ababa, Ethiopia